21

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረምረቃ ትምህርት ቤት

በአዲስ አበባ ከተማ በግል እና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገርአቀፍ ፈተና ውጤቶች ንጽጽር

* ጠጅቱ በሬቻ

ሰኔ 1999 ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ በግል እና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገርአቀፍ ፈተና ውጤቶች ንጽጽር

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ለድህረምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም.ኤ.ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ጠጅቱ በሬቻ

ሰኔ 1999 ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ በግል እና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገርአቀፍ ፈተና ውጤቶች ንጽጽር

በ

ጠጅቱ በሬቻ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ	ፊርማ
የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ
የውጭ ፈታኝ	ፊርማ

የአርእስት ማውጫ

አርእስት ገጽ

ምስጋና.....i

የአርእስት ማውጫ.....ii

የሠንጠረዥ ዝርዝር.....vi

የአባሪ ዝርዝር.....ix

አጠቃሎ.....x

ምዕራፍ አንድ መግቢያ.....1

1.1. የጥናቱ ዳራ.....1

1.2. የጥናቱ ዓላማ.....3

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ.....3

1.4. የጥናቱ ክልልና ገደብ.....4

ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት.....5

2.1. የሥርዓተ ትምህርት እና የቋንቋ መርሐትምህርት የጋራ ባሕርያትና ልዩነት.....5

2.2. የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ መለዮ ባሕርያት.....5

2.3. የቋንቋ ፈተና ምንነት፣ ዓላማ እና አስፈላጊነት.....6

2.3.1. የቋንቋ ፈተና ምንነት.....6

2.3.2. የቋንቋ ፈተና ዓላማ.....7

2.3.3. የቋንቋ ፈተና አስፈላጊነት.....8

2.4. የቋንቋ ፈተናና የቋንቋ ትምህርት ተዛምዶ.....9

2.5. የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች.....9

2.5.1. የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና.....10

2.5.2. የደረጃ መለኪያ ፈተና.....11

2.5.3. ጥንካሬ እና ድክመት መለኪያ ፈተና.....12

2.5.4. የችሎታ መለኪያ ፈተና.....13

2.5.4.1. የችሎታ መለኪያ ፈተና ምንነት.....13

2.5.4.2. የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት አመራረጥ.....13

2.5.4.3. የችሎታ መለኪያ ፈተና አቀራረብ ስልቶች.....15

2.5.4.3.1. ምርጫ-ነክ የአቀራረብ ስልቶች.....16

2.5.4.3.1.1. የምርጫ ጥያቄዎች.....17

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

2.6. የቋንቋ ፈተና መመዘኛዎች 18
2.6.1. አስተማማኝነት.....19
2.6.2 ተገቢነት.....19
2.6.2.1. የይዘት ተገቢነት.....20
2.6.2.2. ላያዊ ተገቢነት.....21
2.6.3. ተተግባሪነት.....22
2.7. በፈተና ዙሪያ የተጠኑ የቀደምት ጥናቶች ቅኝት.....22
ምዕራፍ ሦስት፡-የአጠናን ዘዴ 25
3.1. የፈተናዎች፣ የትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች እና የመምህራን ናሙና አመራረጥ.....25
3.1.1. የፈተናዎች የናሙና አመራረጥ.....25
3.1.2. የትምህርት ቤቶች የናሙና አመራረጥ.....26
3.1.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ.....30
3.1.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ.....32
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና አተናተን ዘዴዎች 32
3.2.1. ፈተናዎች.....33
3.2.2. ከሁለቱ ዓመታት የተሻለ የፈተና ይዘት ብቃት ያለው (ዓመት)
የፈተና ውጤት 34
3.2.3. የጽሑፍ መጠይቆች 34
3.2.3.1. ለተማሪዎች የቀረቡ የጽሑፍ መጠይቆች.....35
3.2.3.2. ለመምህራን የቀረቡ የጽሑፍ መጠይቆች.....36
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃዎች ትንታኔና ከጥናቱ የተገኘ ውጤት 38
4.1. የተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ቅኝትና የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራንና
ተማሪዎች ዳራ.....33
4.1.1 የተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች አጭር ቅኝት 38
4.1.2. የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ.....40
4.2. በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. የቀረቡት ፈተናዎች ከመርሐትምህርቶች እና
ከመማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች ጋር ያላቸው ዝምድና
ትንተና፡፡.....42
4.2.1. በ1997 ዓ.ም. የቀረበው ፈተና ይዘት ከመርሐ ትምህርቱ ይዘት ጋር ያለው ዝምድና
ትንተና 43

4.2.1.1. ፈተናው ከማዳመጥ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና 43
4.2.1.2. ፈተናው ከንግግር ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና 44
4.2.1.3. ፈተናው ከአንብቦ መረዳት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....45
4.2.1.4. ፈተናው ከጽሕፈት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....46
4.2.1.5. ፈተናው ከሥነጽሑፍ ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....47
4.2.1.6. ፈተናው ከሥነልሳን ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....48
4.2.1.6.1. በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች ትንተና.....48
4.2.1.6.2. በቃላት ፍቺ ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች ትንተና 49
4.2.1.6.3. በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች ትንተና 50
4.2.1.7. ፈተናው ከክሂልና ከዕውቀት ይዘቶች ጋር ያለው አጠቃላይ ዝምድና ትንተና.....51
4.2.2. በ1998 ዓ.ም. የቀረበው ፈተና ይዘት ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና 53
4.2.2.1. ፈተናው ከማዳመጥ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና 53
4.2.2.2. ፈተናው ከንግግር ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....54
4.2.2.3. ፈተናው ከንባብ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....55
4.2.2.4. ፈተናው ከጽሕፈት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....56
4.2.2.5. ፈተናው ከሥነጽሑፍ ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....57
4.2.2.6. ፈተናው ከሥነልሳን ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና.....58
4.2.2.6.1. በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች 58
4.2.2.6.2. በቃላት ፍቺ ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች.....59
4.2.2.6.3. በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች 60
4.2.2.7. ፈተናው ከክሂልና ከዕውቀት ይዘቶች ጋር ያለው አጠቃላይ ዝምድና ትንተና.....61
4.3. ከመርሐትምህርቱ ጋር ባላቸው ዝምድና መሠረት በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. ፈተናዎች መካከል ያለው ንፅፅራዊ ትንተና.....63
4.4. የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ተዛምዶ እና ልዩነት 66

4.4.1 የ1997 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ተዛምዶ እና ልዩነት 68
4.4.2. የ1998 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመርሐትምህርቱና ልከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ተዛምዶ እና ልዩነት፡፡.....71
4.5. በሁለት የመንግሥትና በሁለት የግል ትምህርት ቤቶች መካከል የ1997ዓ.ም. ሀገር አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ንጽጽራዊ ትንተና.....74
4.5.1. የሁለት የመንግሥትና የሁለት የግል ትምህርት ቤቶች የ1997ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት.....74
4.5.2. ከመምህራንና ከተማሪዎች በመጠይቁ የተሰጠ ምላሽ 75
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ.....87
5.1. ማጠቃለያ.....87
5.2. የመፍትሔ ሐሳብ.....90
የመሠረታዊ ቃላትና ሐረጋት ብያኔ.....92
ዋቢ ጽሑፎች.....94
አባሪዎች.....98
አባሪ 1፣ ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCAT ION CERTIFICATE EXAMINATION 1997 E.C .Page 001.....98
አባሪ 2፣ ሀገር-አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና፣ ግንቦት/1997ዓ.ም.....102
አባሪ 3፣ ሀገር-አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና፣ ግንቦት/1998 ዓ.ም.....126
አባሪ 4፣ በ1996 ዓ.ም. ለዘጠነኛ ክፍል ተሻሽሎ የቀረበው የመርሐትምህርት ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች፣.....151
አባሪ 5፣ በ1996 ዓ.ም. ለአሥረኛ ክፍል ተሻሽሎ የቀረበው የመርሐትምህርት ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች፣.....156
አባሪ 6፣ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ፡፡.....160
አባሪ 7፣ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ 164
ማረጋገጫ.....168

ምስጋና

ከሁሉም በላይ በዚህ የጥናት ሂደት የተለያዩ ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት፣ የጥናቱን ረቂቅ ደጋግመው እያነበቡ በማረም የማያቋረጥ ድጋፋቸውን ለሰጡኝና ጥናታዊ ጽሑፉ ከዳር እንዲደርስ ለተባበሩኝ አማካሪዬ ለዶ/ር አረጋ ኃ/ሚካኤል ጥልቅ የሆነ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በጥናቱ ወቅት መረጃ በመሰብሰብ እና መጠይቁን በማስሞላት ለረዱኝ የዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር፣ ምክትል ርዕሰ መምህር እና መምህራን፤ የየካቲት 12 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር፣ የሚኒሚዲያ ክፍል ኃላፊና መምህር፣ ሌሎች መምህራንና የቤተ መጻሕፍቱ ሠራተኞች፤ የማጂክ ካርፔት እና የነገው ሰው 2ኛ ደረጃ ርዕሳነ-መምህራንና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፤ የቦሌ ክፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ቤተ-መጻሕፍት ሠራተኞች፣ እንዲሁም ለድህረ-ምረቃ ክፍል ትምህርት ጓደኞቼ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

ለጥናቱ የሚረዱ የተማሪዎች ፈተና ውጤቶችን አዘጋጅተው በመስጠት ለተባበሩኝ የሀገር-አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለእስታትስቲክስ መረጃ ክፍል ኃላፊና ፀሐፊ፤ ለአዲስ አበባ ትምህርት ቤሮ የእስታስቲክስ መረጃ ክፍል፣ እንዲሁም በጥናታዊ ሥራዎች ወቅት መጻሕፍትን በተገቢው መልኩ እንዳገኝ ላይሰለቹ ለረዱኝ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ቤተመጻሕፍት ሠራተኞች በሙሉ በጣም አመሰግናችዋለሁ።

በሁለት ዓመታት የትምህርት ቆይቃዬ ወቅት በእስፖንሰር ሺኘነት ድጋፍ በማድረግ ለተባበሩኝ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ፣ ለቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት፤ እንዲሁም ይህን ጥናት ለማከናወን ይረዳኝ ዘንድ አስፈላጊውን ገንዘብ እንዲሰጠኝ በማድረግ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ፤ በተጨማሪም ይህንን ጥናት በኮፒተር ለተየቡልኝ ይህን ጥናት በኮምፒውተር ለተየቡልኝ ለወሪ/ት ሰብለ፣ ለወሪ/ት ጤናዬ እና ለወሪ/ት ትዝታ ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም ከሁሉም ባላነሰ ይህን ትምህርት እንድቀጥል ሁለገብ ድጋፋቸው ላልተለየኝ ቤተሰቦቼ፤ ለባለቤቴ፣ ለልጆቼ፣ ለእናቴ ፣ለአባቴ፣ ለእህቶቼ፣ ለወንድሞቼ እና ለቀሩት ዘመዶቼና ጓደኞቼ በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የሠንጠረዥ ዝርዝር

ገጽ

ሠንጠረዥ 1- በ1997፣ በአዲስ አበባ የሚገኙ የትምህርት ቤቶች ዓይነት፣ ብዛት እና የተማሪዎችን ቁጥር የሚያሳይ.....27

ሠንጠረዥ 2- በአዲስ አበባ፣ በ1998 ዓ.ም. በ10ሩ ክፍለ ከተሞች (sub -cities) የሚገኙ የ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዓይነትና ብዛት በቁጥርና በመቶኛ ስሌት.....28

ሠንጠረዥ 3- በ 1998 ዓ.ም. የአዲስ አበባ የ10ሩ ክፍለ ከተሞች ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛት.....29

ሠንጠረዥ 4- በ1998 ዓ.ም. የአዲስ አበባ የ10ሩ ክፍለ ከተሞች የመንግሥትና የግል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብዛት 29

ሠንጠረዥ 5- በ 1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ለ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሀገር-አቀፍ ፈተና የተመዘገቡ ተፈታኞች.....30

ሠንጠረዥ 6- የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች ስርጭትና ለጥናቱ የዋለው ብዛት.....36

ሠንጠረዥ 7- የመምህራን የጽሑፍ መጠይቆች ስርጭትና ለጥናቱ የዋለው ብዛት.....37

ሠንጠረዥ 8- በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተሰጡ የ10ኛ ክፍል ማጠቃለያ ብሔራዊ ፈተናዎች የትኩረት ነጥብና ብዛት.....39

ሠንጠረዥ 9- የጽሑፍ መጠይቁን በተገቢው ሁኔታ ሞልተው የመለሱ መምህራን ዳራ.....40

ሠንጠረዥ 10- የጽሑፍ መጠይቁን በአግባቡ ሞልተው የመለሱ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ዳራ.....41

ሠንጠረዥ 11- የ1997 ዓ.ም ፈተና ከማዳመጥ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....43

ሠንጠረዥ 12- የ1997 ዓ.ም. ፈተና ከንግግር ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....44

ሠንጠረዥ 13- የ1997 ዓ.ም. ፈተና ከአንብቦ መረዳት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....45

ሠንጠረዥ 14- የ1997 ዓ.ም. ፈተና ከጽሕፈት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....46

ሠንጠረዥ 15- የ1997 ዓ.ም. ፈተና ከሥነጽሑፍ ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....47

ሠንጠረዥ 16- የ1997 ዓ.ም. ፈተና በሰዋስው ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና.....48

ሠንጠረዥ 17- የ1997 ዓ.ም. ፈተና በቃላት ፍቺ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና.....49

ሠንጠረዥ 18- የ1997 ዓ.ም. ፈተና በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና.....50
ሠንጠረዥ 19- የ1997 ዓ.ም. ፈተና ከክሂልና ከዕውቀት ይዘቶች ጋር ያለው አጠቃላይ ዝምድና.....51
ሠንጠረዥ 20- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና ከማዳመጥ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....53
ሠንጠረዥ 21- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና ከንግግር ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....54
ሠንጠረዥ 22- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና ከንባብ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....55
ሠንጠረዥ 23- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና ከጽሕፈት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....56
ሠንጠረዥ 24- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና ከሥነጽሑፍ ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና.....57
ሠንጠረዥ 25- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና.....58
ሠንጠረዥ 26- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና በቃላት ፍቺ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና 59
ሠንጠረዥ 27- የ1998 ዓ.ም. ፈተና በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና.....60
ሠንጠረዥ 28- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና ከክሂልና ከዕውቀት ይዘቶች ጋር ያለው አጠቃላይ ዝምድና.....61
ሠንጠረዥ 29- ከመርሐትምህርቶቹ ጋር ባላቸው ዝምድና መሰረት በ 1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. ፈተናዎች መካከል ያለው ንፅፅራዊ ዝምድና.....63
ሠንጠረዥ 30- የ 1997 ዓ.ም. ፈተና ይዘት ከመርሐትምህርቶቹ ጋር ባሳየው ልዩነት ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ዝምድና.....68
ሠንጠረዥ 31- የ 1998 ዓ.ም. ፈተና ይዘት ከመርሐትምህርቶቹ ጋር ባሳየው ልዩነት ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ዝምድና.....71
ሠንጠረዥ 32- የ 1997 ዓ.ም. የሁለቱ ዓይነቶች ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ንጽጽር 74
ሠንጠረዥ 33- በመጠይቁ ክፍል አንድ ግላዊ መረጃዎች ውስጥ ለተራ ቁጥር 1.4 እና 1.10 ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኘ ምላሽ.....75
ሠንጠረዥ 34- በመጠይቁ ክፍል አንድ ግላዊ መረጃዎች ውስጥ ለተራ ቁጥር 1.4 እና 1.10 ከግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኘ ምላሽ.....76

ሠንጠረዥ 35- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ውስጥ ለተራ ቁጥር 14 ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኘ ምላሽ.....77
ሠንጠረዥ 36- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ውስጥ ለተራ ቁጥር 14 ከግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኘ ምላሽ.....78
ሠንጠረዥ 37- በመጠይቁ ክፍል አንድ ግላዊ መረጃዎች ውስጥ ለተራ ቁጥር 5 እና 9 ከ12ኛ ክፍል ከመንግሥትና ከግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ.....79
ሠንጠረዥ 38- በመጠይቁ ክፍል አንድ ግላዊ መረጃዎች ውስጥ ለሚገኝ ጥያቄ ለተራ ቁጥር 6 ከ12ኛ ክፍል ከመንግሥትና ከግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ.....80
ሠንጠረዥ 39- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ለሚገኙ ጥያቄዎች ለተራ ቁጥር 10-12 ከ12ኛ ክፍል የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ.....81
ሠንጠረዥ 40- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ለሚገኙ ጥያቄዎች ለተራ ቁጥር 10-12 ከ12ኛ ክፍል የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ.....82
ሠንጠረዥ 41- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ለሚገኙ ጥያቄዎች ለተራ ቁጥር 1 እና 2 ከ12ኛ ክፍል የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ.....84
ሠንጠረዥ 42- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ለሚገኙ ጥያቄዎች ለተራ ቁጥር 1 እና 2 ከ12ኛ ክፍል የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ.....85

የአባሪዎች ዝርዝር

1. ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE EXAMINATION 1997 E.C. page 001.
2. ሀገር-አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና፣ ግንቦት/1997ዓ.ም.::
3. ሀገር-አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና፣ ግንቦት/1998ዓ.ም.::
4. በ1996 ዓ.ም. ለዘጠነኛ ክፍል ተሻሽሎ የቀረበው የመርሐትምህርት ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች::
5. በ1996 ዓ.ም. ለአሥረኛ ክፍል ተሻሽሎ የቀረበው የመርሐትምህርት ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች፣
6. በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ9 እስከ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ::
7. በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ::

አጠቃለ

የዚህ ጥናት ዓላማ በሀገር-አቀፍ ደረጃ በተሰጠው የአሥረኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በመንግሥትና በግል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የውጤት ልዩነትና ደረጃን በመፈተሽ ማነጻጸር ነው።ለጥናቱም ዋና የመረጃ ምንጭ በመሆን በአገልግሎት ላይ የዋሉት በሀገር-አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት የተዘጋጁት የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. ፈተናዎችና የተማሪዎች ውጤቶች ናቸው። እንዲሁም በአጋዥ የመረጃ መሣሪያነት የጽሑፍ መጠይቆች በአገልግሎት ላይ ውለዋል። መጠይቆቹም በ4 ትምህርትቤቶች ለ23 መምህራንና 240 ተማሪዎች ተሰራጭተው መረጃ ተሰብስቦ በትነተናው ተካተዋል።

የጥናቱ ትኩረት የሆነውን የውጤት ንጽጽር ከማየት በፊትም የሁለቱን ዓመታት ፈተናዎች ይዘት በዋናነት ከ9ኛ እና ከ10ኛ ክፍል መርሐትምህርቶች ይዘት፣ በተጨማሪም በታየው ልዩነት መነሻነት ከ9ኛ እና ከ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ይዘት አንጻር ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች አንዱ በሆነው የይዘት ተገቢነት (Content Validity) ተፈትሿል። ስለሆነም የይዘት ብቃት ያለው የ1997 ዓ.ምቱ ፈተና በመሆኑ ለውጤት ንጽጽሩ ዋና የመረጃ መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል።

በተደረገው ፍተሻም በ1997 ዓ.ም. የቀረቡት የፈተና ይዘቶች ከ4 የመርሐትምህርቶች ይዘቶች ጋር አይዛመዱም፤ የ1998 ዓ.ም. ፈተና ይዘቶች የማዳመጥ ክሂልን ይዘት ከማስቀረቱ በስተቀር የማይዛመዱ ይዘቶች የሉትም። በ1997 ዓ.ም. በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቱ ይዘቶች 9 ሲሆኑ፣ በ1998 ዓ.ም. ግን 10 ናቸው። የማዳመጥ ክሂል በ1997 ዓ.ም. ሀገር አቀፍ ፈተና ውስጥ ሲጠየቅ፣ በ1998 ዓ.ም. ሀገር አቀፍ ፈተና ውስጥ ግን አልተጠየቀም። ይህም የ1997 ዓ.ም. ፈተና በክሂሎች ናሙና ስርጭት ማመጣጠን በኩል የተሻለ ጠንካራ ጐን ያለው ፈተና አድርጐታል።

የ1997 ዓ.ም. ፈተና ከመርሐትምህርቶቹ ጋር የማይዛመዱ 4 ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ አንድ ይዘት (ጥምር ቃላት የሚል) በመገኘቱ የዚህን ዓመት የማይዛመዱ ይዘቶች ከ4 ወደ 3 ዝቅ አድርጓቸዋል። እንዲሁም ያልተጠየቁ የፈተና ይዘቶች 9 የነበሩትን የመማሪያ መጻሕፍቱ አንድ ይዘት (የመረጃዎች አጠቃቀም ሥር ዐውደ-ጥበብ፣ ኢንዴክስ የሚለው) ባለመኖሩ ወደ 8 ዝቅ ያደርጉታል። በሌላ በኩል የ1998 ዓ.ም. የማይዛመዱ ይዘቶች የሉትም፤ በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ ይዘቶች 10 የነበሩትን የመማሪያ መጻሕፍቱ አንድ ይዘት (የመረጃዎች አጠቃቀም የሚለው) ባለመኖሩ ወደ 9 ዝቅ ያደርጉታል።

በ1997ዓ.ም. የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና በሁለቱ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች 6.1%ቱ"A" ፣ 27.3%ቱ "B"፣ 60.8%ቱ “C” ፣ 3.5%ቱ “D” ፣ 2.2%ቱ “F” ውጤት አምጥተዋል። እንዲሁም በሁለቱ የግል ትምህርት ቤቶች 23.4%ቱ"A" 45.2% "B"፣ 30.2%ቱ "C"፣ .4%ቱ "D" እና .8% ቱ “F” ውጤት አግኝተዋል። በአጠቃላይ ከውጤቱ የምንረዳው የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አብዛኞቹ (60.8%) "C" ውጤት ያገኙ ሲሆን፣ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ግን አብዛኞቹ "B"ውጤት አግኝተዋል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

በፈተና ምንነት ዙሪያ የተለያዩ የመስኩ ባለሙያዎች የየበኩላቸውን ሀሳብ ሰንዝረዋል። ከእነዚህም ውስጥ Richard (1990:15) ፈተና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተገኘው ዕውቀትና የታየው የባህርይ ለውጥ መመዘኛ እንደሆነ ገልፀዋል። ከዚህ በተጨማሪ Brown (1994:252) ሲያብራሩ፣ ፈተና ማለት በቀላል አገላለፅ በአንድ በተወሰነ ነጥብ ላይ የአንድን ግለሰብ ችሎታ ወይም ዕውቀት መለካት የሚያስችል ዘዴ ነው ብለዋል። Ur (1991:33) እንደገለፁት ደግሞ፣ ፈተና በአንድ ፈታኝ የቀረበን ሥራ ተፈታኝ የሆኑት አካላት ምን ያህል እንደተገነዘቡ እና በሥራ ላይ ማዋል እንደቻሉ ለማወቅ የሚረዳ መሣሪያ ነው።

የቋንቋ ትምህርትና የቋንቋ ፈተና ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። በዚህም መሠረት Harrison (1983:1) እና Hughes (1989:1) እንዳሰፈሩት፣ ፈተና ከመማር–ማስተማር ሂደት ጋር ንድፈ ሐሳባዊና ተግባራዊ ተዛምዶ አለው። ስለዚህ ማስተማርና ፈተና ተነጣጥለው የሚታዩ ነገሮች አይደሉም። ይህም ተፈጥሯዊ የሆነ ዝምድናቸው አንዱ ለአንዱ የዕድገት መሰረት እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። በመሆኑም በፈተናው ውስጥ የሚገኙ መረጃዎች መልዕክት ሊያስተላልፉ የሚችሉት በፈተናው ዝግጅት ወቅት አስፈላጊው ጥንቃቄ የተደረገ እንደሆነ ነው። በተጨማሪም Hughes (1989:2) እንደሚሉት፣ የቋንቋ ትምህርት ለቋንቋ ፈተና፣ የቋንቋ ፈተናም ለቋንቋ ትምህርት መሰረት ሲሆኑ ይታያል።

ይህም በመሆኑ ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት የቋንቋ ፈተናዎች ለረጅም ጊዜያት በስርአት ሲገመገሙና ሲመዘኑ ቆይተዋል። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዘርፍም ከመጀመሪያው ከዳኛቸው ወርቁ (1955) የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ አንስቶ በርካታ ጥናቶች ተጠንተዋል። ከነዚህም መካከል ተስፋዬ ኃይሌ (1964)፣ ታረቀኝ ተፈራ (1993)፣ ዘላለም ጌታቸው (1998)፣ ወዘተ. በቋንቋ ፈተና ላይ የተመሠረቱ ጥናቶች ናቸው። ይሁን እንጂ እስካሁን ድረስ በፈተና ዙሪያ ከተጠኑት ጥናቶች መካከል ለዚህ ጥናት የሚቀርበው የሸዋዬ ተካ (1994) "በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ቤቶች የሚሰጥ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ንፅፅራዊ ምልከታ" በሚል ርዕስ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ የተጠና ጥናት ነው። ነገር ግን የሸዋዬ ተካ (1994) ጥናት ትኩረት በ9ኛ ክፍል የክፍል ፈተናዎች ይዘት ላይ ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በአስረኛ ክፍል አገር-አቀፍ ፈተና ውጤት ላይ ነው።

የዚህ ጥናት አቅራቢም በዚህ ስራ ውስጥ ያካሄደችው ጥናት የግምገማ አቅጣጫ በተማሪዎች ውጤት ላይ የሚያተኩር ይሆናል። በዚህ ርዕስ ላይ የተተኮረበትም ዋና ምክንያት የጥናቱን መነሻ ጥያቄ ይመልሳል ከሚል እምነት የመነጨ ነው። ይኸውም በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የብሔራዊ ፈተና ውጤት ልዩነት ምን ያህል መሆኑን በጥናት የማረጋገጥ ፍላጎት ለጥናቱ መነሻ ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም አጥኚዋ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በመንግሥት ትምህርት ቤት ለበርካታ ዓመታት የአማርኛ ቋንቋን በምታስተምርበት ሂደት ውስጥ በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪዎች የፈተና ውጤት ልዩነት አለ? ካለስ ልዩነቱ ምን ያህል ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ስትጠይቅ የነበረ ሲሆን፣ ለጥያቄው መልስ የማግኘት ፍላጎቷ ይህን ጥናት እንድታካሂድ አነሳስቷታል። ለጥናቱ ሂደትም መጀመሪያ ለውጤት ንፅፅሩ ዋና የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለው ፈተና ብቃት መታወቅ አለበት። በመሆኑም በአገርአቀፍ ደረጃ የተዘጋጀው የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ይዘት ብቃት ከፈተና ሙመዘኛ መስፈርቶች በይዘት ተገቢነት /Content validity/ በዋናነት ከመርሐትምህርቱ ይዘት አንፃር፣ በልዩነት ደግሞ ከመማሪያ መፅሐፉ ይዘት አኳያ ተፈትሿል። በዚህም መሠረት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል፤

1. የ1997 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ይዘት ብቃት ምን ያህል ነው?
2. የ1998 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ይዘት ብቃት ምን ያህል ነው?
3. ከ1997 ዓ.ም. እና ከ1998 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል ፈተናዎች የተሻለ ብቃት ያለው የትኛው ነው?
4. በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአሥረኛ ክፍል አገርአቀፍ ፈተና የውጤት ልዩነት አለ? ካለስ ልዩነቱ ምን ያህል ነው? የልዩነቱ ምክንያትስ ምንድን ነው?

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ለቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ መሻሻል አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል የሚል መነሻ ሀሳብ አለ። Heaton (1975:15) እንደሚሉት፣ የቋንቋ

ትምህርትና የቋንቋ ፈተና የማይነጣጠሉ አካላት ናቸውና በቋንቋ ፈተና ውጤት የታዩ ልዩነቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥም ሲንፀባረቁ የቆዩ ናቸው የሚል ግምት አለ።

1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገርአቀፍ ፈተናን ውጤት በማነጻጸር መገምገም ነው። በዚህ መሰረትም የፈተና ውጤት ትንተናን መሰረት ባደረገ መልኩ በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች በፈተናው ላይ ያገኙትን ውጤት ለመተንተን ይሞክራል። በመሆኑም የጥናቱ ዋና ዓላማ፤

- በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስረኛ ክፍል አገርአቀፍፈተና የውጤት ልዩነትና ደረጃን መፈተሽ ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካትም
  1. የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል ፈተና ብቃት በይዘት ተገቢነት መስፈርት መፈተሽ፣
  2. ከ1997 ዓ.ም. እና ከ1998 ዓ.ም. ፈተና የተሻለ ይዘት ያለውን ለንጽጽሩ በዋና የመረጃ ምንጭነት መምረጥ፣
  3. ይህ የቋንቋ ፈተና ውጤት ልዩነት፣ ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል መፈተሽ ነው።

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

የቋንቋ ፈተናና የቋንቋ ትምህርት ጥብቅ ትስስር አላቸው። በመሆኑም የቋንቋ ትምህርት የቋንቋ ፈተናን ይዘትና አቀራረብ ከመጠቆሙ ጎን ለጎን የቋንቋ ፈተናም የቋንቋ ትምህርት ይዘትንና አካሄድን ሊጠቁም ይችላል። በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተናንና ትምህርትን ለያይቶ ማየት ያስቸግራል (Heaton 1975:1)።

- የዚህ ጥናት አጠቃላይ ጠቀሜታ በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ለተመሳሳይ የክፍል ደረጃ የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ አገርአቀፍ ፈተናዎች በተማሪዎች ላይ ተቀራራቢና ተመጣጣኝ ውጤት እንዲያስገኙ ሲሆን፣ ይህም በሁለቱ መካከል ያለው የውጤት ልዩነት ምን ያህል እንደሆነ በጥናት ከተረጋገጠ በኋላ ችግሩን መቅረፍ የሚገባው ክፍል ትኩረት እንዲያደርግበት ነው።

- እነዚህ ሁኔታዎች የፈጠሯቸውን ችግሮች በማስተዋል ለሚደረጉ ቀጣይ ጥናቶችም ይህ ጥናት መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ሐሳቦችን ያቀርባል። በመሆኑም በዚህም ጥናት መነሻነት የቀጣይ ጥናት አቅራቢዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

- ከላይ በተጠቀሱት ሐሳቦች ከቋንቋ መማር-ማስተማር ጋር ግንኙነት ያላቸው ወገኖች ሁሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሲሆን፣ በተለይ በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ የሚገለገሉበት መርሐትምህርትና የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አንድ አይነት ሆኖ እያለ፣ በአሥረኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ላይ የተራራቀ ውጤት ማስመዝገብ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሻሻል የሚገባ ጉዳይ በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ የትምህርት ቤቶች አስተዳዳሪዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች በከፍተኛ ደረጃ ያሉ አካላት ሁሉ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።

1.4 የጥናቱ ክልልና ገደብ

ይህ ጥናት በናሙናነት በመውሰድ የሚያተኩረው በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ ሁለት የግልና ሁለት የመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ሲሆን፣ እነዚህም ከግል ትምህርት ቤቶች ማጂክ ካርፔት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የነገው ሰው 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆኑ፣ ከመንግሥት ደግሞ ዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የካቲት 12 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጠቃሾች ናቸው። ጥናቱ የሚያተኩረው በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. በሁለት ዓመታት በተሰጡት የአሥረኛ ክፍል አገርአቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤቶች ላይ የተገደበ ሆኖ በዓላማው ውስጥ ለተጠቆመት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ብቻ ነው። በዚህ መሰረት ጥናቱ የክፍል ወይም የሞያሌል ፈተናዎችን ውጤት አይዳስስም። ከ1997 ዓ.ም. በፊትም በአዲስ አበባ በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች በተሰጡት የፈተና ውጤቶች ላይም ይህ ጥናት ትኩረት አያደርግም። ጥናቱ በተጠቀሱት በናሙናነት በተወሰዱ አራት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ውጤት ላይ የተገደበ ይሆናል።

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በዚህ ክፍል ለጥናቱ አጋዥ የሚሆኑ ተዛማጅ ጽሑፎች ይቃኛሉ። በተለይም ከጥናቱ ጋር ጥብቅ ትስስሮሽ ያላቸውና ጥናቱን ለማካሄድ በመነሻነት ያገለገሉት ዓበይት ጉዳዮች ቅድሚያ ተሰጥቷቸዋል።

2.1 የሥርዓተትምህርትና የቋንቋ መርሐትምህርት የጋራ ባሕርያትና ልዩነት

የቋንቋ መርሐትምህርት ከሥርዓተትምህርት የሚፈልቅ፣ አንድን ውስን የቋንቋ ትምህርት እንዴት ማስተማር እንደሚቻል የሚጠቁም፣ የትምህርቱን ዓላማ፣ ይዘት፣ አቀራረብ፣ ጊዜና ግምገማ የሚያመላክት ሰነድ ነው። በመሆኑም ከሥርዓተትምህርት ይልቅ ዝርዝር የሆነ፣ የትምህርት መሣሪያዎች (ጽሑፎች) አዘጋጆች መነሻ ሊሆን የሚችል የትምህርት ይዘቶችን በየደረጃው የሚሸነሽን እና ለተግባር የሚያመቻች እቅድ ነው (Dubin and Olshtain 1986:35; Cunningsworth 1995:53-54)።

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሐሳብ የምንረዳው የቋንቋ መርሐትምህርት አንድ የተወሰነ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራምን ከግብ ማድረስ ይቻል ዘንድ ተማሪ ምን መማር እንዳለበት፣ አስተማሪውም ምን ማስተማር እንዳለበት እና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ምን እንደሆነ በዝርዝር የሚያሳይ በመሆኑ ለየክፍል ደረጃው በሚዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ይዘቶችን አዋቅሮ ለማዘጋጀት እንደመሠረት ሆኖ ያገለግላል።

2.2 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ መለየ ባሕርያት

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በመርሐትምህርቱ የተገለፀትንና እለት በእለት ተግባራዊ በመሆን የሚታዩትን የትምህርት ዓላማዎች ስኬታማ ለማድረግ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ይህም ከመርሐትምህርቱ ጋር ያለውን ቁርኝት በግልፅ ያሳያል (Richards እና Rodgers 1986:24-25፣ Harmer 1991:256)። ለዚህም ነው Nunan (1994:98) የመማሪያ መጻሕፍትና የመርሐትምህርት ግንኙት አስመልክተው «የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ያለምንም ማወላወል መርሐትምህርቱ በተግባር የሚገለጽበት ነው» ያሉት።

ይህም በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ይዘት ሲገመገም፣ ሲሻሻል፣ ሲዘጋጅ፣ ሲፃፍ፣ ወዘተ. የተዘጋጀውን መርሐትምህርት መሠረት ማድረግ እንዳለበት የሚያስገነዝብ በመሆኑ በሁለቱም መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንዳለ ያሳያል። Carter (1973:605) "የመማሪያ መጻሐፍ የተወሰነ የትምህርት ጥናትን የያዘ፣ ሥርዓት ባለው መንገድ የተደራጀ፣ ለተወሰነ የትምህርት ደረጃ የሚዘጋጅና ለአንድ የትምህርት ዘርፍ እንደ ዋና የጥናት ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል መሣሪያ ነው" በማለት ይገልፃሉ።

ከላይ ጥቅሶቹ የሚያስረዱት የቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍት በቋንቋ ሥርዓተትምህርትና በቋንቋ መርሐትምህርት ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው የተማሪውን የቋንቋ መማር ፍላጎት ለማርካት ይችሉ ዘንድ የተመረጡና የተደራጁ የቋንቋ ልምዶችን የያዙ መሆናቸው ነው።

2.3 የቋንቋ ፈተና ምንነት፣ ዓላማ እና አስፈላጊነት

በዚህ የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ንኡስ ክፍል ውስጥ ስለቋንቋ ፈተና ምንነት፣ ዓላማ እና አስፈላጊነት ለማየት ተሞክሯል። በዚህም መሠረት፣ ይህ ጥናት በዚህ ርዕስ የተለያዩ ጸሐፍት ያነሱትን ሐሳብ ዋቢ በማድረግ በአጭሩ ለማቅረብ ይሞክራል።

2.3.1 የቋንቋ ፈተና ምንነት

Harrison (1983:1) እና Alderson and et, al (1995:1)" እንደሚሉት፣ ፈተና ማለት ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ዙሪያ የተገነዘቡትን ዕውቀት ለመለካት፣ ከአንድ የክፍል ደረጃ ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ ለመወሰን፣ ለአንድ ሥራ ብቁ የሆነን ሰው ለይቶ ለመምረጥ፣ እንዲሁም አንድ ሰው ያለውን የዕውቀት ደረጃ ለመረዳት የሚያገለግል መሣሪያ ነው።

Mehrens እና Lehmann (1974:3) እንደሚያስገነዝቡት፣ የቋንቋ ፈተና የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና፣ የመጻፍ ክሂሎችን እንዲሁም የሥነጽሑፍና የሥነልሳን ዕውቀቶችን ከመማራቸው በፊት ያላቸውን ቅድመ–ችሎታ ለመገምገም ወይም ከተማሩ በኋላ የቋንቋ ችሎታቸውን መሻሻል ለመለካትና ምን ያህል ለውጥ እንዳመጡ ለመረዳት የምንመዝንበት ፈተና ነው። ጠቅለል ባለ መልኩ፣ የቋንቋ ፈተና የቋንቋ ችሎታን ለመለካት በጥቅም ላይ የሚውል ከቋንቋ ትምህርት በፊት ወይም በኋላ ሊሰጥ የሚችል፣ በሥርዓት የሚቀርብ የጥያቄዎች ስብስብ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
A.S. LIBRARY

Genesee and Upsher (1996:154) ደግሞ፣ «የቋንቋ ፈተና ስለቋንቋው ምንነት ወይም በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ሊስተዋሉ የሚችሉ ምላሾችን የሚጠይቁ ተግባራትን አካቶ የያዘ ነው። ከምላሹ የሚገኘው ውጤትም የትምህርቱን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ ይተነተናል» በማለት ገልፀውታል። ከዚህም ገለፃ የቋንቋ ፈተና ስለቋንቋ ምንነት፣ በቋንቋው ስለመገልገል ከክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ)፣ እንዲሁም ከዕውቀት ዘርፍ (ሥነልሳን እና ሥነጽሑፍ) የሚጠይቁ ጥያቄዎችን ይዞ ሊዘጋጅ የሚችል መሣሪያ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በተመሳሳይ ሁኔታ Atkins, Hailom and Nuru (1996:171)፣ በቋንቋ ፈተና ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ይዘቶች፣ ከክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) እንዲሁም ከዕውቀት ዘርፎች (ሰዋሰው፣ ቃላት፣ ንበትና ሆሄ) መሆናቸውን በመግለፅ ከላይ የቀረበውን ሃሳብ ያጠናክራሉ።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ፣ የቋንቋን ፈተና ምንነት በሚመለከት የሰፈሩት ጽንሰ ሐሳቦች እንደሚያስገነዝቡት፣ የቋንቋ ፈተና በቋንቋ ትምህርት ወቅት በሚካሄዱ መስተጋብሮች አማካይነት ተማሪዎች በተገነዘቧቸው የቋንቋ ክሂሎችና የቋንቋ ዕውቀቶች ላይ መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ መመዘኛዎች ናቸው።

2.3.2 የቋንቋ ፈተና ዓላማ

በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ፈተና እንደ ዋነኛ የትምህርት መሣሪያ ተደርጎ ሊታይ ይችላል። Heaton (1975:6-7) ሲያብራሩ፣ የፈተና አንዱ ዓላማ የተማሪን ችሎታ ለመመዘን፣ ለማወዳደር ወይም ለመምረጥ ነው። Davies (1968:70) እንዳስገነዘቡት፣ አንድ ፈተና ለተወሰነ ዓላማ ይዘጋጃል፤ ዓላማው ግልጽ ካልሆነ ደግሞ ለመለካት የተፈለገውን ነገር ሊመዝን አይችልም።

Clark and Star (1996:378) በበኩላቸው ሲገልጹ፣ የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች ምን መማር እንዳለባቸው እና ምን እንደተማሩ በመለየት ለመምህራን ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ይረዳል፤ ተማሪዎች ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲለዩ ይረዳቸዋል፤ የተማሪዎችን ሁለንተናዊ ገፅታ በመገምገም መምህራን እርምት ለመውሰድ ያስችላቸዋል፤ ተማሪዎችንም ለበለጠ ሥራ ያተጋቸዋል። ፈተና ተማሪዎች እየተማሩ መሆናቸውንና የሥራቸውን ውጤት ለማየት የዓመቱን ትምህርት በማጠናቀቅ ወደ ተከታዩ የክፍል ደረጃ መሸጋገር የሚገባቸውን ለመለየት ቁልፍ ሚናን ይጫወታል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

በመሆኑም የፈተና ዓቢይ ዓላማ መምህራንንም ሆነ ተማሪዎችን መገምገም ነው። ስለዚህ መምህራን የአሠራር ሂደታቸውን በመፈተሽ ውጤቱን የሚመዝኑበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች ያላቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለመለየት ያስችላቸዋል። Teshome Demisse (1995:28)፣ Underhill (1982:18)ን በመጥቀስ ስለ ቋንቋ ፈተና ሲገልጹ፣ የተለያዩ ፈተናዎች የሚደራጁትና በአብዛኛው ተፈጻሚ የሚሆኑት ለተለያዩ ዓላማዎች ነው። ይኸውም ለምደባ፣ ለዕድገት እንዲሁም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የታየውን የችሎታ እና የብቃት ደረጃን ለመፈተሽ በሚል ሊሆን ይችላል።

በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተና ሲታሰብ የትምህርቱ ይዘት መሠረት ያደረገው ዓላማ ከግብ እንዲደርስ የተማሪዎችን ድክመትና ጥንካሬ በመለየት ፈተናው ለወደፊቱ ማሻሻያዎችን ሊያስገኝ በሚችል መልኩ መዘጋጀት እንዳለበት ነው።

2.3.3 የቋንቋ ፈተና አስፈላጊነት

Heaton (1975:6-7) ሲያብራሩ፣ የፈተና አስፈላጊነት ልክ አንድ የሕክምና ዶክተር መጀመሪያ የበሽተኛውን ሕመም ለማወቅ ምርመራ የሚያደርገውን ያህል ነው። ስለሆነም ፈተና የመምህሩንም ሆነ የተማሪዎቹን ድክመቶች እና ጥንካሬዎች በመመርመር የሕክምናውን ያህል ጠቀሜታ አለው። እንዲሁም መምህሩ የትኛው የቋንቋ ትምህርት ክብደት እንዳለው እንዲያውቅ የሚያስችለው ሲሆን የመርሐትምህርቱን እና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ውጤታማነት ለመገምገም ያስችለዋል። ስለሆነም ጥሩ ፈተና እንደ አንድ የማስተማሪያ መሣሪያ የሚቆጠር ነው።

እንደ Bachman (1990:54) አገላለጽ፣ የቋንቋ ፈተና ሁለት ዋና ዋና ጥቅሞች አሉት፤

1ኛ. በትምህርት ትግበራ እቅድ አውድ ውስጥ ውሳኔ ለመስጠት እንደመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።

2ኛ ለቋንቋ ለመዳና ለቋንቋ ትምህርት ምርምር በሚያስፈልግበት ጊዜ ለችሎታ ወይም ለባሕርይ መለያ አመላካች ሆኖ ያገለግላል። እንዲሁም በትምህርት ሂደት መረጃ በመስጠት ለምዘና ተግባር ያገለግላል።

በአጠቃላይ Heaton (1990:9-18) የቋንቋን ፈተና አስፈላጊነት በዝርዝር ሲገልጹ፣ "የተማሪዎችን የቋንቋ ዕድገት ለውጥ ለማወቅ፣ ተማሪዎችን ለማበረታታት፣ በትምህርት ጊዜ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን ችግሮች ለመለየት፣ የተማሪዎችን ችሎታ ለመፈተሽ፣ ተማሪዎችን በችሎታቸው ለመመደብ፣ ተማሪዎችን እንደየዝንባሌያቸው ለመምረጥ እና የተማሪዎችን ደረጃ ለመወሰን ጠቃሚ ናቸው" ብለዋል።

2.4 የቋንቋ ፈተናና የቋንቋ ትምህርት ተዛምዶ

መፈተንና ማስተማር ጥብቅ ግንኙነት እንዳላቸው በርካታ ምሁራን ይመሰክራሉ። ከእነዚህም ውስጥ Heaton (1975:15) ሲገልፀ፣ በቋንቋ መማር–ማስተማር ሂደት ሁለቱም መስኮች ተነጣጥለው ሊሰጡ አይችሉም። የቋንቋ ትምህርትና የቋንቋ ፈተና ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው የቋንቋ መማር–ማስተማር ሂደት አካሎች ናቸው። በመሆኑም አንደኛውን አካል ከሌላው ነጥሎ ማየት በፍፁም አይቻልም። ስለዚህ የሁለቱን የጠበቀ ትስስር በውል በመገንዘብ ለሁለቱም ክፍሎች አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት ጎን ለጎን ማራመድ ይኖርብናል ብለዋል።

እንደ Hughes (1989:2) አባባል፣ ዘወትር ማስተማር ቀዳሚ፣ መፈተን ደግሞ ተከታይ ሥራ ነው. መባል የለበትም፤ ጥሩ ፈተና ለማስተማር ሂደት እንደ አመላካች ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በአሉታዊ የማስተማር አቀራረብ የተነሳም የትምህርቱ ሂደት ቢሰናከል ፈተና ችግሩን በመጠቆም የመማር–ማስተማር አጠቃላይ ገፅታውን ለማስተካከል ይረዳል። በሌላ በኩል Davies (1988:5) በበኩላቸው ጥሩ ፈተና ያስተማርነውን በመፈተን ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ፈተና ከማስተማር በኋላ የሚመጣ ተከታይ ሂደት ነው. ይላሉ። Bachman (1990:54) የሁለቱን ግንኙነት አስመልክተው ሲገልጹ፣ ፈተናዎች በመማር–ማስተማሩ ሂደት ጠቃሚ የሆነ መረጃ በመስጠትና ለውሳኔ በማብቃት እንዲሁም ምጋቢ ምላሽ በመስጠት ያገለግላሉ።

Dejenie (1994:3) Davies (1968)ን ዋቢ በማድረግ ሲገልጹ፣ "ጥሩ ፈተና በትምህርቱ ሂደት ላይ የተመሠረተ እስከሆነ ድረስ እንደታዛቨር ሠራተኛ የሚቆጠር ነው." ብለዋል። አያይዘውም Hughes (1989:2)ን በመጥቀስ ሲያስገነዝቡ፣ ፈተና ትምህርትን ተከትሎ መቅረብ ያለበት ብቻ ነው ብለን መጠበቅ የለብንም። ነገር ግን ማሰብ ያለብን የጥሩ ፈተናን ደጋፊነትና አስፈላጊም ሲሆን በመጥፎ የማስተማር ሂደት ላይ ተጽዕኖ በማድረግ እንደማስተካከያ ሆኖ በሥራ ላይ ሊውል እንደሚችል ነው፤ ብለዋል።

2.5 የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች

በርካታ ምሁራን የቋንቋ ፈተናዎችን በዓይነት ለመመደብ የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም በተለያዩ ክፍሎች ይከፍሏቸዋል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በዚህ መሠረት Harrison (1983:9) የፈተና ዓይነቶችን በአራት፣ Brown (1994:258) በአምስት፣ Alderson and et, al (1995:11–2) በአምስት፣ Bachman (1990:58–76) በሰባት፣ Heaton (1988:171–3) በአምስት፣ እንዲሁም Hughes (1989:9–14) በአራት ይከፍሏቸዋል። Carroll (1980:74–84) ደግሞ ፈተናው የሚሰጥበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ፣ የፈተና ዓይነቶችን በሦስት ይመድባቸዋል። ይኸውም ቅድመ ትምህርት ፈተናዎች (ብቃት መወሰኛ፣ ቅድመ ችሎታ መለኪያ)፣ የትምህርት ጊዜ ፈተናዎች (ለውጥን፣ ጥንካሬን፣ ድክመትን መለኪያ፣ ሂደታዊ)፣ እንዲሁም ድኅረ–ትምህርት ፈተናዎች (ማጠቃለያ ፈተና፣ ዕድገትን ማሳያ ፈተና) በማለት ይገልፃሉ። ነገር ግን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መልክ መከፋፈል እንደኛውን በሌላው ውስጥ የማካተት ወይም የመዘርዘር እንጂ መሠረታዊ ልዩነት አይታይባቸውም። ለዚህም ማስረጃ ሊሆን የሚችለው ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የCarroll(1980:74-84) የፈተና ዓይነቶችን የመደበበት መንድ ነው።

በአጠቃላይ የመስኩ ምሁራን የቋንቋ ፈተናዎችን በተለያዩ መስፈርቶች በመጠቀም በዓይነት ለመመደብ የበኩላቸውን ሐሳብ ሠንዝረዋል። የፈተና ዓይነቶች መብዛትና መለያየት ምክንያትም የሚቀርቡበት ዓላማ መለያየት እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ። ሆኖም ግን ከእያንዳንዱ መስፈርት አኳያ የጋራ ሆነው የሚጠቀሱትን በመለየት አውጣጥቶ ብያኔ በመስጠት መጠቀም ተገቢ እንደሆነ ለቃውንት ያስገነዝባሉ። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት በተተኳሪነት አራት ዋና ዋና የፈተና ዓይነቶችን ለመዳሰስ ተሞክሯል።

2.5.1 የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና

Heaton (1975:164)፣ Harrison (1983:4)፣ Hughes (1989:145) ሲገልፁ፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች የተማሩትን የቋንቋ ትምህርት ዕውቀት የሚለካ ሳይሆን ያላቸውን የተፈጥሮ ችሎታና ዝንባሌ ለመመዘን የሚጠቅም ነው። በተመሳሳይ መልኩ Brown (1994:258) ሲገልፁ፣ ይህ የፈተና ዓይነት የአንድን ግለሰብ አጠቃላይ ዕውቀት ወይም ብቃት ለማወቅ እና የወደፊቱን ሁኔታ ለመለየት ይረዳ ዘንድ የሚዘጋጅ ፈተና ነው።

Heaton (1990:11) ሲያብራሩ፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ትምህርቱ ለተፈታኞች ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎችን እንደ ቋንቋ ችሎታቸው በቡድን ለመመደብ የሚያስችል ነው። በዚህ የፈተና ዝግጅት ጊዜ በተቻለ መጠን አጠቃላይ ይዘት ያላቸው ነጥቦችን ማካተት ተገቢ ነው። Hughes (1989:14) በበኩላቸው፣ "ይህ የፈተና ዓይነት ባልታቀደ

ወይም አ.–መደበኛ በሆነ መንገድ በተገኘ ግንዛቤ ላይ የሚመሰረት ፈተና ሲሆን ተማሪዎች በአንድ የተወሰነ እንቅስቃሴ ላይ ያላቸውን የብቃት ደረጃ የምንለካበት ነው" ይላሉ።

በአጠቃላይ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ለአንድ የትምህርት መስክ የታቀደን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተፈታኞች በዚያ መስክ ላይ የሚኖራቸውን የብቃት ደረጃ በመለየት ለደረጃው የሚመጥኑ ተማሪዎችን ለማግኘት የሚረዳ ነው።

2.5.2 የደረጃ መለኪያ ፈተና

Heaton (1990:17) ሲገልጹ፣ የደረጃ መለኪያ ፈተና በተፈታኞች መካከል የተገኘውን ውጤት እርስ በርስ አያነጻጽርም፤ ነገር ግን በጥያቄዎች ላይ የአንድን ተፈታኝ ስኬታማነት ያሳያል። በተመሳሳይ ሁኔታ Hughes (1989:9-10)፣ Bachman (1990:71)፣ Brown (1994:257) እና Alderson et, al (1995:293) ሲገልፀ፣ የደረጃ መለኪያ ፈተና ሲዘጋጅ መሠረት የሚያደርገው የቋንቋ ንድፈ ሐሳቦችን ሲሆን በዚህም ዋና ትኩረቱ በቋንቋ ይዘት ላይ ነው። ከዚህ አንፃር የቀረበው ፈተና አጠቃላይ ወይም ሁለገብ የቋንቋ ችሎታ የሚጠይቅ ከሆነ የደረጃ መለኪያ ፈተና ይባላል።

Harrison (1983:6-9) እንደገለጹት፣ የደረጃ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች በአንድ በተወሰነ መስክ ያላቸውን ችሎታ የሚያሳይ ነው። ዋና ተግባሩም በተገኘው ለውጥ አማካይነት ደረጃ ለመስጠት ያስችላል። በተመሳሳይ መልኩ ይህን የፈተና ዓይነት Weir (1993:6) እና Brown (1994:258) እንዳሉት፣ ተማሪዎች ለሚቀጥለው አንድ የተወሰነ ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል ተብሎ ለተገመተ መርሐ ግብር ናሙና ለመውሰድ የሚያገለግል ነው ይላሉ።

የደረጃ እና የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተፈታኞችን በአንድ በተወሰነ ምድብ ውስጥ ለመፈረጅ የሚያስችሉ በሆናቸው እና በመደበኛ መርሐ ግብር ወይም ሊሰጥ ከታሰበው ትምህርት በፊት ያሉ ችግሮችን ለመፈተንና አሰቀድመው የሚቀግቡ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ (Lado 1961፣ Alderson 1988)።

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ሐሳቦች ስናይ፣ የደረጃ መለኪያ ፈተና በአንድ የትምህርት መርሐግብር ላልታቀፉና የተለያየ የትምህርት ዳራ ላላቸው ሰዎች ሊቀርብ የሚችል፣ ከልዩ ልዩ የትምህርት ተቋማት የሚመጡ ተማሪዎች ያላቸውን የቋንቋ

ዕውቀት ለመመዘን የሚሰጥ የፈተና ዓይነት ነው። ዋና ትኩረቱም ተማሪዎች ወደሚገቡበት የትምህርት መስክ ያላቸውን ዕውቀት መለካት ነው።

2.5.3 ጥንካሬ እና ድክመት መለኪያ ፈተና

ይህ የፈተና ዓይነት መምህራን በየጊዜው ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች የሚሰጡት የፈተና ዓይነት ሲሆን የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ምን ያህል እንደሆነ ለመገንዘብ ይረዳል። Hughes (1995:13) ሲገልጹ፣ የጥንካሬ እና ድክመት መለኪያ ፈተና መምህራን በየተለያየ ጊዜ ለተማሪዎቻቸው የሚያቀርቡት ፈተና ሲሆን የሚዘጋጀው ተማሪዎች በየትኛው ክፍለትምህርት ላይ ተጨማሪ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ለመለየት ነው። ይህንኑ ሐሳብ በመጋራት Alderson and et. al (1995:12) ሲያስገነዝቡ፣ ይህ የፈተና ዓይነት ከችሎታ መለኪያ ፈተና ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል፤ የሚለየው ተማሪው በተወሰኑ የቋንቋ ክሂሎችና ንኡስ ዘርፎች ላይ የሚያሳየውን ድክመትና ጥንካሬ የሚመረምር በመሆኑ ነው።

የጥንካሬ እና ድክመት መለኪያ ፈተና ትኩረት የሚያደርገው ከተማሪዎች ወቅታዊ ችግሮች ላይ ሲሆን ይህም ተገቢ የሆነውን የማስተማሪያ ዘዴ ለመለየት ወሳኝ ሚና አለው (Hughes 1989፣ Bachman 1990:60 እና Zimba 2005:20 13-14)። በተመሣሣይ መልኩ Brown (1994:259) እንደገለጹት፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና በተማሪዎች ላይ የታየውን የቋንቋ ይዘት ችግሮች በተከታታይ የሚፈተሽበት ነው። Baker (1989:3) እና Harrison (1983:6) ሲያብራሩ፣ ጥንካሬና ድክመትን ለመለካት የሚዘጋጅ ፈተና በመማር–ማስተማር ሂደት ላይ የታዩትን መሰናክሎች ለይቶ ለማውጣት ሩይዳው ከፍ ያለ ነው።

Rivers (1968፣288) ሲያስገነዝቡ፣ ጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና መደበኛ ያልሆነ ፈተና ሲሆን መምህራን ለራሳቸው ክፍል ተማሪዎች የሚሰጡዋቸው ፈተናዎች ናቸው። እነዚህ ፈተናዎችም የመምህራንንና የተማሪዎችን ድክመትና ጥንካሬ ለማወቅ የሚረዱ ናቸው። እንዲሁም የትኛው የትምህርት ዘርፍ ተጨማሪ ልምምድ ወይም ጥናት እንደ ሚያስፈልገው ይጠቁማሉ፤ በመሆኑም መምህሩ ወደሚቀጥለው ትምህርት ለማለፍ እንዲችል ተማሪዎቹ ምን ያህል ዝግጁ መሆናቸውን ለማወቅ የሚረዳው ነው።

ጠቅለል ባለ መልኩ ከምሁራኑ ሐሳብ እንደምንረዳው፣ የጥንካሬና የድክመት መለኪያ ፈተና በመማር–ማስተማሩ ሂደት ላይ ተማሪዎች የቀረበላቸውን የትምህርት ይዘት መገንዘብና አለመገንዘባቸውን ለማረጋገጥ የሚዘጋጅ የፈተና ዓይነት ነው።

በዚህም መምህራን በተማሪዎች ላይ የታየውን በጎም ሆነ ደካማ ጎን ባቀረቡት ፈተና አማካይነት ለመለየት ያስችላቸዋል። ከታዩት ችግሮችም በመነሳት ለተሻለ ሥራ ሊበቁ ይችላሉ።

2.5.4 የችሎታ መለኪያ ፈተና

የችሎታ መለኪያ ፈተና ከዋና ዋና የፈተና ዓይነቶች አንዱ በመሆኑ እና ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚዛመድ ስለሆነ ከላይ እንደተጠቀሱት የፈተና ዓይነቶች በጥቅል ከማቅረብ ይልቅ ዘርዘር ባለ መልኩ የፈተናው ምንነት፣ የፈተናው ይዘት አመራረጥና አቀራረብ ስልት በሚሉ ሦስት ንዑሳን ርዕሶች ከዚህ በታች ለማየት እንሞክራለን፤

2.5.4.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና ምንነት

Harrison (1983:4)፣ Baker (1989:4)፣ Heaton (1990:13)፣ Zimba (2005:20) ሲገልጹ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና በመማር-ማስተማር ሂደት የተከናወኑትን ድርጊቶች መሠረት አድርጎ የሚቀርብ ፈተና ነው። ከዚህ በተጨማሪ Heaton (1975:163) ሲገልጹ፣ ብዙዎቹ በየአመቱ የሚሰጡ የትምህርት ቤት ፈተናዎች እንዲሁም ማንኛውም በብሔራዊ ደረጃ የተወሰነ የትምህርት ዝርዝር መዳበሩን ወይም መጠናቀቁን ለማወቅ የሚሰጡ ፈተናዎችም የችሎታ መለኪያ ፈተና ናቸው።

Heaton (1988:III)፣ Hughes (1989:10–13) ሲገልጹ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና በቋንቋ ፈተና የእድገት ደረጃ ውስጥ ግንባር ቀደሙ የፈተና አይነት ሆኖ ይገኛል። በመሆኑም ስላለውም በቋንቋ ፈተና ውስጥ ተደጋግሞ የሚገኝ የፈተና አይነት ነው።

በአጠቃላይ የችሎታ መለኪያ ፈተና አንድ ተማሪ በተወሰነ የጊዜ ክልል ውስጥ የተማረውን ነገር የምንመዝንበትና በዚያ ጊዜ ውስጥ የተሰጠውን ትምህርት ምን ያህል እንዳዳበረ የምንገመግምበት የፈተና ዓይነት ነው። Harrison (1983:5)ሲያስገነዝቡ፣ "የችሎታ መለኪያ ፈተና አጠቃላይነት ያለው እና ከትምህርት ሂደት በኋላ የሚሰጥ ሲሆን፣ የጥንካሬና ድክመት ፈተና ግን ዝርዝር የሆኑ የመማሪያ ክፍል ሥራዎችን ያካተተ ነው" ይላሉ።

2.5.4.2 የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት አመራረጥ

ይህ የፈተና ዓይነት ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል መገንዘባቸውን ለመለካት እንዲያስችል በመርሐትምህርቱ ላይ የሠፈሩትን ይዘቶች ከግምት በማስገባት የሚዘጋጅ ነው። በመሆኑም የችሎታ መለኪያ ፈተና በዓመቱ ማጠቃለያ ወይም

ADAMA UNIVERSITY LIBRARY

በትምህርቱ ማብቂያ ላይ መደበኛነቱን ጠብቆ የሚሰጥ ፈተና ነው (Harrison 1983: 4፣ Hughes 1989:10-13፣ Heaton 1990:13፣ 1975፣ X-Xi)።

Finocchiaro and Bromfit (1986:186) ሲያብራሩ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና በአንድ ትምህርት ውስጥ በስርዓተ ትምህርቱ የተዳሰሱትን ነጥቦች በማማሽ አመት ወይም በዓመቱ ማጠቃለያ አልያም በየምዕራፉ ማብቂያ ላይ ተግባራዊ የሚሆን ፈተና ነው ብለዋል። ይህን ሐሳብ በማጠናከር Brown (1994:259) ሲያስገነዝቡ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና በቀጥታ ከመማሪያ ክፍል ትምህርት፣ ከተዳሰሱት ምዕራፎች ባጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርቱን ተመርኩዞ የሚዘጋጅ ነው። በመሆኑም የችሎታ መለኪያ ፈተና በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ከታቀፉ የትምህርት ይዘቶች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው።

Madsen (1983:199)፣ Heaton (1988:III፣1975:X-Xi)፣ Hughes (1989:10-13) ሲያስገነዝቡ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና ባብዛኛው የተማሪውን ተነሳሽነት ለመጨመር የሚሰጥ ሲሆን መምህሩም የራሱን የማስተማር ብቃት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ይፈትሽበታል። በተጨማሪም በመማር-ማስተማር ሂደቱ ላይ ያለው ደካማ ጎን የት አካባቢ እንደሆነ ለመለየት ይረዳዋል። ይህ ፈተና የተወሰነ መርሐትምህርት መጠናቀቁን ለማመልከት የሚዘጋጅ ነው። ለምሳሌ የአመቱ መጨረሻ ፈተናዎች፣ የክፍተኛ 2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናዎችና ብሔራዊ ፈተናዎች ናቸው። እነዚህ ፈተናዎች ከክፍል ፈተናዎች ጋር ይመሳሰላሉ፤ ምክንያቱም ፈተናዎቹ ባጠቃላይ መሠረት የሚያደርጉት በመርሐ ትምህርቱ ላይ ሆኖ የሚመዝኑትም ቀደም ሲል የተማሩትን በመሆኑ ነው።

Hughes (1989:10-13) ሲገልጹ፣ "ይህ ፈተና በመርሐትምህርቱ ክፍለ ትምህርት ዝርዝር ላይ ማለትም በመጻሕፍቱ እና ሌሎች ጥቅም ላይ በዋሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ ያተኩራል" ይሉና ይህ ፈተና ተማሪዎች የተማሩትን በመጠየቃቸው ሚዛናዊነት ሊታይበት ቢችልም በሌላ በኩል ጎጂ ጎን አለው፤ ይኸውም መርሐትምህርቱ በመጥፎ ሁኔታ ከተቀረፀ፣ ወይም መጻሕፍቱ እና ሌሎች የማስተማሪያ መሣሪያዎች አመራረጥ መጥፎ ከሆነ የፈተናው ውጤት ፈሩን የለቀቀና አሳሳች ሊሆን ይችላል። ስለሆነም የፈተና ውጤት ጥሩ መሆን የትምህርቱን ዓላማ ብቃት በትክክል ላያሳይ ይችላል፤ ብለዋል።

Alderson et, al (1995:12) ሲገልጹ፣ ለትምህርት የቀረበውን መርሐትምህርት ወይም የመማሪያ መጽሐፍ መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅና ትምህርቱ ሲጠናቀቅ ለተማሪዎች የሚቀርብ ፈተና ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ Genesee እና Upsher (1996:153) የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች የትምህርቱን ዓላማዎች ወይም የቋንቋውን ይዘቶች ምን ያህል እንደተገነዘቡት መረጃ የሚሰጥ የፈተና ዓይነት ነው በማለት ይገልፀዋል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ምንነት ዙሪያ በምሁራን መካከል ልዩነት ያለ አይመስልም፤ ነገር ግን በይዘት አመራረጥ ላይ ልዩነት ይንፀባረቃል። ይኸውም ልዩነቱ በሁለት የተከፈለ ሲሆን፣ አንደኛው የምሁራን ወገን የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ለትምህርት የቀረበውን መርሐትምህርት መሠረት ማድረግ አለባቸው ሲሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ መርሐትምህርቱን ሳይሆን ዓላማውን መሠረት ማድረግ አለባቸው ይላሉ። ስለዚህ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ለትምህርት የቀረበውን መርሐ ትምህርት ይዘት መሠረት ማድረግ እንዳለባቸው ይታመናል።

Harrison (1983:9) እና Madson (1983:189) ሲገልፀ፣ የመርሐትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፍ ይዘቶች የትምህርቱን ዓላማ በዝርዝር ለማስፈር ታትኖ የሚዘጋጁ እንደመሆናቸው በፈተና ናሙና አመራረጥ ላይ ይበልጥ ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል፤ ይላሉ።

በአጠቃላይ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪው ምን ተምሮ? ምን እንዳወቀ? ለመመዘን የሚዘጋጁ በመሆናቸው ግልፅ የሆነ ዓላማ ለተነደፈላቸው የቋንቋ ትምህርቶች፣ የፈተናውን ይዘቶች፣ በዓላማዎች ላይ መመስረት ያስፈልጋል። የትምህርት ዓላማቸው ግልፅ ላልሆኑት ደግሞ፣ የፈተናውን ይዘቶች፣ በመማሪያ መጽሐፎች እና በመርሐትምህርት ይዘቶች ላይ መመስረት ተገቢ ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

2.5.4.3 የችሎታ መለኪያ ፈተና አቀራረብ ስልቶች

የቋንቋ ፈተና አቀራረብ ስልቶች ጥያቄዎችን ለተፈታኞች የምናቀርብባቸው ዘዴዎች ናቸው። ከላይ ከቀረቡት የተለያዩ ምሁራን ገለጻ አንፃር ለማየት እንደተሞከረው፣ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎች ቀደም ብለው የተማሩዋቸውን ይዘቶች ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን የያዙ መሆን አለባቸው። በመሆኑም ከሌሎች የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች ይልቅ በዚህ ፈተና ውስጥ ምን ማካተት እንዳለብን ለመወሰን ከፍተኛ ጥንቃቄ ይጠይቃል (Heaton 1975:5፣ 1988፣ III: 1990:14)።

Madson (1983:199)፣ Heaton(1988:III)፣ Hughes (1989:10-13)፣ Bachman (1990:60–61) እንደሚያስገነዝቡት፣ በዚህ አይነት ፈተና በተቻለ መጠን ተማሪዎች ቀድመው የተማሩዋቸውን ይዘቶች ሊወክሉ የሚችሉ ናሙና ይዘቶችን ማካተት ብቻ ሳይሆን የጥያቄ አቀራረብ ስልታቸው ብቃት ያለው ተገቢ ናሙናዎችን ከመምረጥ ጎን ለጎን የቋንቋ ፈተና አቀራረብ ዘዴዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

Norman (1988:36-8) እና Ur (1991:35-7) ሲያብራሩ፣ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መገንዘብ አለመገንዘባቸውን ለመፈተሽ ፈተና ወሳኝ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ፈተናው የትምህርቱን አላማ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን የተከተለ ሊሆን ይገባል፤ Weir (1990:42) እንደሚሉት፣ ፈተናው በመማሪያ መፅሀፍ እና በመርሐትምህርቱ ላይ የቀረቡትን ዓላማዎች ለመገምገም የሚችል መሆን አለበት፤ እንዲሁም አንድን የቋንቋ ፈተና ስናዘጋጅ በእውቀት ዘርፎችም ይሁን በክሂል ዘርፎች የጥያቄዎች መደራረብ ወይም መደጋገም መኖር የለበትም።

Hughes (1989:59) ሲገልጹ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና የአቀራረብ ስልቶች ማለት ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ይዘት ላይ ያሳዩትን የባሕርይ ለውጥ እና ያላቸውን ችሎታ ለመለካት የሚያስችል ስልት ነው። የአቀራረብ ስልቶቹም የሚይዟቸው ነጥቦች የሚገኘውን የባህርይ ለውጥ አስተማማኝነት እና ተገቢነት የሚያመላክት፣ ለውጤት አሰጣጥ ወይም የአስተራረም ትክክለኛነት የሚያስገኝ፣ በጊዜና በአቅም ላይ ብክነትን የማያስከትል፣ በማስተማር ሂደት ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ የሚያስገኝ ሊሆን ይገባዋል ብለዋል።

በአጠቃላይ የችሎታ መለኪያ ፈተና ተቀዳሚ ዓላማው መርሐትምህርቱን መሠረት በማድረግ በመማር–ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘት ምን ያህል መጨበጣቸውን እና የትምህርቱ ዓላማ ምን ያህል ግብ መምታቱን የምንፈትሽበት የፈተና ዓይነት ስለሆነ የናሙና አወሳሰዱ ብርቱ ጥንቃቄን ይጠይቃል። ይኸውም ሁሉንም የትምህርት ይዘቶች ለፈተና ማቅረቡ ባይቻልም፣ በዛ ያሉትንና ለትምህርቱ ወሳይ ናሙና ናቸው ተብለው የታመነባቸውን ጥያቄዎች ማውጣት ከፈተና አዘጋጆች የሚጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት ነው።

እነዚህን ነጥቦች መሠረት በማድረግ የቋንቋ ፈተና የአቀራረብ ስልቶችን ምርጫ–ነክ እና ገለፃ–ነክ የአቀራረብ ስልቶች በማለት በሁለት ምድብ መመደብ ይቻላል። ከእነዚህ መካከል ለዚህ ጥናት ይበልጥ ቅርበት ያለውን የምርጫ ነክ የአቀራረብ ስልት በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን።

2.5.4.3.1 ምርጫ–ነክ የአቀራረብ ስልቶች

እንደፈተናዎች አግባፍ ሁኔታ የፈተና አቀራረብ ስልቶች በተለያዩ ምድቦች ይከፈላሉ። በምርጫ–ነክ የአቀራረብ ስልት ሊካተቱ የሚችሉ ጥያቄዎች በፍጥነት ምላሽ ሊገኝ ባቸው የሚችሉና ሊሟሉ የሚችሉትን ጥያቄዎች የሚያጠቃልል ነው። ምክንያቱም እነዚህ የጥያቄ ዓይነቶች አንድ ትክክለኛ መልስ ስለሚኖራቸው ሲሆን፣ ፈተናዎቹም

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በመሣሪያዎች ወይም በሰው ኃይል ሊታረሙ የሚችሉ ናቸው። በመሆኑም ምርጫ ነክ ጥያቄዎች በበርካታ አገራት ተቀባይነትን ያተረፉ እየሆኑ መጥተዋል (Heaton: 1990:30)። Wood (1965) በበኩላቸው ሲገልጹ፣ በምርጫ ነክ የአቀራረብ ስልት የሚዘጋጁ ፈተናዎች ለደረጃው የተዘጋጀውን ሥርዓተትምህርት ሊዳስሱ ይችላሉ። በዚህም በርካታ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ከማስቻሉም በላይ ለእርማት አመች ነው። በምርጫ–ነክ የአቀራረብ ስልት የሚዘጋጁ ጥያቄዎች በርካታ እንደሆኑና ዋና ዋናዎቹ ምርጫ፣ እውነት ሐሰት፣ ማዛመድ፣ ክፍት ቦታ መሙላት እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ።

ከዚህ በመቀጠል በምርጫ–ነክ የአቀራረብ ስልት ውስጥ ሊካተቱ ከሚችሉት ፈተናዎች ውስጥ አንዱና የጥናቱ ትኩረት የሆነውን የብሔራዊ ፈተና ቅርጽን የሚያንፀባርቅ የምርጫ ጥያቄዎችን በመጠኑ ለመዳሰስ ይሞከራል፤

2.5.4.3.1.1 የምርጫ ጥያቄዎች

እንደ Heaton (1975:14)፣ Hughes (1989:59)፣ Ur (1991:93) አገላለጽ፣ በምርጫ–ነክ አቀራረብ ስልቶች አማካይነት ከሚቀርቡት ውስጥ ለማዘጋጀት አስቸጋሪ የሆነው የምርጫ ጥያቄ ዓይነት ሲሆን በእሱም ላይ ተመሥርተው የሚዘጋጁት ጥያቄዎች ለማረም አመቺ ናቸው። በሚዘጋጁበትም ጊዜ ለጥያቄው በአሳሳች መልስነት እስከ አምስት የሚደርሱ አማራጮች እንዲቀርቡ በርካታ ጸሐፍት ይመክራሉ። እንዲሁም Norman (1988:77) እንዳስረዱት፣ የምርጫ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ወቅት ሊያተኩሩባቸው ከሚችሉት ይዘቶች ውስጥ ዕውቀትን መረዳት እና አተገባበርን የሚለኩ መካተት ይኖርባቸዋል። አንድ የምርጫ ጥያቄ በሚዘጋጅበት ጊዜ የጥያቄው ዋና ክፍል መሪ (አምድ) ሲባል የጥያቄውን መልስ ለመመለስ የሚያስችሉ ምርጫዎች አማራጮች ይባላሉ፤ ከእነዚህ አማራጮች ውስጥ አንዱ ትክክለኛ መልስ ሲሆን ሌሎች ቀሪዎቹ አማራጮች አሳሳቾች በመባል ይጠራሉ (Heaton 1975:16-17)።

Heaton (1975:15-18) እና Norman (1988:42-55) እንደሚያብራሩት፣ በምርጫ ጥያቄዎች ውስጥ ዋና ጥያቄ (አምድ) እና አማራጮች በሚዘጋጁበት ጊዜ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገባ ዋና ጥያቄ (አምድ) አንድ ትክክለኛ መልስ እንዲኖረው ማድረግ፣ ተገቢ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም መጠቀም፣ የትምህርቱን ዓላማ ግብ መቸነት የሚያጎለብቱ እንዲሆኑ ማስቻል፣ በአንድ ጊዜ አንድ የቋንቋ ገፅታን መፈተን፣ አሉታዊ አቀራረቦችን ማስወገድ፣ ከተጠቀሙም ግልፅ ማድረግ፣ የተማሪዎችን የሥነልሳን ችሎታ ያገናዘበ ማድረግ፣ የቅለት ክብደት ቅደም ተከተል መጠበቅ፣

ግልፅና አጭር ማድረግ፣ ግልጽ ፍንጮችን አለማካተት፣ የተደጋጋፊነት ባህሪ ያላቸው ጥያቄዎች ማስወገድ ወዘተ. ሲሆኑ አማራጮችን በሚመለከት ደግሞ የቅርጽ ተመሳሳያቸውን ማነልበት፣ የሰዋስዋዊ ግድፈቶችን ማስወገድ፣ ሁሉም መልስ እንዲሆኑ እና መልስ እንደሌላቸው የሚጠቅሱ አማራጮችን አለማዘውተር፣ ግልፅ ያልሆኑ አማራጮችን አለመጠቀም፣ በይዘት ፍፁም የተራራቁ አማራጮችን አለመጠቀም፣ የርዝማኔ ተመሳስሎ እንዲኖራቸው ማድረግ ወዘተ. ናቸው።

2.6 የቋንቋ ፈተና መመዘኛዎች

የቋንቋ ፈተና መመዘኛዎችን በተመለከተ የመስኩ ባለሙያዎች የተለያዩ የአመዳደብ ሥርዓት አላቸው። ለምሳሌ Brown (1994:257) በሦስት (አስተማማኝነት፣ ተገቢነት እና ተተግባሪነት)፣ Harrison (1983:10-13) በአራት (አስተማማኝነት፣ ተገቢነት፣ ተተግባሪነት እና ለያይነት)፣ Heaton (1990:8) በሁለት (አስተማማኝነትና ተገቢነት)፣ Cohen (1991:496-7) በሦስት (አስተማማኝነት፣ ተገቢነት እና ለእርማት አመቺነት)፣ Lado (1961:30-2) በአራት (አስተማማኝነት፣ ተገቢነት፣ ቁጥብነት እና ለእርማት አመቺነት፣ Finocchiaro and Sako (1983:24-31) በአራት (አስተማማኝነት፣ ተገቢነት፣ አጠቃላይነትና ተተግባሪነት)፣ወዘተ. በማለት ይከፍሏቸዋል።

ፈተና ጥሩ የመመዘኛ መሣሪያ እንዲሆን ከተፈለገ በጥንቃቄ መዘጋጀት ይገባዋል። ለዝግጅቱ ደግሞ የጥሩ ፈተና ባሕርያትን ማወቅንና ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል። ፈተናዎችንም አይተን ጥሩ ዝግጅት የተደረገባቸውንና ያልተደረገባቸውን ለመለየት በርካታ መመዘኛዎችን መለኪያ ልናደርግ እንችላለን። ከነዚህ የተለያዩ መመዘኛዎች መካከል አብዛኞቹ የመስኩ ምሁራን የሚስማሙባቸውንና ደጋግመው የሚያነሷቸውን የጋራ ነጥቦች ለማየት ስንሞክር፣ በዋናነት የሚዳሰሱት Lado (1961)ን፣ Harris (1969)ን፣ Bachman (1990)ን፣ በመጥቀስ Grandman and Reed (1997:200-205) ሲገልጹ፣ ፈታኞች ብዙ ጊዜ የጥሩ ፈተናዎች መሠረታዊ ባሕርያት ናቸው ብለው የሚገልጿቸው ባብዛኞቹ ምሁራን ዘንድ የሚጠቀሱት አስተማማኝነት፣ ተገቢነትና ተተግባሪነት የተሰኙ የፈተና መመዘኛዎች ናቸው። አንዳንድ ምሁራን ለአብነት ያህል Finocchiaro and Sako (1983:24-31) አጠቃላይነትን በመጨመር ባሕርያቱን አራት ያደርጓቸዋል። ሆኖም አብዛኞቹ ምሁራን ይህንን የአጠቃላይነት ባሕርይ በተገቢነት ስር ያካትቱታል። ከዚህ በታች በውስጣቸው ሊካተቱ የሚችሉ መመዘኛዎችን እና ሌሎች ጽንሰ ሐሳቦችን ለማቅረብ እንሞክራለን።

2.6.1 አስተማማኝነት ጠ

Hughes (1989:29)፣ Heaton (1990:6)፣ Chohen (1991:496) እና Grandman and Reed (1997:200-205) ሲያስገነዝቡ፣ አስተማማኝነት አንድ ፈተና በተለያየ ጊዜ በተደጋጋሚ ለአንድ ግለሰብ በሚሰጥበት ጊዜ ተመሳሳይ ውጤት ማስገኘቱ ነው። Harrison (1983:10) እና Brown (1994:253-4) ሲገልፁ ፣ በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ፈተናዎች በተለያዩ ጊዜያት ሲቀርቡ በተፈታኞች ላይ ተከታትሎ ተመሳሳይነት ከታየ ፈተናው አስተማማኝነት አለው ማለት ይቻላል። ይኸውም የአንድን ፈተና ውጤት መደጋገም ወይም በቀጣይነት መምጣት የሚያሳይ ሲሆን በዚህም ውጤቱ ላይ ምስስሎሽ ይታያል።

Harrison (1983:11)፣ Hughes (1989:37-42) ሲያስገነዝቡ፣ የአንድን ፈተና አስተማማኝ ነት ከሚያስተጓጉሉ ባህርያት ውስጥ ቢጠቀሱ፣ ረጅምና አሰልቺ አረፍተ ነገሮች ሲካተቱ፣ ፈተናው የተሰጠበት አካባቢ ወይም ሁኔታ፣ የተፈታኞች ወይም የተማሪዎች የጤና ሁኔታ፣ የፈተናው ውጤት አሰጣጥ መንገድ፣ የፈተና ዓይነቶች፣ አመራረጥ ሁኔታ፣ ግልጽነት የጎደላቸው ቃላትና ሐረጋት እንዲሁም መመሪያዎች መካተት ወዘተ. ናቸው።

ጠ

Briere and Brown (1971)ን ዋቢ በማድረግ Cohen (1991:496) ሲገልጹ፣ የፈተናን አስተማማኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ሦስት ዋና ዋና ተፅዕኖዎች አሉ። እነሱም የፈተና ሁኔታዎች፣ አካባቢያዊ ሁኔታዎች እና ግለሰባዊ ሁኔታዎች ናቸው። በመጀመሪያው ውስጥ ሊዳሰሱ ከሚችሉት ውስጥ የፈተናው ዓይነት፣ የእያንዳንዱ የፈተና ይዘት ዓይነት፣ የአጠቃላይ ፈተናዎች ርዝማኔ ይጠቀሳሉ። በሁለተኛው ሁኔታ ውስጥ ፈተናውን ያዘጋጀው አካል የፈተና አወጣጥ ሁኔታ፣ የክፍሉ ሁኔታ (ብርሃን፣ ምቾት)፣ ውጫዊ ድምጾች እና ሌሎች ተፅዕኖዎች ይጠቀሳሉ። በመጨረሻም ግለሰባዊ ሁኔታዎች ከሚባሉት ውስጥ የተፈታኙ አካላዊ እና ሥነልቦናዊ ሁኔታዎችን ያካትታል።

በአጠቃላይ አስተማማኝነት የሚባለው አንድን ፈተና በተለያዩ ጊዜያት ለተፈታኞች በሚቀርብበት ጊዜ የሚገኘውን ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ውጤት ማሳየት ነው።

2.6.2 ተገቢነት

የተለያዩ ምሁራን የቋንቋ ፈተና ተገቢነትን በተመለከተ የበኩላቸውን ሀሳብ ሠንዝረዋል። ከእነዚህም ውስጥ Harrison (1983:11)፣ Hughes (1989:22)፣ Heaton (1990:7፣1975:X)፣ Brown (1994:254)፣ Grandman and Reed (1997:200-205) እና Zimba (2005:22) እንደገለፁት፣ ተገቢነት የሚባለው አንድ የቋንቋ ፈተና መለካት ያለበትን

ችሎታ በትክክል መመዘን ሲችል ነው። በተመሳሳይ መልኩ Bachman (1990)ን፣ እና Messick (1988)ን ዋቢ በማድረግ Grandman and Reed (1997:200-205) እንዲሁም Henning (1987:89)ን ዋቢ አድርገው Alderson and et, al (1995:170) እንዳስገነዘቡት፣ አንድ ፈተና መለካት የሚፈለገውን ነገር ወይም ባህርይ በትክክል መለካት የሚችል ከሆነ ተገቢ ሊባል ይቻላል። ይኸውም ፈተናው የመርሐትምህርቱን ይዘት መሠረት ሲያደርግ ነው።

ጠ

Oller (1979:4) እና Cohen (1991:497) ሲያብራሩ፣ አንድ ፈተና ተገቢ ነው የሚባለው የተፈታኞችን የትምህርት ደረጃ እና የትምህርቱ ዓይነት ከተነደፈበት ሥርዓተትምህርት ጋር ምን ያህል እንደተስማማ የሚያሳይ ነው። እንዲሁም ፈተናው ሊመዝን የሚችለውን ጉዳይ በተገቢ መልኩ መለካት ሲችል ነው።

የአንድ ፈተና ተገቢነት ለማረጋገጥ የምንችልባቸው ከተለያዩ ምሁራን የተሠነዘሩ በርካታ የተገቢነት ባሕርያት ያሉ ሲሆን፣ በተለይ እንደ Harrison (1983:11) አገላለጽ፣ መምህራን የቋንቋ ፈተናዎችን ሲያዘጋጁ በጥቅም ላይ ከሚያውሏቸው ውስጥ ሁለቱ ጉልህ ድርሻ የሚሰጧቸው የይዘት ተገቢነት እና ላያዊ ተገቢነት ናቸው። ስለዚህ ይህ ጥናት የፈተናዎቹን የይዘት ብቃት ለመፈተሽ እነዚህን ማለትም የይዘት ተገዚነትንና ላያዊ ተገቢነትን የፈተናመመዘኛ መስፈርቶች ተግባራዊ ያደርጋል።

2.6.2.1 የይዘት ተገቢነት ጠ

አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው ፈተናው የተመሰረተበትን መርሐ ትምህርት በትክክል ካንፀባረቀ ነው፤ ይህም አንድ የችሎታ መለኪያ ፈተና መሠረት ያደረገውን መርሐትምህርት በአግባቡ ማሳየት እንደሚገባው ያመላክታል።

የይዘት ተገቢነት እንደ Harrison (1983:11)፣ Hughes (1989:22)፣ Cohen (1991:497)፣ Brown (1994:255) አገላለጽ፣ አንድ ፈተና ሊይዝ የሚገባውን ነጥቦች ከእየአይነቱ በናሙናነት ካካተተ የይዘት ተገቢነት አለው ማለት ይቻላል። እንዲሁም አንድን ዓላማ ከግምት ውስጥ አስገብቶ ለተዘጋጀ ፈተና ይዘትን ብቻ መሠረት አድርጎ የሚወጣ ፈተና ሲሆን፣ ይዘትን መሠረት በማድረግ የቀረቡት ጥያቄዎች ምን ያህሉ የቋንቋ ክሂሎችን እና ሌሎች ተገቢ የሆኑ ናሙና ጽንሰ ሀሳቦችን አካቷል የሚለውን ትኩረት ያደርጋል። በተጨማሪም የአንድ ፈተና ውስብስቡ መስፈርት ወይም ባህሪ ተገቢነት ሲሆን ይህም አንድ ፈተና ለመፈተን የሚገባውን ነገር ምን ያህል እንደፈተነ የሚያመላክት ነው። ለምሳሌ አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የሚወጣ ጥያቄ ንባብን ብቻ ለመፈተን የተዘጋጀ መሆን አለበት።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
B.L.S LIBRARY

Anderson et al. (1995:171) «የአንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት የሚወሰነው የፈተናው ይዘት ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ሲተነተን፣ ወካይ የሆነ ተገቢነት ያላቸውን የቋንቋ ክሂሎች መያዝ ካለመያዙ አንፃር ነው» ይላሉ። ከዚህም ፈተናው መያዝ ያለበትን የቋንቋ ክሂሎች በተመጣጣኝ ሁኔታ ይዞ ከተገኘ የይዘት ተገቢነት ያሟላ መሆኑን አለዚያ ግን የይዘት ተገቢነት ችግር ያለበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

እንደ Hughes (1995:23) አመለካከት፣ የይዘት ተገቢነት በሚመለከት ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች አሉ። አንደኛው የአንድ ፈተና ይዘት ተገቢነት ከፍተኛ ሲሆን ለመለካት የታሰበው ጉዳይ በትክክል እንዲለካ ያስችላል የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው በመማር–ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ የሚመለከት ነው።

በአጠቃላይ የይዘት ተገቢነት ማለት በአንድ ፈተና ውስጥ ተማሪው ቀድሞ የተማራቸው ይዘቶች ተመጣጣኝ በሆነ ናሙና ሲቀርቡ ሲሆን በተጨማሪም የእነዚህ ናሙና መገለጫ የሆኑ ጥያቄዎችም የተለያዩ አይነት አቀራረብ ስልት ሲኖራቸው ነው (Harrison 1983:11-12፣ Hughes 1989: 22-23፣ Bachman 1990:25-26)።

2.6.2.2 ላያዊ ተገቢነት

Hughes (1989:27)፣ Bachman (1990:286)፣ Brown (1994:206)) ሲያስገነዝቡ፣ ላያዊ ተገቢነት ተማሪዎችና መምህራን ስለፈተናው ያላቸው አስተያየት አሉታዊ ወይም አዎንታዊ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በዚህም የፈተናው አይነት ለተማሪዎች ቀላል፣ ከባድ፣ ያልተጠበቀ፣ ወዘተ. ሊሆን ይችላል የሚለውን ይመለከታል። ስለሆነም ላያዊ ተገቢነት ከይዘት ተገቢነት ጋር አብሮ ሊሄድ ይችላል። በዚህ የተማሪዎችን ሁኔታ በመፈተሽ ፈተናውን እንዴት እንዳፀኑትና የጠበቁት የፈተና አይነት እንደቀረበላቸው ወዘተ ይዳስሳል። እንዲሁም Alderson and et al. (1995:172-3) ፣ Ingram (1977)ን ዋቢ በማድረግ እና Oller (1979:52)፣ Harris (1969:21)ን ዋቢ በማድረግ ላያዊ ተገቢነት የቀረበውን ፈተና ውጫዊ እሴት ወይም የሰዎችን ተቀባይነት ያመላክታል፤ ይኸውም የፈተናውን አወጣጥ በተመለከተ ተፈታኞች፣ የፈተና አዘጋጆች፣ የትምህርት ባለሙያዎች እና የመሳሰሉት የሚሰጡት አተያይ ነው።

በአጠቃላይ ላያዊ ተገቢነት ፈተናው ለሌሎች ባለሙያዎች፣ ለመምህራንና ለተፈታኞች ተገቢ ሆኖ ተቀባይነትን በማግኘት አዎንታዊ ምላሽ ሲያስገኝ ነው። ይህንንም በመጠይቅ በቃለ መጠይቅና በውይይት ወዘተ. ዘዴዎች ማረጋገጥ ይቻላል።

2.6.3 ተተግባሪነት ጦ

Harrison (1983:12)፣ Weir (1993:25)፣ Brown (1994:253) ሲገልጹ፣ ተተግባሪነት ከፈተናው ዝግጅት፣ ከፈተናው አስተዳደር፣ ማለትም ከጊዜ፣ ከአቅም፣ ከትግበራ እና ከውጤት አሰጣጥ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው ነው። በመሆኑም የአንድን ፈተና በተወሰነ ቦታ በተግባር ላይ መዋልን ያመላክታል። ለአብነት ያህል አስር ሰዓት ሊፈጅ የሚችል የደረጃ መለኪያ ፈተና ለተማሪዎች ቢዘጋጅ ተተግባሪነት አይኖረውም። የፈተና ጥያቄዎች በተሰጠው ሰዓት ውስጥ መጠናቀቅ ይገባቸዋል። ስለሆነም አንድ ፈተና በሚወጣበት ጊዜ ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ለመፈተን የቦታው አመቺነት፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ጉዳዮች ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል።

የአንድን ፈተና ተተግባሪነት ለመጠበቅ የፈተናው ቁጥብነት ከጊዜና ከወጪ አንፃር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ከጊዜ አንጻር ሲባል ዝግጅቱን፣ አጻጻፉን እና ውጤት አሰጣጡን የሚመለከት ሲሆን፣ ከፍጆታ አንጻር ደግሞ የቁሳቁስ እና በግልጽ የሚታዩ የጊዜ ብክነቶችን ያጠቃልላል። ስለሆነም በነዚህ መሠረታዊ ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ፈተናው በቅድሚያ በእቅድና በጥራት መዘጋጀት ይኖርበታል። ፈተናውን ለማዘጋጀት፣ ለማካሄድ፣ ለማረም የሚወስደው ሰዓት፣ የያዘው ቅደም ተከተል፣ የሚያሳትፋቸው የተፈታኞች ብዛት፣ ለፈተናው የሚያስፈልጉት ቁሳቁሶች የአገልግሎት ሁኔታ (ለጊዜው፣ ለረዥም ጊዜ)፣ የወጪው ሁኔታ ወዘተ. የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው (Harrison 1983:12፣ Brown 1994:253)። እንዲሁም Heaton (1975:158) ሲገልጹ፣ የአንድን ፈተና ተተግባሪነት ከሚፈታተኑ ነገሮች ውስጥ የመመሪያዎች ግልጽ አለመሆን፣ የጊዜ አሠጣጥ ችግር፣ የሚቀርቡት አማራጮች ወጥነት ያላቸው አለመሆን ከብዙ በጥቂቱ ይጠቀሳሉ።

2.7 በፈተና ዙሪያ የተጠኑ የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ቀደም ሲል የተጠኑ ጥናቶችን በሚመለከት ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸውን ሌሎች ጥናቶች ለመዳሰስ ተሞክሯል። እነሱም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጁና በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተጠኑት የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች ናቸው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከታዩት ጥናቶች በመጀመሪያ ከቅርብ ጊዜ ሥራነታቸው አንጻር በቅደም ተከተል ለማየት እንሞክራለን።

ዘላለም ጌታቸው (1998) እና ትንሳኤ ብርሃኔ (1988) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ካቀረቡት ጥናት በተጨማሪ ታረቀኝ ተፈራ (1993)፣ ዋልተንጉሥ መኮንን (1991)፣ ንጉሴ ጥላሁን (1989)፣ መንግሻ ከበደ (1984)፣ ንጉሴ ዳኦታ (1978)፣ ሰለሞን ደስታ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

(1976)፣ ዋጋዬ ገብረ አምላክ (1972)፣ ነጋሳ ኤጀታ (1965)፣ ተስፋዬ ኃይሌ (1964) እና ዳኛቸው ወርቁ (1955) የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችን አቅርበዋል። ባጠቃላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከላይ ከተጠቀሱት 12 ጥናቶች በተጨማሪ 9 ጥናቶች ማለትም፣ የዘመኑ ዳኝነት (1995)፣ የዳንኤል ፀሐይ (1997)፣ የማርቆስ ግርማ (1995)፣ የአለነ አብረሃ (1990)፣ የአበበ ከበደ (1975)፣ የአባይነህ ፈለቀ (1995)፣ የባኔ ተስፋዬ (1995)፣ የታደሰ ወልደመስቀል (1963)፣ የወርቁ አለሙ (1979) የመጀመሪያ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች ተሠርተዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት በፈተና ዙሪያ ከተሠሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመራቂ ተማሪዎች ጥናት በተጨማሪ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጁ 13 ጥናታዊ ጽሑፎች አሉ። እነዚህ ጥናታዊ ስራዎችም ከ1989 እስከ 1994 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ጊዜያት የቀረቡ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ 3ቱ በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ላይ ያተኮሩ ሲሆን ሌሎቹ 10ሩ በ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና እና በክፍል ፈተና ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩትን በፈተና ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች ከጥናት ትኩረታቸው አንጻር ጠቅለል ባለ መልኩ ብንፈርጃቸው፣ የዘላለም ጌታቸው (1998) ጥናት እና የትንሳኤ ብርሃኔ (1988) ጥናት ሁለቱም የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፎች በመሆናቸው ሲቀራረቡ፣ የዘላለም ጌታቸው (1998) ጥናት፣ ከታረቀኝ ተፈራ (1993) እና ከዋጋዬ ገብረአምላክ (1972) ጥናት ጋር የ8ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ላይ ትኩረት በማድረጋቸው ያመሳስላቸዋል። እንዲሁም የዘላለም ጌታቸው (1998) የአማርኛ ቋንቋ አፈ-ፈት እና ኢ-አፈ-ፈት ንጽጽር ላይ በማተኮሩ ከሌሎቹ ጥናቶች ይለየዋል።

የትንሳኤ ብርሃኔ (1988) ጥናት፣ የመንገሻ ከበደ (1984) ጥናት፣ የንጉሴ ዳኣታ (1978) ጥናት፣ የነጋሳ ኤጀታ (1965) ጥናት፣ የተስፋዬ ኃይሌ (1964) ጥናት፣ የዳኛቸው ወርቁ (1955) ጥናት ፣ የትዕግስት ታረቀኝ (1994) ጥናት፣ የሽዋስገድ ተ/ዮሐንስ (1993) ጥናት እና የጌትነት አባይ (1989) ጥናት በ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ላይ በማተኮራቸው ይመሳሰላሉ።

እንዲሁም የትንሳኤ ብርሃኔ (1988) ጥናት፣ የታረቀኝ ተፈራ (1993) ጥናት፣ የንጉሴ ጥላሁን (1989) ጥናት፣ የንጉሴ ዳኣታ (1978) ጥናት፣ የሰለሞን ደስታ (1976) ጥናት፣ የሽዋዬ ተካ (1994) ጥናት፣ የትዕግስት ታረቀኝ (1994) ጥናት፣ የጌትነት አባይ (1989) ጥናት ፈተናዎችን ከመርሐትምህርትና ከመማሪያ መጽሐፉ አንጻር በመገምገማቸው ያመሳስላቸዋል።

የዋልተንጉሥ መኮንን (1991) ጥናት፣ የንጉሤ ጥላሁን (1989) ጥናት፣ የሰለሞን ደስታ (1976) ጥናት፣ የሽዋዬ ተካ (1994) ጥናት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚዘጋጁትን ፈተናዎች በመገምገማቸው ተመሳስሎ ይኖራቸዋል። የዋልተንጉሥ መኮንን (1991) ጥናት፣ የመንገሻ ከበደ (1984) ጥናት እና የዋጋዬ ገብረአምላክ (1972) ጥናት፣ በምንባብ ላይ የተመሠረተ ፍተሻ በማድረጋቸው ያመሳስላቸዋል። የነጋሳ ኤጀታ (1965) ጥናት፣ ከዳኛቸው ወርቁ (1955) ጥናት ጋር የፈተና ስህተቶች ላይ በማተኮራቸው ይቀራረባሉ።

በአጠቃላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሁለተኛና በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ፣ እንዲሁም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች በርካታ ሐሳቦችን አንስተዋል። ከዚህ ጥናት ጋር አብዛኞቹ ከሀገር አቀፍ ፈተናነታቸው በተጨማሪ የአንድን ፈተና ብቃት ከመርሐትምህርቱና ከመማሪያ መጻሕፍቱ አንፃር ማየትን በሚመለከት ግንኙነት አላቸው። በተለይ የሽዋዬ ተካ (1994) (ከኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ) ጥናት ትኩረት ምንም እንኳን በክፍል ፈተናዎች ላይ ቢሆንም፣ በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ንጽጽራዊ ጥናት ላይ በማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ያቀራርበዋል። በተጨማሪም የተስፋዬ ኃይሌ (1964) ጥናት፣ ከሀገር– አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በተገኘው መረጃ መሠረት የፈተና ውጤቶችን በ'A'ዎች፣ በ'B'ዎች፣ ወዘተ. በማነጻጸሩ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ይኖረዋል።

ከእነዚህ ተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት በጥናቱ ክንውን ወቅት በርካታ ሐሳቦች ተገኝቷል። ይኸውም የአንድን ፈተና ብቃት ከመርሐ ትምህርትና ከመማሪያ መጽሐፍ ይዘቶች አንጻር መፈተሽን በሚመለከት፣ የግልና የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን ንጽጽር በሚመለከት ፣ የውጤት ንጽጽርን በፊደላት (በ"A"ዎች፣ በ"B"ዎች ወዘተ.) ማድረግን በሚመለከት እና የመሳሰሉትን ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምዕራፍ ሦስት

የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ ምርምርና ንጽጽራዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፣ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ውጤት ግምገማ ዓቢይ ትኩረቱ ይሆናል። የፈተናውን ውጤት ከማየት በፊትም ፈተናውን በዋናነት ከመርሐትምህርቱ አንፃር በመፈተሽ በተጨማሪ በፈተናውና በመርሐትምህርቱ መካከል ባሳየው ልዩነት ላይ ከመማሪያ መጽሐፉ አንጻር ምን ያክል ብቃት እንዳለው ፍተሻ ለማድረግ ተሞክሯል። እንዲሁም በጥናቱ የጽሑፍ መጠይቅ ዓቢይ መረጃዎችን የበለጠ ለማጠናከር አጋዥ የመረጃ ማሰባሰብያ መንገድ ሆኖ ያገለግላል። በዚህ ክፍልም እነዚህን መረጃዎች ለመሰብሰብ በጥቅም ላይ የዋሉ የናሙናዎችን አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችንና የአተናተን ስልቶችን ለመቃኘት እንሞክራለን።

3.1 የፈተናዎች፣ የትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች እና የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዓቢይ የመረጃ ምንጭ በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. በአገርአቀፍ ደረጃ ለ10ኛ ክፍል የተሰጠ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ነው። ስለሆነም በአዲስ አበባ ከተማ በሁለቱ ዓመታት ፈተናውን ከወሰዱ ትምህርት ቤቶች 4ቱን በወካይ ናሙና መሠረት በመምረጥ የፈተና ውጤታቸውን ለመሰብሰብ ተሞክሯል።

3.1.1 የፈተናዎች የናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በሰነድ ፍተሻ ላይ መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓቢይ የመረጃ ምንጭ የሆነው ፈተና የ1997ዓ.ም. እና 1998 ዓ.ም. ሆኖ የሁለት ዓመታት የ10ኛ ክፍል አገርአቀፍ ፈተና ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። እነዚህ ዓመታት የተመረጡበት ምክንያት ፈተናዎቹ ተሻሽሎ በወጣው በአዲሱ መርሐትምህርትና መማሪያ መፅሐፍ ላይ መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው ነው። በመሆኑም የሁለቱን ዓመታት የፈተናዎች ብቃት በዋናነት ከመርሐትምህርቱ ይዘት አንፃር እና በሁለተኛ ደረጃ በፈተናው ይዘትና በመርሐትምህርቱ ይዘት መካከል ባሳየው ልዩነት ከመማሪያ መፅሐፉ ይዘት አንፃር በመፈተሽ የተሻለ ሆኖ የተገኘውን የአንድ ዓመት የፈተና ውጤት በመውሰድ የርዕሱ ትኩረት የሆነውን የግልና የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ውጤት ለማነጻጸር ሲባል ነው። በመሆኑም በተደረገው ፍተሻ የ1997 ዓ.ም. ፈተና የአማርኛ ቋንቋ ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች የይዘት ተገቢነትን ያሟላ በመሆኑ ለውጤት ንጽጽሩ ተመርጦ ዋና የመረጃ ምንጭ በመሆን በሥራ ላይ ውሏል። የዚህም የፈተና

ውጤት ከሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት የተገኘው መረጃ በአባሪ 1ላይ በጥናቱ መጨረሻ ላይ ይገኛል።

3.1.2 የትምህርት ቤቶች የናሙና አመራረጥ

ከአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 1 እንደተቀመጠው በ1997 ዓ.ም. 8 የተለያዩ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዓይነቶች ሲኖሩ ከነዚህም ውስጥ 2ቱ ዓይነት የመንግሥትና የግል ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው። ሌሎቹ 6ቱ ዓይነት የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሃይማኖት ተቋማት የሚያስተዳድሯቸው ናቸው። ባጠቃላይ በእነዚህ በ8ቱ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት 78 ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲገኙ፤ ከነዚህ ውስጥ 21ዱ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች፣ 26ቱ የግል ትምህርት ቤቶች ናቸው። ባጠቃላይ ከ78ቱ ውስጥ 47ቱ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፣ የቀሩት 31፣ የ6ቱ ተቋማት ናቸው (እነሱም በሠንጠረዥ አንድ ላይ የሚተዩት) ። በእነዚህ በ8ቱ የትምህርት ተቋማት ባጠቃላይ 47,212 ወንዶች እና 49,852 ሴቶች፣ በድምሩ 97,064 ተማሪዎች እንደተማሩ ተዘግቧል። እንዲሁም በ1997 ዓ.ም.በ47ቱ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች 38,052 ወንዶች እና 41724 ሴቶች፣ በድምሩ 79,776 ተማሪዎች፣ በግል ትምህርት ቤቶች 2,260 ወንዶች እና 2375 ሴቶች፣ በድምሩ 4635 ተማሪዎች ይስተናገዱ እንደነበር መረጃው ያረጋግጣል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

ሠንጠረዥ 1:– በ1997 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የሚገኙ የትምህርት ቤቶች ዓይነት፣ ብዛትና የተማሪዎች ቁጥር

በአዲስ አበባ (በክልል 14) የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ዓይነትና ብዛት										ጠቅላላ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት	ጠቅላላ የተማሪዎች ብዛት (የ8ቱ ተቋማት)			የሁለቱ ተቋማት ተማሪዎች ብዛት					
														የመንግሥት (GO)			የግል (PR)		
ተ.ቁ	ዓ.ም	ክ. (CH)	ኮ. (FC)	መ. (GO)	ሚ. (MI)	ሕ. (PU)	ግ. (PR)	ድ. (OT)	እ. (MO)		ወ	ሴ	ድምር	ወ	ሴ	ድምር	ወ	ሴ	ድምር
2	1997	3	6	21	13	3	26	4	2	78	47212	49852	97064	38052	41724	79776	2260	2375	4635

መግለጫ (Legend)

GO = Government = የመንግሥት

PR = Private = የግል

LC = Local Community (Pulbic) = የሕዝብ

FC = Foreign Community = የውጪ (ኮሚኒቲ)

MI = Missionary = የሚሽን

OT = Others (NGOS) = የውጭ ድርጅቶች

CH =Church = የክርስቲያን ሃይማኖት

MO =Mosque = የእስልምና ሃይማኖት

ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የ1998 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በሚመለከት የተገኘው መረጃ ከ1997 ዓ.ም. በተለየ ሁኔታ በክፍለ ከተማ ደረጃ የተከፋፈለ ነው። በመሆኑም ከታች በሠንጠረዥ 2 እንደሚታየው አዲስ አበባ በ10 ክፍለ ከተማዎች የተከፈለች ስትሆን፣ በአዲስ ከተማ 7፣ በአቃቂ ቃሊቲ 7፣ በአራዳ 15፣ በቦሌ 14፣ በጉለሌ 12፣ በቂርቆስ 12፣ በኮልፌ ቀራኒዮ 6፣ በልደታ 2፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ 11፣ በየካ 10፣ ባጠቃላይ 96 የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ።

ከነዚህ ውስጥ 24ቱ የመንግሥት ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፣ በመቶኛ ስሌት 25% ናቸው። የግል ትምህርት ቤቶች ደግሞ 37 ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፣ በመቶኛ 38.5% ናቸው። የቀሩት 35ቱ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ድርጅቶችና የሃይማኖት ተቋማት የሚያስተዳድሯቸው ናቸው።

ሠንጠረዥ 2:– በአዲስ አበባ፣ በ1998 ዓ.ም. በ10ሩ ክፍለ ከተሞች (Sub-cities) የሚገኙ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዓይነትና ብዛት በቁጥርና በመቶኛ ስሌት

ተ.ቁ	የትምህርት ቤቶች ዓይነት	አዲስ ከተማ	አቃቂ ቃሊቲ	አራዳ	ቦሌ	ጉለሌ	ቂርቆስ	ኮልፌ ቀራንዮ	ልደታ	ንፋስ ስልክ ላፍቶ	የካ	ጠቅላላ የትምህርት ብዛት	በፐርሰንት (%)
1	ክ. (CH)	1	-	1	-	1	1	-	-	-	-	4	4.2%
2	ውኮ.(FC)	1	-	4	-	-	-	-	-	-	-	5	5.3%
3	መ. (GO)	2	3	3	2	3	2	2	1	3	3	24	25%
4	ማ. (MI)	1	1	4	1	2	1	1	-	1	1	13	13.5%
5	ሕ. (LC)	-	-	2	1	-	1	-	-	1		5	5.3%
6	ግ. (PR)	2	2	1	9	4	7	1	1	5	5	37	38.5%
7	ድ. (OT)	-	1	-	1	2	-	2	-	-	1	7	7.3%
8	አ. (MO)	-	-	-	-	-	-	-	-	1	-	1	1%
	ድምር	7	7	15	14	12	12	6	2	11	10	96	100%

ከታች በሠንጠረዥ 3 ላይ እንደሚታየው፣ በ1998 ዓ.ም. በ10ሩም ክፍለ ከተማ 51,534 ወንዶች እና 52,302 ሴቶች ተማሪዎች በድምሩ 103,836 የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች እንደሚገኙ ተረጋግጧል። ከዚህ ውስጥ ከታች በሠንጠረዥ 4 እንደሚታየው በመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 43,326 ወንዶች እና 43,121 ሴቶች በድምሩ 86,447 ተማሪዎች ሲገኙ፣ በግል የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 3,162 ወንዶች እና 3,362 ሴቶች፣ በድምሩ 6,524 ተማሪዎች መማራቸው ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ ተረጋግጧል።

ሠንጠረዥ 3:– በ1998 ዓ.ም. የአዲስ አበባ የ10ሩ ክፍለ ከተሞች ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛት

ተ. ቁ	ክፍለ ከተማ	ጠቅላላ የተማሪዎች ብዛት		ድምር
		ወ	ሴ	
1	አዲስ ከተማ	4,628	4,697	9,325
2	አቃቂ ቃሊቲ	3,190	2,828	6,018
3	አራዳ	6,711	6,516	13,227
4	ቦሌ	4,706	5,107	9,813
5	ጉለሌ	9,412	9,793	19,205
6	ቂርቆስ	6,946	6,408	13,354
7	ኮልፌ ቀራንዮ	6,065	6,195	12,260
8	ልደታ	393	271	664
9	ንፋስ ስልክ ላፍቶ	3,227	3,273	6,500
10	የካ	6,256	7,214	13,470
	ጠቅላላ ብዛት	51,534	52,302	103,836

ሠንጠረዥ 4:– በ1998 ዓ.ም. የአዲስ አበባ የ10ሩ ክፍለ ከተሞች የመንግሥትና የግል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብዛት

የመንግሥት (Go)		ድምር	የግል (PR)		ድምር
ወ	ሴ		ወ	ሴ	
43,326	43,121	86,447	3,162	3,362	6,524

ከላይ ከተዘረዘሩት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የጥናቱ ትኩረት የሆነው የትምህርት ቤቶች የናሙና አመራረጥ ሁለት ዓይነት ዘዴ የተከተለ ነው። ምክንያቱም ከትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት የየትኛውም የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቁጥር ብዙ በመሆኑ በአመቺነት ናሙና (Convenience Sampling) በመምረጥ የዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ እና የየካቲት 12 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል። የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ የሆኑባቸውም ስላሉ ከተማሪዎች ቁጥር አንጻር ለንጽጽሩም እንዲያመች በዛ ያሉትን በመምረጥ በዓላማ ናሙና (Purposive Sampling) የነገው ሰው እና የማጂክ ካርፔት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጥናቱ እንዲታቀፉ ተደርጓል። በመሆኑም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ከ24ቱ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ 2ቱ እና ከ37ቱ የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ 2ቱ ከላይ በተገለፀው በአመቺነት እና በዓላማ የናሙና አመራረጥ መሠረት ተመርጠው የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY AAU LIBRARY

የጥናቱ የናሙና ተመራጭ የሆኑት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአራዳ ክፍለ ከተማ፣ የካቲት 12 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ሲገኙ፣ የግል ትምህርት ቤቶች ደግሞ የነገው ሰው የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቦሌ፣ የማጂክ ካርፔት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በየካ ክፍለ ከተማ የሠፈሩ ናቸው። በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት 4ቱ ትምህርት ቤቶችም በአዲስ አበባ ውስጥ ካሉት 10 ክፍለ ከተማዎች ውስጥ በ4ቱ የተለያዩ ክፍለ ከተማዎች ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

3.1.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ከሀገር–አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በተገኘው መረጃ መሠረት ከታች በሠንጠረዥ 5 ላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው በ1997 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ለ10ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና የተመዘገቡ ተፈታኞች (የማታና የግል ተፈታኞችን ሳይጨምር) የቀን ተፈታኞች 18,200 ወንዶች፣ 18,616 ሴቶች፣ በድምሩ 36,816 ነበሩ። በተመሳሳይ በ1998 ዓ.ም. የቀን ተፈታኞች 21,335 ወንዶች፣ 21,491 ሴቶች፣ በድምሩ 42,826 እንደነበሩ ተዘግቧል። ከዚህ ውስጥ በናሙናነት የተመረጡት አራቱ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ በ1997 ዓ.ም. በተሰጠው የ10ኛ ክፍል አገርአቀፍ ፈተና ላይ 2058 የቀን (መደበኛ) ተማሪዎችን አስፈትነዋል። እንዲሁም በ1998 ዓ.ም. በተሰጠው የ10ኛ ክፍል አገርአቀፍ ፈተና 4011 የቀን (መደበኛ) ተማሪዎችን አስፈትነዋል። የማታ እና የግል ተፈታኞች የሚማሩበት ሰዓት፣ የእድሜ ክልል እና የሕይወት ልምዳቸው ከቀን ተማሪዎች ይለያል በሚል ግምት በጥናቱ ውስጥ እንዳይካተቱ ተደርጓል። በመሆኑም በዚህ ጥናት የቀን ተማሪዎች ብቻ በናሙናነት ተወስደዋል።

ሠንጠረዥ 5:– በ1997 ዓ.ም. በ1998 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ለ10ኛ ክፍል ሀገር–አቀፍ ፈተና የተመዘገቡ ተፈታኞች

	የቀን (መደበኛ)			የማታ			የግል			ጠቅላላ		
	ወ	ሴ	ድምር	ወ	ሴ	ድምር	ወ	ሴ	ድምር	ወ	ሴ	ድምር
የ1997	18,200	18,616	36,816	2,569	2,454	5,025	4,312	4,715	9,027	25,081	25,787	50,868
የ1998	21,335	21,491	42,826	2,878	2,595	5,473	21,795	20,850	42,645	46,008	44,936	90,944

ለናሙና በተመረጡት በሁለቱ የመንግሥትና በሁለቱ የግል ትምህርት ቤቶች በሁለቱ ዓመታት ያገኙት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የቀን ተማሪዎች ውጤት ከአገርአቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በተገኘው መረጃ መሠረት በ'A'ዎች፣ በ'B'ዎች፣ በ'C'ዎች፣ በ'D'ዎች እና በ'F'ዎች ብዛት ለመሰብሰብ ተሞክሯል። እነዚህ ውጤቶች ከመታየታቸው በፊት የሁለቱ ዓመታት ፈተናዎች በዋናነት ከመርሐትምህርቱ እንዲሁም በተጨማሪ ከመርሐትምህርቱ ጋር ባሳዩት ልዩነት ከመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘት አንጻር ተፈትሸው ብቃት ያለው እና የተሻለ ሆኖ የተገኘው ዓመት ፈተና ተመርጧል። የተመረጠውን የአንድ ዓመት ፈተና ውጤት መሠረት በማድረግም በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች ያሉት ተማሪዎች ያመጡትን ውጤት ከላይ በተገለፀው የውጤት መረጃ መሠረት በፊደላት ለማነጻጸር ተሞክሯል።

ከላይ ከተጠቀሰው የፈተና ውጤት በተጨማሪ ለተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የቀረበ ሲሆን፣ የጽሑፍ መጠይቁን ከአራቱ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጓል። የእነዚህ ክፍል ተማሪዎች መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገበት ምክንያት 11ኞች የጥናቱ ተተኪ የሆነውን የ1998 ዓ.ም. የ10ኛ ክፍል ፈተና የሠሩ ሲሆን፣ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ ክልል ዓመት የሆነውን የ1997 ዓ.ም. የ10ኛ ክፍል ፈተና የሠሩ ናቸው። በመሆኑም መረጃዎችን ከተለያየ አቅጣጫ መሰብሰብ የበለጠ ለጥናቱ ውጤታማነት የሚደገፍ በመሆኑ መጠይቁንም በማስታወስ በተሻለ ሁኔታ ሊመልሱት ይችላሉ ተብሎ እምነት የተጣለባቸው እነዚህ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍሎች ተማሪዎች ሆነው ተገኝተዋል።

የጽሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ከአራቱ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በተለይ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጣም ብዙ ስለሆኑ ለመንግሥትም ሆኑ ለግል ትምህርት ቤት 5%ቱ ያህል የእኩልዮሽ ናሙና አወሳሰድ (Random Sampling Method) በመጠቀም. በናሙናነት ተመርጠው ጠቅላላቸውን በ5% ውጤት በማካፈል በየ20 ተማሪዎች ልዩነት ወይም መነሻነት መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርገዋል። መጠይቁን የሞሉት 193 የመንግሥት ትምህርት ቤት እና 47 የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በድምሩ 240 ተማሪዎች ናቸው።

3.1.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ለቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሉ ሁለት የመንግሥት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ሁለት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ተመርጠዋል። ይህም በመሆኑ በአራቱም ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሙሉ በጥናቱ ተካትተዋል። ስለሆነም ከሁለቱ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ 18 መምህራንን፣ በግል ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ 5 መምህራንን፣ ባጠቃላይ 23 መምህራን ለጥናቱ በናሙናነት ተመርጠዋል። ከነዚህ ውስጥ 15 ያህሉ ለመጠይቁ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ ከ15 ውስጥ 1 መጠይቅ በአግባቡ ስላልተሞላ በጥናቱ ውስጥ ለመጠቀም አልተቻለም። የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቁን እንዲሞሉ የተመረጡበት ምክንያት በተደረገው ቅድመ ጥናት በየዓመቱ የመምህራን የክፍል አመዳደብ በመለዋወጥ የተለያዩ ክፍሎች ይዘው የሚያስተምሩ በመሆናቸው አሁን 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ምናልባት በ1997 እና በ1998 የ10ኛ ክፍል እና የሌላውም ክፍል መምህር የመሆን አጋጣሚው ስለሚኖር መረጃ የማግኘት ዕድሉን የበለጠ ያሰፋል ከሚል ግምት ነው። የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል መምህራን የተመረጡት ደግሞ በአሁኑ ወቅት ጥናቱ ያተኮረባቸውን ተማሪዎች እያስተማሩ ያሉ በመሆናቸው ነው።

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና የአተናተን ዘዴዎች

ይህን ጥናት ለማከናወን ሦስት ዋና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተግባራዊ ሆነዋል። እነሱም የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. ለ10ኛ ክፍል የተሰጡ የሁለት ዓመታት ብሔራዊ ፈተናዎች፣ በዋናነት ለክፍሉ በሥርዓተትምህርት የተዘጋጀ መርሐትምህርት እና ባሳየው ልዩነት በመማሪያ መጻህፍት፣ ከላይ ከተጠቀሱት ከሁለቱ ዓመታት ፈተናዎች በዋናነት ከመርሐትምህርቱና ባሳየው ልዩነት ከመማሪያ መጽሐፉ ይዘት አንጻር የተሻለ ብቃት ያለው የአንድ አመት ፈተና የተማሪዎች ውጤት እና የጽሑፍ መጠይቆች ናቸው። ከላይ የተገለፀት ሦስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች እንዴት እንደተዘጋጁና እንደተተነተኑ ከዚህ በታች ለማመልከት ይሞከራል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
A.U. LIBRARY

3.2.1 ፈተናዎች

ይህ ጥናት በ10ኛ ክፍል ሀገር–አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ለጥናቱ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተሰጡት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. የቀረቡት የሁለት ዓመታት ፈተናዎች ብቻ ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚህ የሁለት ዓመታት ፈተናዎች በ1996 ዓ.ም. ተሻሽሎ የወጣውን መርሐትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ተማሪዎችን ለመመዘን የተዘጋጁ ስለሆኑ ነው። በመሆኑም የፈተናውን ብቃትም ለመፈተሽ ተማሪዎቹ የተማሩበትንና ተሻሽሎ የወጣውን የማስተማሪያ መሣሪያ መሠረት ያደረገውን ፈተና መምረጥ ከጥናቱ ዓላማ አኳያ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ከዚህ አንፃር ከሁለቱ ዓመታት ፈተናዎች በዋናነት ከመርሐትምህርቱ ይዘት እንዲሁም ባሳየው ልዩነት ከመማሪያ መፅሐፉ ይዘት አንጻር በመፈተሽ የተሻለ ብቃት ያለውን ፈተና በመውሰድ የርዕሱ ዋና ትኩረት የሆነውን የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ውጤት ለማነፃፀር እንዲያመች ሲባል ነው። በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ዓመታት ፈተናዎች በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት በስራ ላይ ውለዋል። (የፈተናዎቹ ኮፒ በአባሪ 2 እና 3 ላይ ተቀምጠዋል)።

በሁለቱም ዓመት ፈተናዎች ዘጠና፣ ዘጠና ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን፣ እነዚህን ጥያቄዎች በዋናነት ከመርሐትምህርቱ ይዘት እና በልዩነት ከመማሪያ መጽሐፉ ይዘት አንፃር በአራት የቋንቋ ክሂሎችና በሁለት የእውቀት ዘርፎች በመከፋፈል በ6 ዋናና በ3 ንዑሳን ክፍሎች ለመደልደል ተሞክሯል። የፈተናውን ጥያቄዎች በአይነት፣ በአይነት ለመከፋፈል በሁለት የተለያዩ ዩኒቨርስቲ እና ኮሌጅ ውስጥ ያሉ ሦስት የአማርኛ ቋንቋ እና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህራን በቅድመ ግምገማ ላያዊ ተገቢነት (Face validity) ተሳትፈዋል። ከሦስቱ መምህራን ውስጥ አንዷ አማርኛን በማስተማር ዘዴ ሁለተኛ ዲግሪ ያላት ስትሆን፣ ከቀሪዎቹ ሁለት መምህራን መካከል አንዱ በሥነልሳን፣ ሌላው ደግሞ በሥነጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ እና ስነጽሑፍን በማስተማር ላይ የሚገኙ ናቸው።

ለሦስቱ መምህራን በተናጠል የሁለቱ ዓመታት ፈተናዎች ኮፒ ተደርገው ከተሰጣቸው በኋላ እያንዳንዱን ጥያቄ «የቃላት ጥያቄ፣ የአንብቦ መረዳት ጥያቄ፣

የሰዋስው ጥያቄ . . .» እያሉ ጥያቄዎቹ የሚያተኩሩባቸውን ዓበይት እና ንኡሳን ክሂሎችን እና የዕውቀት ዘርፎችን እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን፣ ከሦስቱ ቢያንስ ሁለቱ የተስማሙበትን የጋራ ምድብ በጥናቱ ውስጥ ለመጠቀም ተሞክሯል። በዚህም መሠረት የሁለቱም ዓመታት ጥያቄዎች ስለማዳመጥ ክሂል የሚያወሱ፣ ስለንግግር ክሂል የሚያወሱ፣ በአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ የተመሠረቱ፣ በጽሕፈት ክሂል ላይ የተመሠረቱ፣ በሥነጽሑፍ ዕውቀት ላይ የተመሠረቱ፣ እና ከሥነልሳን ዕውቀት ደግሞ በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ፣ በቃላት ፍቺ ላይ የተመሠረቱ እና በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች ተብለው በስድስት ዋና ዋናና በሦስት ንዑሳን ምድቦች ተደልድለዋል። የአከፋፈሉ ሂደትም የምሁራንን ሐሳብ መሠረት በማድረግ፣ አጠቃላይ ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝትና ገለጻ ከተደረገ በኋላ ይህንኑ ቅኝት መሠረት ወይም መስፈርት በማድረግ ነው።

3.2.2 ከሁለቱ ዓመታት የተሻለ የፈተና ብቃት ያለው የፈተና ውጤት

ከላይ እንደተገለፀው፣ ምሁራኑ የሠነዘሩትን ሐሳብ መሠረት በማድረግ በመጀመሪያ ከመርሐትምህርቱ ይዘት፣ በመቀጠልም በታየው ልዩነት መነሻነት ከመማሪያ መጽሐፉ ይዘት አንጻር የሁለቱ ዓመታት ፈተናዎች በዓቢይና ንዑሳን ክሂሎች ከተከፈሉ በኋላ በመቶኛ ስሌት ተሰልተው የተሻለውን የአንድ ዓመት ፈተና በመምረጥ በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት በማነፃፀሪያነት አገልግለዋል። ከአገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በተገኘውም መረጃ በ'A'ዎች፣ በ'B'ዎች፣ ወዘተ. በተቀመጠ የተማሪዎች ውጤት መሠረት በመቶኛ በማስላት ለማነፃፀር ተሞክሯል። የእያንዳንዱን ጥያቄ የክብደት ቅለት ደረጃ ለማየት እያንዳንዱ ተማሪ መልስ የሰጠበትን ወረቀት ከፈተናዎች ድርጅት ለማግኘት ተሞክሮ ነበር። ነገር ግን «የእያንዳንዱ ተማሪ የመልስ ወረቀት የግል ምስጢር ስለሆነ አይሰጥም። መስጠት የምንችለው በፊደላት ማለትም በ'A'ዎች፣ በ'B'ዎች፣ በ'C'ዎች፣ በ'D'ዎች፣ እና በ'F'ዎች ብቻ ነው።» የሚል ምላሽ ስለተገኘ ጥናቱን በዚህ ውጤት ለማስላት አስገድዷል።

3.2.3 የጽሑፍ መጠይቆች

ይህን ጥናት የተሳካ ለማድረግ ከፈተናዎች እና ከተፈታኞች ውጤት በተጨማሪ የጽሑፍ መጠይቆች በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት አገልግለዋል።

የጽሑፍ መጠይቆቹ የተዘጋጁት የRichards and Lockhart (1994) ፎርማትን በመከተል ሲሆን፣ ይህም አምስት አማራጮችን የያዘ ነው። አማራጮቹም በደረጃ ከ"በጣም እስማማለሁ" (Strongly Agree) ወደ "በጣም አልስማማም" (Strongly Disagree) የሚወርዱ ናቸው። የጽሑፍ መጠይቆቹም ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍሎች ተማሪዎች እና ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረቡ ናቸው።

3.2.3.1 ለተማሪዎች የቀረቡ የጽሑፍ መጠይቆች

ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ለሰነድ ፍተሻው እንደአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት እንዲውል ታስቦ ነው። ይህም በመሆኑ በመጠይቁ ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን በመስራት ሂደት በመንግሥት እና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን የውጤት ልዩነት ለመረዳት የሚያስችሉ ሆነው ተሰናድተዋል።

ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ጉዳዮች የያዙ መልስ አስመራጭ (ዝግ ጥያቄዎች) እና ነጻ አስተያየትን የሚጠይቁ (ክፍት) ጥያቄዎች ከተማሪዎቹ ዕድሜና የክፍል ደረጃ አንጻር ቀለል በማድረግ በጥናት አቅራቢዋ ከተዘጋጁ በኋላ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ዘዴ ሁለተኛ ዲግሪ ላላቸው ሦስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለአስተያየት ቀርቦ የማሻሻያ ሀሳብ ሰጥተውበታል። ከነሱ የማሻሻያ ሀሳብ በኋላም ለጥናቱ አማካሪ ቀርቦ ማሻሻያ ተሰጥቶባቸዋል። በመጨረሻም በመነሻ ጥናትነት በጥናቱ ላልታቀፉ ሁለት የአዲስ አበባ ከተማ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ16 ተማሪዎች ቀርቦ የመጠይቁን ብቃት ለመፈተሽ ተሞክሯል።

ከመነሻ ጥናቱ በኋላ፣ የመነሻ ጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጧቸውን አስተያየቶችና መልሶች መሠረት በማድረግ ጥያቄዎቹ በተሻለ መልክ ተዘጋጅተዋል (የመጠይቁ ኮፒ በአባሪ 7 ላይ ተቀምጧል)። የተሻሻሉት የጽሑፍ መጠይቆችም መረጃውን ለመመዘኛት በተመረጡት ሁለት የመንግሥትና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች በናሙናነት በተመረጡት ተማሪዎች ልክ እንዲባዙ ተደረገ። መጠይቁን የሚሞሉት በአራት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች እንደመሆናቸው አጥኚዋ በተለያዩ ቀናት በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት ስለጥናቱ ዓላማ ለተማሪዎች ገለጻ በማድረግ መጠይቁን እንዲሞሉ ለማድረግ ሞክራለች። መጠይቁን ለመመዘኛት ለተመረጡት የየክፍሉ ተማሪዎችም 12ኛ የሞዴል ፈተናቸውን እንደጨረሱ እንዲሞሉ

ፈተናውን ከመጀመራቸው በፊት ተሰጥቷቸው ከ3 ሰዓት በኋላ ፈተናውን ሠርተው ሲጨርሱ እንዲሞሉ ተደርጎ መጠይቁን ለመሰብሰብ ተችሏል። ሌሎቹ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ክፍል ውስጥ በመማር ላይ እያሉ ሃያ አምስት ደቂቃ በመስጠት እንዲሞሉ ተደርጎ በተሰጣቸው ጊዜ ሞልተው መልሰዋል።

ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው መልስም በጥንቃቄ የተመረመረ ሲሆን፣ ለአንድ ጥያቄ ሁለት መልስ የሰጡ እና በአግባቡ መጠይቁን ያልሞሉ ተማሪዎች ወረቀት በጥናቱ ውስጥ እንዳይካተት ተደርጓል። በመጨረሻም በመጠይቁ ውስጥ ተማሪዎቹ የሞሉት መልስ ተለቅሞ ከአጠቃላይ የመጠይቁ መላኮች ብዛት አንጻር በቁጥርና በመቶኛ በመቀመጥ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘውን ውጤት እንዲያጠናክር ተደርጓል።

ሠንጠረዥ 6:– የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች ስርጭትና ለጥናቱ የዋለው ብዛት

ተ.ቁ	የት/ቤቱ ስም	የት/ቤቱ ደረጃ	የተሰራጨው ብዛት 12ኛ + 11ኛ	የተመለሱት መጠይቆች ብዛት		ለጥናቱ የዋሉት መጠይቆች ብዛት		በጥናቱ ውስጥ ያልዋለ
				በቁጥር	በመቶኛ ስሌት	በቁጥር	በመቶኛ ስሌት	በቁጥር
1	ዳግማዊ ምኒልክ	2ኛ. ደረጃ ት/ቤት	103 (30+73)	89	43	88	42.7	1
2	የካቲት 12	2ኛ. ደረጃ ት/ቤት	90 (31+59)	76	36.7	76	36.9	
3	የነገው ሰው	2ኛ. ደረጃ ት/ቤት	17 (8+ 9)	17	8.2	17	8.3	
4	ማጂክ ካርፔት	2ኛ. ደረጃ ት/ቤት	30 (12+18)	25	12.1	25	12.1	
	ድምር		240	207	100	206	100	1

3.2.3.2 ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

ለተማሪዎች እንደቀረበው መጠይቅ ሁሉ ለመምህራን የቀረበውም መጠይቅ የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን በመስራት ሂደት በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች መሐከል ያለውን የውጤት ልዩነት ለመረዳት እንዲያመቹ ታስበው በጥናት አቅራቢዋ የተሰናዱ ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ጉዳዮችን የያዙ መልስ አስመራጭ (ዝግ ጥያቄዎች) እና ነፃ አስተያየትን የሚጠይቁ (ክፍት) ጥያቄዎች በጥናት አቅራቢዋ ከተዘጋጁ በኋላ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ዘዴ ሁለተኛ ዲግሪ ላላቸው ሦስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አስተያየት እንዲሰጡባቸው ቀርቦ የማሻሻያ ሐሳብ ሰጥተውበታል። ከነሱ የማሻሻያ ሀሳብ በኋላም ለጥናቱ አማካሪ ቀርቦ ማሻሻያ ከተሰጠበት በኋላ በጥናቱ

2013 ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ላልታቀፉ ሁለት የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቤቶች 10 ለሚሆኑ፣ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመነሻ ጥናትነት ቀርቦ የመጠይቁን ብቃት ለመፈተሽ ተሞክሯል።

ከመነሻ ጥናቱ በኋላ፣ የመነሻ ጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጧቸውን አስተያየቶችና መልሶች መነሻ በማድረግ ጥያቄዎቹ በተሻለ መልኩ ተዘጋጅተዋል (የመጠይቁ ኮፒ በአባሪ 6 ላይ ተቀምጧል)። የተሻሻሉት የጽሑፍ መጠይቆችም መረጃውን ለመመላት በተመረጡት አራት ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥር ልክ ተባዝተው ለመምህራኑ ተሰጥተዋል። በዚህም ከግልና ከመንግሥት ትምህርት ቤት የመጡትን ተማሪዎች ለመለየት ቀደም ሲል አጋጣሚውን ያላገኙ መሆኑን መምህራኑ በሰጡት ጥቆማ መሠረት ተማሪዎቹ እጅ በማውጣት እራሳቸውን እንዲገልፀ ተደርጓል። በመሆኑም ተማሪዎቹ በፊት ካላቸው የትምህርት እንቅስቃሴ ጋር በማገናዘብ መምህራኑ ስለተማሪዎቹ ያላቸውን አስተያየት በመጠይቁ እንዲሞሉ ተደርጓል። መጠይቆቹ በታቀደላቸው አምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ተሞልተው ለጥናት አቅራቢዋ የተመለሱ ሲሆን፣ መጠይቁ የተበተነላቸውና ሞልተው የመለሱት መምህራን ቁጥር እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ተቀምጧል።

ሠንጠረዥ 7:– የመምህራን የጽሑፍ መጠይቆች ስርጭትና ለጥናቱ የዋለው ብዛት

ተ.ቁ.	የት/ቤቱ ስም	የትምህርት ቤቱ ደረጃ	የተሰራጨው ብዛት	የተመለሰው ብዛት		ለጥናት የዋለው ብዛት		በጥናቱ ውስጥ ያልዋለ
				በቁጥር	በመቶኛ ስሌት	በቁጥር	በመቶኛ ስሌት	
1	ዳግማዊ ምኒልክ	2ኛ ደረጃ ት/ቤት	10	4	26.7	4	28.5	
2	የካቲት 12	2ኛ ደረጃ ት/ቤት	8	6	40	6	42.9	
3	የንገው ስው	2ኛ ደረጃ ት/ቤት	2	2	13.3	1	7.1	1
4	ማጂክ ካርፔት	2ኛ ደረጃ ት/ቤት	3	3	20	3	21.4	
	ድምር		23	15	100	14	100	1

ከላይ በተጠቀሰው መሠረት መጠይቁ ተበትኖ ከተመለሰ በኋላ በየመጠይቁ ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች መልሶች ተለቅመው በመውጣት በቁጥርና በመቶኛ እየተሰሉ ከፈተና ውጤቶቹ ግኝት ጋር ተጣምረው መረጃውን በአጋዥነት ለመተንተን አገልግለዋል። ሆኖም ሁሉም የተመለሱት መጠይቆች በጥንቃቄ ተመርምረው ለአንድ ጥያቄ ሁለት መልስ የተሰጠባቸውና በአግባቡ ያልተሞሉ መጠይቆች በጥናቱ እንዲያታቀፉ ተደርገዋል።

ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ትንታኔና ከጥናቱ የተገኘው ውጤት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ዓቢይ ትኩረት የሆነውን በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ውጤት በማነጻጸር ትንታኔ ይሰጣል። በምዕራፍ ሦስት ውስጥ በተጠቀሰው መልኩ የፈተናውን ውጤት ከማየት በፊት የፈተናውን ይዘት በዋናነት ከ9ኛና ከ10ኛ ክፍል መርሐትምህርቶች ይዘት፣ በተጨማሪም በፈተናውና በመርሐትምህርቶቹ ይዘት መካከል ባለው ልዩነት ከ9ኛ እና ከ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ይዘት አንጻር ብቃት ያለው ፈተና መሆን አለመሆኑ በዚህ ምዕራፍ በሦስጠረኛ መልክ ትንታኔው ይቀርባል። በተደረገው ፍተሻም ከሁለቱ ዓመታት ፈተናዎች የተሻለ ብቃት ያለው የፈተና ውጤት የጥናቱ ትኩረት የሆነውን የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ለማነጻጸር ዋና የመረጃ ምንጭ ይሆናል። በተጨማሪም በተመረጡት የናሙና የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ፈተናውን የሠሩ በናሙና የተመረጡ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች እና ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሙሉ የሞሉት መጠይቅ በደጋፊነት ከውጤት ጋር በተያያዘ መልኩ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተተንትኗል።

የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ስለሆነው ስለ 1997 ዓ.ም. እና 1998 ዓ.ም. ፈተናና መጠይቁን ስለሞሉ ተማሪዎችና መምህራን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በቅድሚያ አጭር ትንተና የሚደረግ ሲሆን፣ እሱን ተከትሎም ፈተናዎቹን መነሻ ባደረገ መልኩ የተከፋፈሉ ንኡሳን ርዕሶች ይቀርባሉ። በንኡሳን ርዕሶቹ አካያም የፈተናዎቹን ይዘትና የመርሐትምህርቱን ይዘት፣ በልዩነት የመማሪያ መጽሐፉን ይዘት ዝምድና ይፈተሻል። በቅድሚያ ለዚህ ፍተሻ የሚሆን መረጃ የተገኘባቸውን ፈተናዎች፣ የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉትን መምህራንና ተማሪዎች በአጭሩ ለመቃኘት ይሞክራል።

4.1. የተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ቅኝትና የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ

4.1.1. የተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች አጭር ቅኝት

በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰጡት የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ናቸው። ሁለቱም ፈተናዎች የተዘጋጁት በሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት ነው። የሁለቱም ዓመታት

ADDIS ABABA UNIVERSITY NSE LIBRARY

ፈተናዎች እያንዳንዳቸው ዘጠና፣ዘጠና ጥያቄዎችን ይዘዋል። ፈተናዎቹን ተፈትኖ ለመጨረስም የተሰጠው ጊዜ አንድ ሰዓት ተኩል፣ አንድ ሰዓት ተኩል ነው። ሁለቱም ፈተናዎች በምርጫ ሰጪ የአጠያየቅ ስልት የቀረቡ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ጥያቄም አራት፣ አራት አማራጭ መልሶችን ይዟል። በ1997 ዓ.ም. ፈተና ላይ ሁለት የዝርው ምንባቦች ሲቀርቡ፣ በ1998 ዓ.ም. ፈተና ላይ አንድ የዝርው ምንባብና አንድ አጭር የግጥም ምንባብ ቀርቧል። የ1997 ዓ.ም.ቱ ዝርው ምንባቦች የቀረቡት ከ21ኛው እና ከ84ኛው ጥያቄ በኋላ ነው። ከ1997 ዓ.ም. ዝርው ምንባቦች ውስጥ የመጀመሪያው በሁለት አንቀጾች ወይም በ39 መስመሮች የቀረበ ሲሆን 10 ጥያቄዎች ተዘጋጅተውበታል። የሁለተኛው ደግሞ በአራት አንቀጾች ወይም በ33 መስመሮች የቀረበ ሲሆን 6 ጥያቄዎችም ተዘጋጅተውበታል። የ1998ቱ ዓ.ም. ዝርው ምንባብ ከ42ኛው ጥያቄ በኋላ የቀረበ ሲሆን፣ በ4 አንቀጾች ወይም በ24 መስመሮች የቀረበ ሆኖ 11 ጥያቄዎች ከምንባቡ ውስጥ ወጥተዋል። የ1998 ዓ.ም.ቱ አጭር የግጥም ምንባብ ከ84ኛው ጥያቄ በኋላ የቀረበ ሲሆን በ8 ስንኞች የተቋጠረ ሆኖ 6 ጥያቄዎች ቀርበውበታል። የሁለቱን ዓመታት የፈተና ጥያቄዎች ዓይነትና ብዛት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል።

ሠንጠረዥ 8፡- በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. በሀገር-አቀፍ ደረጃ የተሰጡ የ10ኛ ክፍል ማጠቃለያ ብሔራዊ ፈተናዎች የትኩረት ነጥብና ብዛት

		የ 1997 ዓ.ም. ፈተና		የ 1998 ዓ.ም. ፈተና	
ተ.ቁ	የጥያቄዎቹ ዓይነት	ብዛት		ብዛት	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%
1	ስለ ማዳመጥ ክሂል የሚያወሱ ጥያቄዎች	4	4.4	-	-
2	ስለ ንግግር ክሂል የሚያወሱ ጥያቄዎች	9	10	11	12.2
3	በአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች	14	15.6	22	24.4
4	በጽሕፈት ክሂል ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች	18	20	17	18.9
5	በስነ-ጽሑፍ ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች	18	20	19	21.1
6	በሥነ-ልሳን ሥር				
	6.1. በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች	14	15.6	10	11.1
	6.2. በቃላት ፍቺ ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች	8	8.9	8	8.9
	6.3. በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች	5	5.6	3	3.3
	ድምር	90	100	90	100

4.1.2. የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ

ለዚህ ጥናት በደጋፊነት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሲባል የመምህራኑንና ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ተበትኖላቸው ሞልተዋል። የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት መምህራን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉት በናሙና የተመረጡ በሁለት የመንግሥትና በሁለት የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው። ከዚህ በታች የጽሑፍ መጠይቁን በአግባቡ ሞልተው ለዚህ ጥናት በአጋዥነት የሚረዱ መረጃዎችን የሰጡ መምህራን ዕድሜ፣ ጾታ፣ በመምህርነት የአገልግሎት ዘመን፣የትምህርት ደረጃና የሥልጠና መስክ፣ ወዘተ. የሚያመለክት ሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 9፡- የጽሑፍ መጠይቁን በተገቢው ሁኔታ ሞልተው የመለሱ መምህራን ዳራ

የመምህራኑ ዳራ			እድሜ					ፆታ		በመምህርነት የአገልግሎት ዘመን				የትምህርት ደረጃ			የሠለጠኑበት የትምህርት መስክ			ከ1997-1999ዓ.ም. ያስተማሩበት ክፍል					በሳምንት በአንድ ክፍል የሚገቡበት ክፍለ ጊዜ		በሚገቡበት ክፍል በአማካይ የተማሪዎች ብዛት			
			ከ21-30 ዓመት	ከ31-35 ዓመት	ከ36-40 ዓመት	ከ41--45 ዓመት	ከ45 ዓ. በላይ	ወ	ሴ	ከ1-5 ዓመት	ከ6-10 ዓመት	ከ11-15 ዓመት	ከ16-ዓመት በላይ	ዲፕሎማ	የመጀመሪያ ዲግሪ	ሁለተኛ ዲግሪ	ዐቢይ አማርኛ	ንዑስ አንግሊዝኛ	ንዑስ ሌላ	9ኛ	10ኛ	11ኛ	12ኛ	ከ9ኛ-12ኛ	3	2	40 - 50	51 - 70	71 - 90	91 - 110
የመንግሥት	ብዛት	በቁ.	4	-	-	-	6	6	4	3	1	-	6	1	9	-	10	4	6	2	-	1	-	7	3	7	-	2	7	1
		%	40	-	-	-	60	60	40	30	10	-	60	10	90	-	100	40	60	20	-	10	-	70	30	70	-	20	70	10
ድምር	ብዛት	በቁ.	10					10		10				10			10	10		10					10		10			
		%	100					100		100				100			100	100		100					100		100			
የግል	ብዛት	በቁ.	3	1	-	-	-	4	-	3	1	-	-	-	4	-	4	4	-	-	-	-	-	4	4	-	4	-	-	-
		%	75	25	-	-	-	100	-	75	25	-	-	-	100	-	100	100	-	-	-	-	-	100	100	-	100	-	-	-
ድምር	ብዛት	በቁ.	4					4		4				4			4	4		4					4		4			
		%	100					100		100				100			100	100		100					100		100			

ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተጨማሪ ከአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በናሙና በተመረጡት ሁለት የመንግሥትና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ የተደረገ ሲሆን፤ መጠይቁንም በአግባቡ ሞልተው ለዚህ ጥናት የሚረዱ አጋዥና መረጃዎችን የሰጡ ተማሪዎች ዳራ እንደሚከተለው ይቀርባል፤

ሠንጠረዥ 10፡- የጽሑፍ መጠይቁን በአግባቡ ሞልተው የመለሱ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ዳራ

የተማሪዎች ዳራ	የክፍል ደረጃ		ዕድሜ				ፆታ			የ10ኛን ክፍል ፈተና የተፈተኑበት ዓ.ም.				ከ1ኛ -8ኛ ክፍል የተማሩበት ት/ቤት			የሳምንት ክፍለ ጊዜ ብዛት		
			15-17	18-20	ከ20 በላይ	ድምር	ወንድ	ሴት	ድምር	1997	1998	ድምር	የሚያስተምሩበት ክፍል የተማሪዎች ብዛት	የመንግሥት	የግል	ድምር	ዳግማ. ሚኒልክ	የካቲት 12	ድምር
																	3	2	
የመንግሥት	11ኛ ክፍል	ብ	69	38	3	110	57	53	110	-	110	110	50-70	57	53	110	60	50	110
		%	62.3	34.5	2.7	100	51.8	48.2	100	-	100	100		51.8	48.2	100	54.5	45.5	100
	12ኛ ክፍል	ብ	18	30	6	54	37	17	54	54	-	54	40-60	31	23	54	20	34	54
		%	33.3	55.6	11.1	100	68.5	31.5	100	100	-	100		57.4	42.6	100	37	63	100
	ድምር	ብ	87	68	9	164	94	70	164	54	110	164		88	76	164	80	84	164
		%	53	41.5	5.49	100	57.3	42.7	100	32.9	67.1	100		53.7	46.3	100	48.8	51.2	100
የግል	11ኛ ክፍል	ብ	17	7	-	24	9	15	24	-	24	24	33-48	-	24	24	3	2	-
																	24	-	
		%	70.8	29.2	-	100	37.5	62.5	100	-	100	100		-	100	100	100	-	-
	12ኛ ክፍል	ብ	4	14	-	18	4	14	18	18	-	18	35-44	1	17	18	18	-	-
		%	22.2	77.8	-	100	22.2	77.8	100	100	-	100		5.6	94.4	100	100	-	-
	ድምር	ብ	21	21	-	42	13	29	42	18	24	42		1	41	42	42	-	-
		%	50	50	-	100	31	69	100	42.9	57.2	100		2.4	976.6	100	100	-	-

መምህራኑንና የተማሪዎችን ዳራ ከላይ በሠንጠረዦቹ ለማሳየት ከተሞከረ በኋላ በመቀጠል ዓቢይ የመረጃ ምንጭ የሆኑትን የፈተናዎቹን ይዘት በዋናነት ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር፣ በልዩነት መነሻነት ደግሞ ከመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ጋር ያለውን ዝምድና ለማሳየት በሠንጠረዥ ውስጥ የቀረቡት መረጃዎች ይተነተናሉ።

4.2. በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. የቀረቡት ፈተናዎች ከመርሐትምህርቶች እና፣ ከመማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች ጋር ያላቸው ዝምድና ትንተና

በዚህ ርዕስ ስር በመጀመሪያ የፈተናዎቹ ይዘቶች ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር ያላቸው ዝምድና ይተነተናል። በተጨማሪም በታየው ልዩነት መነሻነት ከመማሪያ መጽሐፉ ይዘቶች ጋር ያለው ተዛምዶ ይፈተሻል። ይኸውም የፈተናዎቹ ይዘቶች ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ባለፈ በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች በክፍል ውስጥ ልምምድ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው። እነዚህ በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የመርሐትምህርት ይዘቶች በአባሪ 4 እና 5 ሥር ተገልጸዋል።

ይህ ጥናት መነሻ የሆነባቸውና በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ዘጠና፣ዘጠና ያህል ጥያቄዎችን ይዘዋል። እነዚህ ዘጠና፣ ዘጠና ጥያቄዎች ከያዟቸው ይዘቶች አንጻር በዚህ ጥናት በስድስት ዋና ዋና እና በሦስት ንዑሳን ክፍሎች ተከፍለዋል። በዚህም መሠረት ፈተናዎቹ ስለማዳመጥ ክሂል የሚያወሱ፣ ስለንግግር ክሂል የሚያወሱ፣ በአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ የተመሠረቱ፣ በጽሕፈት ክሂል ላይ የተመሠረቱ፣ በሥነጽሑፍ ላይ የተመሠረቱ፣ በሥነልሳን ክሂል ሥር ደግሞ በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ፣ በቃላት ፍቺ ላይ የተመሠረቱ እና በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ተብለው በስድስት ዋናና በሦስት ንዑስ ምድቦች ውስጥ ቀርበዋል። (ይህም በሠንጠረዥ 8 ላይ ተመልክቷል)።

4.2.1. በ1997 ዓ.ም. የቀረበው ፈተና ይዘት ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

4.2.1.1. ፈተናው ከማዳመጥ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 11፦ ፈተናው ከማዳመጥ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የማዳመጥ ክሂል	የማዳመጥ ስልት	ከ57-59፤62	ዋና ጥያቄ	4	4.4	1. የልዩ ልዩ ጉባኤዎች መልዕክቶችን ማዳመጥ	10ኛ ክፍል
						2. ውይይት 3. ጭውውት	9ኛ እና10ኛ ክፍሎች
						4. ያዳመጡትን ንግግር ዋናና ዝርዝር ሐሳብ መለየት	9ኛ ክፍል
	ድምር			4	4.4		

የማዳመጥ ክሂልን በሚመለከት በፈተናው ውስጥ የቀረቡት 4 ጥያቄዎች ሲሆኑ፤ በመቶኛ ስሌት 4.4 (4.4%) ናቸው። ይዘታቸውም የማዳመጥ ስልትን የሚገመግሙ ሲሆኑ፤ በመርሐትምህርቱ ውስጥ የሚገኙት ይዘቶች ደግሞ የልዩ ልዩ ጉባኤዎች መልዕክቶችን ማዳመጥ፤ ውይይት፤ ጭውውት እና ያዳመጡትን ንግግር ዋናና ዝርዝር ሐሳብ መለየት የሚሉ ናቸው። እነዚህም ይዘቶች የማዳመጥን ስልት ለማወቅ የሚረዱ ናቸው፤ በመሆኑም በክሂሉ ላይ ለፈተናው የቀረበው ይዘት ከመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘት ጋር ዝምድና አለው።

4.2.1.2. ፈተናው ከንግግር ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 12፡- ፈተናው ከንግግር ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ይዘት መረጃ ዝርዝር	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የንግግር ክሂል	1. ንግግራዊ ባህርይ የሚታይበትን ዐ.ነገር መለየት 2. ጭውውት 3. እርግጠኛ የሆነ ሐሳብን መግለጽ 4. ድንገተኛ ንግግር	ከ51-56፣60፣63፣64	ዋና ጥያቄ	9	10	1. አንድን ሃሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ	9ኛ ክፍል
						2. በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ	9ኛ ክፍል
						3. ውይይት፣ ጭውውት	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						4. ዘገባ በቃል ማቅረብ	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						5. ንግግር	10ኛ ክፍል
						6.የዱብዳ ንግግር	10ኛ ክፍል
						7. ክርክር	10ኛ ክፍል
						8.ያንድን ንግግር ይዘት በራስ አባባል ማሳጠር	10ኛ ክፍል
	ድምር			9	10		

በንግግር ክሂል ስር በፈተናው ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች 9 ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ በመቶኛም ስሌት 10 (10%) ናቸው፤ እነዚህም ንግግራዊ ባሕርይ የሚታይበትን ዐረፍተ ነገር መለየት ጭውውት፣ እርግጠኛ የሆነ ሐሳብን መግለጽ እና ስለድንገተኛ ንግግር ሲሆን፣ በመርሐትምህርቱ ውስጥ የሚገኘው ዝርዝር ይዘት ደግሞ አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ፣ በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ፣ ውይይት፣ ጭውውት፣ ዘገባ በቃል ማቅረብ፣ ንግግር፣ የዱብዳ ንግግር፣ ክርክር፣ ያንድን ንግግር ይዘት በራስ አባባል ማሳጠር የሚሉ ናቸው። እነዚህን ይዘቶች ተማሪው ቀደም ብሎ በክፍል ውስጥ ይማራቸዋል ተብሎ የሚጠበቅ

በመሆኑ በፈተናው ውስጥ መጠየቁ ተገቢነት አለው ለማለት ይቻላል። በመሆኑም በክሂሉ ላይ ለፈተናው የቀረበው ዝርዝር ይዘት ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር ዝምድና አለው።

4.2.1.3. ፈተናው ከአንብቦ መረዳት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 13፡- ፈተናው ከአንብቦ መረዳት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የንባብ ክሂል	አንብቦ መረዳት	ከ22-31፣ ከ85-88	ዋና ጥያቄ	14	15.6	1. የአንድን ዕሁፍ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦች መለየት	10ኛ ክፍል
						2. አንብቦ መረዳት - ነባር ዕውቀትን ከሚነበበው ጋር ማስተሳሰር	10ኛ ክፍል
						3. አንብቦ መረዳትን በተለያየ መንገድ መግለጽ	9ኛ ክፍል
		-				4. ከልዩ ልዩ መግለጫዎች የመረጃ ሐሳብ ማግኘት	9ኛ እና10 ክፍሎች
		-				5. የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም	10ኛ ክፍል
		-				6. የመረጃዎች አጠቀቀም - ዕውደ-ጥበብ - ኢንይክስ	10ኛ ክፍል
	ድምር			14	15.6		

ከላይ በሠንጠረዡ እንደሚታየው በይዘቶች አመዳደብ መሠረት ስለንባብ ክሂል የተጠየቁት 14 ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ በመቶኛ ስሌት 15.6 (15.6%) ናቸው። እነዚህ የፈተናው ጥያቄዎች ከ3ቱ ማለትም የአንድን ጽሑፍ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦች መለየት፣ ነባር ዕውቀትን ከሚነበበው ይዘት ጋር ማስተሳሰር፣ አንብቦ መረዳትን በተለያየ መንገድ መግለጽ ከሚሉት የመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች ጋር ዝምድና አላቸው። ነገር ግን ከላይ በሠንጠረዡ እንደተቀመጠው ሦስቱ የመርሐትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ ይዘቶች ናቸው። እነሱም "ከልዩ ልዩ

መግለጫዎች የመረጃ ሐሳብ ማግኘት፣ የቤተ-መጻሕፍት አጠቃቀም፣ የመረጃዎች አጠቃቀም (ዐውደ-ጥበብ፣ ኢንዴክስ)" የሚሉ ይዘቶች ናቸው።

4.2.1.4. ፈተናው ከጽሕፈት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 14፡- ፈተናው ከጽሕፈት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የጽሕፈት ክሂል	1. አንቀጽን ማስፋፋት 2. የአንቀጽ ኃይለ-ቃል 3. የድርሰት ዓይነቶች 4. ሥርዓተ ነጥብ 5. የጽሑፍ ዓይነት፣ አደረጃጀት 6. የዘገባ ባህርይ	ከ1-6፣ከ9-17፣ 21፣89፣90	ዋና ጥያቄ	18	20	1. አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ	9ኛ ክፍል
						2. ሥርዓተ ነጥቦች	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						3. አንቀፆችን በተለያዩ ስልቶች አደራጅቶ መፃፍ	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						4. ድርሰት	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						5. ዘገባ ማቅረብ	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						6. ማስታወሻ መውሰድ	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						7. የአንድን ጽሑፍ ይዘት በራስ አባባል ማሳጠር	10ኛ ክፍል
	ድምር			18	20		

የጽሕፈት ክሂልን ይዘት በሚመለከት በፈተናው ውስጥ የተጠየቁ ጥያቄዎች 18 ሲሆኑ፣ በመቶኛም ስሌት 20 (20%) ናቸው። የእነዚህ ጥያቄዎች ይዘት "አንቀጽን ማስፋፋት፣ የአንቀጽ ኃይለ-ቃል፣ የድርሰት ዓይነቶች፣ ሥርዓተ ነጥብ፣ የጽሑፍ ዓይነት እና አደረጃጀት እንዲሁም የዘገባ ባሕርይ" በሚሉት ዙሪያ ያጠነጠኑ ናቸው። በዚህ ክሂል ሥር የሠፈሩት የመርሐትምህርት ይዘቶች ደግሞ ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው "አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ፣ ሥርዓተ ነጥቦች፣ አንቀጾችን በተለያዩ ስልቶች አደራጅቶ መፃፍ፣ ድርሰት፣ ዘገባ ማቅረብ፣ ማስታወሻ መውሰድ እና የአንድን ጽሑፍ ይዘት በራስ አባባል ማሳጠር" ናቸው። በመሆኑም የመርሐትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው ይዘቶች ውስጥ

በመንፀባረቁ ተማሪዎቹ እነዚህን ይዘቶች መጠየቃቸው ተገቢ ነው። በተጨማሪም እነዚህ የፈተና ይዘቶች እና የመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች ተመሳሳይ በመሆናቸው ሁሉቱም ከዚህ ክሂል አንጻር ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን እንረዳለን።

4.2.1.5. ፈተናው ከሥነ ጽሑፍ ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 15፡- ፈተናው ከሥነ ጽሑፍ ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የሥነ-ጽሑፍ ዕውቀት	1. ምሳሌያዊ ንግግሮች 2. የግጥም ጽሑፋዊ አቀማመጥ 3. የልቦለድ አላባውያን 4. የፈጠራ ጽሑፍ 5. ረጅምና አጭር ልቦለድ	ከ32-49	ዋና ጥያቄ	18	20	1.የፈጠራ ጽሑፍ	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						2. የልቦለድ አላባውያን	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						3. ግጥም	9ኛ ክፍል
						4. የሥራ እና የፍቅር ቃል ግጥሞች	10ኛ ክፍል
						5. ምሳሌያዊ ንግግር	10ኛ ክፍል
	1. ቅኔ	47-49	ዋና ጥያቄ			-	
	-					6. ፈሊጦች	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
	-					7. ዘይቤአዊ አነጋገሮች	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
	ድምር			18	20		

በዚህ የትምህርት ክፍል ሥር ለፈተና የቀረቡት ይዘቶች 6 ናቸው። ከነዚህ ይዘቶች አንጻር የተሰጡት ጥያቄዎችም 18 ሲሆኑ፣ በመቶኛ ስሌት 20 (20%) ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 15 ጥያቄዎች ከመርሐ ትምህርቶቹ ይዘቶች ጋር ተዛምዶ ያላቸው ሲሆኑ፣ ሦስቱ የቅኔ ጥያቄዎች ግን በሁሉቱም መርሐ ትምህርቶች ውስጥ የሌለ ይዘትን መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው። የፈተናው ይዘቶችም "ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ የግጥም ጽሁፋዊ አቀማመጥ፣ የልቦለድ አላባውያን፣ የፈጠራ ጽሑፍ እና ረጅምና አጭር ልቦለድን እና ቅኔን በሚመለከት ሲሆኑ፣" የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ደግሞ "የፈጠራ ጽሑፍ፣ የልቦለድ አላባውያን፣ ግጥም፣ የሥራ እና የፍቅር ቃል ግጥሞች፣ ምሳሌያዊ ንግግር፣ ፈሊጦች እና ዘይቤአዊ አነጋገሮች" ናቸው።

በእነዚህ የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ 5ቱ ከፈተናው ይዘት ጋር ተዛምዶ ሲኖራቸው፣ የመጨረሻዎቹ 2ቱ ማለትም "ፈሊጣዊ አነጋገሮችና ዘይቤዎች" በፈተናው ውስጥ ያልተካተቱ ይዘቶች ናቸው። ማለትም ፈሊጦችንና ዘይቤዎችን የሚመለከቱ የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ ይዘቶች ናቸው። ስለዚህ በመርሐትምህርቶቹ ያልተካተተ ይዘት ቅኔ በፈተናው ውስጥ በመጠየቁ እና በመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ውስጥ የተካተቱት ፈሊጦችና ዘይቤዎች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ባለመቅረባቸው በዚህ የሥነጽሑፍ ክሣል ሥር ያሉት የፈተናው ጥያቄዎች በተወሰነ ደረጃ ከመርሐትምህርቱ ጋር ተዛምዶ የላቸውም ለማለት ይቻላል።

4.2.1.6 ፈተናው ከሥነልሳን ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

4.2.1.6.1 በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 16፡- በሰዋስው ላይ ከተመሠረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
-የስነልሳን (ሰዋስው) ዕውቀት	1. የዐ.ነገር ሥርዓት 2. መነሻ ቃል 3. የብዙ ቁጥር 4. ነጠላ (ተራ) ዐ.ነገር 5. የያታ ልዩነት አመልካች 6. የማሰሪያ አንቀጽ መጥበቅ 7. የድምፀ-ልሳናት ቦታ ለውጥ 8. የቋንቋ ባህርይ 9. የቃል ክፍል	ከ18-20፣ ከ71-74፣ ከ78-84	ዋና ጥያቄ	14	15.6	1. የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት	10ኛ ክፍል
						2. ቅጥያዎችን መለየት	9ኛ ክፍል
						3. ምዕላዶች	10ኛ ክፍል
						4. የቃላትን ቅርጽ በመደብ፣ በያታ፣ በቁጥር መለየት	9ኛ ክፍል
						5. ተራ እና ውስብስብ ዐ.ነገር	9ኛ ክፍል
						6. የሀረግ ዓይነቶች	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
	10. አሉታዊ ሀሳብ የያዘ ዐ.ነገር	74				-	
	11 ትእዛዛዊ ዐ.ነገር	79				-	
	-					7. መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጎች	9ኛ ክፍል
	-					8. ገላጮች (የስም እና የግሥ)	9ኛ ክፍል
	ድምር			14	15.6		

በዚህ የሥነልሳን ዕውቀት ክፍል ሥር የሰዋስውን ይዘት በሚመለከት በፈተናው ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች ከላይ በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው 14 ሲሆኑ፣ በመቶኛም ስሌት 15.6 (15.6%) ናቸው። እነዚህ 14ቱ የፈተናው ጥያቄዎች በ11 የፈተናው ይዘቶች ላይ ተመስርተው የቀረቡ ሲሆን፣ ከ11ዱ የፈተናው ይዘቶች ውስጥ 2ቱ ይዘቶች ማለትም "አሉታዊ ሀሳብ የያዘ ዐ.ነገር እና ትእዛዛዊ ዐ.ነገር" በመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ውስጥ የሌሉና ከመርሐትምህርቱ ጋር የማይዛመዱ ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች 8 ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ 6ቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ሲጠየቁ፣ 2ቱ ይዘቶች ግን ማለትም "የመሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጎች እና ገላጮች (የስም እና የግሥ)" በፈተናው ውስጥ ያልተካተቱ ይዘቶች ናቸው።

በዚህ የስነ-ልሳን የትምህርት ክፍል ሥር ያለ የሰዋስው ዕውቀትን በሚመለከት ፈተናውና መርሐትምህርቱ ያላቸው ዝምድና ቢያመዝንም በፈተናው ውስጥ ያሉ ሁለት ይዘቶች በመርሐትምህርቶቹ ውስጥ ባለመኖራቸው እና በመርሐትምህርቶቹ ውስጥ የሠፈሩ ሁለት ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ባለመካተታቸው በተወሰነ ደረጃ የፈተናው ይዘትና የመርሐትምህርቱ ይዘት ተዛምዶ ይጎድለዋል ለማለት ያስችላል።

4.2.1.6.2 በቃላት ፍቺ ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 17፡- በቃላት ፍቺ ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የስነ-ልሳን (የቃላት ፍቺ) ዕውቀት	1. በዐ.ነገሮች ውስጥ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ	ከ66-70፣ ከ75-77	ዋና ጥያቄ	8	8.9	1. የቃላት እና የሐረጎች ተመሳሳይ	9ኛ ክፍል
						2. የቃላት እና የሐረጎች ተቃራኒ	9ኛ ክፍል
	2. ጥምር ቃል በዐ.ነገር ውስጥ	77				-	
	-					3. የሚጠብቁና የሚላሉ ድምፆች	9ኛ ክፍል
	-					4. እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	9ኛ ክፍል
	ድምር			8	8.9		

በዚህ የሥነልሳን ዕውቀት ንዑስ ክፍል የሆነው የቃላትን ፍቺ የሚመለከት ይዘት በፈተናው ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች 8 ሲሆኑ፣ በመቶኛም ስሌት 8.9(8.9%) ናቸው። እነዚህ 8 ቃላት ጥያቄዎች በ2 የፈተናው ይዘቶች ላይ የተመሠረቱ ሲሆን፣ ከ2ቱ የፈተናው ይዘቶች ውስጥ አንዱ ማለትም "ጥምር ቃላት በዐነገር ውስጥ" የሚለው የፈተናው ይዘት በመርሐትምህርቶቹ ውስጥ የሌለና ከመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ጋር የማይዛመድ ነው። እንዲሁም የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች 4 ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ 2ቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ሲካተቱ ሌሎቹ 2ቱ "የሚጠብቁና የሚላሉ ድምፆች እና እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ" የሚሉት የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ያልተጠየቁ ናቸው። በመሆኑም በዚህ ከቃላት ፍቺ አንጻር አንድ የፈተናው ይዘት በመርሐትምህርቶቹ ውስጥ የሌለ በመሆኑና ሁለት የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ባለመካተታቸው በተወሰነ ደረጃ ፈተናውና መርሐትምህርቱ የማይዛመዱ መሆናቸውን እንረዳለን።

4.2.1.6.3. በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 18፡- ፈተናው በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ ከተመሠረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
ስነልሳን (ተጠየቃዊ አስተሳሰብ) ዕውቀት	1. የዐ.ነገር መልዕክት፣ አንድምታ 2. የዐ.ነገር መልዕክት መንስዔና ውጤት 3. የክሂሎች ትስስር	7፣8፣50፣61፣65	ዋና ጥያቄ አማራጭ	5	5.6	1. ተጠየቃዊ አስተሳሰብ	10ኛ ክፍል
						2. ተጠየቃዊ አስተሳሰብ - የመንስዔና ውጤት ግንኙነትና ልዩነት	9ኛ ክፍል
	ድምር			5	5.6		

ይህ የስነልሳን ትምህርት ክፍል ንዑስ ይዘት የሆነው የተጠየቃዊ አስተሳሰብ ይዘት በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ 5 ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን፣ በመቶኛ ስሌት 5.6 (5.6%) ነው። እነዚህም ጥያቄዎች ከ3 የፈተናው ይዘት አንጻር የቀረቡ ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች 2 ሲሆኑ፣ እነዚህም የሚያነሷቸው ነጥቦች አኳያ ከፈተናው ይዘት ጋር የቅርብ ተዛምዶ ያላቸው ናቸው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

4.2.1.7. **ፈተናው ከክሂልና ከዕውቀት ይዘቶች ጋር ያለው አጠቃላይ ዝምድና ትንተና**

ሠንጠረዥ 19፡- ከክሂልና ከዕውቀት ይዘቶች ጋር ያለው አጠቃላይ ዝምድና

ዓብይ ትምህርት ክፍል	የትምህርት ክፍል	የጥያቄ ይዘቶች ብዛት	ከመርሐትምህርቱ ጋር የሚዛመዱና የማይዛመዱ ይዘቶች ብዛት		ይዘቶቹ የቀረቡበት ጥያቄ ብዛት	የመርሐ ትምህርት ዝርዝር ይዘቶች ብዛት	በፈተናው ውስጥ የተጠየቁና ያልተጠየቁ የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘቶች ብዛት	
			የሚዛመዱ	የማይዛመዱ			የተጠየቁ	ያልተጠየቁ
1. የቋንቋ ክሂል	1.የማዳመጥ ክሂል	1	1	-	4	4	4	-
	2.የንግግር ክሂል	4	4	-	9	8	8	-
	3.የንባብ ክሂል	1	1	-	14	6	3	3
	4. የጽሕፈት ክሂል	6	6	-	18	7	7	-
	ድምር	12	12	-	45	25	22	3
2.የቋንቋ ዕውቀት	1.የሥነ ጽሑፍ ዕውቀት	6	5	1	18	7	5	2
	2.የሥነልሳን ዕውቀት 2.1. ሰዋሰው 2.2. የቃላት ፍቺ	11	9	2	14	8	6	2
	2.3.ተጠየቃዊ አስተሳሰብ	2	1	1	8	4	2	2
		3	3	-	5	2	2	-
	ድምር	22	18	4	45	21	15	6
ጠቅላላ ድምር		34	30	4	90	46	37	9

ከላይ በሠንጠረዡ የቀረበው አጠቃላይ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ከ34 የጥያቄ ይዘቶች ውስጥ 30ዎቹ ይዘቶች ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር የሚዛመዱ ሲሆኑ፣ 4 ይዘቶች ብቻ አይዛመዱም። እንዲሁም የመርሐትምህርቱ ይዘቶች 46 ሲሆኑ፣ ከነዚህ ውስጥ 37 ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ሲጠየቁ 9ኙ ይዘቶች ግን አልተጠየቁም። ከዚህ ውጤት የምንረዳው አብዛኞቹ የፈተናው ይዘቶች ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር የሚዛመዱ እና አብዛኞቹ የመርሐትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ የተጠየቁ መሆናቸውን ነው። ሌላው ከክሂል ስርጭት አንጻር ስናየው ይህ የ1997 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና የጥያቄዎቹ ብዛት በተመጣጠነ ደረጃ ባይሆኑም ሁሉንም የክሂል ዓይነቶች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ያካተተ ነው። እንዲሁም ከመረጃው እንደምንረዳው ዓቢይ የቋንቋ ክሂል የሆኑት የማዳመጥ

ክሂል፣ የንግግር ክሂል፣ የንባብ ክሂል፣ የጽሕፈት ክሂል እና የቋንቋ ዕውቀት የትምህርት ክፍል ከሆነው ከሥነልሳን ንዑስ ክፍል የተጠየቃዊ አስተሳሰብ የፈተና ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር ይዛመዳሉ። እንዲሁም ዓቢይ የቋንቋ ክሂል ይዘቶችን በሚመለከት ከንባብ ክሂል ከ6ቱ የመርሐትምህርት ይዘቶች ውስጥ 3ቱ በፈተናው ውስጥ አልተጠየቁም። ነገር ግን የሌሎቹ የማዳመጥ፣የንግግር እና የጽሕፈት ክሂል የመርሐትምህርቱ ይዘቶች በሙሉ በፈተናው ውስጥ ቀርበዋል።

የሥነጽሑፍን ዕውቀት ከ "6" ይዘቶች በ "1" ከሥነ-ልሳን ዕውቀት ደግሞ ሰዋስውን ከ11 ይዘቶች በ "2" የቃላት ፍቺን ከ2 ይዘቶች በ "1" የፈተናው ይዘቶች ባጠቃላይ በ "4" የፈተናው ይዘቶች ከመርሐትምህርቱ ጋር አይዛመዱም። ከቋንቋ ዕውቀት የሥነ-ጽሑፍን ዕውቀት ከ7ቱ 2ቱ ከሥነ-ልሳን ዕውቀት ሰዋስውን ከ8ቱ 2ቱ፣ የቃላትን ፍቺ ከ4ቱ 2ቱ ባጠቃላይ 6 የመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ ይዘቶች አላቸው። ሆኖም በአብዛኛው የፈተናው ይዘቶች ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስላላቸው ፈተናው ከመርሐትምህርቱ ጋር ያለው ዝምድና ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል።

በፈተና ይዘትና በመርሐትምህርት ይዘት መካከል ያለው ዝምድና ከፍተኛ መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተቀመጠው ምሁራን በሰፊው ይገልጻሉ። Heaton (1988፡ III፣ 1975 x-xi)፣ Hughes (1989፡10-13)፣ Madsen (1983፡199) ሲያብራሩ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና የተወሰነ የመርሐትምህርት ይዘት መጠናቀቁን ለማመልከት የሚዘጋጅ ነው፤ ለምሳሌ የአመቱ መጨረሻ ፈተናዎች፣ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናዎችና ብሔራዊ ፈተናዎች ናቸው። ምክንያቱም ፈተናዎቹ በአጠቃላይ መሠረት የሚያደርጉት በመርሐትምህርቱ ላይ ሆኖ የሚመዝኑትም ቀደም ሲል የተማሩትን በመሆኑ ነው። ይህን በመደገፍ Brown (1994:259) ሲያስገነዝቡ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና በቀጥታ ከመማሪያ ክፍል ትምህርት፣ ከተዳሰሱት ምዕራፎች፣ ባጠቃላይ ሥርዓተትምህርቱን ብሎም መርሐትምህርቱን ተመርኩዞ የሚዘጋጅ ነው። በመሆኑም የችሎታ መለኪያ ፈተና በሥርዓተትምህርቱ ውስጥ ከታቀፉ የትምህርት ይዘቶች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው።

በመሆኑም ከዚህ ከምሁራኑ ንድፈሐሳብ አንጻር ይህንን ፈተና ስንገመግመው በተመሳሳይ ሁኔታ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አብዛኞቹ የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘቶች

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በፈተናው ላይ ተጠይቀዋል። ነገር ግን ባጠቃላይ 9 የመርሐትምህርቶቹ ዝርዝር ይዘቶች በፈተናው ላይ ባለመጠየቃቸው የቀረቡት የጥያቄዎች ይዘት ናሙናዎች በቂ አይደሉም። ይህም የተወሰኑ የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ባለመቅረባቸው ምክንያት የፈተና ይዘት ናሙናው በቂ አለመሆኑ ከፈተናው የሚጠበቀውን በጎ ምላሽ ወይም ውጤት (Backwash) ይቀንሳል ተብሎ ይታመናል። ሆኖም ግን ከፈተናው ይዘቶች በአብዛኛው ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር የሚዛመዱ በመሆናቸውና አብዛኞቹ የመርሐትምህርት ይዘቶች በፈተናው ውስጥ የተየጠቁ በመሆኑ ፈተናው ከመርሐትምህርቶቹ ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ አለው ለማለት ይቻላል። በተለይ ይህ የ1997 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል ሀገር-አቀፍ ፈተና በፈተናው ውስጥ የክሂሎችን ስርጭት ከማመጣጠንና ሁሉንም የክሂሎች ዓይነት ናሙና በፈተናው ውስጥ በማካተቱ የራሱ የሆነ ጠንካራ ጐን አለው ተብሎ ይታመናል።

4.2.2. በ 1998 ዓ.ም. የቀረበው ፈተና ይዘት ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

4.2.2.1. ፈተናው ከማዳመጥ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 20፡- ፈተናው ከማዳመጥ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

ዓቢይ የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት	%		
የማዳመጥ ክሂል	-	-	-	-	-	1. የልዩ ልዩ ጉባኤዎች መልእክትን ማዳመጥ	10ኛ ክፍል
						2. ውይይት 3. ጭውውት	9ኛእና 10ኛ ክፍሎች
						4. ያዳመጡትን ንግግር ዋናና ዝርዝር ሐሳብ መለየት	9ኛ ክፍል
	ድምር			-	-		

በሠንጠረዡ ላይ በተቀመጠው መረጃ መሠረት የማዳመጥ ክሂልን ይዘት በተመለከተ በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ አልተካተተም። ከሌላ አንጻር የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ግን ይህንን ክሂል በተመለከተ በ4 ተከፍለው ተቀምጠዋል። ስለዚህ ከዚህ ከማዳመጥ ክሂል አንጻር ይህ ፈተና ክሂሎችን ከማመጣጠን አኳያ የተሟላ ናሙና የሌለው መሆኑን እንገነዘባለን።

4.2.2.2. ፈተናው ከንግግር ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 21፡- ፈተናው ከንግግር ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የንግግር ክሂል	1.የቃላዊ ንግግር አጠቃቀም 2. ስለ ልጆች የአነጋገር ስልት 3. ጭውውት 4. መፍትሔ አመንጪ ሃሰብ ለመግለጽ 5. ሀሳብን ማስፋፋት 6. ልማዳዊ ምላሽ፣ አባባል 7. የቅስቀሳ ንግግር 8. ክርክር	ከ28-34፣ ከ36-39	ዋና ጥያቄ አማራጭ	11	12.2	1. አንድን ሃሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ	9ኛ ክፍል
						2. በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ	9ኛ ክፍል
						3. ውይይት፣ ጭውውት	9ኛእና 10ኛ ክፍሎች
						4. ዘገባ በቃል ማቅረብ	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						5. ንግግር	10ኛ ክፍል
						6. የዱብዳ ንግግር	10ኛ ክፍል
						7. ክርክር	10ኛ ክፍል
						8. ያንድን ንግግር ይዘት በራስ አባባል ማሳጠር	10ኛ ክፍል
	ድምር			11	12.2		

በዚህ የንግግር ክሂል በሆነው የትምህርት ክፍል 8 የፈተናው ይዘቶች ቀርበዋል። በእነዚህ ይዘቶች ላይ ተመሥርተው የወጡ ጥያቄዎች 11 ሲሆኑ፣ በመቶኛ ስሌት 12.2 (12.2%) ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች 8 ሲሆኑ፣ እነዚህም ይዘቶች ከላይ በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው ከፈተናው ይዘቶች ጋር የቀረበ ዝምድና ያላቸው ናቸው። ምክንያቱም የመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች የሆኑት "ሐሳብን መግለጽ፣ ንግግርን ማድረግ፣ ውይይት፣ ዘገባ በቃል ማቅረብ፣ ንግግር፣ የዱብዳ ንግግር፣ ክርክር፣ የንግግርን ይዘት በራስ አባባል ማሳጠር" የሚሉት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ይማሩታል ተብሎ ስለሚጠበቅ የፈተናው ይዘት የሆኑትን "ሐሳብን መግለጽ፣ ቃላዊ ንግግር፣ የአነጋገር ስልት፣ ጭውውት፣ ሀሳብን ማስፋፋት፣ ልማዳዊ ምላሽ፣ የቅስቀሳ፣ ንግግር፣ ክርክር" የሚመለከት ጥያቄዎችን ለመመለስ አይቸገሩምና መጠየቃቸው ተገቢነት ያለው ነው ለማለት ይቻላል።

4.2.2.3. ፈተናው ከንባብ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 22፡- ፈተናው ከንባብ ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የንባብ ክሂል	አንብቦ መረዳት	ከ 1-12፣ ከ43-48፣ ከ51-53፣75	ዋና ጥያቄ	22	24.4	1. የአንድን ጽሑፍ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦች መለየት	10ኛ ክፍል
						2. ከልዩ ልዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች መረጃዎችን ማግኘት	10ኛ ክፍል
						3. አንብቦ መረዳት ነባር ዕውቀትን ከሚነበበው ጋር ማስተሳሰር	10ኛ ክፍል
						4. አንብቦ መረዳትን በተለያየ መንገድ መግለጽ	9ኛ ክፍል
	-					5. የመረጃዎች አጠቃቀም - ዐውደ-ጥበብ - ኢንዴክስ እና አጠቃቀሙ	9ኛ ክፍል
	-					6. የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም	10ኛ ክፍል
	ድምር			22	24.4		

የንባብ ክሂልን ይዘት የሚመለከት የተጠየቁት የፈተናው ጥያቄዎች 22 ሲሆኑ፣ በመቶኛ ስሌት 24.4 (24.4%) ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቶቹ ዝርዝር ይዘቶች 6ሲሆኑ፣ ከ6ቱ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ 4ቱ ብቻ ከፈተናው ይዘት ጋር ተዛምዶ አላቸው። የቀሩት ከላይ በሠንጠረዡ እንደሚታየው 5ኛው እና 6ኛው የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ያልተጠየቁ ናቸው። በመሆኑም ከ6ቱ የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ውስጥ 2ቱ ይዘቶች ማለትም "የመረጃዎች አጠቃቀም (ዐውደ ጥበብ፣ ኢንዴክስ እና አጠቃቀሙ) እና የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም" የሚሉት የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ባለመቅረባቸው በተወሰነ ደረጃ ከዚህ ክሂል አኳያ ተዛምዶ የላቸውም ማለት ይቻላል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
NLS LIBRARY

4.2.2.4. ፈተናው ከጽሕፈት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 23፡- ፈተናው ከጽሕፈት ክሂል ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የጽሕፈት ክሂል	1. የዘገባ አቀራረብ 2. የድርሰት አጻጻፍ ስልት ዓይነት 3. የአንቀጽ ምሥረታ 4. የአንቀጽ ኃይለ-ቃል 5. የሥርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም 6. የጅምር ዐ/ነገርን ሀሳብ ማሟላት 7. አጣማሪ ሐረግ 8. ጽሑፍ የማስፋፋት ስልት	41፣50፡ከ54 -57፣ 60፣70፣72፣ ከ76 - 80፣81፣ 82፣84	ዋና ጥያቄ	17	18.9	1. አንድን ሃሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ	9ኛ ክፍል
						2. ሥርዓተ ነጥቦች	9ኛእና 10ኛ ክፍሎች
						3. አንቀፆችን በተለያዩ ስልቶች አደራጅቶ መፃፍ	9ኛእና 10ኛ ክፍሎች
						4. ድርሰት	9ኛእና 10ኛ ክፍሎች
						5. ዘገባ ማቅረብ	9ኛእና 10ኛ ክፍሎች
						6. ማስታወሻ መውሰድ	9ኛ እና10ኛ ክፍሎች
						7. የአንድን ጽሑፍ ይዘት በራስ አባባል ማሳጠር	10ኛ ክፍል
	ድምር			17	18.9		

በዚህ የትምህርት ክፍል የቀረቡት የፈተናው ጥያቄዎች 17 ሲሆኑ፣ በመቶኛ ስሌት 18.9 (18.9%) ናቸው። የእነዚህ ጥያቄዎች ይዘትም ከላይ በሠንጠረዡ በቅደም ተከተል እንደተቀመጡት "የዘገባ አቀራረብ፣ የድርሰት አጻጻፍ ስልት እና ዓይነት፣ የአንቀጽ ምሥረታ፣ ወዘተ. እያሉ እስከ 8 የሚደርሱ" ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች 7 ሲሆኑ፣ እነሱም "አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ፣ ሥርዓተነጥቦች፣ አንቀጾችን በተለያዩ ስልቶች አደራጅቶ መፃፍ፣ ወዘተ." ናቸው። እነዚህ ይዘቶችም ሙሉ በሙሉ ከፈተናው ይዘት ጋር ተዛምዶ አላቸው። ስለዚህ የፈተናው የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ከመርሐትምህርቶቹ ዝርዝር ይዘቶች ጋር ዝምድና አላቸው።

4.2.2.5. ፈተናው ከሥነጽሑፍ ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 24፡- ፈተናው ከሥነጽሑፍ ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የሥነጽሑፍ ዕውቀት	1. ምሳሌያዊ አባባል 2. ፈሊጣዊ አባባል 3. ቃላዊ ግጥም 4. ለተውኔትና ለልቦለድ የጋራ የሆነ 5. የልቦለድ አላባውያን 6. ዘይቤ	ከ13 - 26፣ 58፣59፣64፣ 87፣88	አማራጭ ዋና ጥያቄ	19	21.1	1. የፈጠራ ጽሑፍ	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						2. የልቦለድ አላባውያን	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						3. ግጥም	9ኛ ክፍል
						4. የሥራ እና የፍቅር ቃል ግጥሞች	10ኛ ክፍል
						5. ምሳሌያዊ ንግግር	10ኛ ክፍል
						6. ፈሊጦች	9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች
						7.ዘይቤአዊ አነጋገሮች	9ኛእና10ኛ ክፍሎች
	ድምር			19	21.1		

የሥነጽሑፍ ዕውቀት የሆነውን ይህን የትምህርት ክፍል በሚመለከት በፈተናው ውስጥ ያሉት ይዘቶች 6 ናቸው። እነዚህም "ምሳሌያዊ አባባል፣ ቃላዊ ግጥም፣ ተውኔትና ልቦለድ፣ የልቦለድ አላባውያን እና ዘይቤ" ሲሆኑ፣ እነዚህን ይዘቶች የሚያንፀባርቁ 19 ጥያቄዎች ቀርበዋል፤ በመቶኛም ስሌት 21.1 (21.1%) ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቶቹ ዝርዝር ይዘቶች 7 ሲሆኑ፣ እነሱም የፈጠራ ጽሑፍ፣ የልቦለድ አላባውያን፣ ግጥም፣ የሥራ እና የፍቅር ቃል ግጥሞች፣ ምሳሌያዊ ንግግር፣ፈሊጦች እና ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶችም ከቀረቡት የፈተና ይዘቶች ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው የፈተናው ይዘቶችና የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ይዛመዳሉ ለማለት ያስችላል።

ሌላው ይህን የ1998 ዓ.ም. ፈተና ከ1997 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል ፈተና ለየት የሚያደርገው ነገር በዚህ ትምህርት ክፍል የቅኔ ጥያቄዎችን በፈተናው ውስጥ አለማካተቱ ነው። በርግጥ በመርሐትምህርቶቹ የሥነጽሑፍ ይዘቶች ላይም ቅኔን የሚመለከት ይዘት አልተካተተም። በመሆኑም መርሐትምህርቱ ውስጥ ተግባራዊ እንዲደረግ ያልተቀመጠ ይዘት በፈተናው

ውስጥ ባለመጠየቁ ተገቢ ነው። ነገር ግን ቅኔን የሚመለከት ይዘት እንዴት በመርሐትምህርቱ ውስጥ አልተካተተም የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡

4.2.2..6 ፈተናው ከሥነልሳን ዕውቀት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና ትንተና

4.2.2.6.1 በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች

ሠንጠረዥ 25፡- በሰዋስው ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
የሥነልሳን (ሰዋስው) ዕውቀት	1. ስማዊ፡ ሐረግና ቅጽላዊ፡ ሐረግ 2.ተሳቢን፡ ባለቤት ማድረግ 3. የድምፀ-ልሳናት ቅንጅት ለውጥ 4. ቅጽላዊ ሐረግ 5.ሰዋስዋዊ ስህተት 6. ውስብስብ ዐ/ነገር 7. የቋንቋ፣ ባህርያት 8. የመሸጋገሪያ ቃላት በአጠራጣሪ ሐሳብ	27፣61፣63 ከ65-67 69፣71 74፣84	አማራጭ	10	11.1	1. የቋንቋ መሠረተ ሃሳቦች፣ባህርያት	9ኛ እና10ኛ ክፍሎች
						2. የሐረግ ዓይነቶች	9ኛ እና10ኛ ክፍሎች
						3. ተራና ውስብስብ ዐ/ነገር	9ኛ ክፍል
						4.የቃላትን ቅርጽ በመደብ፣በፆታ፣ በቁጥር መለየት	9ኛ ክፍል
						5.ምዕላዶች	10ኛ ክፍል
						6. ቅጥያዎችን መለየት	9ኛ ክፍል
						7. መሸጋገሪያ ቀላትና ሐረጎት	9ኛ ክፍል
	-					8. ገላጮች (የስም እና የግሥ)	9ኛ ክፍል
	ድምር			10	11.1		

በዚህ በሥነልሳን የትምህርት ክፍል ሥር፣ ንዑስ ክፍል በሆነው የሰዋስውን ይዘት በሚመለከት በፈተናው ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች 10 ሲሆኑ፣ በመቶኛ ስሌት 11.1 (11.1%) ናቸው። እነዚህም 10 የፈተናው ጥያቄዎች በ8 የፈተናው ይዘቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቶቹ ዝርዝር ይዘቶች 8 ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ 7ቱ ከፈተናው ይዘቶች ጋር ተዛምዶ ሲኖራቸው፣ የመጨረሻው አንዱ ማለትም "ገላጮች (የስም እና የግሥ)"የሚለው ይዘት በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቀ ይዘት ነው። ከዚህ አንጻር የፈተናው ይዘቶችና የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች በአብዛኛው (ከ7ቱ ጋር) ተዛምዶ ሲኖራቸው፣ በመጠኑ ማለትም ከአንድ የመርሐትምህርቱ ይዘት አንጻር ተዛምዶ የላቸውም ማለት ይቻላል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

4.2.2.6.2 በቃላት ፍቺ ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች

ሠንጠረዥ 26፡- በቃላት ፍቺ ላይ ከተመሠረቱ የፈተና ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
ሥነልሳን (የቃላት ፍቺ)ዕውቀት	1. በ0/ነገር አውድ ውስጥ የቃላት ትርጉም 2. የመ·ያዊ ቃል ተመሳሳይ 3. የቃላት ምርጫ 4.የቃላት አገባብ 5. በቃል ውስጥ ሆሄ	49፣62፣68፣73፣85፣86፣89፣90	ዋና ጥያቄ አማራጭ አማራጭ	8	8.9	1. የቃላት እና የሐረጎች ተመሳሳይ	9ኛ ክፍል
	-					2. የቃላትእና የሐረጎች ተቃራኒ	9ኛ ክፍል
	-					3. የሚጠቁና የሚላሉ ድምፆች	9ኛ ክፍል
	-					4. እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	9ኛ ክፍል
	ድምር			8	8.9		

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተቀመጠው የሥነልሳን ዕውቀት ንዑስ ክፍል የሆነውን የቃላት ፍቺን በተመለከተ በፈተናው ውስጥ የተጠየቁት የፈተናው ይዘቶች 8 ሲሆኑ፣ በመቶኛም ስሌት 8.9 (8.9%) ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች መሠረት ያደረጉባቸው የፈተናው ይዘቶች 5 ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቱ ይዘቶች 4 ሲሆኑ፣ ከፈተናው ይዘቶች ጋር ተዛምዶ ያለው አንዱ ማለትም የመጀመሪያው የመርሐትምህርት ይዘት "የቃላት እና የሐረጎች ተመሳሳይ" የሚለው ይዘት ብቻ ነው። ሌሎቹ 3ቱ ማለትም "የቃላትና የሐረጎት ተቃራኒ፣ የሚጠቁና የሚላሉ ድምፆች፣ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ" የሚሉት የመርሐትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ያልተጠየቁ ይዘቶች ናቸው። በመሆኑም ከዚህ አንጻር በዚህ ንዑስ

የትምህርት ክፍል አብዛኞቹ የመርሐትምህርቱ ይዘቶች ናሙና በፈተናው ውስጥ ባለመቅረባቸው ፈተናውና መርሐትምህርቱ በጐላ መልኩ ተዛምዶ የላቸውም ማለት ይቻላል።

4.2.2.6.3 በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች

ሠንጠረዥ 27፡- በተጠየቃዊ አስተሳሰብ ላይ ከተመሠረቱ የፈተናው ጥያቄዎች ጋር ያለው ዝምድና

የትምህርት ክፍል	የፈተና ይዘት መረጃ					የመርሐትምህርት ፣ ይዘት መረጃ	
	ይዘት	የቀረበበት ጥያቄ				ዝርዝር ይዘቶች	የቀረበበት የት/ደረጃ
		ቁጥር	ክፍል	ብዛት			
				በቁጥር	%		
ሥነልሳን (ተጠየቃዊ አስተሳሰብ) ዕውቀት	1. የዐ/ነገር መልዕክት፣ አንድምታ 2. የአማራጭ ሀሳብ ይዘት ትርጉም ሰጪነት 3. የአማራጮች ተጠየቃዊነት	35፣40፣ 42	ዋናው ጥያቄ አማራጭ አማራጭ	8	3.3	1. ተጠየቃዊ አስተሳሰብ -የመንስዔና ውጤት ግንኙነትና ልዩነት	9ኛ ክፍል
						2. ተጠየቃዊ አስተሳሰብ	10ኛ ክፍል
	ድምር			3	3.3		

በዚህ ተጠየቃዊ አስተሳሰብ የስነልሳን ዕውቀት ንዑስ የትምህርት ክፍል በሆነው ይዘት ላይ 3 ጥያቄዎች በፈተናው ይዘት ውስጥ የተጠየቁ ሲሆን፣ በመቶኛም ስሌት 3.3 (3.3%) ናቸው። እነዚህ 3 ጥያቄዎችም፡ በ3 የፈተናው ይዘቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እንዲሁም የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች 2 ሲሆኑ፣ እነዚህም ይዘቶች ከፈተናው ይዘቶች ጋር የቀረበ ግንኙነት ስላላቸው የፈተናው ይዘቶችና የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ከዚህ ንዑስ የትምህርት ክፍል አንጻር ሙሉ በሙሉ ተዛምዶ አላቸው ለማለት ያስችላል።

4.2.2.7 ፈተናው ከክሂልና ከዕውቀት ይዘቶች ጋር ያለው አጠቃላይ ዝምድና ትንተና

ሠንጠረዥ 28፡-ፈተናው ከክሂልና ከዕውቀት ይዘቶች ጋር ያለው አጠቃላይ ዝምድና

ዓቢይ የትምህርት ክፍል	የትምህርት ክፍል	የጥያቄ ይዘቶች ብዛት	ከመርሐትምህርቱ ጋር የሚዛመዱና የማይዛመዱ ይዘቶች ብዛት		ይዘቶቹ የቀረቡበት ጥያቄ ብዛት	የመርሐ ትምህርት ዝርዝር ይዘቶች ብዛት	በፈተናው ውስጥ የተጠየቁና ያልተጠየቁ የመርሐትምህርት ዝርዝርይዘቶች ብዛት	
			የሚዛመዱ	የማይዛመዱ			የተጠየቁ	ያልተጠየቁ
1.የቋንቋ ክሂል	1.የማዳመጥ ክሂል	0	0	0	0	4	0	4
	2. የንግግር ክሂል	8	8	-	11	8	8	-
	3. የንባብ ክሂል	1	1	-	22	6	4	2
	4. የጽሕፈት ክሂል	8	8	-	17	7	7	-
	ድምር	17	17	-	50	25	19	6
2. የቋንቋ ዕውቀት	1.የሥነ ጽሑፍ ዕውቀት	6	6	-	19	7	7	-
	2.የሥነ-ልሳን ዕውቀት 2.1 ሰዋሰው	8	8	-	10	8	7	1
	2.2የቃላትፍቺ	5	5	-	8	4	1	3
	2.3.ተጠየቃዊ አስተሳሰብ	3	3	-	3	2	2	-
	ድምር	22	22	-	40	21	17	4
ጠቅላላ ድምር		39	39	-	90	46	36	10

ከላይ በሠንጠረዡ የተቀመጠው አጠቃላይ መረጃ እንደሚያመለክተው በፈተናው ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች 39 ሲሆኑ፣ ሁሉም ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመዱ ናቸው። ከዚህ አንጻር፣ ይህ የ1998 ዓ.ም. የ10ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ጠንካራ ጐን እንዳለው እንረዳለን። እንዲሁም የመርሐትምህርቱ ይዘቶች 46 ሲሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ 36 ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ሲጠየቁ 10 ይዘቶች ግን አልተጠየቁም። በተለይ የዚህ ዓመት ፈተና የጎላ ችግር ከላይ እንደሚታየው የማዳመጥ ክሂልን የሚመለከት በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ በፍፁም አለመካተት ሲሆን፣ በመርሐትምህርቶቹ ውስጥ ግን 4 ቦታ ሰፍረው ይገኛሉ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY AAU LIBRARY

ከላይ እንደተገለፀው ከክሂል አንጻር ሁሉም የፈተናው ይዘቶች ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር ይዛመዳሉ። ነገር ግን ከቋንቋ ክሂል፤ የማዳመጥ ክሂል 4፣ የንባብ ክሂል 2፣ ከሥነልሳን ዕውቀት፤ ሰዋስው 1፣ የቃላት ፍቺ 3፣ ባጠቃላይ 10 የመርሐትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ያልተካተቱ ይዘቶች ናቸው።በፈተናው ይዘትና በመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘት መካከል ያለው ዝምድና ክሂሎችን ከማመጣጠን አኳያ ችግር ያለበት ለመሆኑ የማዳመጥ ክሂልን ይዘት በሚመለከት አንድም ጥያቄ በፈተናው ውስጥ አለመካተቱ ማስረጃ ነው። ከሌሎቹ ክሂሎች አንጻር ግን የፈተናው ይዘትና የመርሐትምርቱ ይዘት ሙሉ በሙሉ ይዛመዳሉ።

በምዕራፍ ሁለት ከተገለፀው የምሁራን ሐሳብ አንጻር ይህን ፈተና ስንገመግመው የይዘት ተገቢነት (Content validity) ችግር ያለበት ነው። የይዘት ተገቢነት እንደ Brown (1994:255)፣ Cohen (1991:497)፣ Hughes (1989:22) እና Harrison (1983:11) አገላለጽ፣ አንድ ፈተና ሊይዝ የሚገባቸውን ነጥቦች ከእየዓይነቱ በናሙናነት ካካተተ የይዘት ተገቢነት አለው ለማለት ይቻላል። ስለሆነም ይዘትን መሠረት በማድረግ የቀረቡት ጥያቄዎች ምን ያህሉ የቋንቋ ክሂሎችን እና ሌሎች ተገቢ የሆኑ ናሙና ጽንሰሀሳቦችን አካቷል የሚለውን ትኩረት ያደርጋል። በመሆኑም የማዳመጥ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶች በመርሐትምህርቱ ውስጥ ቀርቦ በዚህ ፈተና ውስጥ አለመጠየቁ ከክሂሎች የማመጣጠን ስርጭት አንጻር ተገቢነት ይጐድለዋል ለማለት ይቻላል።

4.3 ከመርሐትምህርቱ ጋር ባላቸው ዝምድና መሠረት በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. ፈተናዎች መካከል ያለው ንፅፅራዊ ትንተና

ሠንጠረዥ 29፡- ከመርሐትምህርቱ ጋር ባላቸው ዝምድና በ1997 ዓ.ም. እና በ1998 ዓ.ም. ፈተናዎች መካከል ያለው ንጽጽራዊ ዝምድና

ዓቢይ የትምህርት ክፍል	የትምህርት ክፍል	የጥያቄ ይዘቶች ብዛት		ከመርሐትምህርቱ ጋር የሚዛመዱ እና የማይዛመዱ ይዘቶች ብዛት				ይዘቶቹ የቀረቡበት ጥያቄ ብዛት		የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘቶች ብዛት	በፈተናዎቹ ውስጥ የተጠየቁ እና ያልተጠየቁ የመርሐትምህርት ዝርዝር ይዘቶች ብዛት			
				የሚዛመዱ		የማይዛመዱ					የተጠየቁ		ያልተጠየቁ	
		97	98	97	98	97	98	97	98		97	98	97	98
የቋንቋ ክሂል	1.የማዳመጥ ክሂል	1	0	1	0	-	0	4	0	4	4	0	-	4
	2.የንግግር ክሂል	4	8	4	8	-	-	9	11	8	8	8	-	-
	3. የንባብ ክሂል	1	1	1	1	-	-	14	22	6	3	4	3	2
	4. የጽህፈት ክሂል	6	8	6	8	-	-	18	17	7	7	7	-	-
	ድምር	12	17	12	17	-	0	45	50	25	22	19	3	6
2.የቋንቋ ዕውቀት	1.የሥነጽሑፍ ዕውቀት	6	6	5	6	1	-	18	19	7	5	7	2	-
	2.የሥነልሳን ዕውቀት 2.1 ሰዋስው	11	8	9	8	2	-	14	10	8	6	7	2	1
	2.2 የቃላት ፍቺ	2	5	1	5	1	-	8	8	4	2	1	2	3
	2.3ተጠየቃዊ አስተሳሰብ	3	3	3	3	-	-	5	3	2	2	2	-	-
	ድምር	22	22	18	22	4	0	45	40	21	15	17	6	4
ጠቅላላ ድምር		34	39	30	39	4	0	90	90	46	37	36	9	10

ከላይ በሠንጠረዡ በቀረበው መረጃ መሠረት የማዳመጥ ክሂል በ1997 ዓ.ም. ፈተና ውስጥ ሰ.ጠየቅ፣ በ1998 ዓ.ም. ፈተና ውስጥ ግን አልተጠየቀም። በ1997 ዓ.ም. ፈተና ላይ የቀረቡ ከቋንቋ ክሂል የማዳመጥ፣ የንግግር፣ የንባብ፣ የጽሕፈት ክሂል እና ከቋንቋ ዕውቀት የሥነልሳን ንዑስ ክፍል የሆነው የተጠየቃዊ አስተሳሰብ ከመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘት ጋር

መሉ በመሉ ይዛመዳሉ። ነገር ግን በዚህ በ1997 ዓ.ም. ፈተና ላይ ከቀረቡት 6 የሥነጽሑፍ ይዘቶች ውስጥ በአንዱ፣ ከሥነልሳን ዕውቀት ንዑስ ክፍል ከሆነው 8 የሰዋሰው ይዘቶች ውስጥ በሁለቱ እና ከ5 የቃላት ፍቺ ይዘቶች ውስጥ በአንዱ ባጠቃላይ ከ "4" የመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር አይዛመዱም። ከዚህ አንጻር የ1998 ዓ.ም ፈተና የማዳመጥ ክሂልን ይዘት መሉ በመሉ ከማስቀረቱ በተስተቀር በዓቢይ የቋንቋ ክሂሎችም ሆነ በንዑስ የቋንቋ ክሂሎች ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር መሉ በመሉ ይዛመዳል።

በ1997 ዓ.ም. ይዘቶቹ የቀረቡበትን ጥያቄዎች ብዛት ስንመለከት ለቋንቋ ክሂል 45 ጥያቄዎች ሲቀርቡ፣ ለቋንቋ ዕውቀት 45 ጥያቄዎች ባጠቃላይ 90 ጥያቄዎች ቀርበዋል። ይህ እኩል የሆነ የጥያቄዎች ስርጭት ዓብይ የትምህርት ክፍል ለሆኑት የቋንቋ ክሂል እና የቋንቋ ዕውቀት ሚዛናዊ የሆነው ትኩረት እንደተሰጣቸው ያመለክታል።

በ1998 ዓ.ም. ይዘቶቹ ላይ የቀረቡበትን ጥያቄዎች ብዛት ስናይ የቋንቋ ክሂል ለሆኑት ንግግርን፣ ንባብን፣ ጽህፈትን የሚመለከቱ 50 ጥያቄዎች ሲቀርቡ፣የቋንቋ ዕውቀት ለሆኑት ሥነጽሑፍን፣ የሥነልሳን ንዑስ ክፍል የሆኑት ሰዋሰውን፣ የቃላት ፍቺን እና ተጠየቃዊ አስተሳሰብ 40 ጥያቄዎች ባጠቃላይ 90 ጥያቄዎች ቀርበዋል። ከጥያቄዎቹ ብዛት አንጻር ስናይ በዚህ ፈተና የበለጠ ትኩረት የተሰጠው የማዳመጥ ክሂልን ይዘት ሳይጨምር ዓብይ የቋንቋ ክሂል ለሆኑት ንግግር፣ ንባብና ጽህፈት መሆኑን እንገንዘባለን።

በ1997 ዓ.ም. በፈተና ጥያቄዎች ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች ከቋንቋ ክሂል 3 ይዘቶች ሲሆኑ፣ እነሱም የንባብ ክሂልን የሚመለከቱ ናቸው። እንዲሁም ከቋንቋ እውቀት የሥነጽሑፍ ዕውቀት 2፣ ከሥነልሳን ዕውቀት በሰዋስው 2፣ በቃላት ፍቺ 2 ባጠቃላይ 6 ይዘቶች አልተጠየቁም። በመሆኑም በዚህ አመት በሁለቱም የትምህርት ክፍል በድምሩ "9" የመርሐትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ አልተካተቱም።

በ1998 ዓ.ም. በቋንቋ ክሂል ትምህርት ክፍል አንጻር ከ"25" የመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች ውስጥ 19 ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ሲጠየቁ 6 ይዘቶች ግን አልተጠየቁም። ካልተጠየቁት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል መሉ በመሉ 4 የመርሐትምህርቱ ይዘቶች ያልተጠየቁበት ሲሆን፣ ሌሎቹ 2 ይዘቶች ያልተጠየቁበት ደግሞ የንባብ ክሂል ነው። በዚህ ዓመት ከቋንቋ ዕውቀት የትምህርት ክፍል ከ21 የመርሐትምህርቱ ይዘቶች ውስጥ 17ቱ ሲጠየቁ 4ቱ አልተጠየቁም። ያልተጠየቁትም የሥነልሳን ዕውቀት ንዑስ ክፍል ከሆኑት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
FLS LIBRARY

ከሰዋስው አንድ፣ ከቃላት ፍቺ 3 የመርሐትምህርቱ ይዘቶች ሲሆኑ፣ በሁለቱ ክፍለትምህርት በድምሩ 10 የመርሐትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ አልተካተቱም።

የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. የ10ኛ ክፍል ሀገር-አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከላይ ከቀረበው መረጃ አንጻር ስናነጻጽረው የሁለቱም ፈተና ጥያቄዎች ብዛት እኩል ሲሆኑ ዘጠና፣ ዘጠና ናቸው። የ1997 ዓ.ም. ፈተና በመርሐትምህርቱ ተግባራዊ እንዲደረግ የሠፈረውን የማዳመጥ ክሂል ጥያቄዎች ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ በመጠየቁ ከ1998 ዓ.ም.ቱ ፈተና የተሻለ ጠንካራ ጐን ያለው ፈተና ነው።

ከዚህ አንጻር በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደቀረበው ምሁራን ስለቋንቋ ፈተና ያሉትን ብንጠቅስ Mehrens እና Lehrmann (1974:3) እንደሚያስገነዝቡት፣ የቋንቋ ፈተና የተማሪዎች የማዳመጥ፣ የንግግር፣ የንባብና የፅህፈት፡ ክሂሎችና እንዲሁም የሥነጽሑፍና የሥነልሳን ዕውቀቶችን ከመማራቸው በፊት ያላቸውን ቅድመችሎታ ለመገምገም ወይም ከተማሩ በኋላ የቋንቋ ችሎታቸውን መሻሻል ለመለካትና ምን ያህል ለውጥ እንዳመጡ ለመረዳት የምንመዘንበት ፈተና ነው። ይህን በመደገፍ Anderson. Claphom and wall (1995:171) ሲያብራሩ፣ "የአንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት የሚገለፀው ወካይ የሆኑ ተገቢነት ያላቸውን የቋንቋ ክሂሎች መያዝ ካለመያዙ አንፃር ነው" ይላሉ። ከዚህም ፈተናው መያዝ ያለበትን የቋንቋ ክሂሎች በተመጣጣኝ ሁኔታ ይዞ ከተገኘ የይዘት ተገቢነት ያሟላ መሆኑን አለበለዚያ ግን የይዘት ተገቢነት ችግር ያለበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

የይዘት ተገቢነት በሚመለከት Hughes (1995:23) ሁለት መሠረታዊ ነጠቦችን ያስቀምጣሉ፣ ይኸውም አንደኛው የአንድ ፈተና ይዘት ተገቢነት ከፍተኛ ሲሆን ለመለካት የታሰበው ጉዳይ በትክክል እንዲለካ ያስችላል የሚል ሲሆን፣ ሌላው በመማር-ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ወይም ውጤት (Backwash) የሚመለከት ነው። ይኸውም የይዘት ተገቢነት ከፍተኛ ከሆነ ተፅዕኖው ወይም ውጤቱ (Backwash)አዎንታዊ ይሆናል፣ ካልሆነ ደግሞ በተቃራኒው አሉታዊ ይሆናል። ከዚህ አንጻር የ1998 ዓ.ም.ቱ ፈተና የማዳመጥ ክሂልን ባለማካተቱ የይዘት ተገቢነት ችግር ስላለበት ውጤታዊ (Backwash) ምላሹ አሉታዊ ሊሆን ይችላል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ከምሁራን ሐሳብም የምንረዳው የ1997 ዓ.ም. ፈተና በመርሐትምህርቱ የቀረበውን ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች በተመጣጠነ መልኩ በማካተቱ የተሻለ ፈተና መሆኑን ያረጋግጣል።

እንዲሁም የ1998 ዓ.ም. ፈተና የማዳመጥ ክሂልን ባለማካተቱ በክሂሎች ናሙና ስርጭት በኩል አንድ ጉድለት ታይቶበታል። የ1998 ዓ.ም. ፈተና ጠንካራ ጐን የሆነና ከ1997 ዓ.ም. ፈተና የተሻለ የሚያደረገው በፈተናው ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በሙሉ ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር የሚዛመዱ በመሆናቸው ነው። ሌላው የመርሐትምህርቱ ይዘቶች ባጠቃላይ 46 ሲሆኑ፣ ከነዚህ ውስጥ የ1997 ዓ.ም. ፈተና 37 ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ሲጠየቁ 9 አልተጠቁም፤ በ1998 ዓ.ም. ፈተና 36 ይዘቶች ሲጠየቁ 10 ይዘቶች አልተጠየቁም፤ ከዚህ አንፃር በ1 ይዘት የ1997 ዓ.ም. ፈተና የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ከላይ ከተዘረዘሩት መረጃዎችና የምሁራን ንድፈሐሳብ አንጻር የ1997 ዓ.ም. ፈተና ከይዘት ተገቢነት አንጻር በመርሐትምርቶቹ ውስጥ የቀረቡትን ሁሉንም የክሂል አይነቶች የሚመለከት ናሙናዎችን በፈተናው ውስጥ በማቅረቡ የተሻለ ፈተና ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

ባጠቃላይ የሁለቱንም ዓመት ፈተናዎች ይዘት ስናጤን በአብዛኛው ከመርሐትምህርቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ናቸው። ነገር ግን በተናጠል የእያንዳንዱን ዓመት ፈተና ይዘት ስናይ የ1997 ዓ.ም. ሁሉንም የክሂል ዓይነቶች በናሙናነት በማካተቱ እና በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምርት ይዘቶች ከ1998 ዓ.ም.ቱ ፈተና በ1 አንሶ በመገኘቱ ከ1998 ዓ.ም. ፈተና ይዘት የተሻለ ነው ሊባል ይችላል። እንዲሁም የ1998 ዓ.ም. ፈተና የፈተናዎቹ ይዘቶች ከመርሐትምርቱ ይዘቶች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚዛመዱ በመሆናቸው ከ1997ዓ.ም. ፈተና ይዘት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ይህንን ከዚህ በላይ በቀረቡት መረጃዎች አማካኝነት በፈተናዎቹና በመርሐትምህርቶቹ መካከል በተደረገው ፍተሻ የተገኘውን ውጤት ይዘን ከመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች አንጻርስ ምን ይመስላል የሚለውን ከዚህ በታች ለማየት ተሞክሯል።

4.4. የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ተዛምዶ እና ልዩነት፣

በዚህ ሥር የጥናቱ ዋና ትኩረት የሆነውን የመንግሥት እና የግል ትምህርት ቤት ውጤት ለማነጻጸር መጀመሪያ የጥናቱ ዋና የመረጃ ምንጭ የሆኑትን ፈተናዎች ከይዘት ተገቢነት አንጻር በመፈተሽ ብቃቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የፈተናዎቹን የይዘት ተገቢነት ለማረጋገጥ የሁለቱንም ዓመት ፈተናዎች ቀደም ሲል በክፍል 4.3 ከ9ኛ እና ከ10ኛ ክፍል መርሐትምህርት ይዘት ጋር በማነጻጸር በተገኘው ውጤት መነሻነት በተጨማሪ የፈተናዎቹን ይዘት ከ9ኛ እና ከ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች

አንጻር የተደረገውን ፍተሻና ውጤት በሠንጠረዥና በትንተና መግለጽ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በክፍል 4.3 ትንተና የፈተናው ይዘቶች በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መርሐትምህርቶች ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር የማይዛመዱ ይዘቶች ምናልባት በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ሊኖሩና ተማሪዎቹ ሊማሩት ይችላሉ ከሚል አኳያ ነው። ከተማሩ ደግሞ በፈተናዎቹ ጥያቄዎች ውስጥ መጠየቃቸው ተገቢነት አለው። እንዲሁም በመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ውስጥ ቀርበው በፈተናዎቹ ጥያቄዎች ውስጥ ያልተጠየቁ ይዘቶች፣ ምናልባት በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ካልቀረቡ አለመጠየቃቸው ተገቢ ሊሆን፣ አለዚያ ቀርበው ከሆነ ግን ያለመጠየቁ በሁለቱም የማስተማሪያ መሣሪያዎች እያለ(ማለትም በመርሐትምህርቶቹና በመማሪያ መጻሕፍቱ) ተገቢ አለመሆኑን በእርግጠኝነት ለመወሰን ጠቀሜታ ስላለው ነው። ባጠቃላይ የሁለቱን ዓመት ፈተናዎች ከይዘት ተገቢነት (content validity) አንጻር በማነጻጸር የትኛው የተሻለ ብቃት እንዳለው ለመወሰን ከመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ባለፈ በመማሪያ መጻሕፍቱስ ምን ይመስላል የሚለውን ለማጣራት ሲባል ነው።

በመሆኑም ከዚህ በታች የሁለቱንም ዓመታት ፈተናዎች ይዘት ከመርሐትምህርቱ ጋር የማይዛመዱትን እና በመርሐትምሕርቱ ውስጥ እያሉ በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁትን ይዘቶች መነሻ በማድረግ ከ9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች መማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች ጋር ያላቸውን ዝምድናና ልዩነት በቅደም ተከተል በሠንጠረዥ አማካይነት በትንተና ለማቅረብ ተሞክሯል።

4.4.1. የ1997 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመርሐትምህርቱ እና ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ተዛምዶ እና ልዩነት

ሠንጠረዥ 30፡-የ1997ዓ.ም. ፈተና ይዘት ከመርሐትምህርቱ ጋር ባሳየው ልዩነት ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ዝምድና

ዓቢይ የትምህርት ክፍል	የትምህርት ክፍል	ከመርሐትምህርቱ ጋር የማይዛመዱ የፈተናው ይዘቶች ዓይነትና ብዛት	ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር የሚዛመዱ የፈተናው ይዘቶች ዓይነትና ብዛት	የመጽሐፉ ክፍልና ገጽ		በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቱ ይዘቶች ዓይነትና ብዛት	በፈተና ወስጥ ያልተጠየቁ የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ዓይነትና ብዛት	የመጻሕፍቱ ክፍልና ገጽ	
				9ኛ ገጽ	10ኛ ገጽ			9ኛ ገጽ	10ኛ ገጽ
1.የቋንቋ ክሂል	1. የንባብ ክሂል					1.ከመግለጫ መረጃ ሐሳብ 2.የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም 3. የዕረጃዎች አጠቃቀም -አውደ ጥበብ -ኢንያክስ	1.የስዕላዊ መግለጫ ጥያቄዎች (ግራፍ 9ኛ) (ሠንጠረዥ10ኛ) 2.የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም፣(መመሪያ 9ኛ) በምንባብ መልክ(10ኛ) -	52፣ 75-76 55 -	12-15 112 -
2. የቋንቋ ዕውቀት	1.የሥነጽሑፍ ዕውቀት	1. ቅኔ	-			1.ፊሊጣዊ አነጋገሮች 2.ዘይቤአዊ አነጋገሮች	1. ፊሊጣዊ አነጋገሮች 2. ዘይቤአዊ አነጋገሮች	39፣131፣130	18-19 27፣57፣63፣74፣75፣109፣116
	2.የሥነልሳን ዕውቀት 2.1 ሰዋስው	1.አሉታዊ ዐረፍተ ነገር 2. ትእዛዛዊ ዐ/ነገር	- -			1.መሸጋገሪያ ቃላት (ሐረጐች) 2.ገላጮች (የስም፣የግስ)	1.አያያዥ (መሸጋገሪያ ቃስት) 2.የስም ገላጭ (ምስል የሚከስቱ ቡሚል)	110 -	- 157
	2.2.የቃላት ፍቺ	1.ጥምር ቃላት	1.ጥምር ስሞች (ቃል)	69	28	1.የሚጠበቁና የሚላሉ ድምፆች 2.እማሬያዊና ፍካሬያዊ ትርጉም	1.ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚለጡት የተለያየ ፍቺ 2. እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	78-79 85-87	111 -
ድምር		4	1			9	8		
የሁለቱ ውጤት ልዩነት		3	-1			8	-1		

የመርሐትምህርቶቹ እና የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ልዩነት ውጤት 3 የማይዛመዱ ይዘቶች እና 8 ያልተጠየቁ ይዘቶች ይሆናል። (1 የማይዛመድ እና 1 ያልተጠየቀ በመማሪያ መጻህፍቱ ምክንያት ስለተቀነሰ)

በምዕራፍ ሁለት ላይ ለማስፈር እንደተሞከረው የመማሪያ መጽሐፍ ከሚያካትታቸው ይዘቶች አራቱ የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ) እና ተጓዳኝ የክሂል ዘርፎች የሚባሉት የስነልሳንና የሥነጽሑፍ ይዘቶች ሲሆኑ፣ እነዚህም ይዘቶች ሊገመገሙ፣ ሊሻሻሉና ሊዘጋጁ የሚችሉት በተዘጋጀው መርሐትምህርት ላይ ተመስርተው በመሆኑ የእነዚህ ይዘቶች ተግባራዊ መሆን የመርሐትምህርቱን ዓላማ፣ ግብ ከማድረሱ አኳያ ከፍተኛ ሚና አለው (Nunan 1994:98)። ከዚህ ከምሁራኑ ሐሳብ አኳያ የአሥረኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መጻሕፍት ላይ ስለሚመሠረት ከመርሐትምህቶቹ ባለፈ ከእነዚህ መጻሕፍት ጋር ያለውን ተዛምዶና ልዩነት ለማየት ተሞክሯል።

ከላይ በሠንጠረዡ ላይ በተቀመጠው መረጃ መሠረት የ1997ዓ.ም. ሀገር አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ይዘቶቹ ከመርሐትምህርቱ ጋር የማይዛመዱ 4 ይዘቶች ሲሆኑ፣ እነሱም ቅኔ፣ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር፣ ትእዛዛዊ ዐ/ነገር እና ጥምር ቃላት ናቸው። ከእነዚህ ከ4ቱ በመርሐትምህርቶቹ ውስጥ ያልቀረቡ ነገር ግን በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ከ9ኛ እና ከ 10ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍቱ ይዘቶች አኳያ ስንፈትሽ በ3 ይዘቶች ማለትም በቅኔ፣ በአሉታዊ፣ ዐ/ነገር እና በትእዛዛዊ ዐ/ነገር አይዛመዱም። ነገር ግን በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መርሐትምህርቶች በ4ኛ ደረጃ የማይዛመደውን ከአንድ ይዘት ማለትም ከ "ጥምር ቃላት" ጋር የመማሪያ መጻህፍቱ ይዘት ይዛመዳል። ይህም ይዘት በ9ኛ ክፍል መጽሐፍ ገጽ 69 እና በ10ኛ ክፍል መጽሐፍ ገጽ 28 ላይ ይገኛል። ስለዚህ በፈተናው ውስጥ ከቀረቡት ከመርሐትምህርቶቹ ጋር የማይዛመዱ 4 ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍቱ አንድ ይዘት በመገኘቱ የዚህ ዓመት ፈተና የማይዛመዱ ይዘቶችን ወደ 3 ዝቅ አደርጐታል። ምክንያቱም ተማሪዎች ይህንን ይዘት ማለትም "ጥምር ቃላት"ን በሚመለከት በመማሪያ መጻህፍቱ አማካይነት ይማሩታል ተብሎ ስለሚጠበቅ በፈተናው ውስጥ መጠየቁ ተገቢ ሊያደርገው ይችላል።

ሌላው በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ብዛት 9 ሲሆኑ፣ እነሱም በሠንጠረዡ ላይ ተጽፈው ይገኛሉ። በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመማሪያ መጽሐፉ ይዘቶች ብዛት ግን 8 ናቸው። ይኸውም የመርሐትህርቶቹን 3ኛው ይዘት የሆነው "የመረጃዎች

አጠቃቀም ብሎ በእሱ ሥር ዐውደጥበብ፣ ኢንዴክስ" የሚለው ይዘት በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የለም። በመሆኑም ተማሪዎች ይህንን ይዘት አይማሩትም ተብሎ ይታመናል። ያልተማሩትንም ይዘት መጠየቅ የለባቸውም። በመሆኑም በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቱን ይዘቶች በአንድ (የመረጃዎች አጠቃቀም ብሎ በእሱ ሥር ዓውደ ጥበብ፣ ኢንዴክስ በሚለው) ይዘት ይቀንሰዋል ማለት ነው። ስለዚህ የዚህ ዓመት በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ ይዘቶችን የመማሪያ መጻሕፍቱ ወደ 8 ዝቅ ያደርጉታል።

በአጠቃላይ በመርሐትምህርቶቹና በመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ላይ በተደረገው ፍተሻ የ1997 ዓ.ም.ፈተና ይዘቶች ከመርሐትምሐርቱና ከመማሪያ መጽሐፉ ይዘቶች ጋር የማይዛመዱ 3 የፈተና ይዘቶች ሲኖሩት፣ 8 በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምርቶችና የመማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች አሉበት።

4.4.2 የ1998 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመርሐትምህርቱ እና ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ተዛምዶ እና ልዩነት፤

ሠንጠረዥ 31፡- የ1998 ዓ.ም. ፈተና ይዘት ከመርሐትምህርቱ ጋር ባሳየው ልዩነት ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያለው ዝምድና

ዓቢይ የትምህርት ክፍል	የትምህርት ክፍል	ከመርሐትምህርቱ ጋር የማይዛመዱ የፈተናው ይዘቶች ዓይነትና ብዛት	ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር የሚዛመዱ የፈተናው ይዘቶች አይነትና ብዛት	የመጽሐፉ ክፍልና ገጽ		በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ዓይነትና ብዛት	በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ዓይነትና ብዛት	የመጻሕፍቱ ክፍልና ገጽ	
				9ኛ ገጽ	10ኛ ገጽ			9ኛ ገጽ	10ኛ ገጽ
1.የቋንቋ ክሂል	1.የማዳመጥ ክሂል	0	0	-	-	4. ባጠቃላይ የማዳመጥ ክሂልን ይዘት	4. ባጠቃላይ የማዳመጥ ክሂልን ይዘት		
	2.የንባብ ክሂል					1.የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም	1.የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም -(በመመሪያ) (በምንባብ መልክ)	55 -	- 112
						2.የመረጃ አጠቃቀም -አውደጥበብ -ኢንይክስ	-		
2. የቋንቋ ዕውቀት	1.የሥነልሳን ዕውቀት 1.1 ሰዋስው					1. ገላጭ (የስም የግስ)	1.ምስል የሚከስቱ በሚልየስም ገለጭ ብቻ፤	-	157
	1.2.የቃላት ፍቺ					1.የቃላትና የሐረጋት ተቃራኒ 2. የሚጠብቁና የሚላሉ ድምፆች 3. እማሬያዊና ፍክሬያዊ ፍቺ	1. የቃላት ተቃራኒ 2. ሊጠብቁና ሊላሉ ሁለት ትርጉም ያላቸው ቃላት 3. እማሬያዊና ፍክሬያዊ ፍቺ	52 8፤ 79 85 - 87	- 111 -
	ድምር	0	0			10	9		
የሁለቱ ውጤት ልዩነት		0	0	-	-		-1(9)		

በዚህ የመርሐትምህርቶቹ እና የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ልዩነት ውጤት የማይዛመዱ የሉም።1(የመረጃዎች አጠቃቀም ብሎ በሥሩ ዓውደ ጥበብ፣ ኢንዴክስ የሚለው) ይዘት በመማሪያ መጻሕፍቱ ስለተቀነሰ ያልተጠየቁ ይዘቶች 9 ይሆናሉ።

በተዛማጅ ጽሑፎች ውስጥ ለማቅረብ እንደተሞከረው፣ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንድን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በማብራራት ትምህርቱ ሊይዛቸውና ሊሸፍናቸው የሚችሉትን ዝርዝር ነጥቦች በማካተት የከፍለጊዜውን ስርጭት፣ ለቋንቋው ትምህርት የተሰጠውን ትኩረት ዘርዘር ባለ መንገድ በማስፈርና በመግለጽ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። በተጨማሪም በመርሐትምህርቱ የተገለፀትንና እለት በእለት ተግባራዊ በመሆን የሚታዩትን የትምህርት ዓላማዎች ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ የሚጫወተው ሚና ከመርሐትምህርቱ ጋር ያለውን ቁርኝት በግልጽ ያሳያል (Richards እና Rodgers 1986፡ 24-25; Harmer 1991፡256)። ለዚህም ነው nunan (1994:98) የመማሪያ መጻሕፍትና የመርሐትምህርት ግንኙነት አስመልክተው "የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ያለምንም ማወላወል መርሐትምህርቱ በተግባር የሚገለጽበት ነው" ያሉት።

በዚህ መሠረት የ1998 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከላይ በሠንጠረዡ ላይ በሠፈረው መረጃ መሠረት በፈተናው ይዘቶች ውስጥ ከመርሐትምህርቱ ሆነ ከመማሪያ መጻህፍቱ ይዘቶች ጋር የማይዛመዱ ይዘቶች የሉትም። ይህ የዚህ ዓመትን ፈተና ተማሪዎች የተማሩትን መጠየቅ የሚገባውን ይዘት ከመጠየቁ አንጻር የይዘት ተገቢነት (content validity) በማሟላት ጠንካራ ጐኑ ጐልቶ የሚታይ ነው።

በሌላ በኩል በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍሎች መርሐትምህርቶች ይዘቶች 10 ሲሆኑ፣ በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍሎች መማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች 9 ናቸው። ይሽውም ከንባብ ከሂል 2ኛው የመርሐትምህርቱ ይዘት የሆነው "የመረጃ አጠቃቀም ብሎ በሥሩ አውደ ጥበብ፣ ኢንዴክስ" የሚለው ይዘት በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የለም። ስለዚህ ይህንን ይዘት ተማሪዎች ይማሩታል ተብሎ አይጠበቅም። ያልተማሩትን ይዘት ደግሞ መጠየቅ የለባቸውም። በመሆኑም የመማሪያ መጻህፍቱ ይህንን ይዘት ባለማካተታቸው በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቱን ይዘቶች በአንድ ይዘት በመቀነስ ወደ 9 ዝቅ ያደርጉታል።

በአጠቃላይ በመርሐትምህርቶቹና በመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ላይ በተደረገው ፍተሻ፣ የ1998 ዓ.ም. ፈተና ይዘት ከመርሐትምህርቱና ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር የማይዛመዱ የፈተና ይዘቶች የሉበትም። ነገር ግን 4 የማዳመጥ ክሂልን ይዘቶች በሙሉ ጨምሮ 9 በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቶችና የመማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች አሉት።

የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ሁለቱም ፈተናዎች ከላይ ከተገለጹት መረጃዎች የምንገነዘበው አብዛኛው የፈተናዎቹ ይዘቶች ከመርሐትምህርቶቹም ሆነ ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን ነው። ነገር ግን ምንም እንኳን ሁለቱም ፈተናዎች ማለትም የ1997 ዓ.ም. ፈተና ሁሉንም የክሂል አይነቶች በናሙናነት በፈተናው ውስጥ በማካተቱና የ1998ዓ.ም. ፈተና ደግሞ የፈተናው ጥያቄ ይዘቶች በሙሉ ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር በመዛመዳቸው የየራሳቸዉ የሆነ ጠንካራ ጐኖች ቢኖቸውም፤ ከይዘት ተገቢነት (content validity) እና ከይዘት አጠቃላይነት (Content Comprehensiveness) አኳያ ሁሉንም ክሂሎች በናሙናነት በፈተናው ውስጥ በማካተቱ የ1997 ዓ.ም. ፈተና የተሻለ በመሆን ሚዛን የሚደፋ ነው። በመሆኑም የጥናቱ ዋና ትኩረት የሆነውን በተመረጡት ሁለት የመንግሥት (የካቲት፡ 12 እና ዳግማዊ ምኒልክ) እና ሁለት የግል (ማጂክካርፔት እና የነገው ሰው) ትምህርት ቤቶች ናሙናነት ለማነጻጸር ከሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በተገኘው መረጃ መሠረት የ1997 ዓ.ም. ፈተና በዋና የመረጃ ምንጭነት ያገለግላል። (መረጃው በአባሪ 1 ላይ ይገኛል)።

4.5 በሁለት የመንግሥትና በሁለት የግል ትምህርት ቤቶች መካከል የ1997 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ንጽጽራዊ ትንተና

4.5.1 የሁለት የመንግሥትና የሁለት የግል ትምህርት ቤቶች የ1997 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት

ሠንጠረዥ 32፡- የ1997ዓ.ም. የሁለቱ አይነቶች ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ንጽጽር

ተ.ቁ	ሁለት የመንግሥት ት/ቤቶች			ሁለት የግል ት/ቤቶች		
	የተማሪዎች ብዛት	በፊደል የተሰጡ ውጤቶች	በመቶኛ ስሌት (%)	የተማሪዎች ብዛት	በፊደል የተሰጡ ውጤቶች	በመቶኛ ስሌት (%)
1	172	A	6.1	58	A	23.4
2	767	B	27.3	112	B	45.2
3	1707	C	60.8	75	C	30.2
4	98	D	3.5	1	D	.4
5	63	F	2.2	2	F	.8
ድምር	2807		100	248		100

ከሀገር-አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በተገኘው መረጃ መሠረት ከላይ በሠንጠረዡ ለማሳየት እንደተሞከረው፣ በ1997 ዓ.ም. የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናን በሁለቱ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች 2,807 ተማሪዎች ተፈትነዋል። ከነዚህም ውስጥ 172 ተማሪዎች "A" ሲያመጡ፣ ይህም በመቶኛ ስሌት 6.1 (6.1%) ነው። "B" ያመጡ ተማሪዎች 767 ሲሆኑ፣ ይህም በመቶኛ ስሌት 27.3(27.3%) ነው። እንዲሁም 1707 ተማሪዎች "C" ውጤት ሲያገኙ፣ በመቶኛም ስሌት 60.8 (60.8%) ነው።"D" ያገኙ ተማሪዎች 98 ሲሆኑ፣ በመቶኛ ስሌት 3.5 (3 5%)ነው። እንዲሁም 63 ተማሪዎች "F" ውጤት ሲያገኙ፣ በመቶኛም ስሌት 2.2 (2.2%) አግኝተዋል። በተመሳሳይ በዚሁ አመት በ1997 ዓ.ም በሁለቱ የግል ትምህርት ቤቶች ባጠቃላይ 248 ተማሪዎች ተፈትነዋል። ከእነዚህ ውስጥ 58 ተማሪዎች"A" ሲያገኙ፣ ይህም በመቶኛ ስሌት 23.4 (23.4%) ነው። እንዲሁም 112 ተማሪዎች "B" ውጤት ሲያመጡ፣ ይህም በመቶኛ ስሌት 45.2 (45.2%) ነው። የ"C" ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ደግሞ 75 ሲሆኑ፣ ይህም በመቶኛ ስሌት 30.2 (30.2%) ነው። በሌላ በኩል "D" ያመጣ ተማሪ 1 ብቻ ሲሆን፣ ይህም በመቶኛ ስሌት .4 (.4%) ነው። እንዲሁም 2 ተማሪዎች "F" ውጤት ያገኙ ሲሆን፣ በመቶኛ ስሌት .8 (.8%) ነው።

ከዚህ ውጤት ልዩነት የምንረዳው በሁሉም ደረጃ ያገኙትን ውጤት ስናጤን የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ ሆነው ተገኝተዋል። በተለይ በ"A" እና በ"B" ውጤት ስናይ የግል ትምህርት ቤቶች የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ መሆኑን እንረዳለን። ይኸውም "A" በማግኘት በመቶኛ ስሌት በ17.3 (17.3%፣) "B" በማግኘት በመቶኛ ስሌት በ17.9 (17.9%)የግል ትምህርት ቤቶች የተሻለ ሆነው ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሰው ውጤት የምንረዳው የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች አብዛኞቹ የ"C" ውጤት ያገኙ ሲሆን፣ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ግን አብዛኞቹ የ"B" ውጤት አግኝተዋል።

ለዚህ የግል ትምህርትቤቶች ተማሪዎች ውጤት ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ውጤት የተሻለ ሆኖ መገኘት ምክንያት መፈተሽ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ባይሆንም እግረመንገዳችንን ይህ የውጤት ልዩነት ምን ሊሆን ይችላል? ስንል ለዚህ በመጠኑም ቢሆን ፍንጭ ሊሰጥ የሚችል ሐሳብ በጥናቱ ውስጥ በአጋዥ የመረጃ መሣሪያነት በተበተነው መጠይቅ ላይ ከመምህራንና ከተማሪዎች ዳራ፣ ስለትምህርት አሰጣጥ ሂደቱ እና ስለ ፈተናው ከሰጡት አስተያየት ግንዛቤ ለመውሰድ ከዚህ በታች ከውጤቱ ጋር በተያያዘ አለፍ አለፍ በማለት ምላሻቸውን ለማቅረብ ተሞክሯል።

4.5.2 ከመምህራንና ከተማሪዎች በመጠይቁ የተሰጠ ምላሽ

ሠንጠረዥ 33፡- በመጠይቁ ክፍል አንድ ግላዊ መረጃዎች ውስጥ ለተራ ቁጥር 1.4 እና 1.10 ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የተማሪዎች ቁጥር	የመምህራን ብዛት	
			በቁጥር	%
1.4	በሚገቡባቸው ክፍሎች በአማካይ የተማሪዎች ብዛት	1. 51-70 2. 72-90 3. 91.-110	2 7 1	20% 70% 10%
		ድምር	10	100%
1.10	በሳምንት አንድ ክፍል የሚገቡበት ክፍለ ጊዜ ብዛት	ክፍለ ጊዜ	ብዛት	%
		3 2	3 7	30% 70%
		ድምር	10	100%

በሠንጠረዥ እንደተመለከተው፣ ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች 10 መምህራን የተሰጠ ምላሽ በሚገበባቸው ክፍሎች በአማካይ የተማሪዎች ብዛት ከ71-90 መሆኑን በ7 መምህራን መልስ ተሰጥቷል። ይህም በመቶኛ ከመምህራን 70%ቱ የሰጡት ምላሽ ነው። በተመሳሳይ በሳምንት አንድ ክፍል የሚገበብት ክፍለ ጊዜ ብዛት ለሚለው ጥያቄ በ7 መምህራን ማለትም 70%ቱ መምህራን 2 ክፍለ ጊዜ ብለዋል። በተመሳሳይ የግል ትምህርት ቤት መምህራን ለዚሁ ጥያቄ የመለሱትን ከዚህ በታች ለማየት ብንሞክር፣

ሠንጠረዥ 34፡- በመጠይቁ ክፍል አንድ ግላዊ መረጃዎች ውስጥ ለተራ ቁጥር 1.4 እና 1.10 ከግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የተማሪዎች ቁጥር	የመምህራን ብዛት	
			በቁጥር	%
1.4	በሚገበባቸው ክፍሎች በአማካይ የተማሪዎች ብዛት	ከ40-50	4	100
		ድምር	4	100
1.10	በሳምንት አንድ ክፍል የሚገበብት ክፍለ ጊዜ ብዛት	ክፍለ ጊዜ	ብዛት	%
		3	4	100%
		ድምር	4	100%

በሠንጠረዥ እንደተመለከተው ለግል ትምህርት ቤቶች መምህራን "በሚገበባቸው ክፍሎች በአማካይ የተማሪዎች ብዛት" ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ከ 40-50 የሚል ምላሽ በ4ቱም መምህራን ተሰጥቷል፤ ይህም በመቶኛ 100% ነው። በተመሳሳይ "በሳምንት" አንድ ክፍል የሚገበብት ክፍለ ጊዜ ብዛት ለሚለው ጥያቄ በ4ቱም መምህራን 3 ክፍለ ጊዜ የሚል ምላሽ ተገኝቷል፤ ይህም በመቶኛ 100% በሆኑ መምህራን ማለት ነው።

ከዚህ ሠንጠረዥ 33 እና 34 የመንግሥት ትምህርት ቤቶች እና የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን መጠይቅ ምላሽ የምንረዳው፣ በመንግሥት ትምህርት ቤት በአንድ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች ቁጥር በአብዛኛው፣ በአማካይ ከ71-90 እንደሆነና፣ የአማርኛ ቋንቋ የክፍለ ጊዜ ስርጭትም በአብዛኛው በሳምንት 2 ክፍለ ጊዜ እንደሆነ ነው። እንዲሁም የግል ትምህርት ቤት በአንድ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች ቁጥር በአማካይ 40-50 ሲሆን፣ የአማርኛ ቋንቋ የክፍለ ጊዜ ስርጭትም በሳምንት 3 ክፍለ ጊዜ እንደሆነ ነው። ይህ የግል ትምህርት ቤት

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በአንድ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ መሆንና የአማርኛ ቋንቋ የክፍለ ጊዜ ስርጭት ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች በሳምንት በአንድ ክፍለ ጊዜ መጨመር ምናልባት ለውጤቱ መሻል የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል ተብሎ ይታመናል።

ሠንጠረዥ 35፡- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ውስጥ ለተራ ቁጥር 14 ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የመምህራን ምላሽ በተለያዩ የስምምነት ደረጃዎች											
		በጣም እስማማለሁ 5		እስማማለሁ 4		እርግጠኛ አይደለሁም 3		አልስማማም 2		ፍፁም አልስማማም 1		ድምር	
		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት	
		ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%
14	አሁን በማስተምርበት ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ ነው ብዬ አምናለሁ።	1	10	-	-	1	10	2	20	6	60	10	100

እላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ የምንገነዘበው፣ "አሁን በማስተምርበት ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ ነው ብዬ አምናለሁ።" ለሚለው ሐሳብ የመንግሥት ትምህርት ቤት መምህራን 6ቱ ማለትም 60% "ፍፁም አልስማማም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይኸውም ከላይ አብዛኞቹ ማለትም 70% በሳምንት 2 ክፍለ ጊዜ የሚል ምላሽ ስለሰጡ ይህ ክፍለ ጊዜ በቂ አለመሆኑን በዚህ ምላሻቸው አረጋግጠዋል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY AAU LIBRARY

ሠንጠረዥ 36፡- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ውስጥ ለተራ ቁጥር 14 ከግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የመምህራን ምላሽ በተለያዩ የስምምነት ደረጃዎች											
		በጣም እስማማለሁ 5		እስማማለሁ 4		እርግጠኛ አይደለሁም 3		አልስማማም 2		ፍፁም አልስማማም 1		ድምር	
		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት	
		ጋፋቱበ	%	ጋፋቱበ	%	ጋፋቱበ	%	ጋፋቱበ	%	ጋፋቱበ	%	ጋፋቱበ	%
14	አሁን በማስተምር በት ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ ነው ብዬ አምናለሁ	-	-	2	50	-	-	2	50	-	-	4	100

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው የግል ትምህርት ቤት መምህራን " አሁን በማስተምርበት ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ ነው በዬ አምናለሁ::" ለሚለው የመጠይቁ 14ኛ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 2 መምህራን ማለትም 50%ቱ "እስማማለሁ" ሲሉ፣ 2 ማለትም 50%ቱ "አልስማማም" ብለዋል ከላይ የግል ትምህርት ቤት ሁሉም መምህራን በሳምንት 3 ክፍለጊዜ በአንድ ክፍል እንደሚገቡ መልሰዋል:: ስለዚህ 50%ቱ በሳምንት 3 ክፍለ ጊዜ በቂ መሆኑን ሲስማሙ 50%ቱ ደግሞ አልተስማሙም::

የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ለዚህ ለ14ኛው ጥያቄ የሰጡትን መልስ ከሠንጠረዥ 35 እና 36 ስናጤን፣ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች መምህራን ቀደም ሲል ከሰጡት ምላሽ 70%ቱ በሳምንት 2 ክፍለ ጊዜ በአንድ ክፍል እንደሚገቡ መልሰዋል:: ለዚህ ጥያቄም የሰጡት ምላሽ 60%ቱ "በፍፁም አልስማማም" የሚል ነው:: ስለዚህ በሳምንት የ2 ክፍለ ጊዜ ስርጭት በትምህርት ቤቱ መምህራንም ተቀባይነት እንዳላገኘ እንገነዘባለን:: ምክንያቱም መሸፈን የሚገባቸውን የትምህርት ይዘት በብቃት እንዳይወጡ አግዷቸው ይሆናል::

ይህም የክፍለ ጊዜ ስርጭት መለያየት ለውጤቱ ከግል ትምህርት ቤቶች ማነስ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታመናል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ለውጤት ንጽጽሩ በይዘት ተገቢነት ብቃት የተመረጠውን የ1997ዓ.ም. ፈተና የሠሩ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን የመጠይቅ ምላሽ ለማቅረብ ተሞክሯል።

ሠንጠረዥ 37፡- በመጠይቁ ክፍል አንድ ግላዊ መረጃዎች ውስጥ ለተራ ቁጥር 5 እና 9 ከ12ኛ ክፍል ከመንግሥትና ከግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የመንግሥት ት/ቤት			የግል ት/ቤት		
		የተማሪዎች ብዛት	ብዛት	%	የተማሪዎች ብዛት	ብዛት	%
5	ባላችሁበት ክፍል ያሉት ተማሪዎች ብዛት	40-60	54	100	35-44	18	100
9	በሳምንት አማርኛ የምትማሩበት ክፍለ ጊዜ ብዛት	ክፍለ ጊዜ	ብዛት	%	ክፍለ ጊዜ	ብዛት	%
		3	20	37	3	18	100%
		2	34	63			

በሠንጠረዡ ላይ እንደተቀመጠው፣ ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በተገኘው ምላሽ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች "ባላችሁበት ክፍል ያሉት ተማሪዎች ብዛት" ለሚለው ከ40-60 በሚል በ54ቱም ተማሪዎች ተመልሷል። የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ግን ለዚሁ ተማሳሳይ ጥያቄ 18ቱም ከ35-44 የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። እንዲሁም "በሳምንት አማርኛ የምትማሩበት ክፍለ ጊዜ ብዛት ስንት ነው?" ለሚለው ጥያቄ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች 34ቱ ማለትም 63%ቱ 2 ሲሉ፣ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች 18ቱም 3 በማለት መልሰዋል። ይህ የተማሪዎች ምላሽ ከላይ መምህራን የሰጡትን መልስ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል።

ሠንጠረዥ 38፡- በመጠይቁ ክፍል አንድ ግላዊ መረጃዎች ውስጥ ለሚገኝ ጥያቄ ለተራ ቁጥር 6 ከ12ኛ ክፍል ከመንግሥትና ከግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ		የመንግሥት ት/ቤቶች ተማሪዎች			የግል ት/ቤቶች ተማሪዎች		
			በመንግሥት	በግል	ድምር	በመንግሥት	በግል	ድምር
6	ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የተማሩበት ትምህርት ቤት	ብዛት	31	23	54	1	17	18
		%	57.4	42.6	100	5.6	94.4	100

ከተሰጠው ሠንጠረዥ መረጃ እንደምንገነዘበው፣ "ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የተማሩበት ትምህርት ቤት" ለሚለው ጥያቄ ከ54ቱ የ12ኛ ክፍል የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውስጥ 31ዱ በመቶኛ 57.4%ቱ በመንግሥት ትምህርት ቤት እንደተማሩ ምላሽ ሲሰጡ፣ የ12ኛ ክፍል የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውስጥ ደግሞ ከ18ቱ 17ቱ፣ በመቶኛ 94.4%ቱ በግል ትምህርት ቤት የተማሩ መሆኑን አረጋግጠዋል። ከዚህ የተማሪዎች መልስ የምንረዳው አብዛኞቹ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃም ከመንግሥት ትምህርት ቤት የመጡ መሆናቸውን ነው። እንዲሁም አብዛኞቹ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃም በግል ትምህርት ቤት የተማሩ መሆኑን ሲሆን፣ ይህም ለአሁኑ ውጤታቸው የተሻለ መሆን የራሱ ድርሻ ሊኖረው ይችላል ተብሎ ይታመናል፡

በሠንጠረዡ እንደተቀመጠው "የአባት (የአሳዳጊ) የትምህርት ደረጃ" ለሚለው የ12ኛ ክፍል የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ከ54 ተማሪዎች ውስጥ 20ዎቹ "ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ናቸው" ሲሉ፣ ይህም በመቶኛ ስሌት 37 (37%) ነው። ይህም ከሌሎቹ ከፍተኛው ፐርሰንት ነው። እንዲሁም "የእናት (የአሳዳጊ) የትምህርት ደረጃ" ለሚለው ጥያቄ 22 ተማሪዎች በመቶኛ 40.7% "ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ናቸው" በማለት መልሰዋል። ይህም ከሌሎቹ ከፍተኛው ነው። ከዚህ የምንረዳው የአብዛኞቹ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ወላጆች (እናትና አባት ወይም አሳዳጊዎች) የትምህርት ደረጃ በማንበብና መጻፍ ደረጃ እንደሆነ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
YES LIBRARY

ሠንጠረዥ 39፡- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ለሚገኙ ጥያቄዎች ለተራ ቁጥር ከ10-12 ከ12ኛ ክፍል የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የተማሪዎች ምላሽ በተለያዩ የስምምነት ደረጃዎች											
		በጣም አስማማለሁ 5		አስማማለሁ 4		አርግጠኛ አይደለሁም 3		አልስማማም 2		ፍፁም አልስማማም 1		ድምር	
		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት	
		ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%	ጋፋቱ	%
10	በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያለው ቤተመጻሕፍት የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሟሉ መጻሕፍት አሉት።	12	22.2	14	25.9	14	25.9	6	11.1	8	14.8	54	100
11	ትምህርት ቤቱ ቤተ መጻሕፍትን ለመጠቀም እንድትችሉ ፕሮግራም ያመቻችላችኋል።	12	22.2	15	27.8	10	18.5	8	14.8	9	16.7	54	100
12	የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ንቁ እንቅስቃሴ ያደርጋል።	10	18.5	17	31.5	8	14.8	8	14.8	11	20.4	54	100

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው፣ "በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያለው ቤተመጻሕፍት የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሟሉ መጻሕፍት አሉት?" ለሚለው ለ10ኛው ጥያቄ ከ12ኛ ክፍል የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ "እስማማለሁ" እና "እርግጠኛ አይደለሁም" በእኩል ደረጃ በ14፣ በ14 ተማሪዎች ምላሽ ተሰጥቷል። ይህም በመቶኛ 25.9% ሲሆን የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ነው። በተመሳሳይ ለ11ኛው ጥያቄ ማለትም "ትምህርት ቤቱ ቤተመጻሕፍትን ለመጠቀም እንድትችሉ ፕሮግራም ያመቻችላችኋል? "ለሚለው ጥያቄ 15

ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ በ27.8% "እስማማለሁ" በማለት መልሰዋል። እንዲሁም "የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር-ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ንቁ እንቅስቃሴ ያደርጋል?" ለሚለው ለ12ኛው ጥያቄ 17 ተማሪዎች፣ በመቶኛ 31.5% የሆኑ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ "እስማማለሁ" የሚል አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 40፡- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ለሚገኙ ጥያቄዎች ለተራ ቁጥር ከ10-12 ከ 12ኛ ክፍል የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የተማሪዎች ምላሽ በተለያዩ የስምምነት ደረጃዎች											
		በጣም እስማማለሁ 5		እስማማለሁ 4		እርግጠኛ አይደለሁም 3		አልስማማም 2		ፍፁም አልስማማም 1		ድምር	
		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት	
		ጋራቱ በ	%	ጋራቱ በ	%	ጋራቱ በ	%	ጋራቱ በ	%	ጋራቱ በ	%	ጋራቱ በ	%
10	በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያለው ቤተመጻሕፍት የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሟሉ መጻሕፍት አሉት።	2	11.1	2	11.1	7	38.9	2	11.1	5	27.8	18	100
11	ትምህርት ቤቱ ቤተ መጻሕፍትን ለመጠቀም እንድትችሉ ፕሮግራም ያመቻችላችኋል።	1	5.6	5	27.8	4	22.2	5	27.8	3	16.7	18	100
12	የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ንቁ እንቅስቃሴ ያደርጋል።	7	38.9	5	27.8	3	16.7	3	16.7	-	-	18	100

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተቀመጠው፣ "በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያለው ቤተመጻሕፍት የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሟሉ መጻሕፍት አሉት?" ለሚለው ለ10ኛው ጥያቄ ከ12ኛ ክፍል የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ በከፍተኛ ደረጃ በ7 ተማሪዎች ይህም በመቶኛ 38.9% " እርግጠኛ አይደለሁም" የሚል ነው። በተመሳሳይ ለ11ኛው ጥያቄ "ትምህርት ቤቱ ቤተ- መጻሕፍትን ለመጠቀም እንድትችሉ ፕሮግራም ያመቻችላችኋል?" ለሚለው ጥያቄ 5፣5 ተማሪዎች በእኩል ደረጃ "እስማማለሁ" እና "አልስማማም" የሚል

አዎንታዊና አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም በመቶኛ በሁለቱም 27.8% ነው። እንዲሁም ለ12ኛው ጥያቄ "የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር-ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ንቁ እንቅስቃሴ ያደርጋል?" ለሚለው ጥያቄ በከፍተኛ ደረጃ በ7 ተማሪዎች በመቶኛ 38.9% በሆነ ደረጃ "በጣም እስማማለሁ" የሚል አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ከተገኘው ምላሽ የምንረዳው የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ቤተ-መጻሕፍት የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሟሉ መጻሕፍት በተወሰነ ደረጃ እንዳሉት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ተማሪዎች ቤተመጻሕፍትን ለመጠቀም እንዲችሉ በተወሰነ ደረጃ ፕሮግራም እንደሚያመቻችላቸው እና አስተዳደሩም መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር-ማስተማር ሂደቱን የተሳካ ለማድረግ በተወሰነ ደረጃ ንቁ እንቅስቃሴ እንሚያደርግ ነው። በሌላ በኩል ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከተገኘው ምላሽ የምንገነዘበው የትምህርት ቤቱ ቤተመጻሕፍት የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሟሉ መጻህፍት ይኑረው አይኑረው እንደማያውቁ ነው። እንዲሁም ተማሪዎች ቤተመጻሕፍትን ለመጠቀም እንዲችሉ ትምህርት ቤቱ ፕሮግራም ያመቻቻልም፣ አያመቻችምም በሚል "በእኩል ደረጃ" አስተያየት ሰጥተውበታል። ስለዚህ በዚህ በሁለቱ ጥያቄዎች ዙሪያ ከመንግሥት ትምህርት ቤት ይልቅ በግል ትምህርት ቤት ችግር እንዳለ ይጠቁማል። ግን ይህ ከሆነ እንዴት ውጤታቸው የተሻለ ሆነ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፤ ሆኖም ምናልባት እነሱ ከሰጡት የመጠይቅ ምላሽ እንደምንረዳው ቤተሰቦቻቸው አብዛኞቹ የተማሩ በመሆናቸው መጻሕፍትን ወላጆቻቸው አሟልተውላቸው የማንበብ እድል አግኝተው ይሆን የሚል ግምት ያጭራል። በሌላ በኩል ግን ለ12ኛ ጥያቄ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር-ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ንቁ የሆነ እንቅስቃሴ እንደሚያደርግ በከፍተኛ ደረጃ ከተማሪዎች ምላሽ ተሰጥቷል። በዚህ በግል ትምህርት ቤት ከመንግሥት ትምህርት ቤት የተሻለ ቁጥር እንዳለ እንረዳለን። ይህም ለግል ትምህርት ቤት ውጤት ተሸሎ መገኘት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል።

ሠንጠረዥ 41፡- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ለሚገኙ ጥያቄዎች ለተራ ቁጥር 1 እና 2 ከ12ኛ ክፍል የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የተማሪዎች ምላሽ በተለያዩ የስምምነት ደረጃዎች											
		በጣም እስማማለሁ 5		እስማማለሁ 4		እርግጠኛ አይለሁም 3		አልስማማም 2		ፍፁም አልስማማም 1		ድምር	
		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት	
		ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%
1	ፈተናው በክፍል ውስጥ የምማረውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማንፀባረቅ ችሎታዬን ለመመዘን ብቁ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።	7	13	20	37	11	20.4	13	24.1	3	5.6	54	100
2	ፈተናው ከባድ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።	5	9.3	13	24.1	5	9.3	21	38.9	10	18.5	54	100

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው “ፈተናው በክፍል ውስጥ የምማረውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማንፀባረቅ ችሎታዬን ለመመዘን ብቁ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።” ለሚለው ለ1ኛው ጥያቄ ከ12ኛ ክፍል የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ 20 ተማሪዎች “እስማማለሁ” የሚል የአዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ይህም በመቶኛ 37% ሆኖ ከፍተኛ ደረጃን የያዘ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ለ2ኛው ጥያቄ “ፈተናው ከባድ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።” ለሚለው ጥያቄ 21 ተማሪዎች “አልስማማም” በማለት መልሰዋል”። ይህም በመቶኛ 38.9% ሲሆን፣ ከሌሎቹ አማራጮች የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ 42፡- በመጠይቁ ክፍል 2.1 ለሚገኙ ጥያቄዎች ለተራ ቁጥር 1 እና 2 ከ12ኛ ክፍል የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	የተማሪዎች ምላሽ በተለያዩ የስምምነት ደረጃዎች											
		በጣም እስማማለሁ 5		እስማማለሁ 4		እርግጠኛ አይደለሁም 3		አልስማማም 2		ፍፁም አልስማማም 1		ድምር	
		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት		ብዛት	
		ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%	ጋፋቱህ	%
1	ፈተናው በክፍል ውስጥ የምማረውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማንፀባረቅ ችሎታዬን ለመመዘን ብቁ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።	5	27.8	5	27.8	5	27.8	-	-	3	16.7	18	100
2	ፈተናው ከባድ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።	4	22.2	4	22.2	1	5.6	7	38.9	2	11.1	18	100

ከላይ በሠንጠረዥ እንደተቀመጠው "ፈተናው በክፍል ውስጥ የምማረውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማንፀባረቅ ችሎታዬን ለመመዘን ብቁ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።" ለሚለው ለ 1ኛው ጥያቄ ከ12ኛ ክፍል የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ 5፣5 ተማሪዎች በእኩል ደረጃ ለ 3ቱም ከከፍተኛ ደረጃ የሚጀምሩ አማራጮች ማለትም "በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ እና እርግጠኛ አይደለሁም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም በመቶኛ ለ3ቱም 27.8% በእኩል ደረጃ ነው። እንዲሁም ለ2ኛው ጥያቄ "ፈተናው ከባድ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።" ለሚለው ጥያቄ በከፍተኛ ደረጃ 7 ተማሪዎች "አልስማማም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም በመቶኛ 38.9% ነው።

ከእነዚህ ጥያቄዎች እኳያ የሁለቱን ትምህርት ቤቶች ምላሽ ስናጠቃልል የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ፈተናው በክፍል ውስጥ የሚማሩትን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማንፀባረቅ ችሎታቸውን ለመመዘን ብቁ ሆኖ እንዳገኙት አብዛኞቹ ተማሪዎች "በእስማማለሁ"

አመንታዊ ምላሽ ገልፀዋል። እንዲሁም የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ፈተናው በክፍል ውስጥ የሚማሩትን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማንፀባረቅ ችሎታቸውን ለመመዘን ብቁ ሆኖ እንዳገኙት አብዛኞቹ ተማሪዎች ገልፀዋል። በተጨማሪም የመንግሥትም ሆነ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ፈተናው ከባድ ሆኖ እንዳላገኙት በምላሻቸው አረጋግጠዋል። በሌላ በኩል የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የፈተና ውጤታቸው የአብዛኞቹ "C" ሲሆን፣ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ግን የፈተና ውጤታቸው የአብዛኞቹ "B" ነው። ከዚህ አኳያ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የመጠይቁ ምላሽና ውጤታቸው በተወሰነ ደረጃ በተለይ በዚህ በ2ኛው ጥያቄ ምላሽ ላይ ተቃርኖ የፈጠረ ይመስላል። የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ግን የመጠይቁ መልስ አሰጣጣቸው ከፈተናው ውጤት ጋር የሚዛመድ ሆኖ ተገኝቷል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ

የዚህ ዋና አላማ በአዲስ አበባ ዋና ከተማ በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገርአቀፍ ፈተናን ውጤት ማነጻጸት ነው። በመሆኑም ጥናቱ በ1997 ዓ.ም. እና በ1998ዓ.ም. በሀገር-አቀፍ ደረጃ ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በቀረበው የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተና ውጤት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም በመሆኑ በጥናቱ አራተኛው ክፍል ላይ እነዚህን ፈተናዎች ከፈተና መመዘኛ መሥፈርቶች አንዱ በሆነው በይዘት ተገቢነት ብቃታቸው ተፈትሾ የተሻለው ፈተና የ1997 ዓ.ምቱ ፈተና ለውጤት ንጽጽሩ ተመርጧል። በመሆኑም የጥናቱ ዓቢይ ትኩረት ለሆነው የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች የውጤት ንጽጽር ይህ የ1997 ዓ.ም. ፈተና የመረጃ ምንጭ ሆኖ በማገልገል የተገኘው ውጤትና በደጋፊ መረጃ ማሰባሰቢያነት ለመምህራንና ለተማሪዎች በተበተኑ የጽሑፍ መጠይቆች ከውጤቱ ጋር በተያያዘ የተገኙ ምላሾች ተፈትሸው ተተንትነዋል። በዚህ ክፍልም በቀደሙ የጥናቱ ክፍሎች መረጃ መነሻነት የማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ ቀርቧል።

5.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ውስጥ ትንታኔውን መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት የማጠቃለያ ሐሳቦች ላይ ተደርሷል፤

ሀ. የ1997ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. ፈተናዎች ከመርሐትምህርቱ ጋር ባላቸው ዝምድና መሠረት ሲነጻጸሩ፣ የማዳመጥ ክሂል በ1997 ዓ.ም. ከ34 የፈተናው ጥያቄ ይዘቶች ውስጥ 30ዎቹ ይዘቶች ከመርሐ ትምህርቱ ይዘቶች ጋር የሚዛመዱ ሲሆን 4 ይዘቶች ግን አይዛመዱም። የ1998 ዓ.ም. ፈተና የማዳመጥ ክሂልን ይዘት ሙሉ በሙሉ ከማስቀረቱ በስተቀር ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር ይዛመዳል። በ1997 ዓ.ም. በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች 9 ሲሆኑ፣ በ1998 ዓ.ም. ደግሞ 10 ናቸው።

በአጠቃላይ የሁለቱንም ዓመታት ፈተናዎች ይዘት ስናጤን በአብዛኛው ከመርሐትምህርቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ናቸው።

ለ. የ1997ዓ.ም. ፈተና ከ9ኛ እና ከ10ኛ መርሐትምሕርቶች ጋር ከማይዛመደው ከአንድ ይዘት ማለትም "ጥምር ቃላት" ጋር የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘት ይዛመዳል። ስለዚህ በፈተናው

ውስጥ ከቀረቡት ከመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ጋር የማይዛመዱ 4 ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ አንድ ይዘት በመገኘቱ የዚህ ዓመት ፈተና የማይዛመዱ ይዘቶችን ከ 4 ወደ 3 ዝቅ አድርጐታል። ሌላው በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቶቹ ይዘቶች ብዛት 9 ሲሆን፣ በፈተናው ውስጥ ያልተጠየቁ የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ብዛት ግን 8 ናቸው።

ሐ. የ1998 ዓ.ም. ፈተና ውስጥ ያልተጠየቁ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች 9 ናቸው። ስለዚህ የመማሪያ መጻሕፍቱ ያልተጠየቁ የመርሐትምህርቶቹን ይዘቶች ከ 10 ወደ 9 ዝቅ ያደርጉታል።

መ. የ1997 ዓ.ም. ፈተና ሁሉንም የክሂል ዓይነቶች በናሙናነት በፈተው ውስጥ በማካተቱ የጥናቱ ንዑስ ትኩረት ከሆነው ከይዘት ተገቢነት (Content Validity) እና ከይዘት አጠቃላይነት (Content Comprehensiveness) አኳያ የተሻለ ፈተና በመሆን ሚዛን የሚደፋ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የጥናቱ ዋና ትኩረት ለሆነው በናሙናነት የተመረጡ ሁለት የመንግሥት እና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች ውጤት ለማነጻጸር ዋና የመረጃ መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል።

ከሀገር-አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በተገኘው መረጃ መሠረት በ1997 ዓ.ም. የ 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና በሁለቱ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች 2,807 ተማሪዎች ተፈትነዋል። ከነዚህ ውስጥ 172ቱ "A" ፣ 767ቱ "B"፣ 1707ቱ "C"፣ 98ቱ "D"፣ 63ቱ "F"የሚለውን ውጤቶች አግኝተዋል። በዚሁ ዓመት በ1997 ዓ.ም. በሁለቱ የግል ትምህርት ቤቶች 248 ተማሪዎች ተፈትነዋል። ከነዚህ ውስጥ 58ቱ "A"፣ 112ቱ "B"፣ 75ቱ "C"፣ 1ዱ "D"፣ 2ቱ "F" ውጤቶች አግኝተዋል። ይህንን በመቶኛ ስሌት ስናየው "A" ያመጡት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች 6.1% ሲሆኑ፣ የግል ትምህርት ቤቶች ግን 23.4% ናቸው። እንዲሁም "B" ያገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች 27.3% ሲሆኑ፣ የግል ትምህርት ቤቶች ደግሞ 45.2% ናቸው። "C" ያመጡ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች 60.8% ሲሆኑ፣ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ግን 30.2% ናቸው። "D" ውጤት ያገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች 3.5% ሲሆኑ፣ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ግን .4% ናቸው። እንዲሁም "F" ያመጡ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች 2.2% ሲሆኑ፣ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ግን .8% ናቸው።

በአጠቃላይ ከውጤቱ የምንረዳው የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አብዛኞቹ (60.8%) "C" ውጤት ያገኙ ሲሆን፣ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ግን አብዛኞቹ ተማሪዎች "B"

ውጤት አግኝተዋል። በመሆኑም በዚህ በ1997 ዓ.ም. የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ውጤት የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል።

ሠ. ከውጤቱ ጋር በተያያዘ ከመምህራን በመጠይቁ የተሰጠ ምላሽ፣ ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች መምህራን አብዛኞቹ የሚገቡባቸው ክፍሎች በአማካይ የተማሪዎች ብዛት ከ71-90 እንደሆነና በሳምንት አንድ ክፍል የሚገቡበት ክፍለ ጊዜ ብዛት 2 እንደሆነ አብዛኞቹ መምህራን ገልፀዋል። የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ግን በሚገቡባቸው ክፍሎች በአማካይ የተማሪዎች ብዛት ከ40-50 እንደሆነና በሳምንት አንድ ክፍል የሚገቡበት ክፍለ ጊዜ ብዛት 3 መሆኑን ሁሉም መምህራን ገልፀዋል።

ረ. ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ምላሽ ባሉበት ክፍል ስለተማሪዎች ብዛት ለቀረበው ጥያቄ ከ40-60 እንደሆኑ ገልፀዋል። እንዲሁም የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ብዛት ከ35-44 የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። በሳምንት አማርኛ የሚማሩበትን ክፍል ጊዜ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች 63%ቱ 2 ሲሉ፣ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች 100%ቱ 3 በማለት መልሰዋል። ይህ የተማሪዎች ምላሽ ከላይ መምህራን የሰጡትን መልስ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል።

- ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የተማሩበት ትምህርት ቤትን በሚመለከት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አብዛኞቹ (57.4%ቱ) በመንግሥት ትምህርት ቤቶች እንደተማሩ ሲገልጹ፣ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ግን አብዛኞቹ (94.4%ቱ) በግል ትምህርት ቤቶች የተማሩ መሆኑን በመጠይቁ ምላሽ ላይ አረጋግጠዋል።

በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ያለው ቤተመጻሕፍት የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሟሉ መጻሕፍት እንዳሉት፣ ትምህርት ቤቱ ቤተመጻሕፍትን ለመጠቀም መርሐግብር (ፕሮግራም) እንደሚያመቻችላቸው እና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር-ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ንቁ እንቅስቃሴ ማድረጉን የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አብዛኞቹ "እስማማለሁ" በሚል አዎንታዊ ምላሽ ገልፀዋል። የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችም ለእነዚሁ ተመሳሳይ ጥያቄዎች ለመጀመሪያው "እርግጠኛ አይደለሁም" ለሁለተኛው "እስማማለሁ" እና "አልስማማም" በእኩል ደረጃ ለሦስተኛው "በጣም እስማማለሁ" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ በግል ትምህርት ቤቶች ከመጀመሪያው ጥያቄ አካያ የቤተመጻሕፍት መሟላት ችግር እንዳለ ፍንጭ

ይሰጣል። ሌላው ለሦስተኛው ጥያቄ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ንቁ የሆነ እንቀስቃሴ እንደሚያደርግ በከፍተኛ ደረጃ ከተማሪዎች ምላሽ ተሰጥቷል። ይህ በግል ትምህርት ቤቶች ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች በተሻለ ቁጥጥር እንዳለ ያሳያል። ይህም ለውጤታቸው የተሻለ ሆኖ መገኘት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይታመናል።

- ፈተናው በክፍል ውስጥ የተማሩትን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማንፀባረቅ ችሎታቸውን ለመመዘን ብቁ ሆኖ ማግኘታቸውን በሚመለከት፣ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አብዛኞቹ "እስማማለሁ" በሚል አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በተመሳሳይ ለዚሁ ጥያቄ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ እና እርግጠኛ አይደለሁም" የሚል በእኩል ደረጃ ለሦስቱም ምላሽ ሰጥተዋል። የዚህን አማካዩን ውጤት ብንወስድ "እስማማለሁ"፣ ከሚለው አዎንታዊ ምላሽ ላይ እንደርሳለን። እንዲሁም ፈተናው ከባድ ሆኖ ስለማግኘታቸው፣ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች አብዛኞቹ "አልስማማም" የሚል መልስ ሲሰጡ፣ የግል ትምህርት ቤቶችም አብዛኞቹ "አልስማማም" በሚል ፈተናው ከባድ አለመሆኑን አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። እዚህ ላይ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ፈተናው ካልከበዳቸው ለምን ውጤታቸው አብዛኞቹ "C" ሆነ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል።

5.2 የመፍትሔ ሐሳብ

ይህ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ከፈተና ዓይነቶች ውስጥ የሚመደበው በችሎታ መለኪያ ፈተናነት ነው። የችሎታ መለኪያ ፈተና ደግሞ በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው፣ በመርሐትምህርቱ ብሎም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ተመሥርቶ መዘጋጀት ይኖርበታል። በመርሐትምህርቱ ብሎም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ተመስርቶ ያልተዘጋጀ ፈተና የተማሪውን ችሎታ በትክክል ሊመዝን አይችልም። በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ለማነፃፀር ፈተናው መጀመሪያ ብቃት ያለው መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል። ከዚህ አንጻር ከጥናቱ በተገኘው ውጤት የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ቀርበዋል፤

- ከይዘት አኳያ ከጥቂት የፈተናው ይዘቶች በስተቀር አብዛኞቹ ከመርሐትምህርቱ ይዘቶች ጋር የሚዛመዱ እና ከጥቂት የመርሐትምህርት ይዘቶች በስተቀር አብዛኞቹ በፈተናው ውስጥ የተጠየቁ ናቸው። ስለሆነም ፈተናውና መርሐትምህርቱ በአብዛኛው ይዛመዳሉ

ADDIS ABABA UNIVERSITY A.U.B LIBRARY

ለማለት ይቻላል። ችሎታን በትክክል ለመለካትና የመማር-ማስተማር ሂደቱን ለማገዝ በትበት ፈተናውን በመርሐትምህርቱ ላይ መሠረት አድርጎ ማዘጋጀቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው የበለጠ ተሻሽሎ እንዲቀጥል ጥረት መደረግ አለበት።

- ከክሂል ስርጭት አንጻር የ10ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና እንደ 1997 ዓ.ምቱ ፈተና ከማዳመጥ ክሂል ጀምሮ ሁሉንም የክሂል ዓይነቶች ይዘት በተመጣጠነ ደረጃ በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ እንዲካተት ቢደረግ።
- በመርሐትምህርቱ ውስጥ ከሌሉ የፈተናው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ "አንድ" መገኘቱ እና በፈተናው ውስጥ ባልተጠየቁ የመርሐትምህርቱ ይዘቶች ውስጥ "አንድ" በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አለመኖር የመርሐትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፉን ግንኙነት በመጠኑ የሚቀንስ ነው።በመሆኑም ለወደፊቱ እንዲሻሻል እና ግንኙነታቸው የጠበቀ እንዲሆን ቢደረግ።
- የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አብዛኞቹ "B" ውጤት ሲያገኙ፣ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አብዛኞቹ "C" ውጤት አምጥተዋል። በመሆኑም የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ከዚህ በበለጠ እንዲያሻሽሉ። የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችም ችግሮቻቸው ተጠንቶ ውጤታቸው የሚሻሻልበት መንገድ ቢፈለግ።

ከመምህራንና ከተማሪዎች የመጠይቅ ምላሽ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ውጤት ዝቅ ያለበት ምክንያት ፍንጭ ሊሆን የሚችል፦

ሀ. በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣

ለ. በሳምንት አማርኛ የሚማሩበት ክፍለ ጊዜ ማነስ፣ እንደሆነ በመጠይቁ ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለሆነም ይህ ችግራቸው የበለጠ ተጠንቶ በዚህ ዙሪያ እንዲሻሻል መደረግ አለበት። እንዲሁም የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች የልምድ ልውውጥ በማድረግ የመማር-ማስተማር የአሠራር ሂደታቸውን ቢለዋወጡ እና ቢማማሩ ውጤቱን ለማመጣጠንና ለማሳደግ እንደሚቻል የዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት ነው።

የመሠረታዊ ቃላትና ሐረጋት ብያኔ

ለእርማት አመቺነት	Scorability
መለያየት	Discrimination
ላያዊ ተገቢነት	Face Validity
መርሐ ትምህርት	Syllabus
መርሐ ግብር	Program
መሻሻልን መለኪያ ፈተና	Progressive test
መዋቅራዊ	Structural
መጋቢ ምላሽ	Feedback
ማስወገድ	Discard
ምርጫ ሰጪ	Mulitiple choose
ምርጫ ነክ	Objective
ምዘና	Measurement
ሥነ ድምፀልሳናዊ	Phonological
ሰዋስዋዊ	Grammatical
ቁጥብነት	Economy
ቃላዊ	Lexical
ቅደም ተከተላዊ	Chronological
ቅድመ ትምህርት ፈተና	Pre-course test
ብቃትን መወሰኛ ፈተና	Placement test
ተቀባይ ክሂል	Receptive skill
ተተግባሪነት	Practicality
ተገቢነት	Validity
ተግባቦታዊ (መስተጋብራዊ)	Communicative
ተፅዕኖ፣ ውጤት	Back wash
ችሎታ(ብቃት)	Competence
ንድፈ ሐሳቦች	Theories
አማራጮች	Alternatives
ዋናው ጥያቄ (አምድ)	Stem
አሳሳች መልስ	Distracters
አስተማማኝነት	Reliability
አጠቃላይነት	Comprehensiveness

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ወጥነት (ፅኑዕነት)	Consistency
የልዩነት ደረጃ	Discrimination level
የመግቢያ ፈተና	Entrance
የማረም ሂደት	Scoring process
የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና	Aptitude test
የተብራራ	Explicitly
የትምህርት ጊዜ ፈተና	On-course test
የችሎታ መለኪያ ፈተና	Achievement test
የናሙና ፈተና	Sample item
አሳሳች	Distractor
የእርማት አስተማማኝነት	Scorer reliability
የዝግጁነት	Readiness
የይዘት ተገቢነት	Content Validity
የጥያቄ አይነቶች	Items
የፈተናዎች ትንተና	Test analysis
የፈተና ምዘና	Evaluating Tests
ደረጃ መለኪያ ፈተና	Proficiency test
ድህረ ትምህርት ፈተና	End-of-course test
ገለፃ ነክ	Subjective
ግለሰባዊ	Individual
ጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና	Diagnostic test
ፈተና	Test

ዋቢ መጻሕፍት

ሽዋዬ ተካ (1994) "በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጥ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ንፅፅራዊ ጥናት።" በኤዱኬሽን ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ።ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ (ያልተተመ)።

ተስፋዬ ኃይሌ (1964) "የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ተፈታኞች ለምን በአማርኛ ፈተና ጥሩ ውጤት አያመጡም?" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

ታረቀኝ ተፈራ (1993) "ሀገር አቀፍ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐትምህርት ጋር ያለው ዝምድና።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ትምህርት ሚኒስቴር ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ኢንስቲትዩት (1996) <u>የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሐትምህርት</u> አዲስ አበባ።

ትምህርት ሚኒስቴር አ/ት/ቢሮ/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም (1997) <u>የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ</u>። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት።

ትምህርት ሚኒስቴር አ/ት/ቢሮ/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም(1997) <u>የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ</u>። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት።

ዓለም እሸቱ (1997) <u>መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ</u>። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ዘላለም ጌታቸው (1998) "በአማርኛ እና በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ንጽጽራዊ ግምገማ" የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

ዳኛቸው ወርቁ (1955) "ከ1954 ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ የአማርኛ የፈተና ወረቀቶች ውስጥ የተሰበሰበ ስህተትና የማሻሻያ ዘዴዎች።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጹሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

Alderson, C. (1988) "Testing English for Specific Purposes: How Specific can we Get?" In Arthur Hughes (ed). <u>Testing English for University Study</u>: (PP. 16-28). Hong Kong: Modern English Publication in Association with the British Council.

Alderson, J. et al. (1995) Language Test Construction and Evaluation. Cambridge: Cambridge University Press.

Atkins, J., Hailom Banteyerga and Nuru Mohammed. (1996) Skill Development Methodology Part 2. Addis Ababa University: Department of Foreign Languages and Literature.

Bachman, L. F. (1990) Fundamental Consideration in Language Testing. Oxford: Oxford University Press.

Baker, D. (1989) Language Testing: A Critical Survey and Practical Guide. London: Eduward Arnold.

Brown, H. D. (1980) Principle of Language Learning and Teaching. New Jersy: Prentice-Hall, Inc.

_____(1994) Principle of Language Learning and Teaching. New Jersey: Profice Mull Regent.

Carroll B. J. (1980) Testing Communicative Performance: an Interim Study. Oxford: Pergamon Press Ltd.

Carter, V. Good (1973) Dictionary of Education. Sanfrancisco: Mcgraw-Hill Book Company.

Clark, L. and Star, I (1996) Secondary and Middle School Teahching Methods. Upper Saddle: Prentice Hall Inc.

Cohen, A. (1991) Second Language Testing: In Murcia Teaching English as a Second or Foreign Language: Second Edition.Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Cunningworth, A. (1989) Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials. Oxford: Adivision of Herenemarm Education Books Ltd.

_____ (1995) Choosing Your Course Book. London The Bath Press.

Davies, A. (1968) Language Testing symposium. London: Oxford University Press.

_____(1988)"Communicative Language Testing." In Arthur Hughes (ed), Testing English for University Study. (PP. 5-15). Hong Kong: Modern English Publication in Association with the Biritish Councile.

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

Dejenie Leta (1994) "LANGUAGE TESTING AND ITS PRACTICAL APPLICATION" Department of Foreign Language and Literature. A.A.U. (Unpublished).

Dubin, F.and E. Olshtain (1986) Course Design: Developing Programs and material for Language Learning .Cambridge: Cambridge University Pess.

Finocchiaro, M. and Sako, S. (1983) Foreign Language Testing. Apractical Approach. New York: Regents Publishing Campany,Inc.

Finocchiaro, M. and Brumfit, C. (1986) The Fundamental National Approach From Theory to Practice. Oxford: Oxford University Press.

Genessee, F. and Upsher, J. A. (1996) Classroom-based Evaluation in Second Language Education: Oxford: Oxford University Press.

Grandman,H.L and D.J. Reed (1997) "Assessment and Second Language Teaching" In M. BarDovi-Harling andB. (ed). Beyond Methods: Components of Second Lnaguage Teacher Education. (pp 200-2005). New York: Mc Graw-Hill.

Harmer, J. (1991) The Practice of English Language Teaching. Longman Group.

Harrison A. (1983) A Language Testing Handbook. London: Macmilan Publishers Ltd.

Heaton, J. B. (1975) Writing English Language Tests. London: Longman Group Limited.

_____ (1988) Writing English Language Tests. London: Longman.

_____(1990) Class Room Testing. London: Longman.

Hughes, A. (1989) Testing for Language Teachers: Cambridge Handbooks for Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

_____ (1995) Testing for Language Teachers (Second Edition). Cambridge: Cambridge University Press.

Lado, R. (1961) Language Testing. London: Lowe and Brydone Ltd.

Lissitz, R. W. and W. D. Schafer (2002) Assessment in Educational Reform: Both Means and Ends. Boston: Allyn and Bacon.

Madsen, H. S. (1983) Techniques in Testing. New York: Oxford University Press.

Mehrens, W. A. and L. Lehmann (1974) Standardized Tests in Education. (2nd ed.) New York: Holt, Rinehart and Winston.

Norman G. (1988) How to Construct Achievement Test. Englewood Clifts. New Jersey: Prentice, Inc.

Nunan D. (1994) Teaching and Reading in Foreing Language. London :clays LTD.

Oller, J. W. (1979) Language Test at School. London: Longman Group Limited.

Richards , Jack. C. , and Lockhart, C.(1994) Reflective Teaching in Second Languge Classrooms. Cambridge: Cambridge University Press

Richards, J. C. (1990) The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J. C. and T. S Rodgers (1986) Approaches and Methods in Language Teaching: A Description and analysis. Cambridge: Cambridge University Press.

Rivers, W. M. (1968) Teaching Foreign Language Skills. Chicago: University of Chicago Press.

Teshome Demisse (1995) "The Consruction and Validation of A Test in English for Tertiary Education with Reference to Addis Ababa University." PHD Thesis (un Publsihed).

Ur, P. (1991) A Course In Language Teaching: Practice and Theory. Cambridge: Cambridge University Press.

Weir, C. J. (1990) Communication Language Testing. Hertfordshire: Prentice Hall International (Uk) Ltd.

_____ (1993) Understanding and Developing Tests. London: Prentice Hall.

Wood, D. (1965) Test Construction Development and Interpretation of Achievement Test. Chicago: Charles Merrill Books Inc.

Zimba, R. (2005) Inaugural Lecture. Namaibia: University of Zambia Press.

ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE EXAMINATION (1997 E.C.) Page: 001

Subject: Amharic/ALL Region: Addis Ababa Date: 9/05/2007

ክለሳ-1

School Name	A	%A	B	%B	C	%C	D	%D	F	%F	NotRgs	%-	IXT	%I
MAGIC CARPET (R)	43	38	56	49	15	13	0	0	0	0	1	1	3	
TOTAL:	43	38	56	49	15	13	0	0	0	0	2	2	3	

ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE EXAMINATION (1997 E.C.) Page: 001

Subject: Amharic/ALL Region: Addis Ababa Date: 9/05/2007

School Name	A	%A	B	%B	C	%C	D	%D	F	%F	NotRgs	%-	IXT	%I
YENEGEW SEW (R)	15	11	56	42	60	45	1	1	2	1	1	1	0	
TOTAL:	15	11	56	42	60	45	1	1	2	1	2	1	0	

ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE EXAMINATION (1997 E.C.) Page: 001

Subject: Amharic/ALL Region: Addis Ababa Date: 9/05/2007

School Name	A	%A	B	%B	C	%C	D	%D	F	%F	NotRgs	%-	IXT	%I
MENILIK II (R)	95	6	461	30	905	58	52	3	43	3	1	0	134	
TOTAL:	95	6	461	30	905	58	52	3	43	3	2	0	134	

ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE EXAMINATION (1997 E.C.) Page: 001

Subject: Amharic/ALL Region: Addis Ababa Date: 9/05/2007

School Name	A	%A	B	%B	C	%C	D	%D	F	%F	NotRgs	%-	IXT	%I
YEKATIT 12 (R)	77	6	306	24	802	64	46	4	20	2	1	0	16	
TOTAL:	77	6	306	24	802	64	46	4	20	2	2	0	16	

ኦገ6-2

ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት
የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ
ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና
ግንቦት / 1997 ዓ.ም

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 — የዚህ ጥራዝ መለያ: 84
የጥያቄ ብዛት: 90 — የተፈቀደው ጊዜ 1:30

መመሪያ ፦ ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀጽ በጥሞና በማንበብ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 ድረስ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተስማሚያቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ /ምረጥ።

ዓለማችን መቼም ቢሆን የለውጥ ሂደቷን አቋርጣ አታውቅም። ህይወት ካለው ፍጡር እስከ ግዑዙ ድረስ ሁሉም በዚሁ የለውጥ ሂደት ውስጥ ማለፋቸው የግድ ነው። ከዛሬ ሀምሳ ዓመትና ከዚያም በላይ የነበረው ትውልድ ቦታውን ለቋል። አሮጌው በአዲስ መተካቱ የግድ እንደሆነ ሁሉ አዲስ የሚመጣውም የማንነቱ መሠረት የሚገነባው በአሮጌው ላይ መሆኑ አያጠራጥርም። ይህም በመሆኑ ዛሬ የቆምነው ምን ላይ ነው? ነገስ ወዴት ነው የምንጓዘው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የምናገኝላቸው የትናንቱን ማህደር ስናገላብጥ ብቻ ነው።

1. አንቀጹ ሀሳቡን ለማስፋፋት የተጠቀመበት ስልት ምንድን ነው?

A. ትንተና — C. ማወዳደርና ማነፃፀር
B. ምስያ — D. ምክንያትና ውጤት

2. አንቀጹ አንድነቱን የጠበቀ እንዲሆን ያደረገው ዐ.ነገር የቱ ነው?

A. ሦስተኛው — C. የመጨረሻው ዐ.ነገር
B. ሁለተኛ ው ዐ.ነገር — D. ሁሉም

3. የአንቀጹ ንኡስ ቃል ሊሆን የሚችለው ስንተኛው ዐ.ነገር ነው?

A. የመጀመሪያው — C. የመጨረሻው
B. ሁሏተኛው — D. ሦስተኛው

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

4. አንቀጹ የቀረበበት ቅርፅ የትኛው ነው?

A.

C.

B.

D.

5. አንቀጹ ስንት ዘርዛሪ ዐ.ነገሮች አሉት ?

A. 5
B. 7
C. 4
D. 6

<u>መመሪያ</u>፡- ከተራ ቁጥር 6 እስከ 21 ድረስ ለተሰጡት ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው ባህርይ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ / ምረጭ።

6. ቱርክ ... ከኮሚሽኑ ጋር ቀጥተኛ ውይይት ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለችም። በሚለው ዐ.ነገር ነጠብጣቡ የገባበት ምክንያት የትኛው ነው?

A. ሀሳቡ እንደሚቀጥል ለመግለፅ
B. ለዐ.ነገሩ ሀሳብ ትኩረት ለመስጠት
C. ስምን ከስም ለመለየት
D. ከውስጡ የተቀነሰ ሀሳብ መኖሩን ለማሳየት

7. ከእናቴ መለየት ባልፈልግም በሞት ተለየችኝ። የሚለው ዐ.ነገር ምን ማለት ነው ?

A. እናቴን ስላልፈለግኳት በሞት ተለየችኝ።
B. እናቴን በመፈለጌ በሞት ተለየችኝ።
C. እናቴን ብፈልጋትም በሞት ተለየችኝ።
D. እናቴን እንደምፈልጋት በሞት ተለየችኝ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

8. ሰውዬው መ·ልሜ ብሎ ከከሰረ በኋላ ተቸግሮ ሞተ። የሚለውን በሌላ አባባል ብንፅፈው የትኛው ትክክል ይሆናል ?

A. ከተቸገረ በኋላ መ·ልሜ ብሎ ከሰረ።
B. በመቸገሩ መ·ልሜ ብሎ ከሰረ።
C. መ·ልሜ ብሎ ስለሰከረ ሞተ።
D. በመክሰሩ ምክንያት ተጎሳቁሎ ሞተ።

9. ከእንግዲህ ወዲያ የምትፈልገውን ነገር _____።ጅምር ዐ.ነገሩን የሚያሟላው የትኛው ነው?

A. ሲያሟላህ·ልህ ራስህን ቻል።
B. ስላሟላህ·ልህ ራስህን ቻል።
C. ባሟላህ·ልህ ራስህን ቻል።
D. ያሟላህ·ልህ ራስህን ቻል።

10. ከሚከተሉት ውስጥ የቴሌግራምና የደብዳቤ የጋራ ባህርይ የትኛው ነው ?

A. መልዕክቱ በምስጢር ቋንቋ መቅረቡ
B. መልዕክቱ በጽሁፍ ለተቀባዩ መድረሱ
C. ክፍያው በቃላቱ ልክ መሆኑ
D. መልዕክቱ አሥር መሆኑ

11. ከሚከተሉት ውስጥ የዘገባ ባህርይ **ያልሆነው** የትኛው ነው ?

A. ከግል አስተያየት ይልቅ በሀቅ ላይ ማተኮር
B. ጊዜና ስፍራን በግልጽ መጠቀም
C. በቀላልና ግልጽ ቋንቋ መቅረብ
D. ለቋንቋ ውበት ትኩረት መስጠት

12. ከ1170 የሚበልጡ አሽከርካሪዎች የፌዴራል መንጃ ፈቃድ ማግኘታቸውን የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ገለፀ። የሚለው ይህ ዐ.ነገር ከየትኛው የፅሁፍ ዓይነት ይካተታል?

A. ቃለ-ጉባኤ
B. ልብወለድ
C. ዘገባ
D. ንግግር

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

13. የሀሳብ ድግግሞሽ በያዙ ቃላትና ሐረጋት የተገነባው ዐ.ነገር የትኛው ነው?

A. የሸበተ ማራኪ ፂም ያላቸው በትህትና የታጀቡ ዐይነት ሰዎች አልፎ አልፎ ያጋጥማሉ።
B. ሊላውን መምሰል መቻል ትልቅ ተሰጥዖ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።
C. እያሳቀ ግን የወቅቱን ፍጥጫ ጥሩ አድርጎ ያስገንዝባል።
D. የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት ከፍተኛ የሆነ መዋዕለ ንዋይና ገንዘብ ያስፈልጋል።

14. " ወደ እናት አባቱ ቤት ተመልሼ ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የአገራችንን ትምህርት መ.ጨ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን እንድማር ተወሰነ። እዚያ እኔና ገብረየስ ሁለታችን ሆነን ይህኑ ያገራችንን ትምህርት ጀመርን።" ይህ ዕሁፍ ከየትኛው ይመደባል?

A. ሪፖርት
B. ልብወለድ
C. ተውኔት
D. የህይወት ታሪክ

15. "የሾላ ወተት ሕዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ብዙ ሂደቶችን ማለፍ አለበት። በመጀመሪያ ወተቱ በፋብሪካ ውስጥና ከፋብሪካ ውጭ ካሉ ላሞች ይሰበሰባል።...» ይህ ጽሁፍ ለየትኛው የድርሰት ዐይነት ምሳሌ ይሆናል?

A. አስረጅ
B. ስዕላዊ
C. ተራኪ
D. አወዳዳሪ

16. በሥርዓተ ነጥቡ አቀማመጥ ትክክለኛው የትኛው ነው?

A. "ያንን ልጅ አያችሁት" "እንዴት የሚገርም ነው።" ብላ እንደተናገረች እንገምታለን።
B. "ያንን ልጅ አያችሁት? እንዴት የሚገርም ነው!" ብላ እንደተናገረች እንገምታለን።
C. ያንን ልጅ አያችሁት? እንዴት የሚገርም ነው።ብላ እንደተናገረች እንገምታለን።
D. "ያንን ልጅ አያችሁት? እንዴት የሚገርም ነው።"ብላ እንደተናገረች እንገምታለን።

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

17. ቃላት በአጠቃቀም ረገድ መደበኛ ኢመደበኛ ፀያፍ የሚባሉ ምድቦች አሏቸው። የሚለውን ዐ.ነገር በሥርዓት ለማንበብ መጠቀም ያለብን ሥርዓተ ነጥብ የትኛውን ነው ?

A. ሠረዝ
B. ጭረት
C. ድርብ ሠረዝ
D. ነጠላ ሰረዝ

18. ከሚከተሉት ውስጥ የዐ.ነገር ሥርዓትን ጠብቆ የተፃፈው የትኛው ነው?

A. ፊቱን እየተመለከተ በመስታወቱ ውስጥ እጆቹን ታጠበ።
B. እየተመለከተ በመስታወቱ ውስጥ ፊቱን እጆቹን ታጠበ።
C. እጆቹን ታጠበ ፊቱን በመስታወቱ እየተመለከተ።
D. በመስታወቱ ውስጥ ፊቱን እየተመለከተ እጆቹን ታጠበ።

19. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛ መልእክት ለማስተላለፍ የሚችለው ዐ.ነገር የትኛው ነው ?

A. ወንድሟ መታመሙን ሰምታ ልትጠይቀው ሄደች።
B. ወንድሟ ከታመመ ልትጠይቀው ሰምታ ሄደች።
C. ወንድሟ ስለታመመ ሰምታ ልትጠይቀው ሄደች።
D. ወንድሟ ልትጠይቀው ሰምታ እንደታመመ ሄደች።

20. ከሚከተሉት ውስጥ የአፃፃፍ ሥርዓቱ ተስተካክሎ የቀረበው የትኛው ዐ.ነገር ነው?

A. አመለወርቅ ሰርታ የጨረሰች ይመስላል ቤቷን።
B. አመለወርቅ ቤቷን ሰርታ የጨረሰች ይመስላል።
C. አመለወርቅ የጨረሰች ይመስላል ቤቷን ሠርታ።
D. አመለወርቅ የጨረሰች ቤቷን ሰርታይመስላል።

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

21. ከአንድ መሥሪያ ቤት ለሌላ መሥሪያ ቤት ደብዳቤ ቢጻፍ በላኪው አድራሻ አጠቃቀም ትክክለኛው የትኛው ነው?

A. ቁጥር
ቀን
ፖ.ሣ.ቁ
ከ -

B. ቁጥር
ቀን
ከ -
ፖ.ሣ.ቁ

C. ቀን
ቁጥር
ከ -
ፖ.ሣ.ቁ

D. ከ -
ቀን
ቁጥር
ፖ.ሣ.ቁ

መመሪያ ፡ ከዚህ ቀጥሎ አጠር ያለ ምንባብ ቀርቧል። በጥሞና በማንበብ ከተራ ቁጥር 22 እስከ 31 ድረስ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተገቢ የሆነውን መልስ ምረጥ/ጭ።

...ስነጽሑፍ የሰው ልጅ ገጠመኝ ማንፀባረቂያ፣ የሰው ልጅ የህይወት መልኮች መግለጫ ነው ብለናል።የሰው ገጠመኝና የህይወት መልክ ደግሞ ስፍር ቁጥር የለውም። ህይወት ባለብዙ ፊርጅ፣ ባለብዙ ቀለም መሆኗም ግልጽ ነው።ስለዚህ የስነጽሑፍ ክልል እዚህ ድረስ ነው ተብሎ ሊገደብ አይችልም ማለት ነው ። ስነጽሁፍ ማንኛውንም የሰው ልጅ ገጠመኝ የተከሰተንና ሊከሰት የሚችልን ነገር እንዲሁም በሰው የምናብ አድማስ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብን ነገር ሁሉ ሊያካትት ይችላል። መጠነ ርእዩ እጅግ ሰፊ ብቻም ሳይሆን ገደብ አልባም ነው። የሰው ልጅ አያሌ ተግባራት፣ በምናቡ የሚፈጥረው ዓለምን የአለመ. ፍጡራን፣ በሰውና በሰው መካከል ያሉ ግንኙነቶች፣ በሰውና በማህበረሰብ፣ በሰውና በእንስሳት፣ በሰውና በተፈጥሮ መካከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶች በስነጽሁፍ ውስጥ እንደአስፈላጊነታቸው ሊካተቱ ይችላሉ። ስነጽሁፍ በነዚህ በተጠቀሱት ግንኙነቶች ውስጥ የሚከሰቱትን ተቃርኖዎችና ህልውናዊ ትግሎች ይይዛል። ከነሱም ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሰው ልጅ ህይወት አያሌ መልኮችና ብዙ አቅጣጫዎች ስለሚኖሩት የስነጽሁፍ መጠነ ርእይ ውሱንነት አይኖረውም። በአጠቃላይ ስነጽሁፍ የሚቀዳው ከሰውና ከተፈጥሮ በመሆኑ ምንጩ የማይደርቅና ዘለዓለማዊ ነው። ይህም በመሆኑ በስነጽሁፍ ላይባል የሚችል ነገር የለም ማለት ነው። በስነጽሁፍ ላይባል የሚችል ነገር የለም ሲባል ግን ሁሉም ነገር ተግበስብሶ እንዳለ በጥሬው ይቀመጣል ማለት አይደለም። የሚባለው ነገር ተመርጦና ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በተወሰነ

ስርዓትና ልክ ተቀነባብሮ ነው እሚቀርበው። ስነጽሁፍ የተለያዩ ዘሮች ወይም ቅርጾች ያሉት በመሆኑም የሚባለው ነገር፣ የሚገለጸው የህይወት መልክና ሰዋዊ ተግባር እንዲሁም ምናባዊ አለም በነዚህ ቅርጾች ባህሪና አቅም መሰረት መሆን ይኖርበታል። እያንዳንዱ የስነጽሁፍ ዘር ሊያካትት የሚችለው ህይወት ወይም የማህበረሰብ ገጽታ ቅርጹ በሚችለው አቅም የተመጠነ ስለሚሆን ደራሲው ኪነጥበባዊ ምርጫ እንዲያደርግ ይገደዳል። የምርጫውም መሰረት የግለ አስተውሎቱና የምናብ ኃይሉ ነው።

በተደጋጋሚ ስነጽሁፍ የሀሳብ መግለጫ፣ የገጠመኝ ማንፀባረቂያ መሆኑ ተወስቷል። ስለዚህ የመኖሩ አንዱ ምክንያት ሰዎች ስለገጠመኛቸው ለመናገር ያላቸው ፍላጎት ነው ማለት እንችላለን። የሰው ልጅ በተፈጥሮው ሀሳቡን የመግለጽ፣ ስለአየውና ስለታዘበው፣ ስሜቱን ስለነካውና ስላስጨነቀው ነገር የመናገር ፍላጎት አለው። ይህ ደግሞ ከማህበራዊነቱ ባህርያዊ ግፊት የመጣ ነው። ሰው ስለአለመ. የተገነዘበውን በጎም ሆነ ክፉ ነገር ለሌሎች ማካፈል ይፈልጋል። ስለራሱ ማንነትና ስለአካባቢው ምንነት የተገነዘበውን ይገልጻል። በአጠቃላይ የገጠመኙን ልዩልዩ መልኮች ለሌላው መንገር ይወዳል። እንዲህ ያለው ውዴታ በሁሉም ሰዎች ዘንድ የሚገኘው ላቅ ባለ ደረጃ ነው። ከያንያን ከሌላው ሰው በተለየና በበለጠ ሁኔታ ስለህይወት የመናገርና የመግለጽ ፍቅር አላቸው። ለዚህም ነው አድካሚውንና አስጨናቂውን የድርሰት ስራ በህቅ የሚጋተሩት፣ ህይወትን እንደታዘቡት እንደተመለከቱት ለሌላው ለማሳየት ከውስጥ የሚፈነቅላቸው።

(ዘሪሁን አስፋው፣ የሥነጽሁፍ መሠረታውያን፣ ገጽ 3-4)

22. በፀሀፊው እምነት ለሥነጽሁፍ መኖር አንደኛው ምክንያት ምንድን ነው?

A. የአሳታሚ ድርጅቶች መኖር
B. የሰዎች ተፈጥሮን የመታዘብ ችሎታ
C. ጠንካራ ደራሲያን መኖር
D. ሰዎች ስለገጠመኛቸው ለመናገር ያላቸው ፍላጎት

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

23. "የሰው ልጅ ሀሳቡን የመግለጽ ፍላጎት ከማህበራዊነቱ ባህርያዊ ግፊት የመጣ ነው" ሲባል ምን ማለት ነው?

A. በማህበር መኖር ሀሳብን ለመግለጽ መሠረታዊ ምክንያት ነው።
B. ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ሀሳቡን የመግለጽ ፍላጎት አለው።
C. ሰው በማህበር መኖሩ ሀሳቡን እንዲገልጽ ተዕእኖ አሳድሮበታል።
D. በማህበር የሚኖር ፍጡር ሁሉ ሀሳቡን በቋንቋመግለጹ ባህርያዊ ነው።

24. "...እንዲህ ያለው ውዴታ" የሚለውን ሀረግ በያዘው ዐ.ነገር ውስጥ በጥቆማ የተነገረው የትኛው ነው?

A. ሀሳብን ለሌላው የመግለጽ ፍላጎት
B. ባህርያዊ ግፊት
C. ደራሲ የመሆን ፍቅር
D. የሥነጽሁፍ ችሎታ

25. ከሚከተሉት የግንኙነት መልኮች መካከል ፀሀፊው በጽሁፉ ውስጥ **ያልገለፀው** የትኛውን ነው?

A. በሰውና በእንስሳት መካከል ያሉ ግንኙነቶች
B. በተፈጥሮና በተፈጥሮ መካከል ያሉ ግንኙነቶች
C. በሰውና በሰው መካከል ያሉ ግንኙነቶች
D. በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያሉ ግንኙነቶች

26. በፀሀፊው አገላለጽ ሥነጽሁፍ ምንጩ የማይደርቅና ዘለዓለማዊ ነው የተባለው ለምንድን ነው?

A. ህይወት ባለብዙ ዘርፍ በመሆኗ
B. ሥነጽሁፍ ገደብ የለሽ በመሆኑ
C. የሰውን ልጅ ገጠመኝ ማንፀባረቂያ በመሆኑ
D. የሚቀዳው ከሰውና ከተፈጥሮ በመሆኑ

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

27. "እያንዳንዱ የሥነጽሁፍ ዘርፍ ሊያካትት የሚችለው ህይወት ወይም የማህበረሰብ ገጽታ ቅርጹ በሚችለው አቅም የተመጠነ ስለሚሆን ..." ማለት ምን ማለት ነው?

A. የሥነጽሁፍ ዓይነቶች በማህበረሰቡ ገጽታ የተመጠኑ ናቸው።
B. የሥነጽሁፍ ዓይነቶች በሰው ልጅ ገጠመኝ ልክ ይወሰናሉ።
C. እያንዳንዱ የሥነጽሁፍ ዓይነት ሊያቀርብ የሚችለው ህይወት በቅርጹ የተገደበ ነው።
D. ሥነጽሁፍ ሁሉንም ነገር አግበስብሶ አያቀርብም።

28. ስፍር ቁጥር የለውም የተባለው ምንድን ነው?

A. የሥነጽሁፍ መልክ
B. የሰው ልጅ የፈጠራ ሥራ
C. የሰው ልጅ የአስተሳሰብ አድማስ
D. የሰው ልጅ ገጠመኝ

29. የሥነጽሁፍ ክልል እዚህ ድረስ ነው ተብሎ ሊገደብ አይችልም የተባለው ለምንድን ነው ?

A. ሥነጽሁፍ የፈጠራ ስራ በመሆኑ
B. ሥነጽሁፍ በርካታ ደራሲያን የሚሰማሩበት መስክ በመሆኑ
C. ህይወት ባለብዙ ፊርጅ ስለሆነች
D. የሰው ልጅ ህይወት መገለጫዎች ብዙ ስለሆኑ

30. ጸሀፊው **የምናብ አድማስ** ሲል ምን ማለቱ ነው?

A. የአስተሳሰብ ጥራት
B. የሥነጽሁፍ ብቃት
C. አእምሯዊ ርቀት
D. የፈጠራ ልክ

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

31. ሥነጽሁፍ መጠነ ርእዩ እጅግ ሰፊ ብቻ ሳይሆን ገደብ አልባም ነው የተባለው ለምንድን ነው?

A. በሥነጽሁፍ የማይዳሰስ እውናዊም ሆነ ምናባዊ ህይወት አለመኖሩን ለመግለጽ ነው።
B. የሥነጽሁፍን አስቸጋሪ ገጽታ ለማስገንዘብ ነው።
C. ሥነጽሁፍ የማይዳስሰው የህይወት መስክ ጥቂት መሆኑን ለመግለጽ ነው።
D. የሥነጽህፍ ሥራ ሊመረመር የማይችል መሆኑን ለመጠቆም ነው።

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 32 እስከ 49 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ይገኛሉ:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ በአጠያየቁ መሰረት ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጭ/ ምረጥ::

32. "ከመረቁ አውጡልኝ ከስጋው ጾመኛ ነኝ::" የተሰኘው አባባል ከሚከተሉት ውስጥ ከየትኛው ጋር የበለጠ ይስማማል ?

A. እንኳን ዘንቦብሽ ድሮም ጤዛ ነሽ::
B. አልሸሹም ዞር አሉ::
C. ሁሉም አማረሽን ገበያ አታውጣት::
D. ሀይማኖት የግል አገር የጋራ ነው::

33. "የራስ ምታት ኪኒን ለምኔ ለምኔ፣
ፍቱን መድሃኒቱ ከንፈርህ ነው ለእኔ::" በሚለው ግጥም የገጣሚውን ጸታ የሚጠቁመን ቃል የትኛው ነው?

A. ከንፈርህ
B. ለእኔ
C. የራስ ምታት
D. መድሃኒቱ

34. "እኔ የማይገባኝ ይኸ የአይጥና ድመት ጨዋታ ነገር ነው::" የሚለው ምንን ያመለክታል?

A. ፈላጊና ተፈላጊን
B. አሳዳጅና ተሰዳጅን
C. አለቃና ምንዝርን
D. ጠፊና አጥፊን

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

35. በልቦለድ ጽሁፍ ውስጥ ታሪኩ ስለሚከናወንበት ጊዜና ቦታ መለየት የምንችለው የትኞቹን ጥያቄዎች በመጠየቅ ነው?

A. መቼ እና የት
B. የት እና ለምን
C. እንዴት እና መቼ
D. ለምን እና እንዴት

36. _____እሾህ ላጣሪው::
ተገቢው የመነሻ ሀረግ የትኛው ነው?

A. አፈር ለገፊው
B. ሀብት ለአጥፊው
C. አሸዋ ለገንቢው
D. ስራ ለሰሪው

37. «ክበር በሰው እጅ ያምር
ሲይዙት ያደናግር:: » ለሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ተመጣጣኙ የትኛው ነው?

A. በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ
B. ለተቀማጭ ስማይ ቅርቡ ነው
C. ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ
D. ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጪት

38. «ዝንብ ቢሰበሰብ ጋን አይክፍትም" ለሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ተቃራኒ የሆነ መልእክት የያዘው አማራጭ የትኛው ነው?

A ለአምሳ ጋን አንድ አለሙ ይበቃል።
B. ከብዙ አዋቂ አንድ ጠንቋራ ይሻላል።
C. ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል።
D. ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር።

39. "የፈጠራ ጽሁፍ ቢሆንም ተአማኒነቱ ሊያጠራጥረን አይገባም:: " ሲባል ምን ማለት ነው?

A. ልቦለድ ጽሁፍ የማይመስል ታሪክ ሊሆን ይችላል::
B. ልቦለድ ጽሁፍ እንደመሆኑ እምነታችንን እንዲያገኙድል አይጠበቅም::
C. ልቦለድ ጽሁፍ ተጨባጭነት የሌለው መሆኑ መረሳት የለበትም::
D. ልቦለድ ጽሁፍ ሊሆን የሚችልና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ይጠበቃል::

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

40. ግዛም በጽሁፋዊ አቀማመጡ የሚገኘው በምን መልኩ ነው?

A. ድብልቅልቅ አይነት ነው።
B. ድርድር በሆነ መልኩ ነው።
C. በቤት ነው።
D. ዝርው በሆነ መልኩ ነው።

41. የልቦለድ መዋቅር ወይም ትልም የሚገነባበትን ፍሬ ነገር አስመልክቶ የታሪኩ የጀርባ አጥንት ነው የሚባለው የትኛው ነው?

A. ግጭት
B. መቼት
C. ገፀባህርይ
D. ታሪክ

42. ረጅም ልቦለድ እና አጭር ልቦለድ ድርሰቶችን በሚመለከት የትኛው ትክክል ነው?

A. ብዙ አጫጭር ልቦለዶች አንድ ረጅም ልቦለድ ይሆናሉ።
B. እንደስያሜያቸው አጭሩ የረጅሙ ቁራጭ ነው።
C. የሚጋሩት ነገር ቢኖርም ሁለቱም የየራሳቸው ቅርጽና ባህርያት አሏቸው።
D. የረጅሙን ታሪክ አንድ ክፍል ይዞ በመቅረብ ይለያያሉ።

43. የረጋ ውኆች _____።
ተገቢው የመደምደሚያ ሀረግ የትኛው ነው?

A. ለጤና ይጠቅማል
B. ቢገኝ ይመረጣል
C. በጣም ያረካል
D. ቅቤ ይወጣዋል

44. ተንጋለው ቢተፉ _____።
ተገቢው የመደምደሚያ ሀረግ የትኛው ነው?

A. ከማጥፋት አይተርፉ
B. ተመልሶ ባፉ
C. ትዝብት ነው ትርፉ
D. ክልክ አያልፉ

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

45. _____ ብቅል ያወጣዋል::
ተገቢው የመነሻ ሀረግ የትኛው ነው?

A. ሆድ ያባውን
B. ውስጥ የያዘውን
C. የተደበቀውን
D. አልረጋ ያለውን

46. የልቦለድ አላባውያን ከሚባሉት ውስጥ **የማይካተተው** የትኛው ነው?

A. አንባር
B. ገለባ
C. ጭብጥ
D. ትልም

47. "እንደዚህ ለምልሞ ፈክቶ የሚታየው
ይህ አትክልታችን አዲስ አበባ ነው ::" በሚለው ቅኔ ውስጥ ሰምና ወርቁን አካቶ የያዘው ሀረግ የትኛው ነው?

A. አዲስ አበባ ነው
B. ይህ አትክልታችን
C. እንደዚህ ለምልሞ
D. ፈክቶ የሚታየው

48. «ቤታችን ተሰርቶ በመንታ መንገድ
እናያለን ሁሉን ሲወጣ ሲወርድ ::"
በሚለው ቅኔ ውስጥ ወርቁ የትኛው ነው?

A. ተመላላሹን ሁሉ እናያለን።
B. ወጪ ወራጁን እናያለን።
C. አላፊ አግዳሚውን እናያለን።
D. የሚሾም የሚሻረውን እናያለን።

49. « እዚያ ማዶ ሆና ትጣራለች እናት
ና ብላ ነው እንጂ ሌላ ምን ሙያ አላት::»
በሚለው ቅኔ ውስጥ ሰሙ የትኛው ነው?

A. እንድመገብ እየጠራችኝ ነው::
B. ና ከማለት ውጪ ሌላ አታውቅም::
C. ቶሎ እንድደርስ በመፈለጓ ነው::
D. የትም እንድሄድ አትፈቅድልኝም::

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

<u>መመሪያ</u>፦ ከተራ ቁጥር 50 እስከ 65 ድረስ የተሰጡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ እንደየአጠያየቃቸው ባህርይ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ / ምረጭ።

50. ሰዎች ይበልጥ በተነኩ ቁጥር የዜና ተፈላጊነት የዚያኑ ያህል ከፍ ይላል። ይህን ዐ.ነገር መሠረት በማድረግ መንስኤና ውጤትን በይበልጥ የሚገልፀው የትኛው ነው?

A. ለዜና ተፈላጊነት የሰዎች መነካት መንስኤ ነው።
B. የዜና ተፈላጊነት ለሰዎች መነካት ውጤት ነው።
C. ለሰዎች መነካት መንስኤው የዜና ተፈላጊነት ከፍ ማለት ነው።
D. የሰዎች መነካት ለዜና ተፈላጊነት ውጤት ነው።

51. አይ! ምነው!የሚለው አባባል የትኛውን ያመለክታል?

A. ዛቻን
B. ልመናን
C. ምክርን
D. ቁጣን

52. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ንግግራዊ ባህርይ የሚታይበት ዐ.ነገር የትኛው ነው?

A. አስፈላጊ ነው ብለው ካመኑበት እንግዳዎን እዚህ ማሳረፍ ይችላሉ።
B. አልፎ አልፎ ስለተመሳሳይ ፊደሎች አጠቃቀም አጠር ያለ መግለጫ ይሰጣል።
C. እንዴ! አንት ከይሲ ወግድልኝ ከዚህ ! አሉት።
D. ባአገር መከላከያ በረዳት አዛዥነት ማገልገላቸው ተገለጠ።

53. <u>ኡኡቴ</u>! አንተን ደግሞ እዚህ ምን አመጣህ? በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቱን ያመለክታል?

A. ግነት
B. ብሶት
C. ጥላቻ
D. ንቀት

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

54. ከዚህ በታች በተመለከተው ሥውውት የተቋረጠውን የንግግር ሀሳብ እንዲቀጥል ያደረገው ማነው?

አቶ በላይ - "እረ እናንተ ሰዎች አንድ በሏቸው"
አቶ ተቀባ- "ምነው ጃል በቃ እንግዲህ... በማይመለከታችሁ አትግቡ"
ወ / ሮ ባንቺይደሩ- በፊጣሪ እንደ እናንተ ያለ ሰው እንዲህ አይባባልም። ረጋ ብላችሁ ተነጋገሩ።"
ወ / ሮ ላቀች- " እንግዲህ ካላችሁ ምን ይደረጋል ይሁን እንጂ"

A. ወ/ ሮ ላቀች
B. ወ/ ባንቺይደሩ
C. አቶ በላይ
D. አቶ ተቀባ

55. በጣም እርግጠኛ, የሆነ ሀሳብን አጥብቆ መግለፅ ሲፈለግ ከሚከተለው የትኛው ትክክል ይሆናል ?

A. እንዴታ
B. በጄ
C. እኮ
D. እህስ

56. አንድ ሰው በአንድ ግብጥ ላይ አንድን ጉዳይ አስመልክቶ ድንገት ንግግር እንዲያደርግ ቢጋበዝ በቅድሚያ ማድረግ ያለበት ምንድን ነው?

A. ንግግሩን ለማዘጋጀት ጊዜ እንዲሰጠው መጠየቅ
B. ስለምን መናገር እንዳለበት ጋባጮቹን መጠየቅ
C. የንግግሩን ሀሳብ በፍጥነት በአእምሮው ማደራጀት
D. ማስታወሻውን አዘጋጅቶ ነጥቦችን በቅደም ተከተል ማስፈር

57. ከሚከተሉት ውስጥ ጫጫታ በበዛበት አካባቢ ማዳመጥን የተሳካ ለማድረግ የሚረዳው ስልት የትኛው ነው?

A. ከተቻለ ጫጫታውን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ መሞከር
B. የሚደመጠውን ድምጽ ከፍ ለማድረግ መሞከር
C. ሀሳብን ሰብስቦ ለማዳመጥ መሞከር
D. ሁሉም ተስማሚ ስልቶች ይሆናሉ።

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

58. ከማዳመጥ ጋር የሚድ የማይያያዘው ተግባር የትኛው ነው?

A. ኤግዚብሽን መገመብኘት
B. ትረካን መከታተል
C. ውይይት ላይ መሳተፍ
D. በተከራካሪነት መሳተፍ

59. ለረጅም ሰዓት የሚደረግን ንግግር ብናዳምጥ የማዳመጥ ፍላጐታችን ምን ሊሆን ይችላል?

A. የማዳመጥ ፍላጎታችን ቀስ በቀስ ይጨምራል።
B. ንግግር በተራዘመ ቁጥር የማዳመጥ ፍላጎታችን ከመቀሰቀሱ ባሻገር ተናጋሪም እንሆናለን።
C. የማዳመጥ ፍላጎታችን ቀስ በቀስ ይቀንሳል።
D. እንደተናጋሪው የአቀራረብ ስልትና እንደሚቀርበው ነገር የማዳመጥ ፍላጎታችን ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል።

60. ጥሩ ንግግር ለማድረግ የማይጠቅመው የትኛው ነው?

A. የአድማጭን ማንነት ማወቅ
B. በቅድሚያ አድማጭን ማነቃቃት
C. በሠንጠረዥ ለማቅረብ መሞከር
D. ርዕሰ ጉዳዩን ጠንቅቆ መረዳት

61. "አሸባሪነት ከውበት ጋር ይመሳሰላል:: " ሲባል የበለጠ ምንን ሊያመለክት ይችላል?

A. ውበትም ሆነ አሸባሪነት የሚወሰነው በተመልካቹ አይን ነው።
B. ውበትን የሚያደንቁ ስለአሸባሪነት የበለጠ ይረዳሉ ማለት ነው::
C. አሸባሪነት ቆንጆን ይፈልጋል ለማለት ነው::
D. ቆንጆ ነገርን ሁሉም ይፈልገዋል ለማለት ነው::

ADDIS ABABA UNIVERSITY FLE LIBRARY

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

62. በአንድ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ያዳመጡትን ሀሳብ ለሌላ ሰው በአጭሩ ለማስረዳት ቢፈለግ ከሚከተሉት የተሻለው ስልት የቱ ነው?

A. የተነገረውን ሁሉ መመዝገብ
B. የሚያዳምጡትን በተቻለ አቅም በቃል ለመያዝ መሞከር
C. በቴፕ ቀርጾ መያዝ
D. ዋናና ንዑሳን ሀሳቦችን ለመለየት መሞከር

63. በአንድ ውይይት ወቅት ከተሣታፊዎች ከሚጠበቁት ችሎታዎች መካከል **የማይመደበው** የትኛው ነው?

A. የግል ሀሳብን ብቻ በተቻለ አቅም ለማሳመን መሞከር
B. ለተወያዮች ሀሳብ በፋ ግምት መስጠት
C. የውይይቱን አዝማሚያ መረዳት
D. መቼ አዲስ ሀሳብ ማንሣት እንደሚገባ መለየት

64. ከሚከተሉት ውስጥ የአንድን ሰው ንግግር ለመረዳት አስቸጋሪ ከሚያደርጉት መካከል የሚጠቀሰው የትኛው ነው?

A. የሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ እንግዳ መሆን
B. የሚጠቀምባቸው ቃላት ውስብስብ መሆን
C. የሚጠቀምባቸው ቃላት ጠማር መሆን
D. ሁሉም ምክንያት ናቸው።

65. የቋንቋን ትምህርት ስንማር የትኞቹን ክሂሎች እናዳብራለን?

A. የማዳመጥ፣ የንግግር፣ የንባብና የጽሕፈት
B. የማዳመጥ፣ የንባብ፣ የጽሕፈትና የሰዋስው
C. የመናገር፣ የመስማት፣ የማዳመጥና የመፃፍ
D. የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የስነጽሁፍና የሰዋስው

APPROVED ADDIS ABABA UNIVERSITY

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

መመሪያ :- ከተራ ቁጥር 66 እስከ 70 ድረስ በቀረቡት ዐ.ነገሮች ውስጥ ከግርጌያቸው ለተሰመረባቸው ቃላት ትክክለኛ ፍቺዎቻቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ / ምረጥ።

66. የያዛቸው መግነጢሳዊ ፍቅር በብዙዎች ዘንድ መገረምን ፈጥሯል።

A. ጊዜያዊ
B. ዘላቂ
C. ጽኑ
D. አጉል

67. በልጅነታችን አፈር ፈጭተን ያደግንበት ሚዳ ዳዋ በልቶት አገኘነው።

A. ቁጥቋጦ
B. ምስጥ
C. ጫካ
D. አረም

68. በኋለኛው ዕድሜው ልፈጪ መሆኑ ደጋግሚ እንዳደንቀው አድርጎኛል።

A. ነገረኛ
B. ቁምነገረኛ
C. ዋዘኛ
D. ውለታበሲ

69. በዚች ምድር ስንኖር የሕልውናችንን አልፋና አሜጋ ለማወቅ ዘወትር እንጥራለን።

A. ፈጣሪ
B. ጉበና መፈጠሪሻ
C. መሰረት
D. መነሻና መድረሻ

70. በእነሱ ላይ የሚታየው ራሮት በሌሎችም ላይ ቢታይ የት እንደርስ ነበር ?

A. ትህትና
B. ምሬት
C. ርህራሄ
D. ትእቢት

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

መመሪያ፦ ከተራ ቁጥር 71 እስከ 84 ድረስ ለተሰጡት ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው ባህርይ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ / ምረጭ።

71. እንግዶቹ ይመጣሉ ተብሎ ይገመታል። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የማሰሪያ አንቀፁ መነሻ ቃል የትኛው ነው ?

A. አገማመት
B. ገምቶ
C. ግመታ
D. ገመተ

72. የብዙ ቁጥር ሥርዓትን ተከትሎ **ያልተፃፈው** የትኛው ነው?

A. ወደ ከተማው ብቅ እንዳልን ቤተክርስቲያኖች በብዛት መታየት ጀመሩ።
B. አንዳንድ መፃህፍት ዋጋቸው ከአንባቢው አቅም በላይ ነው።
C. ወደ ጥቃት አካባቢ አራዊት ጫካው ውስጥ ይጎማለላሉ።
D. የከተማው ደብራቶች ደወሎቻቸውን ሲደውሉ አረፈዱ።

73. ከሚከተሉት የትኛው ነጠላ ዐ.ነገር ነው ?

A. እስከዛሬ ይመጣል ብለው ቢጠብቁትም ሳይመለስ ቀረ።
B. መልካም አጀማመራቸውን አድንቀውና ሥራቸውንም አበረታተው ተመለሱ።
C. የመሟገቻ ሀሳባቸውን ለባህል ችሎት ያሰማሉ።
D. ትዝታቸውን በቦዘ አመለካከት ሲያፈልቁት ቁጭ ብላ ታዳምጣቸዋለች።

74. አሉታዊ ሀሳብ የያዘው ዐ.ነገር የትኛው ነው ?

A. ብዙ ሰዎች ሙስናን ለመዋጋት አይነሱም።
B. ጉቦኝነት በዓለም ዙሪያ ዜጎችን ለከፍተኛ ችግር ይዳርጋል።
C. ተስፋ ቆርጠው በቆሙበት የቀሩ ሰዎች አሉ።
D. ሰዎች የጠበኝነት ባህርይን ከእንስሳት ወርሰዋል ይላሉ።

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

75. ዳጎስ ያለ ሽልማት የሚያስገኝ ውድድር ተካሂደ። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል **በተቃራኒነት** ሊገባ የሚችለው የትኛው ነው?

A. ቀጨጭ ያለ
B. ከሳ ያለ
C. ኮስመን ያለ
D. አነስ ያለ

76. በሰልፉ ላይ የነበረው ቱማታ እጅግ ያስፈራል። ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒው የትኛው ነው?

A. ዝምታ
B. ለቅሶ
C. ጩኸት
D. ድምፅ

77. በጥምር ቃል **ያልተደራጀው** ዐ.ነገር የትኛው ነው?

A. ሀገረ ገዢው ለእስረኞች ምህረት ሰጥተዋል።
B. ብረታብረትን ሰብስቦ እንደገና ለሥራ ማዋል ይቻላል።
C. እጀ ጠባቡን ለብሶ የበዓሉን አከባበር በአድናቆት ይከታተላል
D. በሀገ መንግሥቱ የሴቶችና የህፃናት መብት ተከብሯል።

78. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የያታ ልዩነትን **የማያመለክተው** የትኛው ነው ?

A. ባዝራ
B. አጎት
C. ፍየል
D. ወንድም

79. መርሻ ቁርሱን ሳይበላ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ። የሚለውን ዐ.ነገር ወደ ትዕዛዛዊ ዐ.ነገር ብንለውጠው የትኛው ማሰሪያ አንቀጽ ትክክል ይሆናል ?

A. ይሂድ ይሆናል
B. ይሂዳል
C. ሂዲ.ል
D. ይሂድ

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

80. እብቅና ፍሬ በነፋስ ይለያል። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ ማሰሪያ አንቀፁ ጠብቆ ሲነበብ የትኛውን ያመለክታል?

A. አስደራጊውን
B. ድርጊቱን
C. አድራጊውን
D. ማድረጊያውን

81. ደራሽ ወንዝ ብዙ ሰዎችን ይነዳል። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የገባውን ቅፅል ማሰሪያ አንቀፅ አድርገን ብንጠቀምበት የትኛው ትክክል ነው?

A. በጊዜ ደርሶ መታየቱ ጥሩ ነው።
B. መፅሐፍ መድረስ ያስደስታል።
C. ወንድሙን ለማየት ፈጥኖ ደረሰ።
D. የበዓሉ አደራረስ ያስገርማል።

82. በፈቃዱ አባቱን መሰለ።
በፈቃዱ አባቱን መለሰ። በሚሉት ሁለት ዐ.ነገሮች መካከል የትርጉም ለውጥ ያስከተለው የትኛው ነው?

A. የሐረጉ አወቃቀር
B. የግስ ቦታ መቀያየር
C. የቃሉ አቀማመጥ
D. የሆሄያት ቦታ መቀያየር

83. ቋንቋ ሥርዓት ባለው መንገድ የተሰበሰቡ ትእምርቶች ስብስብ ነው። የሚለውን ባህርይ ለመግለፅ የትኛው ትክክል ነው?

A. መረገ → መገረ
B. ኤሮፕሌን → አውሮፕላን
C. ቀለሰ → ሰቀለ
D. ቴፕሪኮርደር → መቅረፀ ድምፅ

84. የቃል ክፍልን በተመለከተ ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

A. አጠራር
B. መጥራት
C. ጠራ
D. ጥሪ

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 85 እስከ 90 ድረስ ለቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ ምረጫ::

በሕዝብ ፊት ንግግር ማድረግ ለብዙዎቻችን ይከብዳል:: ሰዎችን ማሳመን ካልቻልን ይኼ ሥራ ቢቀርብን ይሻላል:: ልምድም ስለሌለን ይሆናል:: ልምዱም እያለን ተናግረን ለውጤት አንበቃም:: የምንናገረው ሰዎች ሀሳባቸውን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲዘጋጁ ይሆናል:: ግን ይህ ውጤት ሁሌም አይገኝም:: በተለይ የማስተባበር ኃላፊነት ላይ ከሆንን ተናግሮ የማሳመን ብቃት ሊኖረን ይገባል:: ተናግሮ ለማሳመን የሚችል ንግግር መረጃን የያዘ የግፊት ኃይል ያለውና ለተግባር መጣር የሚችል ነው:: የሚከተሉትን ለማድረግህ እርግጠኛ ሁን።

የንግግርህ መጀመሪያ ዜማዊ ቃና ያለውና ከልብ የመነጨ ስሜትህን የሚያሳይ ይሁን:: ከዚያ በቀጥታ ወደ ጉዳይህ ግባ:: አንዳንዴ ስሜታቸውን እንዲያሳዩ በመጋበዝ መጀመር ትችላለህ:: "ኤድስ እያደረሰ ስላለው አልቂት ሰሞኑን ሪፖርት ሲደረግ ራሳችሁን አልያዛችሁም? " አይነት አጠያየቅ:: የሰውነት እንቅስቃሴም ትኩረት ለመያዝ ይጠቅማል:: "አንተ ምን ትላለህ? " በሚያስበል ሀሳብ መጀመር ትችላለህ:: አንራ ለማለት አይደለም:: የአድማጮችህን ትኩረት አግኝ::

ዋናውን ችግር ነጥለህ አውጣው:: የመኪና ማቆሚያ በሰፈርህ እንዲሠራ እየቀሰቀስክ ይሆናል:: መንገድ ላይ ያለጠባቂ ሲንከረፈፉ የሚውሉ ህፃናት መኖራቸውንና በመኪና አደጋ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳይ አሳይ:: ጉዳት እየደረሰባቸው እንደሆነ ከነገርካቸው ሰዎች ይነሳሉ:: ቁጭ ብሎ ሞትን የሚጠብቅ የለም::ወጣቶች በአካባቢህ ስለኤድስ መረጃ የላቸውም:: የፀረ ኤድስ ክበባት ቢቋቋሙና ወጣቶቹ በክበባቱ ቢሰባሰቡ ስለ ኤች አይ . ቪ ኤድስ መረጃ ሊያገኙና ራሳቸውን ሊጠብቁ እንደሚችሉ ንገራቸው:: ሰዎች ከሞት ማምለጥ ይፈልጋሉ:: ለችግሩ የመፍትሔ ሐሳብ ማቅረብ ሲባልም ይኸ ነው::

ወጣቶች በክበባቸው ስለኤድስ ምንነት ካወቁ በኋላ መመካከርና ራሳቸውን መጠበቅ ይጀምራሉ:: በበሽታው የተያዙትን ይረዳሉ:: ስለአካባቢያቸውና ስለራሳቸው ኃላፊነት እንዲሰማቸው የወደፊቱን የህይወት ራዕይ እንዲመለከቱ ያስፈልጋል:: ይህ ሲሆን በኤድስ መጠለፍ እየቀረ ይሄዳል:: ጭንቀትና ስጋት የሌለበት የደስተኞች ሰፈር ይሆናል:: ይኸንን ተናገር:: ጭንቀትና ስጋት የሚፈልግ የለም::

ADDIS ABABA UNIVERSITY

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

ለተግባር እንዲነሱ ጋብዝ። ክበባቱን ለማቋቋም ድጋፍ ያስፈልግ ይሆናል። የክበቡን መሪዎች መምረጥና የገቢ ማግኛ በዓል ማዘጋጀት ያስፈልግ ይሆናል። ዓላማውን ለጋዜጠኞች መንገር ካስፈለገ ለመገናኛ ብዙሃን ጽሁፎችን የመላክ ሥራ ይኖራል። ሥራውን ሁሉም ተከፋፍሎ እንዲይዘው ጠይቅ። ሰዎች መገለልን አይወዱም። ይሳተፋሉ። እና አላማህም እየተሳካ ነው ማለት ይሆናል።

(ህላዌ - ልዩ እትም፤ ቅጽ 1፤ ቁጥር 8፤ ህዳር 1996፤ ገጽ 7)

85. በምንባቡ መሠረት የምንናገርበትን ዓላማ አስመልክቶ ይበልጥ አስተያየት የተሰጠበት አንቀጽ የትኛው ነው?

A. 4ኛው
B. 5ኛው
C. 2ኛው
D. 1ኛው

86. ለምንባቡ ርዕስ ቢፈለግ ይበልጥ ተስማሚ የሚሆነው ርዕሰ ጉዳይ የትኛው ነው?

A. ጥሩ ተናጋሪነት
B. አስተባባሪነት
C. ማሳመን
D. ምን እንፈልጋለን

87. ከምንባቡ ይዘት አኳያ የተተኮረበት የህብረተሰብ ክፍል የትኛው ነው?

A. ወጣቶች
B. አዋቂዎች
C. ሴቶች
D. ልጆች

88. የምንባቡ ሃሣብ ተጠቃልሎ የቀረበበት የፅሁፍ ክፍል የትኛው ነው?

A. መካከለኛ አካባቢ
B. መጀመሪያና መጨረሻው
C. መጨረሻው አካባቢ
D. መጀመሪያው አካባቢ

89. የምንባቡ ፍሬ ነገር አቀራረብ ሲታይ አደረጃጀቱ ምን ዓይነት ነው?

A. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እንደገና ወደ ዝርዝር
B. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እንደገና ወደ አጠቃላይ
C. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ
D. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

90. የምንባቡ ይዘት ሲመረመር የአንቀጾቹ ቅደም ተከተሎች በየትኞቹ ቁልፍ ቃላት የተደራጁ ናቸው?

A. ማስተባበር፣ ትኩረት፣ ራዕይ፣ ችግር፣ መፍትሔ፣ ተግባር
B. ማስተባበር፣ መፍትሔ፣ ችግር፣ ተግባር፣ ራዕይ፣ ትኩረት
C. ማስተባበር፣ ትኩረት፣ ችግር፣ መፍትሔ፣ ራዕይ፣ ተግባር
D. ማስተባበር፣ችግር፣ራዕይ ፣ተግባር፣ መፍትሔ፣ ትኩረት

ሽባ6-3

ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት
የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ
የአማርኛ ቋንቋ ፈተና
ግንቦት 1998 ዓ.ም.

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 **የዚህ ጥራዝ መለያ: 84**
የጥያቄ ብዛት: 90 **የተፈቀደው ጊዜ: 1:30**

<u>መመሪያ</u>:- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረበውን አንቀፅ መሠረት ያደረጉ ናቸው:: አንቀፁን በጥሞና ካነበብክ/ሽ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢውን መልስ ከተሠጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ::

የእድገት አለመስተካከል ችግሮች ስፋት ያላቸውና በርካታ ናቸው:: በትድመ ልደት ወቅት የተከሰቱት ችግሮች በግልጽ ሳይታዩና ሳይታወቁ ከልደት በኃላ ለበርካታ ወራትና አመታት ሊቆዩ ይችላሉ:: በዚህም የተነሳ የድህረ ልደት ችግሮች ተደርገው ይቆጠራሉ:: ለምሳሌ ያህል የአጥንት መጣመም በድህረ ልደት የምግብና የፀሐይ ብርሃን እጥረት የሚያስከትለው ችግር ተደርጐ ይወሰዳል:: ሆኖም የሕክምና መረጃዎች እንደሚገልፀት የአጥንት መጣመም በአብዛኛው የሚታየው ከመወለጃ ጊዜያቸው በፊት በተወለዱ ህፃናት ላይ ሲሆን ይህም በመጨረሻዎቹ የቅድመ ልደት ወራት በማህፀን ውስጥ የሚኖረውን ንጥረ ነገር ካለማግኘት ጋር የተያያዘ እንደሆነ አድርገው ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ የሚጥል ህመምና የአእምሮ ችግር የመሳሰሉት የድህረ ልደት ችግሮች ተደርገው ይወሰዳሉ:: ምክንያቱም አንድ ህፃን እንደተወለደ እነዚህ ችግሮች እንዳለበትና እንደሌለበት ለማረጋገጥ ባለመቻሉ ሲሆን የተጠቀሱት ህመሞች መንስኤ በእርግዝና ወቅት ነፍሰ ጡሯን ለረጅም ጊዜ የቆየ ከፍተኛ ረሃብ ሲገጥማት እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ::

/ፍስሐ፣ 1990፣ 58/

1. የዚህ አንቀፅ መንደርደሪያ ዐነገር የትኛው ነው?

   A. በዚህም የተነሳ የድህረ ልደት ችግሮች ተደርገው ይቆጠራሉ::
   B. ሆኖም የሕክምና መረጃዎች እንደሚገልፀት... እንደሆነ አድርገው ነው::
   C. የእድገት አለመስተካከል ችግሮች ስፋት ያላቸውና በርካታ ናቸው::
   D. በትድመ ልደት ወቅት የተከሰቱት ችግሮች... ሊቆዩ ይችላሉ::

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

2. የአንቀፁ ኃይለ ቃል የሚገኘው የት ላይ ነው?

A. በአንቀፁ መጀመሪያ ላይ
B. በአንቀፁ በስተመነሻና በስተመድረሻ
C. በአንቀፁ መካከል ላይ
D. በአንቀፁ በስተመድረሻ

3. በአንቀፁ ውስጥ ሁለተኛውን ዐ.ነገር ከሦስተኛው ዐ.ነገር ጋር ያጣመረው ሀረግ የትኛው ነው?

A. በቅድመ ልደት
B. ለምሳሌ ያህል
C. በዚህም የተነሳ
D. በአንቀፁ በስተመድረሻ

4. ከላይ የቀረበው አንቀፅ አካሄድ የትኛውን ይመስላል?

A. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር
B. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ
C. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እንደገና ወደ አጠቃላይ
D. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እንደገና ወደ ዝርዝር

5. በአንቀፁ አማካኝነት እንዲተላለፍ የተፈለገው ጉዳይ ምንድን ነው?

A. የእድገት አለመስተካከል ችግሮችና መንስኤያቸው
B. የቅድመ ልደት ችግሮችና ምልክቶቻቸው
C. የድህረ ልደት ችግሮች፣ ምልክቶችና መፍትሄያቸው
D. የቅድመ ልደትና ድህረ ልደት ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው

ADDIS ABABA UNIVERSITY
A.U. LIBRARY
ILS LIBRARY

J27

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 6 እስከ 12 የቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተለውን ሠንጠረዥ መሠረት ያደረጉ ናቸው:: ሠንጠረዡን በጥሞና ካነበብክ/ሽ በኃላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ::

አንድ ድርጅት ለመግዛት ያሰባቸውን የመጻሕፍት ዓይነት፣ብዛትና ዋጋ የያዘ የሠንጠረዥ መግለጫ::

ተ.ቁ.	የመጽሐፉ ስም	የደራሲው ስም	የመጽሐፉ ዓይነት	የታተመበት ዓ.ም.	የገጽ ብዛት	የመጽሐፉ መሸጫ ዋጋ/ብር	የማከፋፈያ ዋጋ ቅናሽ 20%	የአከፋፋይ መሸጫ ዋጋ/ብር	የሚፈለገው ትኧ ብዛት	በትላ ዋጋ/ብር
1	ወላፈን	ምህረት አዲስ	ልቦለድ	1991	516	23.00	4.60	18.40	200	3680
2	የሌሊት ፀሐይ	እስክንድር ምናቡ	ልቦለድ	1991	464	20.50	4.10	16.40	150	2460
3	ሳግ ወይስ ሳቅ	ልዑል ከበደ	ግጥም	1992	89	9.75	1.95	7.80	50	390
4	ራሮትና ሌሎችም አጫጭር ልቦለዶች	መንግሥተአብ ተስፋዬ	ልቦለድ	1992	146	13.50	2.70	10.80	100	1080
5	የኋልዩሽ ገብ	ዶ/ር ምትኩ አስታጥቄ	ታሪክ	1991	360	18.00	3.60	14.40	50	720
6	ኢትዮጵያና የልጅ እያሱ ዘመነ መንግሥት	መገርሣ ዳባ	ታሪክ	1990	254	15.00	3.00	12.00	60	720
7	የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ	ፈለቀ ተድላ	ጠቅላላ ዕውቀት	1989	94	8.00	1.60	6.40	80	512
8	የአማርኛ ባይተዋር ቃላት መፍቻ	አርቅይሁን አብራራው	ጠቅላላ ዕውቀት	1992	75	9.00	1.80	7.20	100	720
9	የምቀኝነት ሥነ ልቦና	ሠረፀብርሃን አምባዬ	ጠቅላላ ዕውቀት	1988	125	7.50	1.50	6.00	70	420
10	አዲሱ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ በኢትዮጵያ	ዶ/ር አልማዝ በለጠ	ጠቅላላ ዕውቀት	1991	230	16.50	3.30	13.20	50	660

ሀ.አ.ፈ...ድ የ1998 ዓ.ም. የአ..አጠ.ሠ..ደ.ት.ም.ማ. የአማርኛ ፈተና

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

6. እንዲገዙ ከታሰቡት ውስጥ ከአከፋፋይ መሸጫ ዋጋ አንፃር የየትኛው መጽሐፍ ዋጋ አነስተኛ ነበር?

A. ሳግ ወይስ ሳቅ
B. የደብዳቤ ኦፃፃፍ መመሪያ
C. የምቀኝነት ሥነልቦና
D. የአማርኛ ባይተዋር ቃላት መፍቻ

7. በ1992 ዓ.ም. ከታተሙት መጻሕፍት መካከል ከገጽ ብዛት አንፃር ዝቅተኛው የማን ነበር?

A. የምህረት አዲስ
B. የዶ/ር ምትኩ አስታጥቄ
C. የልዑል ከበደ
D. የእርቅይሁን አብራራው

8. ከመጻሕፍት ጠቅላላ ዋጋ አንፃር ከ1988-1992 ዓ.ም. ድረስ የታተሙት መጻሕፍት ዓይነቶች ዝርዝር ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ በቅደም ተከተል ሲቀመጥ የትኛው ትክክል ነው?

A. ታሪክ፣ ግጥም፣ ልቦለድ፣ ጠቅላላ ዕውቀት
B. ግጥም፣ ታሪክ፣ ጠቅላላ ዕውቀት፣ ልቦለድ
C. ጠቅላላ ዕውቀት፣ ልቦለድ፣ ታሪክ፣ ግጥም
D. ልቦለድ፣ ግጥም፣ ጠቅላላ ዕውቀት፣ ታሪክ

9. በድርጅቱ እንዲገዙ ከተዘረዘሩት መጻሕፍት መካከል ለጠቅላላ ዕውቀት አገልግሎት የሚውሉት ብዛት በመቶኛ ሲሰላ ምን ያህሉን ይሸፍናሉ?

A. 5.49%
B. 12%
C. 33%
D. 49.45%

10. በድርጅቱ እንዲገዙ ከታሰቡት መካከል ዝቅተኛ ቅጂ የተጠየቀባቸው የመጻሕፍት አይነቶች የትኞቹ ናቸው?

A. ልቦለድ
B. ግጥም
C. ታሪክ
D. ጠቅላላ ዕውቀት

11. በድርጅቱ እንዲገዙ ከታሰቡት የመጻሕፍት አይነቶች መካከል ከፍተኛ ቅጂ የተጠየቀባቸው የትኞቹ ናቸው?

A. ጠቅላላ ዕውቀት
B. ግሥጎም
C. ልባለድ
D. ታሪክ

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

17. "እጅአጠር" በመሆኔ ካሰብኩት ለመድረስ አልቻልኩም። በሚለው ዐንገር ውስጥ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ለተቀመጠው ፊሊጣዊ አባባል ተመሳሳይ ሊሆን የሚችለው ቃል የትኛው ነው?

A. መናጢ
B. ንፉግ
C. ለጋስ
D. ምቀኛ

18. እንኳን አንች ሄደሽ አሳይተሽኝ፣
እንዲያውም ከድሮው መንገደኛ ነኝ። ለሚለው ግጥም አቻ ሊሆን የሚችለው ምሳሌያዊ አባባል የትኛው ነው?

A. አመድ በዱቄት ይስቃል።
B. የወደደና ያበደ አንድነው።
C. ትሻልን ሰድጂ ትብስን አመጣሁ።
D. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛነሽ።

19. ምድር ገዘገዘች ቅጠል ምንጣፏን፣
በጣም ደስ እንዲላት መኖሪያቸው ደን። በሚለው ግጥም ውስጥ ተናጋሪው ሀሳቡን ለማጉላት የተጠቀመበት የዘይቤ አይነት ይትኛው ነው?

A. ሰውኛ
B. ተምሳሌት
C. ተለዋጭ
D. ግነት

20. ንብረት ገዳና ነው የመጣ ከጥንት፣
ትልቁ ትንሹ የሚጓዝበት፣
ደግሞም የሮጠ ሰው የሚቀድምበት። ለሚለው ግጥም አቻ ሊሆን የሚችል ምሳሌያዊ አባባል የትኛው ነው?

A. ፈረስ ያደርሳል እንጅ አይዋጋም።
B. ድር ቢያብር አንበሣ ያስር።
C. ልጅ ቢሮጥ እስከ ጓሮ።
D. ከመጠምጠም መማር ይቅደም።

21. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በተውኔትና በልቦለድ ውስጥ ሊጠቀስ የሚችለው የትኛው ነው?

A. ገበር
B. ተዋናይ
C. ምዕራፍ
D. ገፀ-ባህርይ

ADDIS ABABA UNIVERSITY YES LIBRARY

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

22. በልቦለድ ውስጥ ደራሲው ለተደራሲያን የሚያስተላልፈው መልዕክት ምን ይባላል?

A. ትልም
B. መቼት
C. ታሪክ
D. ጭብጥ

23. የአንድ ልቦለድ ጽሑፍ ታሪክ የማን ታሪክ ነው?

A. የገፀ ባህርያት
B. የደራሲው
C. የተደራሲው
D. የህብረተሰቡ

24. "ሠዶ ማሳደድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ::" ለሚለው ምሳሌያዊ አባባል በተቃራኒው ሊቀርብ የሚችለው ተረትና ምሳሌ የትኛው ነው?

A. ቁጭ ብሎ የሠቀሉትን ቆሞ ማውረድ ያስቸግራል::
B. ሳይቃጠል በቅጠል::
C. እርጥብ ከደረቅ ይነዳል::
D. ሰሚ ያጣ ጆሮ ከጉረቤት ያጣላል::

25. ሰውዬው የእንጨት ሽበት ናቸው:: የተሰመረበት ፈሊጣዊ አባባል ፍቺው ምንድን ነው?

A. ሙሉ ፀጉራቸው የሸበቱ
B. ግብሩ ቀላል ሰው
C. ሀብታቸው ከእንጨት ሽበት ጋር የሚመሳሰል
D. አፋቸው እንዳመጣ የሚናገሩ

26. ቆላ ደጋ መርገጡ እስሩ እንዲጠብቅበት አድርጉታል:: ለተሰመረበት ፈሊጣዊ አባባል ተመሳሳይ ሀሳብ የትኛው ነው?

A. በተለያየ ስፍራ መኖሩ
B. ለሥራ ብሎ ከቆላ ወደ ደጋ መጓዙ
C. መዘላበዱ
D. መዋሸቱ

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 27 እስከ 42 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን በጥሞና ካነበብክ/ሽ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ እንደየአጠያየቁ ባህርይ ተገቢውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ።

27. አጠራጣሪ የሆነ ሀሳብን ለመግለፅ ሲፈለግ ከሚከተሉት የትኛውን መጠቀም ይቻላል?

A. ያም ሆነ ይህ
B. ሊሆን ይችላል
C. በመሆኑም
D. ይሁን እንጅ

28. አድባር ይቀበልህ/ሽ የሚለውን ቃላዊ ንግግር የምንጠቀመው ምን ጊዜ ነው?

A. ሰው በተለያዩ ምክንያቶች የመኖሪያ አካባቢውን ለቆ ወደ ሌላ ስፍራ ሲሄድ
B. የምናውቀው ሰው በጋብቻ ምክንያት ከወላጆቹ ቤት ሲወጣ
C. አንድ ሰው ከእስር ቤት ሲወጣ
D. አንድ ሰው ወደ እስር ቤት ሲገባ

29. አዛውንቶች የልጅ አስተዳደግን በተመለከተ የራሳቸው ዘመን ጥሩ፤ ያሁኑ ደግሞ መጥፎ መሆኑን ለመግለፅ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት ያነጋገር ስልት ከሚከተሉት የትኛው ሊሆን ይችላል?

A. ዋ! እቴ የኛ ጊዜ መቼ እንዲህ ነበር! ባልን መንከባከብ እንጅ ለራሳችን ግድ አልነበረንም!
B. የአሁኑ ጊዜ ጋብቻ ደግሞ ጋብቻ መሆኑ ነው? ሳይጋቡ የሚፋቱ!
C. የዱሮው ልጅ ምኑ ይነሳል! አንድ ጉርሻ ካገኘ በዚያው ያድራል።
D. ልጅስ ዱሮ ቀረ! ዕቃ እንጠልጥለን ሲያይ ሮጦ የሚቀበል! የአሁኑማ...!

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

30. ቀጥሎ በቀረበው ጭውውት የሁለቱ ሰዎች አለመግባባት ተወግዶ ስምምነት ላይ መድረሳቸው የተመለከተው በየትኛው ሀሳብ ነው?

ወ/ሮ አልማዝ - የኔ ልጅ እባክህን ምክሬን ስማኝ፣ ስጦታዬንም ተቀበለኝ።
ባያብል - የእናት ወጉን እንዳደረስ ሰው... መውለድሽን እጠራጠራለሁ! ልጄ ስትይ አታፍሪም!
ወ/ሮ አልማዝ - ማ! አንተ ጉድ! ምን ያሳፍረኛል! በቃ! በቃ ብያለሁ በቃ! በሽታዬን አትቀስቅስብኝ!
ባያብል - መውለድ ብቻውን አይበቃም! ዋናው ማሳደጉ ነው! (በቁጣ)
ወ/ሮ አልማዝ - የአባትህ በደል ቢበዛብኝ፣ ሀብቴን ቀምቶ ቢያባርረኝ ጊዜ እንዳይርብህ ብዬ ትቼህ ሄድኩ። ምን አጠፋሁ ልጄ!
ባያብል - ይህን አላቅም ነበር እማ፣ ተይው ይቅር በቃ!...

A. ይህን አላቅም ነበር ... ይቅር በቃ
B. የኔ ልጅ እባክህን ... ተቀበለኝ
C. መወለድ ብቻውን አይበቃም...
D. ምን አጠፋሁ ልጄ!

31. ከሚከተሉት ዐነገሮች መካከል መፍትሄ አመንጪ ለሆነ ንግግር ምላሌ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

A. እባክህን ተወው! ምን እንዳይመጣ ይለያለት!
B. ይህ ዛሬ ብቻ አይደለም ተደጋግሞ የታዬ ነውና አያስደንቅም።
C. የኛ ነገር አብቅቶለታል! የሚሆነውን ዝም ብሎ መቀበል ነው።
D. ዋናው ነገር በችግሩ አሳሳቢነት ዙሪያ ለመወያየት መነሳታችን ነው።

32. በአንድ ማህበረሰብ ጉጂ ልማዶች የመኖራቸውን ያህል በአርአያነት የሚጠቀሱ ጠቃሚ ልማዶችም አሉ። በሚል የመንደርደሪያ ሀሳብ ንግግር ቢደረግ ጽንሰ ሀሳቡን ለማስፋፋት ጠቃሚው መንገድ የትኛው ነው?

A. በሀተታ መግለጽ
B. በንፅፅር መግለጽ
C. በምክንያትና ውጤት ማብራራት
D. በምሳሌ ማብራራት

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

33. "እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገራችሁ" ለሚል ሰው የሚሰጠው ልማዳዊ ምላሽ የትኛው ነው?

A. እንኳን ተሻገርን
B. እንኳን አብሮ አሸጋገረን
C. ምን አዲስ ነገር ተገኘና
D. ከየትኛው ዘመን

34. አንድን ህመምተኛ ከቤቱ/ከሆስፒታል ጠይቀን ስንወጣ በሽተኛውን ለማፅናናት ከምንጠቀምባቸው ንግግራዊ አባባሎች መካከል የትኛው ትክክል ነው?

A. በቃ! ይገላግልህ
B. እግረ ደረቅ ያድርግልህ
C. የዋለውን አያሳድርብህ
D. በወጣው ይተካልህ

35. "በሱ የደረሰ አይድረስባችሁ ዘመዶቼ! እንዲያው ሰውዬው እሱ ሆኖ ነው እንጂ ሌላ ቢሆን ... ስንትና ስንት ያደርግ ነበር? ወይኔዶ!" የሚለው አባባል አንድምታው ምንድን ነው?

A. ነገሩን ማሳነስ
B. ነገሩን ማለሳለስ
C. ማስታረቅ
D. ማፅናናት

36. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ወይም ሐረጐች መካከል ለቅስቀሳ ንግግር የሚውልን መሠረተ ነባብ የያዘው የትኛው ነው?

A. የኤች አይቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የተገኘባቸው ሰዎች ማድረግ የሚገባቸው ጥንቃቄ::
B. ለጭነትና ለኮርቻ ከብቶች የሚደረግ እንክብካቤ::
C. ከቀንድ ከብቶች የምናገኘው ጥቅም እንዲጨምር ለቀንድ ከብቶች የምናደርገውን እንክብካቤ ማሻሻል አለብን::
D. አህያ የሚሰጠው አገልግሎት ፈረስና በቅሎ ከሚሰጡት አገልግሎት ይበልጣል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY LES LIBRARY

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

37. ከሚከተሉት አባባሎች መካከል ከምሬት ንግግር ጋር ግንኙነት ያለው የትኛው ነው?

A. መቼ ነው ከትከሻዬ የሚወርደው?!
B. አይማረኝ ላልምርህ!
C. ነገሩ ሁሉ እጅ እጅ ይላል::
D. ከእንግዲህስ ይበቃኛል ሩጫዬ እዚህ ድረስ ነው!

38. በሁለት ሰዎች መካከል የሚካሄድ የሀሳብ ፍልሚያ ተግባራዊ የሚደረግበት የንግግር አይነት የትኛው ነው?

A. ጭውውት
B. ውይይት
C. ክርክር
D. አስተያየት

39. ቆይ ብቻ! ነብር አየኝ በል! ዛሬማ ምን ታደርግ! የሚለው አባባል ምንን ያመለክታል?

A. ቁጣን
B. ዛቻን
C. መደነቅን
D. ማሞገስን

40. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል አማራጭ ሀሳብ የያዘው የትኛው ነው?

A. የአንድ ሀገር እድገትና ልማት ከማህበረሰቡ ውጭ አይታሰብም::
B. "የሰው ሀገሩ ምግባሩ" ይባላልና የትም ብሄድ ሠርቼ መኖር እችላለሁ::
C. "እልፍ ሲሉት እልፍ ይሻላል" ነውና ብሰደድ እመርጣለሁ::
D. በሰው ሀገር ደልቶኝ ከምኖር ይልቅ በሀገሬ ከወገኔ ጋር መቸገርን እመርጣለሁ::

41. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል ስለዘገባ አቀራረብ <u>እውነትነት የሌለው</u> የትኛው ይሆናል?

A. ዘገባ በጽሁፍ ሊቀርብ ይችላል::
B. ዘገባ በቃል ሊቀርብ ይችላል::
C. ዘገባ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ሊቀርብ ይችላል::
D. ዘገባ ሲቀርብ የአቅራቢው የግል አስተያየት ሊኖር ይችላል::

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

42. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል <u>በተጠየቃዊ መንገድ</u> የቀረበው ሀሳብ የትኛው ነው?

A. ዕድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች መምረጥም ሆነ መመረጥ ህገ-መንግሥታዊ መብታቸው ነው። ዕፀገነት ዕድሜዋ 21 ዓመት ነው። ይሁንና ደፋር ተናጋሪ አይደለችም። ስለዚህ ዕፀገነት መምረጥም ሆነ መመረጥ አትችልም።

B. በፕላዝማ ስክሪን የሚቀርብ ትምህርት የግል ክትትልን ይጠይቃል። ክትትል ያደረጉ ተማሪዎች ደግሞ ጥሩ እውቀት ሊገበዩ ይችላሉ። ሶፊያ በፕላዝማ የሚቀርበውን ትምህርት በሚገባ እየተከታተለች ነው። ስለሆነም ሶፊያ ጥሩ እውቀት ልትገበይ ትችላለች።

C. የህግ ትምህርት ያላቸው ሰዎች በዳኝነት ሥራ ላይ መሠማራታቸው ዳኝነቱን ፍትሃዊ እንዲሆን ያደርጋል። ሂሩትና ተፈራ የህግ ባለሙያ በመሆናቸው በዳኝነት ሥራ ላይ ተሠማርተዋል። የሂሩት በዳኝነት ሥራ መሰማራት ግን ፍትህን ያዛባል። ምነው ቢሉ "ምን ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ" ነውና ነገሩ።

D. ውበት እንደተመልካቹ ነው። ሄርሜላ እዚህ ግቢ የማትባል ግን አንደበተ ቁጥብ ልጅ ናት። አፍቃሪዋ በሄርሜላ ቁጥብነት እጅጉን ተማርኳል። ይሁንና ቁጥብነት እንደ ውበት መቆጠር የለበትም።

<u>መመሪያ</u>:- ከተራ ቁጥር 43 እስከ 53 ድረስ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሚከተለው ምንባብ መሠረት ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ።

የትናንትን እርካብ በእግራችን ረግጠን መወጣጫውን በእጆቻችን ጨብጠን የትናንት ነገ ላይ ተገኘን። አቅጣጫዋን እንደሳተች ጀልባ ባካኝ ልንሆን አልያም ገበገዘ ቀዛፊ እንደሚያሽቃብጣት ጀልባ ከምኞታችን ባሻገር ያለውን የድካማችንን ፍሬ ልንሰበስብ ስንካሰብ አዲስ ብለን ከጠራነው ዓመት ላይ ዘጠኝ ድፍን ወራቶች ነገሩብን አልያም ነገድንባቸው።

"ግና ከነዚህ የወራት ገጆዎች አንዲቷን የቀናት ሰንበሌጥ ሳር መዘን ግልፋፊዎን በመጣል ፍሬዋን መቁጠር የምንችል ስንቶቻችን እንሆን? ከምርቱ ይልቅ ገለባው እያየለብን እንዲሁ ብቻ በመኖርና ባለመኖር አረንቋ ውስጥ ገብተን የምንባሽርስ? በቸልተኝነትና በዋዛ በፈዛዛ አልያም ስለነገ ባለማሰብ "እኔ ከሞትኩ..." እንዳለችው እንስላ የራሳችንን ምኞትና የተንደላቀቁ ኑሮ ስናሟሙቅ የነገውን ጨቅላ እና ከገሬቤት የሚወጣውን እረፍት ነሺ የረሀብ ሰቆቃዊ ጥሪ ችላ ያልንስ?

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

እናት ምድር ኢትዮጵያችን ጥንተ ተፈጥሮዋ መካን አልነበረም:: ዛሬ ግን መካንነቷ ይፈታተናት ይሟል:: ከምድሯ ልምላሜ የተነሳ የአረንጓዴ ስጋጃ ተምሳሌትነቷ ተዘክሮ ተመስክሮላት ነበር:: የምድሯን እምብርት ሰቅስቆ የሚጋልብ ይመስል የነበረው የአብራኳ ሀብት የሆነውም የአባይ ተፋሰስ፣ "ውልደቴ አቢሲኒያ እድገቴና ሞቴ እስክንድሪያ" ያለ ሆኗል:: ብቻ ሁሉም ነገር "ድንገቴ" ሆኗል:: የዚህ ግርፋት ተጠቂው ደግሞ ታዳጊ ይሻል፤ ረሀብ ቀጠሮ አይሰጥምና::

እስከመቼ በባህር ማዶ እርጥባን መተማመን ይቻላል? ከረሀብ ማስታገሻነቱ ይልቅ የበላይነት ወሬ ማናፈሻና ሀገራዊ ወኔን መስለቢያ ለሆነው እህል እስከመቼ ስናንጋጥጥ ውለን እናድራለን? ሁላችንም በያለንበት መስክ የበኩላችንን መወጣት ችለን፣ "ለወገን ደራሽ ምስጉን ነው!" የሚለውን ብሂል ለማጉላትና ይበል ለሚያሰኝ ተግባር ለመንቀሳቀስ ጊዜው አሁን ነው::

/ዕድሜ፣ ሰኔ 1995፣ ገጽ 19 /

43. ሁለተኛውን አንቀጽ ለመገንባት ከተካተቱት ባለተቃራኒ ሀሳብ ሀረጐች መካከል ተነባቢነት ጐልቶ <u>የማይታይበት</u> የትኛው ነው?

A. ግልፋፊዋን በመጣል ፍሬዋን መቁጠር
B. ከምርቱ ይልቅ ገለባው
C. በቸልተኝነትና በዋዛ ፈዛዛ አሊያም ስለነገ ባለማሰብ
D. እንዲሁ ብቻ በመኖርና ባለመኖር

44. የመጀመሪያውን አንቀጽ ሀሳብ ይዞ ለቀጣዩ በመሸጋገሪያነት መንደርደሪያ የሆነው ሀረግ የትኛው ነው?

A. ዘጠኝ ድፍን ወራቶች
B. ግና ከነዚህ የወራት ጐጂዎች
C. ነጐዱብን ወይም ነጐድንባቸው
D. ግና ከነዚህ

45. በመጀመሪያውና በሁለተኛው አንቀጾች ጐልቶ የሚወጣና የሚያገናኛቸው የማወዳደሪያ ሀሳብ የትኛው ነው?

A. ብክነትና ፍሬያማነት
B. ገለባና ብክነት
C. ትናንትናና ነገ
D. ጊዜና ምርት

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

46. "ዘጠኝ ድፍን ወራት ነጐዱብን ወይም ነጐድንባቸው::" በሚለው አገላለጽ የተሰመረበት ሀረግ ምንን ያመለክታል?

A. በፍጥነት ያለፈውን ታሪክ
B. በሥራ ያለፈውን ጊዜ
C. ተጣብቦ ያመለጠውን ጊዜ
D. በቸልታ የታለፈውን ጊዜ

47. በመጀመሪያው አንቀጽ በይበልጥ የተተኰረበት ዋና ሀሳብ ምንድነው?

A. ጊዜ
B. ብክነት
C. በጊዜው መሥራት
D. ጊዜና ብክነት

48. "... የትናንት ነገ ላይ፣ የነገ ትናንት ላይ ተገኘን::" የሚለው አባባል ስለየትኛው ጊዜ የሚናገር ነው?

A. ስለዘንድሮ
B ስለመጪው
C ስለዛሬ
D. ስለነገ

49. "ስንካለብ" የሚለውን ቃል አገባብ በትክክል የሚገልፀው የትኛው ነው?

A. ስንባክን
B. ስንዋትት
C. ስንባትል
D. ስንሯሯጥ

50. የምንባቡ አንቀጾች አደረጃጀት ሲታይ ወደየትኛው የድርሰት አፃፃፍ ስልት ያመዘነ ሆኖ ይገኛል?

A. ትረካ
B. አወዳዳሪ
C. አስረጅ
D. ሳቢያና ውጤት

51. "ተጠቂው ደግሞ ታዳጊ ይሻል::" ሲል ምን ያመለክታል?

A. የልጆችን ተሳትፎ ግድ ይላል::
B. የሚረከበውን ትውልድ ይጠብቃል::
C. የሚያድነው ይፈልጋል::
D. ታዳጊዎችን ያሳትፋል::

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

52. "እኔ ከሞትኩ..." እና "ውልደቴ አቢሲኒያ... " የተሰኙት አባባሎች የሚዛመዱበት ጉዳይ የትኛው ነው?

A. ሁለቱም ስለጊዜ ይናገራሉ::
B. ለሀገር ጥቅም አለመስጠትን ምሳሌነት ይናገራሉ::
C. በሰውኛ ዘይቤ የቀረቡና ነባራዊውን ሁኔታ የሚያንፀባርቁ ናቸው::
D. ስለብክነትና ቸልተኝነት የሚገልፁ ሀሳቦች ናቸው::

53. ለምንባቡ የበለጠ ተስማሚ የሚሆነው ርዕስ የትኛው ነው?

A. እናት ኢትዮጵያ
B. ከትናንት እንማር
C. ጊዜው አሁን ነው
D. ነገ የእኛ አይደለም

<u>መመሪያ:-</u> ከጥያቄ 54 እስከ 60 ያሉትን ጥያቄዎች ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዐ.ነገሮች መሠረት በማድረግ መልስ/መልሽ::

1. አንድ ድርሰት ቋንቋው በጣም ያማረ ሆኖ በውስጡ ቁም ነገር ላይኖርበት ይችላል::
2. የድርሰት መሠረት የሀሳብ ፍሬ ነገር ነው::
3. ማንኛውም ድርሰት በውስጡ ፍሬ ነገር ከሌለው ዋጋው ጐደሎ ይሆናል::
4. የቃላት አሰካክ፣ የቋንቋው አጠቃቀም፣ በጠቅላላው የጽሑፉ አቀራረብ ውብ ሆኖ ሳለ፤ ሀሳቡ ፍሬ የሌለው ባዶ ሆኖ ሲገኝ ድርሰቱን ጐደሎ ያደርገዋል::

54. ከዚህ በላይ ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዐ.ነገሮች በማስተካከል አንቀጽ ሲመሰረት ትክክለኛው የዐ.ነገሩ ቅደም ተከተል የትኛው ነው?

A. 4፣ 3፣ 2፣ 1
B. 2፣ 4፣ 3፣ 1
C. 2፣ 3፣ 1፣ 4
D. 4፣ 2፣ 1፣ 3

55. የአንቀፁ ጎይለ ቃል ሊሆን የሚችለው ዐ.ነገር በተራ ቁጥር ስንት የተለገፀው ነው?

A. 1
B. 2
C. 3
D. 4

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

56. የአንቀፁ ቅርጽ የትኛውን ሥዕላዊ መግለጫ ይመስላል?

A. 

B.

C. 

D.

57. ከሚከተሉት ውስጥ ስለዘገባ አዘገጃጀት <u>ትክክል ያልሆነው</u> የትኛው ነው?

A. ዘገባውን ከመጻፍ በፊት አስተዋጽኦ መንደፍ አያስፈልግም::
B. በዘገባው የመጀመሪያ ገጽ በመሀል ላይ የዘገባውን ርዕስ መፃፍ
C. የዘገባው ርዕስ በተፃፈበት ገጽ የቀኝ ግርጌ ላይ የተፃፈበትን ቀንና ቦታ መፃፍ
D. የዘገባው ርዕስ በተፃፈበት ገፅ በርዕሱ ግርጌ የዘጋቢውን ስም መፃፍ

58. "እንደዴሊ" በሚለው አነጣጣሪ ሀረግ ሊመሠረት የሚችለው ዐ.ነገር የትኛው ነው?

A. ልጁ እንደዴሊ ፈጣን በመሆኑ የማራቶን ተሸላሚ ሆነ::
B. የት/ቤት ግንባታው ሥራ እንደዴሊ በመጓዙ በ1998 ለግልጋሎት አልዋለም::
C. ልጁ እንደዴሊ ድንጋይ ልብሱና ትራሱ በመሆኑ ቅዝቃዜ አይሰማውም::
D. ልጁ እንደዴሊ ታማኝ በመሆኑ በሰው ዘንድ ተቀባይነት አለው::

59. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል በአወዳዳሪ አገላለፅ የቀረበው የትኛው ነው?

A. አህያ በዱላ እየተነረተም ቢሆን አገልግሎቱን አያቋርጥም::
B. ግመልና አህያ ለመጓጓዣ አገልግሎት የሚውሉ አንስሳት ናቸው::
C. ግመል ለመጓጓዣ ከመዋሉም በላይ ወተቱም ጠቀሜታ ይሰጣል::
D. ግመል የበረሃ ባቡር የመሆኑን ያህል አህያም የገጠር ንጉሥ ነው::

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

60. የአንድ ሰው ንግግር እንዳለ መወሰዱን ለማመልከት ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ትክክል ነው?

A. "'የዋሁ" ልጅ መጣ:: አለ::
B. የዋሁ ልጅ መጣ?
C. "እረፍ! ዝምበል!" አለ::
D. እረፍ! ዝምበል! አለ::

<u>መመሪያ</u>:- ከተራ ቁጥር 61 እስከ 71 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: በአጠያየቁ መሠረት ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጭ/ምረጥ::

61. "የልጅ አስተዋይ"ና "አስተዋይ ልጅ" በተሰኙት ሀረጎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

A. የመጀመሪያው ስማዊ ሀረግ ሲሆን ሁለተኛው ቅጽላዊ ሀረግ መሆኑ
B. የመጀመሪያው ግሣዊ ሀረግ ሲሆን ሁለተኛው ቅጽላዊ ሀረግ መሆኑ
C. የመጀመሪያው ቅጽላዊ ሀረግ ሲሆን ሁለተኛው ስማዊ ሀረግ መሆኑ
D. የመጀመሪያው መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን ሁለተኛው ግሣዊ ሀረግ መሆኑ

62. "ይነሳል" የሚለው ቃል "ይወሳል" የሚል ፍቺ የሚኖረው በየትኛው ዐንገር ውሰጥ ነው?

A. ልጁ ለፖስፖርት ማውጫ ፎቶ ይነሳል::
B. ሰዎቹ በልተው ከጨረሱ ግሮሰቡ ይነሳል::
C. ፊልጁ የጠላውን ሰው ሲያነሱ ፊት ይነሳል::
D. ደግ የሰራ ሰው ምንጊዜም ስሙ ይነሳል::

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 8.4

63. ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት ፈታኞችን ወደ መፈተኛ ጣቢያዎች ልኳል። በሚለው ዐነገር ውስጥ የተለመረበትን ተሳቢ፣ የዐነገሩ ባለቤት በማድረግ እንደገና ሲፃፍ የትኛው ትክክል ይሆናል?

A. ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት ወደመፈተኛ ጣቢያዎች ፈታኞችን ልኳል።
B. ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት ፈታኞች ወደየመፈተኛ ጣቢያዎች ተላኩ።
C. ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት ለፈታኞች የውሎ አበል ክፍያ ፈፀመ።
D. ፈታኝ መምህራን ከአዲስ አበባ ወደየመፈተኛ ጣቢያቸው ተንቀሳቀሱ።

64. ከሚከተሉት አባባሎች መካከል ናፍቆትን ለመግለጽ የምንጠቀምበት የትኛው ነው?

A. በአይነሥጋ
B. በአይነ ቁራኛ
C. በአይኑ ላይ ዞረ
D. በአይኔ መጣህ

65. ከሚከተሉት የትውስት ቃላት መካከል የድምፀ-ልሳናት ቅንጅት ለውጥ የተደረገበት የትኛው ነው?

A. ቆንስላ
B. ኮት
C. ቴሌቪዥን
D. ደሞክራሲ

66. "ቀይ" ከሚለው ቃል ሊመሠረት የሚችለው ቅጽላዊ ሀረግ የትኛው ነው?

A. ቀይ ሽሚዝ
B. ቀይ ቲማቲም
C. ብስል ቀይ
D. ቀይ ጠርሙስ

67. ከሚከተሉት ዐነገሮች መካከል ሰዋሰዋዊ ስህተት የሚታይበት የትኛው ነው?

A. የለማ ወጣቶች የከንፈር ወዳጅነት "አንድ ለአንድ" በሚል መርህ የተገደበ አይደለም።
B. ሙሽራ ማለት የአንድ ቀን ንጉሥ እንደማለት ይቆጠራል።
C. "ማግለልና መድልዎ ይቁም" የሚለው አባባል ምንን ያመለክታል?
D. "ሲሆን ባልዘፈንሽ፣ ከዘፈንሽም ባላፈርሽ" የሚባሉትን ምሳሌ አታውቂምን?

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

68. ግለሰብን ወይም ድርጅትን ወክሎ በፍርድ ቤት የሚከራከር ግለሰብ ምን ተብሎ ይጠራል?

A. ተሟጋች
B. አቃቤ-ህግ
C. ጠበቃ
D. ወንጀል መርማሪ

69. ከሚከተሉት ውስጥ ለውስብስብ ዐ.ነገር ምላሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. የአማርኛ ምላሌያዊ ንግግሮች በዋቢነት ይጠቀሳሉ::
B. ሀገራችንን ከድህነት አረንቋ ማውጣት አያዳግትም::
C. የዝምታን ወርቅነት እንደክሶ እያንገሸገሻት ትጨልጣለች::
D. ህዝቦች በሥልጣኔ በመገስገሳቸው ከችግር ተላቀዋል::

70. በሠለጠነው ዓለም የአንድ ዓሣድ ድርጅት የሂሳብ ኃላፊ የንግድ ድርጅቱን ሂሳብ በአግባቡ እንደሚመራው ሁሉ፤ _____ :: የሚለውን ጅምር ዐ.ነገር ለሚሟላት የትኛው አማራጭ የተሻለ ነው?

A. የራሳችንን ገቢና ወጪ መመርመር እንደሁኔታው የሚታይ ይሆናል::
B. በየግላችን የየራሳችንን ገቢና ወጪ የሂሳብ ጉዳይ በአግባቡ እንድንመራው የግድ ነው::
C. የራሳችንን የገቢና ወጪ ሂሳብ በሥርኣት ለመምራት ማሰብ የማይታሰብ ነው::
D. የራስን ለመምራት ከቶ የማይቻልበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል::

71. የኤድስ ወረርሽኝ በሀገር ልማት ላይ እያደረሰ ስላለው አሉታዊ ተፅዕኖ፤ በአማርኛ ቋንቋ ተፅፎ የቀረበን ሀሳብ የመሻኮንገር ሕዝቦች በራሳቸው ቋንቋ ሀሳቡን አንስተው ሲወያዩ የሰማ ሰው ከቋንቋ ባህሪያት ውስጥ ስለየትኛው እንዲያስብ ይገደዳል?

A. የቋንቋን መወለድ፣ ማደግ፣ መሞት
B. የቋንቋን መወራረስ
C. የቋንቋን ሥርዓታዊነት
D. የቋንቋን ምሉእነት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 72 እስከ 84 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ጥያቄዎቹን በጥሞና ካነበብክ/ሽ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ እንደአጠያየቁ ባህሪይ ተገቢውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ::

72. ኤድስ ከማይተላለፍባቸው መንገዶች መካከል በጋራ መብላት፣ በአንድ ላይ መማር ወይም መጫወት፣ _____ :: ጅምሩን ለማሟላት የትኛው የተሻለ ነው?

A. ባልተቀቀለ መርፌና ምላጭ መጠቀም የመሳሰሉት ይገኙበታል
B. በአንድ አለመወሰንና ልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት ማካሄድ የመሳሰሉት ይገኙበታል
C. ራስን ከበሽተኛው ማግለልና በአንድ የመመገቢያ ዕቃ አለመጠቀም የመሳሰሉት ይገኙበታል
D. ጉን ለጉን መቀመጥ፣ እጅ መጨባበጥ፣ ቡና አብሮ መጠጣት የመሳሰሉት ይገኙበታል

73. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል በትክክለኛው የቃላት ምርጫ የተገነባው ዐ.ነገር የትኛው ነው?

A. የበልግ ዝናብ ስላልጣለ ገበሬዎቹ እሮሮን ተዳረጉ::
B. የበልግ ዝናብ ስላልጣለ ገበሬዎቹ ለችግር ተዳረጉ::
C. የበልግ ዝናብ ስላልጣለ ገበሬዎቹ ብድር ተዳረጉ::
D. የበልግ ዝናብ ስላልጣለ ገበሬዎቹ መከራቸውን ተዳረጉ::

74. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል ትክክለኛው ዐ.ነገር የትኛው ነው?

A. የአለቃውን ይሉኝታ ሳያገኝ ከሥራው በመቅረቱ ማስጠንቀቂያ ደረሰው::
B. የአለቃውን ይሰሙላ ሳያገኝ ከሥራው በመቅረቱ ማስጠንቀቂያ ደረሰው::
C. የአለቃውን ይሁንታ ሳያገኝ ከሥራው በመቅረቱ ማስጠንቀቂያ ደረሰው::
D. የአለቃውን ቸርነት ሳያገኝ ከሥራው በመቅረቱ ማስጠንቀቂያ ደረሰው::

75. ጐፈሬው ለሚዶ ታማረልኝ ለኔ፣
ጥርሱ ለውቅራት ታማረልኝ ለእኔ፣
ዓይኑ ለቀጭን ኩል ታማረልኝ ለእኔ፣
ትከሻው ለኩታ ታማረልኝ ለእኔ፣
አጥንቱን አልበላው ውሻ አይደለሁ እኔ። ለሚለው ተመሳሳይ ሀሳብ የያዘው ዐ.ነገር የትኛው ነው?

A. ፀጉሩ፣ ጥርሱ፣ አይኑና ትከሻው ካማረ አጥንቱ ቀጫጫ ቢሆንም ግድ የለኝም።
B. አይኑ፣ ጥርሱ፣ ፀጉሩ... ካማረ ቁመናው ባያምርም እወደዋለሁ።
C. የእኔ ጉዳይ የእርሱ ውበት መገለጫ ከሆኑት አይኑና ጥርሱ... እንጅ ከዘር ሀረጉ አይደለም።
D. ሰውን የማፈቅረው በዘር ሀረጉ እንጅ በእርሱ አይን፣ ጥርስና ፀጉር አይደለም።

76. ገፈታትረው ገደል የከተቱኝን ሽማግሌዎች እንዳየኋቸው ቂም ያረገዘው ልቤ ሊበቀላቸው ቋመጠ። _____ ባህሉ እንጂ ሰዎቹ ተፈጥሮአዊ ጭካኔ እንደሌላቸው በትምህርት የተገራው በሳሉ አእምሮዬ ሹክ አለኝ።

በባዶ ቦታው ውስጥ መግባት ያለበት አጣማሪ ሀረግ የትኛው ነው?

A. ስለሆነም
B. ዳሩ ግን
C. ስለዚህም
D. በጣም ግን

77. ድርሰት ማለት የታሪክና የተውኔት ፀሐፊዎች፣ ባለቅኔዎች፣ ፈላስፋዎች፣ ተማሪዎች... ሥርኣት ባለው መንገድ የሚጽፉትን ሀሳብ በቋንቋ የመግለጫ ጥበብ ሲሆን፣ ኢልቦለድ ድርሰት በሀቅ ላይ የተመሠረተና እውነትነቱ በመረጃ ሊረጋገጥ የሚችልን ጉዳይ የያዘ ጽሁፍ ነው። ልቦለድ ድርሰት ደግሞ ከደራሲው ምናባዊ አተያይ የሚመነጭን ይዘት ያካተተ፣ ኩሸትና የቋንቋ ውበት ጐልተው የሚታዩበት የፈጠራ ጽሁፍ ነው።

ይህ አጭር አንቀፅ የቀረበበት የድርሰት አይነት ከየትኛው ይመደባል?

A. ገላጭ ድርሰት
B. ተራኪ
C. አመዛዛኝ
D. ሥዕላዊ

78. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል ስለ አንቀፅ ትክክለኛ ሀሳብ <u>ያልያዘው</u> ዐ.ነገር የትኛው ነው?

A. አንቀጽ ለአንድ ጽሁፍ ውበት ለመስጠት ሲባል የሚገ-ረድና የራሱ ተጠየቃዊ የሀሳብ ፍሰት ያለው ነው።
B. የአንቀጽ መሪ ዐ.ነገር የአንቀፁን አውራ ነጥብ የሚይዝና በሱ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ዝርዝር ዐ.ነገሮችን ያስለፈ ማለት ነው።
C. አንቀጽ አንድን ሀሳብ ከሚያብራሩ፣ ከሚተርኩ፣ ከሚገልፁ... ነገሮች የተገነባ ነው።
D. አንቀጽ የራሱ የሆነ አንድነትና ጥምረት ያለው የጽሁፍ አነስተኛ ክፍል ነው።

79. መሬት ሁሉን አይነት ሀብት ትሰጣለች፤ በመጽሐፍ ውስጥም እንዲሁ የጥበብ ሁሉ አይነት ተፅፎ ተቀምጧል፤ ግን የመሬት ሀብትም ሆነ በመጽሐፍ ያለ ጥበብ ካልደከመበት አይገኝም። የሚለው ጽሑፍ የተስፋፋበት ስልት የትኛው ነው?

A. ምክንያትና ውጤት
B. ምሳሌ
C. ንፅፅር
D. ሀተታ

80. በተረጋጉና በበለፀጉ ሀገሮች የምናያቸው ትላልቅ ተቋማት ለሚያልፉ ግለሰቦች ጥቅም ሳይሆን፤ ለማያልፈው ለሀገራቸው ጥቅም ይሠራሉ። ግለሰቦችን ለማኖር ሲሉ ምንም አይነት ሥልጣን፣ ሀብትና ክበሬታ ቢኖራቸው ጥፋት ከፈፀሙ ግለሰቦችን ለሕግ አሳልፈው ይሰጣሉ። በዚህ ላይ ቅልጥፍናና ሌሎች የአመራር ቅመሞችን እየጨመሩ ተቋሞቹ በየጊዜው ሳይፈርሱ ስራቸውን ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋሉ። ይህ ደግሞ የዘመናዊና የዲሞክራሲያዊ አሠራር መገለጫ ነው። ይህ አንቀፅ የተስፋፋበት መንገድ የትኛው ነው?

A. ሀተታ
B. ምሳሌ
C. ንፅፅር
D. ብያኔ

81. ሽቶዋ ያውዳል። ጡቶቿ ጠላት ላይ የተደገኑ ሮኬቶች ይመስላሉ። ጥቁር ሹራብ ለብሳለች። የልብ ቅርጽ ያለው ያንገት ጌጧ ከጡቶቿ መሀል ይታያል። ቶሎ ብሎ ዓይኑን ከጡቶቿ ላይ ነቀለ። ፈገግ አለች። ትኩስ የተሸለቀቀ በቆሎ እሸት የሚመስሉትን ጥርሶቹን አሳያትና 'አምን' አላት። ይህ ጽሑፍ የቀረበበት የድርሰት አይነት ከየትኛው ይመደባል?

A. አመዛዛኝ
B. ተራኪ
C. አሰረጅ
D. ሥዕላዊ

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

82. "ለጋሷ" እህቴ መጣች:: በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የገባው ትዕምርተ ጥቅስ ግልጋሎቱ ምንድን ነው?

A. የአንድ ሰው ንግግር እንዳለ መወሰዱን ማመልከት
B. እህቱ ለጋስ ሳትሆን ንፉግ መሆኗን ማመልከት
C. የእህቱ ለጋስነት የበዛ መሆኑን ማመልከት
D. ሀሳቡ ከአንድ ጽሑፍ ላይ የተወሰደ መሆኑን ማመልከት

83. አንድ ቋንቋ ተናጋሪውን የሚያግባባ በቂ መድበለ ቃላት ቢኖረውም፣ ምሉዕነት የሌለው ሊሆን ይችላል:: የሚለው ሀሳብ በሌላ መንገድ ሲገለጽ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ይስማማዋል?

A. ቋንቋው የቋንቋውን ተናጋሪዎች ሀሳብ ለሃሳብ ቢያለዋውጥም እንኳን ባህሉ ወይም አካባቢው ያላወቀውን ወይም ያልደረሰበትን በመግለፁ በኩል የተሟላ ላይሆን ይችላል::
B. ቋንቋው የታችኛውን የህብረተሰብ ክፍሎች ቢያግባባም እንኳን የላይኛውን የህብረተሰብ ክፍል የማግለል አቅም የለውም::
C. ቋንቋው በመዝገበ ቃላት የሠፈረ ቃል ቢኖረውም እንኳን መደበኛ የሆነ ቋንቋ ሥርዓትን ያልተከተለ ነው::
D. ቋንቋው ገና በማደግ ላይ ያለ በመሆኑ የአካባቢውን ሕዝብ ፍላጐትና ምኞት የመግለፅ አቅም ላይኖረው ይችላል::

84. በዘፈቀደ የተፈጠሩ ትዕምርቶች ለተፈላጊው የመግባባት አገልግሎት ይውሉ ዘንድ ህብረተሰቡ _____ ተቀብሎ የሚጠቀምበት የቃላት አሰካክና የዐ.ነገር አመሠራረት አለ:: በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ በባዶ ቦታ ሊገባ የሚችለው ቃል የትኛው ነው?

A. በምንቸገረኝ
B. በይሁን
C. በይገባኛል
D. በይስሙላ

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 85 እስከ 90 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ በግጥሙ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ::

የድንቁርና ሌት ጨለማ አለፈ፣
የማስተዋል ንጋት ብርሃን ተነጠፈ::
ድካምና ሙያ እውቀትና ጥበብ፣
ወጣ እንደጨረቃ ተዘራ እንደኮከብ::
ካራቱ ማእዘን እየለየ ቦታ፣
በምስራቅ በምዕራብ ተገኘ ብልጭታ::
ደመናውን ቀዶ ማስተዋል ፈለቀ፣
ትምህርት ተፋፋመ ተስፋፋ ደመቀ::

/ከበደ ሚካኤል፣ የቅኔ ውበት፣ 1994/

85. ከድንቁርና አንባር በአጥቂነት የተገለፁት ቃላት የትኞቹ ናቸው?

A. ድካም፣ ሙያ፣ ማስተዋል፣ ትምህርት
B. ማስተዋል፣ ብርሃን፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት
C. ሌት፣ ጨለማ፣ ድካም፣ ደመና
D. ማስተዋል፣ ብርሃን፣ ዕውቀት፣ ጥበብ

86. የትምህርትን መፋፋምና መስፋፋት ለመግለጽ በቅርባቸው የአድራጊ ዋስ ሆነው የቀረቡት ቃላት የትኞቹ ናቸው?

A. ማስተዋል፣ መብራት፣ መፋፋምና መስፋፋት
B. ማወቅ፣ መዝራት፣ መገኘት፣ መቅደድ
C. መውጣት፣ መፍለቅ፣ ማለፍ፣ መድመቅ
D. መውጣት፣ መዝራት፣ ዕውቀት፣ ጥበብ

87. ደመናውን እንደቀደደ የተገለፀው ነገር በሌላኛው ስንኝ የተከሰተው በምን መልኩ ነው?

A. እንደንጋት ብርሃን
B. እንደሚፈልቅ ነገር
C. እንደሚፋፋምና እንደሚስፋፋ ነገር
D. እንደሚወጣና እንደሚዘራ ነገር

የትምህርት ዓይነት መለያ: 01 የዚህ ጥራዝ መለያ: 84

88. ግጥሙ የቀረበው በየትኛው የተለመደ የምጣኔ አይነት ነው?

A. በወል ቤት
B. በሰንጉመገን ቤት
C. በቡሄ በለ ቤት
D. በቅኔ ቤት

89. በግጥሙ ውስጥ ድንቁርና የተመሰለባቸውን ቃላት የያዘው አማራጭ የትኛው ነው?

A. ንጋት፣ ብርሃንና ጥበብ
B. ጨረቃ፣ ከዋክብትና ብልጭታ
C. ሌት፣ ጨለማና ደመና
D. ድካም፣ ሌትና ጨለማ

90. ከየስንኞቹ የመነሻ ሀረጉች ውስጥ ረጅም ሊባል የሚችለው ቃል ስንት ሆሄ ይዞ ይገኛል?

A. 5
B. 6
C. 4
D. 8

አባሪ 4

በ1996 ዓ.ም ለዘጠነኛ ክፍል ተሻሽሎ የቀረበው የመርሐትምህርት ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች

የመጀመሪያው የትምህርት ክፍለ - ዓመት

የትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት
ሰዋስው	ሳይሳዊ የሆኑ የቋንቋ መሠረተሐሳቦችን መሠረት በማድረግ ስለቋንቋ ምንነትና አጀማመር ያስረዳሉ።	1. የቋንቋ መሠረተሐሳቦች
	- በአማርኛ ቃላት ውስጥ የጥብቀት ባህርይን ይዘረዝራሉ። - መነሻ ቅጥያዎችን ከነባ ምዕላዶች ውስጥ ለይተው ያመለክታሉ። - መነሻ ቅጥያዎችን በነባ ምዕላዶች ላይ በመጨመር የትርጉም ለውጥ ማስከተላቸውን ይገልፃሉ። - መድረሻ ቅጥያዎችን ከነባ ምዕላዶች ውስጥ ለይተው ያመለክታሉ። - በነባ ምዕላዶች ላይ መድረሻ ቅጥያዎችን በመጨመር የትርጉም ለውጥ ማስከተላቸውን ያመለክታሉ። - የቃላትን ቅርጽ በመደብ፣ በፆታ በቁጥር ለይተው ይናገራሉ።	2. የሚጠበቁና የሚላሉ ድምፆች 3. ቅጥያዎችን መለየት 3.1. የመነሻ ቅጥያዎች 3.2. የመድረሻ ቅጥያዎች 3.3. የቃላትን ቅርጽ በመደብ፣ በፆታ፣ በቁጥር መለየት
	- የአማርኛን የቃላት ክፍሎች ለይተው ይዘረዝራሉ።	4. ቃል፣ ሐረግና ዐ.ነገር 4.1. የአማርኛ ቃላት ክፍሎች
	- የሀረግ መሠረቱ ቃል መሆኑን ተረድተው የስማዊ እና የግሳዊ ሀረጎችን ምሳሌ ያቀርባሉ። - ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ለይተው ያስረዳሉ። - ከተራ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ስማዊና ግሳዊ ሀረጐችን ለይተው ያመለክታሉ። - ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ።	4.2. የሀረግ ዓይነቶች 4.3. ተራ እና ውስብስብ ዐ.ነገሮች 5. እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

የትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት
ንግግር ዕህፈት	- አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል ይገልፃሉ። - ያንድን ንግግር ወይም ጽሁፍ ሀሳብ በራሳቸው አባባል ያቀርባሉ።	6. አንድን ሃሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ
ዕህፈት	- ሥርዓተነጥብ የሌለውን ዕሁፍ በተማሩዋቸው ሥርዓተነጥቦች አሟልተው ይፅፋሉ። - የነጠላ ሠረዝና ትዕምርተ-ጥቅስን ተጨማሪ አገልግሎት በመረዳት ምሣሌ የሚሆኑ አረፍተ ነገሮችን በዕሁፍ ያቀርባሉ።	7. ሥርዓተነጥቦች - ነጠላ ሰረዝ - ትዕምርተ ጥቅስ
ሥነ - ልሳን	- መሸጋገሪያ ቃላትንና ሐረጎችን ከእነተግባራቸው ለይተው ይዘረዝራሉ። - በተለያዩ ዕሁፎች ውስጥ ያሉ መሸጋገሪያ ቃላትንና ሐረጎችን ለይተው ተግባራቸውን ይገልፃሉ። - ገላጮችን ለይተው ያወጣሉ። - የስምና የግስ ገላጮችን ለይተው ለማመልከት የሚጠቅሟቸውን ሁኔታዎች ያመለክታሉ።	8. መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጎች 9. ገላጮች /የስም እና የግስ/
ማዳመጥ	- የአንድን ንግግር ዋናና ዝርዝር ሀሳቦች ለይተው ይገልፃሉ። - በማዳመጥ ወቅት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ይዘረዝራሉ።	10. ያዳመጡትን ንግግር ዋናና ዝርዝር ሀሳብ መለየት
	- አንድን ንግግር አዳምጠው የማጠቃለያ ሀሳብ ይሰጣሉ።	11. ለአንድ ንግግር የማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት
ንግግር	ዝግጅት አድርገውና በተገቢዎቹ የንግግር አቀራረቦች ተጠቅመው ንግግር ያደርጋሉ።	12. በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ
ማዳመጥና ንባብ ማዳመጥና ንባብ	- ከሚያነቧቸው ዕሁፎችና ከሚያዳምጧቸው ወይይቶች ውስጥ መንስኤና ውጤት የሆኑትን ሀሳቦች ለይተው ይገልፃሉ። - በመንስኤና ውጤት የተገናኙ ሃሳቦችን በጽሁፍና በንግግር ይገልፃሉ። -መረጃዎችን በማሰባሰብ ውሳኔ ሃሳብ ላይ ይደርሳሉ። - ሁኔታዎችን ተመልክተው ማስረጃ እያቀረቡ በእርግጠኝነት ነው እያሉ ይደመድማሉ። - ሁኔታዎችን ተመልክተው ይሆናል እያሉ ይደመድማሉ /መላ ይመታሉ/።	13. ተጠየቃዊ አሰተሳሰብ 13.1. የመንስኤና ውጤት ግንኙትና ልዩነት። 13.2 ውሳኔ ሃሳብ ላይ መድረስ 13.2.1 በእርግጠኝነት "ነው" እያሉ መደምደም 13.2.2 ሁኔታዎችን ተመልክቶ "ይሆናል" እያሉ መደምደም

የትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት
ማዳመጥና መናገር	- ሥርዓትን ጠብቀው ውይይት ያደርጋሉ።	14. ውይይት
ፅህፈት	- ቃለ-ጉባኤ ይይዛሉ። - አንቀፆችን በተለያዩ ስልቶች አደራጅተው ይፅፋሉ። - በድርጊት፣ በጊዜና በቦታ ቅደምተከተል የተደራጁ የትረካ አንቀፆች ይፅፋሉ። - በመንስኤና ውጤት የተደራጁ አንቀፆችን ይፅፋሉ።	15. ቃለ-ጉባኤ 16. አንቀፆችን በተለያዩ ስልቶች አደራጅቶ መፃፍ 16.1. በትረካ ስልት 16.2. በመንስኤና ውጤት ዝምድና
ሰዋስው	-ለቃላት እና ለሐረጎች ተመሳሳይ እና ተቃራኒያቸውን ይሰጣሉ።	17. የቃላት እና የሐረጎች ተመሳሳይና ተቃራኒ
ንባብና ፅህፈት	- የንባብ ፍጥነታቸውን እንደንባባቸው ዓላማና እንደፅሁፉ ይዘት የሚወሰን መሆኑን ይገልፃሉ። - የሚያነቡትን ፅሁፍ ቀጣይ ይዘት ገምተው ማስረጃ እያቀረቡ ይገልፃሉ። - ያነበቡትን ፅሁፍ አስተዋፅኦ አሟልተው ያቀርባሉ። - ያነበቡትን ፅሁፍ ዋና ዋና ሀሳቦች የያዘ ማጠቃለያ ይፅፋሉ። - በግርፍ ንባብ የአንድን ፅሁፍ አጠቃላይ ሀሳብ ይገልፃሉ።	18.አንብቦ መረዳትን በተለያየ መንገድ መግለጽ። 19.የግርፍ ንባብ።

ሁለተኛው የትምህርት ክፍለ - ዓመት

የትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት
ንባብ፣ ፅህፈትና ንግግር	- ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ተከትለው የተባሉትን ያከናውናሉ። - የቀላል መሣሪያዎችን አሠራርና አጠቃቀም ይገልፃሉ። - በቤተ መጻሕፍት ይገለገላሉ።	20. ልዩ ልዩ መመሪያዎች 21. የቤተ-መጻሕፍት አጠቃቀም
ንባብ	- በዐውደ-ጥበብ ይገለገላሉ። - በኢንዴክስ ይገለገላሉ። - ከልዩ ልዩ መግለጫዎችን የሚገኙትን የመረጃ ሃሳብ ይገልፃሉ።	22. የመረጃዎች አጠቃቀም 2.2.1. ዐውደ ጥበብ 2.2.2. ኢንዴክስ እና አጠቃቀሙ 23. ከልዩ ልዩ ማግለጫዎች የመረጃ ሃሳብ ማግኘት
ፅህፈት	- ተራኪና ስዕላዊ ድርሰቶችን ይፅፋሉ።	24. ድርሰት 3. ተራኪና ስዕላዊ
ማዳመጥና ጽሕፈት	- ከሚያዳምጡትና ከሚያነቡት ማስታወሻ ይይዛሉ። - የዕለት ገጠመኛቸውን በዐውደ-ዕለት ይመዘግባሉ።	25. ማስታወሻ መያዝ
ጽህፈት	- የሥራ ደብዳቤ ይፅፋሉ።	26. የሥራ ደብዳቤ
ንግግርና ጽህፈት	- መግቢያ ሀተታና መደምደሚያ ያለው ሪፖርት/ዘገባ በቃልና በፅሁፍ ያቀርባሉ። - የአንድን ፅሁፍ ሃሳብ ያሳጥራሉ። - አንድን ፅሁፍ ማብራሪያዎችና ምሣሌዎችን አክለው አስፋፍተው ይፅፋሉ።	27. ዘገባ ማቅረብ 28. ማሳጠርና ማስፋፋት
	- የራሳቸውንና የሌላን ሰው የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ።	29. ግለ ታሪክ
ስነ-ጽሁፍ	- የስነ-ጽሁፍ ዘርፎችን (የፈጠራ) ለይተው ይገልፃሉ። - የአገራችንን ታዋቂና ቀዳሚ የስነ-ጽሁፍ ሰዎችና ስራዎቻቸውን ይጠራሉ።	30. የፈጠራ ጽሑፍ (ስነ-ቃል ፣ ግጥም፣ ልቦለድ ድራማ)
	- የልቦለድን ዘሮች በመረዳት፣ እነማን እንደሆኑ ያመለክታሉ - አጭር ልቦለድ አንብበው ስለ አለባውያን በተለይም ስለ ታሪኩና ገፀ-ባህርያቱ ያስረዳሉ።	31. የልቦለድ አለባውያን እና ዘዴዎች (በተለይ ታሪክ እና ገፀ-ባህርያት)

የትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት
	- ስለአነበቡት ወይም ስለተመለከቱት ድራማ (ተውኔት) ታሪክና ገፀ-ባህርያት ይናገራሉ።	32. ድራማ (ታሪክና ገፀ-ባህርያቱ)
	- ግጥም ይገጥማሉ። - የተወሰኑ የግጥም አይነቶችን ከምጣኔያቸው በመነሳት ለይተው መናገር ይችላሉ። - የአንድን ግጥም ይዘት ማስረዳት ይችላሉ።	33. ግጥም
	- በፈሊጦች እና ዘይቤያዊ ንግግሮች ይገለገላሉ። - አነባባሪ፣ ተለዋጭና ሰውኛ ዘይቤዎችን ለይተው ያስረዳሉ።	34. ፈሊጦች እና ዘይቤአዊ ንግግሮች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ቤተ መጻሕፍት

አባሪ 5

በ1996 ዓ.ም. ለአሥረኛ ክፍል ተሻሽሎ የቀረበው የመርሐትምህርት ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች

የመጀመያው የትምህርት ክፍለ-አመት

የትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት
ሰዋስው	የቋንቋን መሰረታዊ ባህርያት በዝርዝር ያስረዳሉ።	1. የቋንቋ መሰረታዊ ባህርያት
ሰዋስው	- የምዕላድን ምንነት ያስረዳሉ። - ነባና ጥገኛ ምዕላዶችን ከቃላት ውስጥ ለይተው ያመለክታሉ። - የሀረግ አይነቶችን ለይተው ያመለክታሉ። - ሀረጎች እንዴት እንደሚመሠረቱ ያስረዳሉ።	2. ምዕላዶች 3. የሀረግ አይነቶች - ቅጽላዊ - ተውሳከ ግሣዊ - መስተዋድዳዊ
ፅሕፈት	- በምክንያትና ውጤት ዝምድና ስልት አንቀጽ ይፅፋሉ። - በገላጭ አግባብ ስልት አንቀጽ ይፅፋሉ።	4. የአንቀጽ አግባብ ስልት - ምክንያትና ውጤት - ገላጭ
ፅሕፈት	በሠረዝ፣ በሁለት ነጥብ ከሠረዝና ከቅንፍ ይገለገላሉ።	5. ሥርዓተ ነጥቦች - ሠረዝ (-) - ሁለት ነጥብ፣ከሠረዝ (:-) - ቅንፍ {( )}
ማዳመጥና መናገር	- የልዩ ልዩ ጉባኤ ሃሳቦችን ፣ መልእክቶችን አዳምጠው የተረዱትን ይገልፃሉ። - በልዩ ልዩ ርእሶች ላይ ሳይዘጋጁ ንግግር ያደርጋሉ። - በተለያዩ ርእሰ - ጉዳዮች ዙሪያ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ያደርጋሉ። - የማነቃቂያና የቅስቀሳ ንግግሮች ዓላማና ባህሪ ይገልፃሉ።	6. የልዩ ልዩ ጉባኤዎች መልእክቶችን ማዳመጥ 7. ንግግር 7.1. የዱብዳ (ያለ ዝግጅት የሚደረግ) ንግግር
ንባብ፣ ንግግር/ ማዳመጥ	- በሀቅና በግል አስተያየት መካከል ያለውን ልዩነት ይገልፃሉ። - የሚቀርቡላቸውን ሀሳቦች የሀቅ ወይም የግል አስተያየት እያሉ ይገልፃሉ።	8. ተጠየቃዊ አስተሳሰብ 8.1. የሀቅና የግል አስተያየት
	- አንብበውና አዳምጠው ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተው ይገልፃሉ።	8.2. የአንድን ፅሁፍ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦች መለየት

የጥን ሀረግ ክፍል	ዝርዝር ዓላማ	ይዘት
ማዳመጥና ንግግር	- በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ይጨዋወታሉ - በተለያዩ ማህበራዊ፣ ምጣኔያዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ። - አካባቢያዊ፣ ወቅታዊና አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ ምንጮች አሰባስበው ይከራከራሉ።	9. ጭውውት 10. ውይይት 11. ክርክር
ንባብ	- ከልዩ ልዩ መግለጫዎች መረጃዎች እንዴት እንደሚገኙ ያስረዳሉ።	12. ከልዩ ልዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች መረጃዎችን ማግኘት
	- ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ተከትለው የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ። - ቅደም ተከተላዊ የአሠራር ሂደትን በማወቅ የተለያዩ ተግባራትን ቅደምተከተላዊ አሠራር ያዘጋጃሉ።	13. መመሪያዎችን መከተል፣ ማዘጋጀት
	- ነባር ዕውቀታቸውንና ከሚነበበው የሚያገኙትን መረጃ መሠረት አድርገው የአንድን ዕሁፍ ቀጣይ ይዘት ይገምታሉ፣ አንድምታ ይፈጥራሉ፣ ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ። - አንብበው በተረዱት መሠረት ያነበቡትን ዕሁፍ ያጠቃልላሉ። - ያነበቡትን ዕሁፍ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦች፣ መረጃዎችን በተለያየ መንገድ አደራጅተው ይገልፃሉ።	14. አንብቦ መረዳት -ነባር ዕውቀትን ከሚነበበው ጋር ማስተሳሰር - መገመት - ድምዳሜ ላይ መድረስ - እንድምታ - ማጠቃለያ

የሁለተኛው የትምህርት ክፍለ-ዓመት

የትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓለማ	ይዘት
ፅሕፈት/ማዳመጥ	- ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ይይዛሉ።	15. ማስታወሻ መውሰድ
ንግግርና ጽህፈት	- ያንድን ንግግር/ፅሁፍ ይዘት በራሳቸው አባባል አሳጥረው ያቀርባሉ።	16. ያንድን ንግግር /ፅሁፍ ይዘት በራስ አባባል አሳጥሮ ማቅረብ
ፅሕፈት	- ገላጭ ድርሰት ይፅፋሉ። - አመዛዛኝ ድርሰት ይፅፋሉ።	17.ድርሰት 17.1 ገላጭ ድርሰት 17.2 አመዛዛኝ ድርሰት
ፅሕፈት/ ንግግር	- በዘገባ አባባፍ ትኩረት የሚሰጣቸውን ነጥቦች ይዘረዝራሉ። - ዘገባ ያቀርባሉ። - በተለያዩ ጉዳዮች ቅርፀን፣ ይዘቱንና አቀራረቡን የጠበቀ የንግድ ስራ ደብዳቤ ይፅፋሉ።	18. ዘገባ ማቅረብ 19.የንግድ ሥራ ደብዳቤ
ሥነ-ፅሁፍ	- የፈሊጣዊ ንግግሮችን መልእክት ያስረዳሉ።	20.ፈሊጣዊ ንግግሮች
	- በአነባባሪ ዘይቤ የቀረቡ አባባሎችን ይተረጉማሉ፣ በዘይቤው በመገልገል ሃሳባቸውን ማቅረብ ይችላሉ። - በተለዋጭ ዘይቤ ይጠቀማሉ። - በሰውኛ ዘይቤ የቀረቡ ሀሳቦችን ያብራራሉ። - ተምሳሌታዊ እና የግነት ባህርያት ያለባቸውን ዘይቤዎች ለይተው ያመለክታሉ። - ተምሳሌትን እና ግነትን በመጠቀም ሀሳባቸውን አጉልተው ያቀርባሉ።	21. ዘይቤዎች 21.1አነባባሪ፣ተለዋጭና ሰውኛ 21.2 ተምሳሌት እና ግነት
	- በምሳሌዊ ንግግር የሚቀርቡ አስተያየቶችንና ልምዶችን ይገነዘባሉ፣ እነርሱም በንግግርና በጽሑፍ ውስጥ ምሳሌያዊ ንግግርን በመጠቀም ሀሳባቸውን ያጎላሉ።	22.1 ምሳሌያዊ ንግግር
	- የሥራ እና የፍቅር ቃል ግጥሞችን ለይተው ያመለክታሉ። -ባካባቢያቸው የሚደመጡ የፍቅርና የሥራ ቃል ግጥሞችን አሰባስበው ያቀርባሉ።	22.2. የሥራና የፍቅር ቃል ግጥሞች
	- የረጅም ልቦለድ ባህሪያትን ይለያሉ።	23. ልቦለድ ጽሁፍ
	- የልቦለድ አላባውያንን በቁጥርና በስም ያመለክታሉ። - የመቼትን ምንነትና በልቦለድ ውስጥ ያለውን ሚና ያስረዳሉ።	24.የልቦለድ አለባውያን 24.1. መቼት

የትምህርት ክፍል	ዝርዝር ዓለማ	ይዘት
ሥነ-ፅሁፍ	- ጭብጥ በልቦለድ ሥራ ውስጥ ያለውን ሚና ያመለክታሉ፡፡	24.2 ጭብጥ
	- የግጥም ምጣኔና ምትን አገልግሎት ያስረዳሉ፡፡ - ግጥም ከዝርው ጽሁፍ የሚለይበትን ሁኔታ ያመለክታሉ፡፡ - የቀረቡላቸውን መንቶ ግጥሞች በዝርው ያቀርባሉ፡፡	25. ግጥም

አባሪ 6

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ9 እስከ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን፣ የቀረበ የጸሑፍ መጠይቅ።

የተከበሩ መምህር፣

የዚህ ጽሑፍ መጠይቅ ዋና ዓላማ በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ውጤት ንጽጽራዊ ጥናት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ ነው። ጥናቱ ተፈላጊውን ግብ ሊመታ የሚችለው ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ሲቻል በመሆኑ የእናንተ ቅን ምላሽ በጣም አስፈላጊ ነው። ግልጽነት በጎደለው ነጥብ ላይ ማብራሪያ መጠየቅ ትችላላችሁ። ለሚደረግልኝ ትብብርም በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ።

ማሳሰቢያ፣

ሀ. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፤

ለ. ከግል ትምህርት ቤት የመጡ ማለት ከአንደኛ እስከ 8ኛ ክፍል በግል ትምህርት ቤት የተማሩ ተማሪዎች ማለት ነው።

ሐ. ከመንግሥት ትምህርት ቤት የመጡ ማለትም ከአንደኛ እስከ 8ኛ ክፍል በመንግሥት ትምህርት ቤት የተማሩ ማለት ነው።

ክፍል አንድ፡– ግላዊ መረጃዎች

መመሪያ አንድ፡– በተዘጋጀው ☐ ውስጥ የሚመለከትዎ ላይ ይህን ምልክት "✓" ያድርጉ፤ በክፍት ቦታ ደግሞ መልስዎን ይጻፉ፤

1.1 ዕድሜ _____ 1.2 ሥርዓተ ፆታ _____

1.3 የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት _____

1.4 በሚገቡባቸው ክፍሎች በእያንዳንዱ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት _____

1.5 የትምህርት ደረጃ፡– ዲፕሎማ ☐ የመጀመሪያ ዲግሪ ☐ ሁለተኛ ዲግሪ ☐ ሌላ ____

1.6 የአገልግሎት ዘመን _____

1.7 የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት

7.1 ዐቢይ _____ 7.2 ንዑስ _____

1.8 አማርኛን ያስተማሩባቸው የክፍል ደረጃዎች እና ዓመተ ምህረት

9ኛ ☐ ፣ ዓ.ም. _____ 10ኛ ☐ ፣ ዓ.ም. _____

11ኛ ☐ ፣ ዓ.ም. _____ 12ኛ ☐ ፣ ዓ.ም. _____

1.9 በያዝነው የትምህርት ዘመን (በ1999 ዓ.ም.) አማርኛን የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ፣ 9ኛ ☐ 10ኛ ☐ 11ኛ ☐ 12ኛ ☐

1.10 በአንድ ክፍል በሳምንት የሚገቡበት የክፍለ ጊዜ ብዛት _____

ክፍል ሁለት:– አጠቃላይ ጥያቄዎች

2.1 ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ካሉት አማራጮች ውስጥ የበለጠ ትክክለኛ ነው ብለው የወሰኑትን በመምረጥ ከየጥያቄዎቹ በላይ ካሉት አምስት ቁጥሮች በአንዱ ላይ ብቻ ትክክል በሚል የ"✓" ምልክት ያድርጉ። ከየጥያቄዎቹ በላይ ያሉት ቁጥሮችም የሚከተሉትን ሀሳቦች የሚወክሉ ናቸው፤

5 = በጣም እስማማለሁ 3 = እርግጠኛ አይደለሁም 1 = በፍጹም አልስማማም
4 = እስማማለሁ 2 = አልስማማም

ተራ ቁጥር	ጥያቄዎች	በጣም እስማማለሁ	እስማማለሁ	እርግጠኛ አይደለሁም	አልስማማም	ፍፁም አልስማማም
		5	4	3	2	1
1	ከመንግሥትም ሆነ ከግል ትምህርት ቤት ከመጡ ሴት ተማሪዎች ይልቅ ወንዶቹ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያመጣሉ።					
2	ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከመጡ ተማሪዎች ውስጥ ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ወንዶቹ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያመጣሉ።					
3	ከግል ትምህርት ቤት ከመጡ ተማሪዎች ውስጥ ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ወንዶቹ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያመጣሉ።					
4	በሥነ ጽሑፍ ትምህርት ላይ ከግል ትምህርት ቤት የመጡት ከመንግሥት ት/ቤት ከመጡት የተሻለ ውጤት አላቸው።					
5	በሰዋሰው ትምህርት ላይ ከግል ትምህርት ቤት የመጡት ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከመጡት የተሻለ ውጤት አላቸው።					

ተራ ቁጥር	ጥያቄዎች	በጣም እስማማለሁ	እስማማለሁ	እርግጠኛ አይደለሁም	አልስማማም	ፍፁም አልስማማም
		5	4	3	2	1
6	በአዳምጦ የመረዳት ክሂል ትምህርት ወቅት ከግል ትምህርት ቤት የመጡት ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከመጡት የተሻለ ተሳትፎ ያሳያሉ።					
7	ከግልና ከመንግሥት ትምህርት ቤት የመጡት ተማሪዎች ደረጃቸው ስለሚለያይ አንድ ላይ አደባልቆ አማርኛን ማስተማር ያስቸግራል።					
8	በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ላይ ከግልና ከመንግሥት ትምህርት ቤት በመጡት መካከል የጎላ የውጤት ልዩነት የለም።					
9	በአማርኛ የፅሀፈት ትምህርት ወቅት ከግል ትምህርት ቤት የመጡት ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከመጡት ይልቅ በጣም ይቸገራሉ።					
10	በአማርኛ የንግግር ቋንቋ ላይ በተመሰረቱ ጥያቄዎች የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግሥት ትምህርት ቤት ይልቅ የተሻለ ውጤት ያስመዘግባሉ።					
11	በአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትምህርት ላይ ለተመሠረቱ ጥያቄዎች ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ይልቅ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ያገኛሉ።					
12	ለጅምር ዓረፍተ ነገሮች ጨራሽ የአማርኛ ጥያቄዎች የተሻለ መልስ የሚሰጡት ከግል ትምህርት ቤት ከመጡት ይልቅ ከመንግሥት ትምህርት ቤት የመጡት ናቸው።					
13	በአማርኛ አውዳዊ የቃላት ፍቺ ጥያቄዎች የተሻለ መልስ የሚመልሱት ከመንግሥት ትምህርት ቤት ይልቅ ከግል ትምህርት ቤት የመጡት ናቸው።					
14	አሁን በማስተምርበት ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ ነው ብዬ አምናለሁ።					

2.2 ደረጃ ሰጪ–ጠቋሚ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በአራቱ የቋንቋ ክሂሎችና በሁለቱ የፅውቀት ዘርፎች ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች ተዘርዝረዋል። ከነሱ ውስጥ ከግል ትምህርት ቤት ለመጡትና ከመንግሥት ትምህርት ቤት ለመጡት ተማሪዎች በጣም የሚቀለውን 1ኛ፣ ቀጥሎ የሚቀለውን 2ኛ፣ 3ኛ . . . እያሉ እስከ 6ኛ ድረስ ደረጃ ይስጧቸው።

ተ.ቁ	የጥያቄ ዓይነቶች	ደረጃ /ክቀላል ወደ ከባድ/	
		ከግል ት/ቤት የመጡ	ከመንግሥት ት/ቤት የመጡ
1	የአማርኛ ቋንቋ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች		
2	የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ጥያቄዎች		
3	የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች		
4	የአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ጥያቄዎች		
5	የአማርኛ ቋንቋ የሥነ ልሳን ጥያቄዎች		
6	የአማርኛ ቋንቋ የሥነ ጽሑፍ ጥያቄዎች		

2.3 ነጻ አስተያየት የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች

1. ለተማሪዎች አጭር ፈተና አዘውትረው ይሰጣሉ?

   ሀ. እሰጣለሁ ☐ ለ. አልሰጥም ☐

2. የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ሲማሩ ከግል ትምህርት ቤት ከመጡት ይልቅ ከመንግሥት ትምህርት ቤት የመጡት ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘግባሉ?

   አዎ ☐ ለ. አይደለም ☐

3. ለሁለተኛ ጥያቄ መልስዎ "አዎ" ከሆነ በርስዎ አስተያየት ከመንግሥት ትምህርት ቤት የመጡት ለምን ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ይመስሎታል?

   _____
   _____
   _____

4. ትምህርት ሚኒስቴር ለአሥራ አንደኛ ክፍል ያዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ ከመንግሥት ትምህርት ቤት ለመጡት ተማሪዎች ይከብዳል ብለው ያስባሉ? ለምን? (የአሥራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ብቻ የሚመልሱት) _____
   _____
   _____

ውድ ጊዜዎን ሰውተው ይህን የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላት ስለተባበሩኝ ከልብ አመሠግናለሁ።

ጠጅቱ በሬቻ

አባሪ 7

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ።

ውድ ተማሪዎች፣

የዚህ የጽሑፍ መጠይቅ ዋና ዓላማ በግልና በመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ውጤት ንጽጽራዊ ጥናትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ ነው። ጥናቱ ተፈላጊውን ግብ ሊመታ የሚችለው ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ሲቻል በመሆኑ የእናንተ ቅን ምላሽ በጣም አስፈላጊ ነው። ግልጽነት በጎደለው ነጥብ ላይ ማብራሪያ መጠየቅ ትችላላችሁ። ለሚደረግልኝ ትብብርም በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ።

ማሳሰቢያ፣

ሀ. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፤

ክፍል አንድ፡– ግላዊ መረጃዎች

መመሪያ አንድ፡– ቀጥሎ በቀረቡት ዝርዝር አማራጮች ፊት ለፊት በተሰጠው ሣጥን ☐ ይህን ምልክት «✓» አድርጉ፤ በክፍት ቦታ ላይ ደግሞ መልሳችሁን ጻፉ።

1. ዕድሜ _____ 2. ዕድሜ _____ 3. የክፍል ደረጃ 11ኛ ☐ 12ኛ ☐
4. የትምህርት ቤታችሁ ስም _____
5. ባላችሁበት ክፍል ያሉት የተማሪዎች ብዛት _____
6. ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የተማራችሁበት ትምህርት ቤት ስም _____
   የግል ☐ የመንግሥት ☐
7. የአባት/ያሳዳጊ/ የትምህርት ደረጃ፡– ሰርተፍኬት ☐ ዲፕሎማ ☐
   የመጀመሪያ ዲግሪ ☐ ሁለተኛ ዲግሪ ☐ ሌላ _____
   ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ☐ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ☐
8. የእናት/ያሳዳጊ/ የትምህርት ደረጃ፡– ሰርተፍኬት ☐ ዲፕሎማ ☐
   የመጀመሪያ ዲግሪ ☐ ሁለተኛ ዲግሪ ☐ ሌላ _____
   ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ☐ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ☐
9. በሳምንት አማርኛ የምትማሩበት የክፍለ ጊዜ ብዛት _____

ክፍል ሁለት:– አጠቃላይ ጥያቄዎች

2.1 ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ካሉት አማራጮች ውስጥ የበለጠ ትክክለኛ ነው ያላችሁትን በመምረጥ ከየጥያቄዎቹ በላይ ካሉት አምስት ቁጥሮች በአንዱ ላይ ይህን "✓" ምልክት አድርጉ። ከክፍት ቦታዎቹ በላይ ያሉት ቁጥሮችም የሚከተሉትን ሐሳቦች የያዙ ናቸው።

5 = በጣም እስማማለሁ
4 = እስማማለሁ
3 = እርግጠኛ አይደለሁም
2 = አልስማማም
1 = ፍጹም አልስማማም

ማስታወሻ፣ በዚህ መጠይቅ ውስጥ "ፈተና" ተብሎ የተጠቀሰው በ1997 እና 1998 ዓ.ም. የተሰጠ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ሲሆን "ጥያቄዎች" የተባሉትም ከላይ በተጠቀሰው ፈተና ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች የሚያመለክቱ ናቸው።

ተራ ቁጥር	ጥያቄዎች	በጣም እስማማለሁ	እስማማለሁ	እርግጠኛ አይደለሁም	አልስማማም	ፍፁም አልስማማም
		5	4	3	2	1
1	ፈተናው በክፍል ውስጥ የምማረውን የአማርኛ ትምህርት በማንፀባረቅ ችሎታዬን ለመመዘን ብቁ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።					
2	ፈተናው ከባድ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።					
3	በፈተናው ምንባብ ላይ ተመርኩዘው የቀረቡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተቸግሬ ነበር።					
4	በፈተናው ላይ የቀረቡት የቃላት ፍቺ ጥያቄዎች ቀላል ነበሩ።					
5	ሰዋሰውን ተመርኩዘው የቀረቡት ጥያቄዎች ከባድ ነበሩ። (ለምሳሌ:– የቃላት ምስረታን፣ የድምፅ መጥበቅና መላላትን ... የሚመለከቱ ጥያቄዎች)					
6	ሥነ ቃልን የተመረኮዙት ጥያቄዎች ከባድ ነበሩ። (ለምሳሌ:–ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ፈሊጦች፣ ቅኔዎች)።					
7	በንግግር ቋንቋ ላይ የሚያተኩሩት ጥያቄዎች ከባድ ነበሩ። (ለምሳሌ:– ስለክርክር፣ ስለውይይት . . .የሚጠይቁ ጥያቄዎች)።					
8	ጅምር አረፍተ ነገሮችን በማሟላት ላይ የተመረኮዙት ጥያቄዎች ቀላል ነበሩ።					

ተራ ቁጥር	ጥያቄዎች	በጣም እስማማለሁ	እስማማለሁ	እርግጠኛ አይደለሁም	አልስማማም	ፍፁም አልስማማም
		5	4	3	2	1
9	ከጽሕፈት ጋር የተያያዙት የፈተና ጥያቄዎች ቀላል ነበሩ። (ለምሳሌ:– ስለሥርአተ ነጥብ፣ ስለአረፍተ ነገር አጻጻፍ፣ ስለአንቀፅ አጻጻፍ . . .የሚጠይቁ ጥያቄዎች)።					
10	በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያለው ቤተ መጻሕፍት የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሟሉ መጻህፍት አሉት።					
11	ትምህርት ቤቱ ቤተ መጻሕፍትን ለመጠቀም እንድትችሉ ፕሮግራም ያመቻችላችኋል።					
12	የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መምህራንን በመቆጣጠርም ሆነ የመማር–ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ንቁ እንቅስቃሴ ያደርጋል።					

2.2 ከዚህ በታች በአራቱ የቋንቋ ክሂሎችና በሁለቱ የፅሁፍ ዘርፎች ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች ተዘርዝረዋል። ከነሱ ውስጥ በጣም የሚቀላችሁን 1ኛ፣ ቀጥሎ የሚቀላችሁን 2ኛ፣ 3ኛ፣ . . . እያላችሁ እስከ ስድስተኛ ድረስ ደረጃ ስጧቸው።

ተ.ቁ	የጥያቄ ዓይነቶች	ደረጃ /ከቀላል ወደ ከባድ/
1	የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች፣	
2	የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ጥያቄዎች (ለምሳሌ እንድትወያዩ፣ እንድትከራከሩ . . .)፣	
3	የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች፣	
4	የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ጥያቄዎች (ለምሳሌ:– ስለሥርአተ ነጥብ፣ ስለዓረፍተ ነገር አጻጻፍ፣ ስለ አንቀጽ አጻጻፍ . . . የሚጠይቁ ጥያቄዎች)፣	
5	የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሥነ ልሳን ጥያቄዎች (ለምሳሌ:– የቃላት ምስረታ፣ የድምጽ መጥበቅና መላላትን የሚመለከቱ ጥየቄዎች)፣	
6	የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሥነ ጽሑፍ ጥያቄዎች (ለምሳሌ:– የተረትና ምሳሌ፣ የልቦለድ፣ የግጥም ጥያቄዎች)፣	

2.3 ነፃ አስተያየት የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች፣

1. ስለ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በተለይም ከክብደት ቅለቱ አንጻር ያላችሁን አስተያየት ባጭሩ ግለጹ፤

_____

_____

_____

2. ስለ አማርኛ መምህራን የማስተማር ተነሳሽነት ያላችሁን አስተያየት ባጭሩ ግለፁ፤

_____

_____

_____

3. ስለትምህርት ቤቱ አስተዳደር (ርዕሰ መምህር፣ ምክትል ርዕሰ መምህር፣ ዩኒት ሊደር ወዘተ.) የመማር ማስተማሩን ሂደት የማመቻቸት ተነሳሽነት ባጭሩ ብትገልጹ። _____

_____

_____

4. ስለወላጆቻችሁ ለትምህርታችሁ ድጋፍ ስጪነት ያላችሁን አስተያየት ባጭሩ ግለጹ።

_____

_____

_____

ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ ይህን የጽሑፍ መጠይቅ
በመመላት ስለተባበራችሁኝ ከልብ አመሠግናለሁ።

ጠጅቱ በሬቻ

ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተጠቀሰው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአማርኛን ማስተማር መርሃ ግብር ተማሪ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ ሥራ መሆኑና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኳቸውን ተዛማጅ ጽሑፎችና የመረጃ ምንጮች በሙሉ በአግባቡ የጠቀስኩ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ጠጅቱ በሬቻ

ፊርማ _____

አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ትምህርት

አዲስ አበባ

ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም.